የሕግ ፍልስፍና

(የምዕራባውያን የሥነ-ሕግ እና ሞራል ፍልስፍናዎች)

ዳዊት በዛብህ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ

© All rights reserved

ጸሐፊ፡ ዳዊት በዛብህ

አንደኛ ዕትም ታህሳስ 2013 ዓ.ም

ሁለተኛ ዕትም የካቲት 2014 ዓ.ም

ሶስተኛ ዕትም መስከረም 2016 ዓ.ም

© አንተነህ አያሌው
የሽፋን ስዕል

ማውጫ

1. ጥንታዊ የግሪክ ፈለስፎች እና የሕግና ፍትሕ ፅንሰ ሐሳብ
   1.1 የሕግጋቱ ድምፅ፡- ሶቅራጥስ
   1.2 ሕግ ፍትሕ እና ሪፐብሊክ፡- አፍላጦን
   1.3 የተፈጥሮ ሕግ ፅንሰት - አሪስጣጣሊስ
   ሕግ የሞራል ፍልስፍና እና ፍትሕ
   1.4 ምግባራዊነት
   1.5 ጠቀሜታዊነት
   1.6 ግዴታዊነት
   1.7 ሕግ እና ፍትሕ
2. የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና
   ብሉይ የተፈጥሮ ሕግ ፈለስፎች
   2.1 ሶፊስቶች እና አንጻራዊነት
   2.2 ስቶይኮች እና የተፈጥሮ ሕግ
   2.3 የአምላክ ከተማ ቅዱስ ኦግስቲን
   2.4 መነኩሴው ፈለስፋ - ቶማስ አኩይናስ
   ዘመናዊ የተፈጥሮ ሕግ ፈለስፎች
   2.5 የዓለምዓቀፍ ሕግ አባት፡- ሁጎ ግሮቲየስ
   2.6 ዘመናዊ የተፈጥሮ ሕግ - ጆን ፊኒስ
   2.7 ከኢ አማኒነት ወደ አማኝነት- ሲ ኤስ ሉዊስ
3. የሕገ ሰብ ፍልስፍና
   ቀዳማይ የሕገ ሰብዕ ፈለስፎች
   3.1 የሂዩም መቀስ - ዴቪድ ሂዩም
   3.2 የሉዓላዊ አካል ትእዛዝ - ጆን ኦስቲን
   3.3 የሕግ ፅንሰ ሐሳብ፡- ኤች ኤል ኤ ሃርት
   3.4 ትርጉም እና መርህ፡- ሮናልድ ዶርኪን
   3.5 ፍፁማዊ የሕግ ስርዓት- ሃንስ ኬልሰን
   ጽርፈተ ሕገ ሰብዕ
   3.6 የሕግ ውስጣዊ ውቅር - ሮን ፉለር

3.7 ታሪካዊ ሥነ ሕግ- ቮን ሳቭኒ
4. ማኅበረሰባዊ ውል እና የግለሰብ ነፃነት
4.1 ሕገ-አራዊት ፡ ጆን ሆብስ
4.2 ሕዝባዊ ፍቃድ፤ ዣን ዣክ ሩሶ
4.3 ማኅበረሰባዊ ውል ፡ ጆን ሎክ
4.4 የፍትሕ ቀመር፤ጆን ሮውልስ
4.5 ስለነፃነት፤ ጆን ስቲዋርት ሚል
5. የገሃዳዊ ሥነ-ሕግ ፍልስፍና
5.1 ፈለስፋው ዳኛ፡- ኦሊቨር ዌንደል ሆልምስ
5.2 የሕግ ጥርጣሬ፡- ፍራንክ ዥሮም
5.3 ማኅበረሰባዊ የሕግ ፍልስፍና፡- ሮስኮ ፓውንድ
6. ነቂሳዊ የሕግ ፍልስፍና
6.1 ጆርገን ሃበርማስ- የተግባቦት አመክንዮ
6.2 ድህረ-ዘመናዊ የሕግ ፍልስፍና
6.3 ሴት- ተኮር የሕግ ፍልስፍና
6.4 ሕግ እና ሥነ ምጣኔ
8. የብዝሃ- ሕግ ፍልስፍና
1.1 የአውሮፓ መንፈስ እና ኢትዮጲያዊ ፍልስፍና
1.2 ከጥንታዊነት ወደ ዘመናዊነት
1.3 ምሥራቃዊነት ወይስ ምዕራባዊነት
9.ሕግ፤ ፍትሕ እና ፖለቲካ
9.1 ማኪያቬሊ- የልዑል መካሪ
1.2 አሌክሲስ ዲ ቶክቪል- አሳሽ ፈለስፋ
1.3 ፍሬድሪክ ሄግል- የታሪክ ተማሪ
1.4 ኤድመንድ በርክ - ፀረ አብዮተኛ
1.5 አሌክሳንደር ሃሚልተን - ፌዴራሊስት
1.6 ካርል ማርክስ - ማርክሲስት የሕግ ፍልስፍና
9 ሕግ፣ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ
ዋቢ መፃሕፍት

ሐተታ ዘ ምክንያት

ይህን ድርሳን ለማዘጋጀት እንድነሳሳ ያደረጉኝን ገፊ ምክንያቶች በጥቂቱም ቢሆን ለአንባቢዎቼ የማስረዳት ሞራላዊ ግዴታ አለብኝ። ቀዳሚው ምክንያት የሀገራችን ዘመናዊ የሕግ ስርዓት በአብዛኛው ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ የተቀዳው ከሀገራችን ውጪ ካሉ የሕግ ምንጮች ነው። ሀገራችን ለዘመናት የተዳደረችበት ፍትሐነገስት ራሱ ከመካከለኛው ምሥራቅ የተወረሰ መሆኑ ሳያንስ በ1950 ዎቹ የፀደቁት የሕግ ድርሳናት ደግሞ ከአውሮፓ ሀገራት ተኮርጀው በሀገራችን የተተከሉ ናቸው። ይህ አካሄድ እንደ ባህል ከመወሰዱ የተነሳ በ1950ቹ ከተካሄደው ከፍተኛ የሕግ ንቅለ ተከላ (Legal Transplantation) ጀምሮ እስካሁን ድረስ የሀገሪቱን ዋና ዋና አዋጆች እና መመሪያዎችን ቃል በቃል በመተርጎም ወደ ሀገራችን የሕግ ስርዓት መደባለቅ የተለመደ ተግባር ሆኗል።

በመሆኑም የአሜሪካውያንን እና የአውሮፓውያንን ሕግጋት ቀስ በቀስ እየቀዳን በፓርላማዎቻችን ማፅደቅ እና ማስፀደቅ እንደ ባህል እና አስገዳጅ ሁኔታ መታየቱ ካልቀረ እነዚህ ሕግጋት የፈለቁበትን የፍልስፍና ምንጭ እና የፈሩበትን የአስተምህሮ ተክል ማወቅ የሕግጋቱን መሠረታዊ ባህሪ እና ታሪክ ለመረዳት አይነተኛ ሚና ይጫወታል። የፈረንጅ ሕግጋትን ቆርጦ መቀጠል የሀገራችን የፍትሕ ስርዓት ባህል መሆኑ እንዲቀየር ከፈለግንም የሕግጋቱን ፍልስፍናዊ መሠረት በቅድሚያ ማወቅ ይጠበቅብናል። ይሁን እንጂ የአውሮፓ እና የአሜሪካ ሥነ-ሕግ በጥልቀት ለማጥናት ከስፋቱ አንጻር አዳጋች በመሆኑ ይህ ሥራ አመላካች እና አቅጣጫ ጠቋሚ ብቻ በመሆን እንደሚያገለግል አምናለሁ።

ሁለተኛው ምክንያት በሀገራችን ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሕግ ፍልስፍና የተሰጠው ስፍራ አነስተኛና ከዘርፉ ግዝፈት አንጻር ሲተያይ አሳሳቢ ነው። በርግጥ ይህ የሆነበት ምክንያት ዋናው የፍልስፍና የትምህርት ክፍል ራሱ እንደ ትምህርት ዘርፍነት መቀጠል አቅቶት በተማሪ ማጣት ሰበብ የሚዘጋ እና የሚከፈት ህልውናውም በቋፍ ላይ ያለ መሆኑ ሲታይ ለሕግ ፍልስፍና አነስተኛ ስፍራ መሰጠቱ ብዙም የሚገርም አይደለም። በዚህም ምክንያት በሕግ ትምህርት ቤቶቻችን የሕግ ፍልስፍና ብዙም ትኩረት አይሰጠውም። በዚህም ምክንያት ትምህርቱ እንደ ፍልስፍና ሳይሆን እንደ ሕግ የሚያስተምሩት በመሆኑ ተማሪዎቹ ላይ ትምህርቱ ማሳረፍ ያለበትን ተጽዕኖ ሳያሳድር በከንቱ ያልፋል። የዚህ ችግር መሠረት ከአያሌ ጉዳዮች ጋር የሚገናኝ በመሆኑ ጥልቅ ነው፤ መፍትሔው ሰፊ እና ሁሉን ያሳተፈ መሆን እንዳለበት የሚያጠራጥር ባይሆንም

የሕግ ፍልስፍናን ከእናት የትምህርት ዘርፍ ፍልስፍና ጋር ማቆራኘት ግን መሠረታዊ እና ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል።

ሦስተኛው ምክንያት በሀገራችን ሀገር በቀል የሆኑ ባህላዊ የሕግ ስርዓቶች መኖራቸው ይታወቃል። በብሔር ብሔረሰቦች ዘንድ የተለመዱ ባህላዊ የሕግ ስርዓቶች የራሳቸው የሕግ ፍልስፍና ያላቸው ቢሆንም በሕዝቡና በባህል መሪዎቹ ሕሊና ውስጥ ያሉ እንደመሆኑ በጽሁፍ አልሰፈሩም። ከዚህም በተጨማሪ ከአውሮፓ ከቀዳናቸው ሕግጋት ጋር ሳይቀላቀሉ እና ሳይደባለቁ የሚኖሩ በመሆናቸው በባህላዊ የሕግ ስርዓቶች እና በመጤ እና ዘመናዊ የሕግ ሰርዓቶች መሀከል እስከ ዛሬም ያልተስተዋለ ትልቅ ገደል አለ። ይህንን ገደል የሚሞላ ሀገር በቀል የሥነ- ሕግ ፍልስፍና መፍጠሩ ለነገ ይደር የማይባል አስገዳጅ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ይህ ድርሳን የአውሮፓ የሥነ ሕግ ፍልስፍናዎችን ለሕግ ባለሙያዎች እና ለሕዝቡ በቀላል እና በሚረዳው ቋንቋ ማቅረቡ በሚቀጥሉት ጊዜያት ሀገር- በቀል የሕግ ፍልስፍና ለሚፈጥሩ ጥልቅ አሳቢዎች እንደመደላደል ያገለግላል የሚል እምነት አለኝ። እውቁ ፈለስፋ በተደጋጋሚ ጊዜ "ፍልስፍና በሀገራችን ወንበር የላትም" በማለት የሚያቀርበውን ቁጭት ወለድ ትችት መፍታት የምንችለው እንደዚህ ዓይነት ሥራዎችን ከነግድፈታቸውም ቢሆን ለሕዝብ መወያያነት ማቅረብ ስንችል ነው።

አራተኛው ምክንያት የአማርኛ ቋንቋ አብዛኛውን ጊዜ ለሥነ-ጽሁፍ፣ ለመንግስት ሥራ፣ ለታሪክ ሰነዶች ማዘጋጃነት እና ለስርዓተ አምልኮ ከመዋል ውጪ ለፍልስፍና ሲውል ማየት የተለመደ አይደለም። ታዋቂው ባለቅኔ ይህንን ሲያስረዳ "የኢትዮጲያ መንፈሳውያን ፈላስፎች ምናባቸው ሰፊ፤ ሃሳባቸው ረቂቅ ሆኖ ሳለ የፍልስፍናቸው ሐሳብ ፀሐይ ሲሞቅ የኖረው ቅኔ ማህሌቱ ዙሪያ ብቻ በሚገኙት የግራና የቀኝ ጌቶች ሕሊና ነው"[1] ይላል። በመሆኑም የአማርኛ ቃላት ቅኔን ብቻ ሳይሆን ደረቅ የአመክንዮ ቃላትን የመሸከም አቅማቸውን ጭምር መፈተሽ ይኖርብናል፤ የአማርኛ ቋንቋ የቅኔ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን የአመክንዮ፤ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ መቀመሪያ ሊሆን ይገባል። ቋንቋው ከሕዝብ መግባቢያነት አልፎ ፍልስፍናን ማፍለቂያ እና ማስተላለፊያ ሲሆን ሰፊ ሕዝብ የሚጠቀመው እንደመሆኑ ፍልስፍናን ራሱን የሕዝብ መግባቢያ እና ማስተማሪያ ማድረግ ይቻላል። በፈረንጅ አፍ ሳይሆን በአማርኛ ቋንቋ መፈላሰፍ ቀላልና የተለመደ ተግባር መሆን ይኖርበታል።

1 ኤፍሬም ስዩም፤ ተዋነይ ብሉይ የግዕዝ ቅኔያት ፍልስፍና፤ ውርስ ትርጉም፤ 2006፤ ገጽ ii

ምዕራፍ አንድ

ጥንታዊ የግሪክ ፈላስፎች እና የሕግ ፅንሰ ሃሳቦቻቸው

"ያልተመረመረ ሕይወት መኖር ያልተገባ ነው"

የምዕራባዊ ሃገራት ስልጣኔ የተጠነሰሰው በግሪክ ፍልስፍና ውስጥ መሆኑ የሚያጠራጥር ጉዳይ ባይሆንም *"የግሪክ ፍልስፍና ለየት የተወሰደ ነው?"* የሚለው ሐሳብ ግን እስካሁን ድረስ እያከራከረ ይገኛል። የግሪክ ፍልስፍና ስንል በተለይም በእነሶቅራጥስ እና ድህረ ሶቅራጥስ ዘመን ያለውን መሆኑ ሊሠመርበት ይገባል። አብዛኞቹ የቅድመ ሶቅራጥስ አሳቢዎች እና ፈላስፎች ትኩረታቸው የምናየው ግኡዛዊ ዓለም ከየት መጣ፣ ከምን ተሰራ እና በመጨረሻስ ምን ይሆናል የሚሉት ሐሳቦች ነበሩ። ሶቅራጥስ አዲስ በሆነ መንገድ የሰው ልጆች የምርምር እና የፍልስፍና ጀማሬ እና መሠረት ግዑዛዊው ዓለም ሳይሆን ራሱ ሰው መሆን እንዳለበት አስረግጦ አስተምሯል።

በዚህም ምክንያት የቅድመ ሶቅራጥስ ፈላስፎች ምድር የተሰራችው ከእሳት፣ ከውሃ፣ ከአፈር ወይስ ከንፋስ እያሉ የሚጨቃጨቁበትን መድረክ ሙሉ ለሙሉ ለውጦ ሰዎች የፈጠሯቸው ሐሳቦች እና ልማዶች ራሳቸው እንዲመረመሩ እና እንዲፈተሹ አደርጓል። በዚህም ምክንያት ሶቅራጥስ *"ያልተመረመረ ሕይወት መኖር ያልተገባ ነው"* በሚለው ሐሳቡ ይታወቃል፣ ሐሳቦችን መበየን እና መተርጎም የተጀመረው በራሱ በሶቅራጥስ ምልልስ (Socratic dialogue) ወቅት መሆኑ ይነገራል።

ከሶቅራጥስ በኋላ ያሉ ፈላስፎችም ይህንኑ ባህል ቀጥለውበታል። የሶቅራጥስ ተማሪ የነበረው አፍላጦን በበኩሉ የሶቅራጥስ ሐሳቦችን እና የሕይወት ዘይቤ በተለያዩ ድርሳናት ከማዘጋጀት አልፎ የራሱን የፍልስፍና ትምህርት ቤት ከፍቶ ብዙ ፈላስፎችን አፍርቷል። ሶቅራጥስ ያሳለፈው ሕይወት እና ያስተማራቸው ፍልስፍናዎች አፍላጦን ለትውልድ ባያስተላልፋቸው በታሪክ ውስጥ ተቀብረው ይቀሩ ነበር።

አፍላጦን የተለያዩ "የሶቅራጥስ ምልልሶችን" በርዕስ እና በዓይነት ከፍፍሎ በተለያዩ ድርሳናት አስቀምጧቸዋል። እነዚህ ድርሳናት ሶቅራጥስ በተዘዋወረባቸው እና ባስተማረባቸው ቦታዎች በሰዎች መኖሪያ ቤት፣ በመንገድ ላይ፣ በገበያ ቦታ፣ በፍርድ አደባባይ፣ በእስር ቤት፤ ከአንድ ግለሰብ ጋር ወይም ከጥቂት ወይም ብዙ ሰዎች ጋር የተደረጉ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የተደረጉባቸውም አርዕስቶች እና ምክንያቶች ስለሀገር፣ ፍቅር፣ መንግስት፣ ሕግጋት፣ አማልክት፣ ሕይወት፤ እምነት እና መሰል ጉዳዮች ናቸው። አፍላጦን እነዚህን ሁሉ የሶቅራጥስ ውይይቶች እና ምልልሶች ስዕላዊ በሆነ መንገድ ከማቅረቡ የተነሳ ብዙ ሰዎች አንዳንዶቹን ውይይቶች ራሱ አፍላጦን በምናቡ ፈጥሯቸው ነው? ወይስ የእውነት ሶቅራጥስ በሕይወት እያለ ያደረጋቸው ናቸው? እያሉ ይጠይቃሉ። ከዚህም በተጨማሪ የሶቅራጥስ ሐሳብ የቱ ጋር አብቅቶ የአፍላጦን ሐሳብ የቱ ጋር ይጀምራል የሚሉት ጭብጦች እስካሁን እንዳከራከሩን ይገኛሉ።

ከአፍላጦን ቀጥሎ የተነሳው ታላቁ ፈላስፋ "አሪስጣጣሊስ" / አሪስቶትል/ ሲሆን እሱም ቢሆን የአፍላጦን የፍልስፍና ትምህርት ቤት ተማሪ እና አፍላጦንን ለሃያ ዓመታት እየተከተለ የተማረ ፈላስፋ ነበር። አሪስቶትልም ሶቅራጥስ እና አፍላጦን የጀመሩትን የፍልስፍና አድማስ የማስፋት ሥራ ወርሶ ከግብ እንዲደርስ ብዙ ልፋት እና ድካም የቀላቀለ ትግል አድርጓል። አስተማሪው የነበረውን የአፍላጦንን ዲበአካላዊ ፍልስፍና በመተቸት የራሱን የፍልስፍና ጉዞ የጀመረው አሪስጣጣሊስ ከቀደሙት ሁለቱ ፈላስፎች የበለጠ የፍልስፍና ሐሳቦችን እና ድርሳናትን እንዲሁም

የረቀቁ አስተምህሮዎችን ለውጤት አብቅቷል። ከዚህም የተነሳ እስከ ዛሬ ድረስ በማኅበረሰባዊ እና ተፈጥሯዊ የጥናት መስኮች የምናውቃቸው ዋና ዋና የጥናት ዘርፎችን ለመጀመሪያ ጊዜ የከፋፈለው እርሱ ነው። እነዚህ ፈላስፎች ከብዙ ሥራዎቻቸው ውስጥ ስለሕግ እና ፍትሕ አስተዳደር የነበራቸውን አመለካከት ባጭሩ ለመዳሰስ እንሞክራለን።

የሕግጋቱ ደምፅ - ሶቅራጥስ

"የሕግጋቱ ድምፅ ይወቅሰኛል"

ለዘመናት የቆየን የሕይወት ዘይቤ እና ስርዓት ለመቀየር መሞከር ከባድ ብቻ ሳይሆን አደገኛም ሊሆን ይችላል። ሶቅራጥስ (470-399) በዘመኑ የነበረውን የአኗኗር ስልት እና ፍልስፍና ላይ ጥያቄ ያስነሳ እና የተቸ እንደመሆኑ ብዙ ጠላቶች ተነስተውበት ነበር። በዚህም ምክንያት "የወጣቱን አእምሮ አበላሽተሃል እና አማልክቱን ተሳድበሃል" የሚሉ ክሶች ቀርበውበት በአቴና አደባባይ ከአምስት መቶ በላይ አባላት ባሉት የፍርድ ሸንጎ ፊት ቀርቦ የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል እድል ተሰጥቶት ነበር። በዚህም ወቅት ራሱን እና ፍልስፍናውን በሚገባ የተከላከለ ቢሆንም ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሞት ፍርድ ተጥሎበታል። ሶቅራጥስ በእስር ቤት ሆኖ የሞት ፍርዱ የሚፈጸምበትን ቀን እየተጠባበቀ ሳለ ፍልስፍናውን በሚያስተምርበት ወቅት የሚያውቁት ባለሀብቶች ወደ ሌላ ከተማ ሊያስመልጡት ሴራ ጠንሰሱ። ይህንን ዕቅድ ክሪቶ የተባለ የሶቅራጥስ ወዳጅ ለሶቅራጥስ በመንገር አሳምኖት ከወህኒ ቤት እንዲያስመልጠው በማስብ ልከውት ነበር።

በመሆኑም አንድ ቀን ክሪቶ እራሱ ሶቅራጥስ ወዳለበት የወህኒ ክፍል ከጥበቃው ጋር ተመሳጥሮ በመግባት ይህንን ሐሳብ ይነግረዋል። ሶቅራጥስ እና ክሪቶ በዚያች አነስተኛ ክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን ውይይት አፍላጦን ክሪቶ በሚለው አስደናቂ ድርሳን በዝርዝር አስፍሮታል። ክሪቶ ያቀረበውን

የማምለጥ ሐሳብ ሶቅራጥስ ሙሉ ለሙሉ ያልተቀበለው በመሆኑ ክሪቶ ሶቅራጠስን እስከመለመን ደረጃ ደርሶ ነበር፤ ሶቅራጥስ ሚስት እና ልጆች ስላሉት ለእነሱ እንኳን ብሎ ሕይወቱን እንዲያተርፍ፣ ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የከሰሱት ሰዎችም በእኩይ ተግባራቸው ተደስተው እንዳይኖሩ እና የአቴንስ ሕዝብ ልብም እንዳይሰበር በማባበል ይጠይቀዋል።

ሶቅራጥስ የተላለፈበት የሞት ፍርድ ኢ-ፍትሐዊ መሆኑን ቢያውቅም ከእስር ቤት ማምለጡ ግን የባሰ ሕገወጥነት እና ኢ-ፍትሐዊ መሆኑን ለክሪቶ ለማስረዳት ይሞክራል። በአቴንስ ከተማ በኖረበት ሰባ ዓመታት የአቴንስ ሕግጋት እንቅፋት ሆነውበት እንደማያውቁ እንዲያውም ራሱን በፍቃዱ አስገዝቶ የኖረ እንደነበር ያወሳል። ሕግጋቱ የተለያዩ ቢሆኑም በአንድ ስርዓት እና ስብዕና የታቀፉ እንደመሆናቸው ድምፃቸውን ጥርት ባለ መንገድ እንደሚሰማና ከድቷቸው ቢሸሽ እንደሚወቅሱት ጭምር ይናገራል። በአቴንስ ከተማ ይህን ሁሉ ዓመታት ሲኖር በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከሕግጋቱ ጋር ውል እንደፈፀመ እና እስከ ዛሬ መብቱን እየጠበቁ እንዳኖሩት አሁን ግን በጥቂት ሰዎች ሴራ አማካኝነት ከሕግጋቱ ጋር የፈጸመውን ውል ሊያፈርስ እንደማይገባ እየደጋገመ ለክሪቶ ይነግረዋል።

He claims that a citizen is necessarily, given the benefits he has enjoyed under the laws of the city, their slave, justly required to do whatever they ask, and more forbidden to attack them than to violate his own parents. That would be retaliation—rendering a wrong for the wrong received in his unjust condemnation—and retaliation is never just. But what if he chose to depart not in an unjust spirit of retaliation, but only in order to evade the ill consequences of the unjust condemnation for himself and his friends and family? As if recognizing that loophole, Socrates also develops a celebrated early

> version of the social contract—a‘contract’ between the laws or the city and each citizen, not among the citizens themselves—with the argument that now, after he is condemned by an Athenian court and has exhausted all legal appeals, he must, in justice to his implicit promise, abide by the laws’final judgment and accept his death sentence.[1]

አንድ ዜጋ በመሠረቱ በከተማዋ ሕግጋት ከለላ ስር ሆኖ ባጣጣማቸው ጥቅሞች ምክንያት እንደ ባርያ ሕግጋቱ የሚጠይቁትን ሁሉ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ሕግጋቱን መጣረስ በወላጆቹ ላይ እንደማመጽ የከፋ መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል። ይህ በቀል ይሆናል፤ በኢ-ፍትሐዊነት ለደረሰብን ክፋት ክፋትን መመለስ፤በቀል ደግሞ ሁልጊዜም ኢ-ፍትሐዊ ነው። በተጨማሪም የሕግጋቱ አንድነት የማይገረሰስ እና የማይነጣጠል እንደመሆኑ አንዱን አክብሬ አንዱን እጥሳለሁ ማለት ሁሉን እንደመጣስ እና እንዳለማክበር እንደሚቆጠር ተናግሯል።

ሶቅራጥስ **“የሕግጋቱ ድምፅ ይወቅሰኛል”** ያለውን እንደ ምሳሌ ልንወስደው እንችላለን። ሕግጋቱን በሰው ወክሎ እንደሚያናግሩት ማድረጉ ከእነርሱ ጋር ስምምነት ላይ መድረሱን ያስረዳለታል። ይህ ስምምነት ወይም ውል በኋላ ላይ የተለያዩ ፈላስፎች አስፋፍተው በመንግስት እና በሕዝብ፣ በመንግስት እና በግለሰብ መሀከል የሚደረግ ውል መሆኑን ለማስረዳት ሞክረዋል። ሶቅራጥስ የተላለፈበትን የሞት ፍርድ ለመፈጸም የተዘጋጀለትን መርዝ ለመጠጣት ሲሰናዳ እንኳን አጠገቡ የነበረውን ክሪቶ ሕግጋቱን ስለማክበር እያስተማረውና ከሰዎች የተበደረውን እዳ በእርሱ ስም ሆኖ እንዲከፍልለት እያሳሰበው ነበር። ለእርሱ ፍትሐዊ ሕግጋት በኢ-ፍትሐዊ ሰዎች እጅ ገብተው ፍርድ ቢሰጥባቸውም ለሕግጋቱ ክብር ስንል ኢ-ፍትሐዊውን ፍርድ መቀበል ይኖርብናል።

1. John M. Cooper, Plato’s Complete Works (Hackett, 1997), p. 37-38

ሶቅራጠስን ሞት የፈረደበት ችሎት አምስት መቶ አንድ አቴናውያን በፈራጅነት (Jury) የተሰየሙበት ነበር። ፈራጅ ሸንጎ አሁንም ቢሆን በምዕራቡ ዓለም የሚገኝ አሠራር ሲሆን በወንጀል የተከሰሰ ሰው በእኩዮቹ የፍርድ ጉባኤ ፊት(Jury of his peers) ቀርቦ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚሰጥበት ወይም በነፃ የሚለቀቅበት ስርዓት ነው። ሶቅራጠስን ለመዳኘት የተገኙት አምስት መቶ አንድ አቴናውያን ሲሆኑ ከዚህ በፊት በፍርድ ሸንጎ አባልነት ያገለገሉ ጎልማሳ ወንድ የአቴንስ ከተማ ነዋሪዎች ናቸው። በፍርድ ሂደቱ የሶቅራጠስ ከሳሾች በአንድ ወገን፤በሌላ ወገን ሶቅራጠስ ሆነው በግልፅ አደባባይ ክርክራቸውን አሰምተዋል። በቅድሚያ ክሳቸውን ያቀረቡት ከሳሾች በዋናነት ያቀረቡት መከራከሪያ “የወጣቶችን አእምሮ ያበላሻል እና አማልክቱን ይሳደባል” የሚል ነበር። በእርግጥ እነዚህ ክሶች ከጀርባ ላለው እውነተኛ ክስ እንደ መከለያ ሆኑ እንጂ ሶቅራጠስ የወጣቱን አእምሮ አበላሽቶ ወይም አማልክቱን ተሳድቦ አልነበረም።

ሶቅራጠስ በአቴንስ መንገዶች እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ወቅት አቴንስ ቀድሞ ከነበራት ክብር ወድቃ፣ የከተማዋ ንግድ ተቀዛቅዞ፣ የባህር ወደቦቿ ቀድሞ ከነበራቸው የብዙ ህዝቦች መናኃሪያነት ወርደው፣ የሚፈሩት የአቴንስ ጣዖት አምልኮ ቤተ-መቅደሶች ክብር እና አስፈሪነት ቀንሶ ነበር። ለዚህ ምክንያቱ ሶቅራጠስ ሳይሆን አቴንስ በተደጋጋሚ ከአጎራባች የከተማ አስተዳደሮች ጋር ያደረገችው ጦርነት ነበር። ለምሳሌ “ስፓርታ” የተሰኘችው ከተማ አቴንስን በመውረር “የስልሳዎቹ ጉባኤ” በሚል የአስተዳደር ስርዓት አቴንስን ለተወሰነ ጊዜ አስተዳድራለች። ይህ አስተዳደር አቴናውያንን የሚያስጨንቅ እና በትንሽ ትልቁ ነገር እየፈለገ ቀረጥ የሚጥልባቸው፣ የሚያሥራቸው እና የሚገድላቸው ነበር። እንግዲህ ሶቅራጠስ ከቀረበበት ክስ አንዱ እነዚህ “የስልሳዎቹ ጉባኤ” አስተዳዳሪዎች በሶቅራጠስ ትምህርት ተዕዕኖ ስር የወደቁ ስለነበር ለከተማችን መውደቅ እና መቃጠል ሶቅራጠስ በተዘዋዋሪም ቢሆን እጁ አለበት። ይህም ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮ ሳይንስ ተመራማሪ ነን እያሉ ፀሐይ እና ጨረቃ አማልክት ሳይሆኑ ብርሃን የሚረጩ እንደ ምድር ያሉ የህዋ አካላት ናቸው እያሉ የሚያስተምሩት ሰዎችም የሶቅራጠስ ደጋፊዎች እና አድናቂዎች ናቸው።

ከሁሉም በላይ በየመንገዱ ለሰዎች “ንግግር አስተማሪዎች ነን፤ሌሎችንም ተግባራዊ ክህሎቶች እናስተምራለን” የሚሉት “ሶፊስቶች” እንደ መንፈሳዊ አባት የሚያዩት ራሱን ሶቅራጠስን ነው። በመሆኑም በእነዚህ አስተምህሮቶቹ ወጣቶችን ለቆየው እና ሲወርድ ሲወራረድ ለመጣው የአቴንስ ባህል፣ ወግ እና ልማድ ያለውን ንቀት እንዲያዳብሩ ያደርጋል። በጣም የሚገርመው ነገር ግን ሶቅራጠስ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ሶፊስቶችን እንደተቃወመ ኖሮ መጨረሻ ሶፊስት ተብሎ መከሰሱ የቀረበበትን ክስ ሐሰትነት የሚያሳይ ነው። ሶቅራጠስ በክስ ሂደቱ ራሱን ለመከላከል ባሰማው የክስ መከራከሪያ የአቴንስ ከተማ እንደ ሃይለኛ ፈረስ ቢሆን እርሱ እንደ ተርብ ወግ ልማዳቸውን እየነካካ የሚያነቃቸው እንጂ ሌላ አላማ እንደሌለው ነው። የፍርድ ሸንጎው ክርክሩን ከሰማ በኋላ በሚስጥር ድምፅ የሰጠ ሲሆን በዚህም ድምፅ መሠረት ከአምስት መቶ አንዱ አባላት 263ቱ ጥፋተኛ ሲሉት 234ቱ ጥፋተኛ አይደለም፣ የተቀሩት 4 አባላት ደግሞ ድምፅ ከመስጠት ተቆጥበው ነበር።

ከዚህ የምንረዳው የፍርድ ሂደቱ ምን ያህል ከባድ እና የተጋጋለ እንደነበር እና ሶቅራጠስም ጥፋተኛ የተባለው በጥቂት የቁጥር ልዩነት እንደሆነ ነው። ጥፋተኛ ከተባለ በኋላ የሞት ቅጣቱ እንዲነሳለት በተለምዶ እንደሚደረገው ተከሳሹ ቤተሰቡን እና ልጆቹን ይዞ በፍርድ ሸንጎው ፊት ልመና እንዲያቀርብ የሚደረግ ቢሆንም፤ ሶቅራጠስ ሞት ይገባሃል ብላችሁ ከፈረዳችሁብኝ በኋላ ቅጣቱን አንሱልኝ ብዬ መለመን ለእኔም ሆነ ለእናንተ ውርደት በመሆኑ አላደርገውም ሲል መልስ ሰጥቷል። ከዚህ የምንረዳው የአቴንስ ዴሞክራሲ እና ባህል እየወደቀ ስለሄደ የዚህን አይቀሬ ወድቀት የሚላክከበት ሰው ሲፈልጉ ሶቅራጠስን ስላገኙ እንጂ ሶቅራጠስ በርግጥም አማልክቶችን ተሳድቦ ወይም የወጣቶችን አእምሮ ባልተገባ ትምህርት መርዞ አልነበረም።

ሕግ፤ ፍትሕ እና ሪፐብሊክ - አፍላጦን

“ፈላስፎች ነገሥታት ፤ ነገሥታትም
ፈላስፎች ሊሆኑ ይገባል”

አፍላጦን (423-347) የሶቅራጥስን ፍልስፍና በጽሑፍ ማስቀረቱ ለዓለም ያበረከተው ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሆነ አይተናል። ይሁን እንጂ ድርሳናቱ በሙሉ በሶቅራጥስ ንግግሮች ስለተሞሉ የእርሱ አስተዋጽኦ አልነበረም ማለት አንችልም። አንዳንዴ ሶቅራጥስን እና ጓደኞቹን እንደ ገፀ ባሕሪያት በመጠቀም በእነርሱ ውስጥ የራሱን ሐሳብ ይናገር እንደነበር ብዙዎች ይስማማሉ።

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ከሚታወቁለት ሥራዎች መሀከል ዋነኛ የሆነው (ሪፐብሊክ) የተሰኘ ሥራው ከፍተኛ ተቀባይነት ከማግኘቱም አልፎ እስካሁን ድረስ የፖለቲካዊ ፍልስፍናዎቹ ሁሉ መሠረት ተደርጎ ይታሰባል። ይህ ድርሳን ብዙ ጉዳዮችን የሚዳስስ ቢሆንም ስለፍትሕ ጥልቅ ሐሳቦችን አንስቶ አብራርቷል። ድርሳኑ ሲጀምር የፍትሕን ምንነት በመጠየቅ ነው። ሶቅራጥስ ከሁለት ወዳጆቹ ጋር እየተጓዘ ፍትሕ ምን እንደሆነ ይጠይቃቸዋል። ይህ ውይይት የመጽሐፉን ምዕራፍ አንድ እና ሁለት በሙሉ የሚሸፍን ሲሆን ሶቅራጥስ ስለፍትሕ ምንነት ከወዳጆቹ ጋር የሚያደርገው ውይይት አንዳንዴም እሰጣ-ገባ ወዳጆቹ በጉዳዩ ላይ ያላቸውን የተሳሳተ አመለካከት ሲያስቀይራቸው እናያለን።

በውይይታቸው ፍትሕ ምንድነው፤ ፍትሐዊ የምንሆነው ለማን ጥቅም ብለን ነው? ፍትሐዊ ባንሆን ማን ይጎዳል?የሚሉ ጥያቄዎች እና ሐሳቦች ላይ ሰፊ ውይይት የሚደረግ ሲሆን ምዕራባዊ የሕግና የፖለቲካ

ፈላስፎች ላለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ስለፍትሕ የሚጽፉት፣ የሚጠይቁት እና የሚያብራሩት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሶቅራጥስ ከወዳጆቹ ጋር በጥልቀት የተወያየበትን እና የተጨቃጨቀበትን ጉዳይ ነው። ይህ ድርሳን ወይም በዚሁ ድርሳን ላይ የተጻፉ አናባቢ መጻሕፍትን ማንበብ እና ማጥናት በሕግ ወይም ፖለቲካ ላይ መመራመር ለሚፈልግ ሰው አስገዳጅነት ያለው ተግባር ነው።

> Until philosophers are kings, or the kings and princes of this world have the spirit and power of philosophy, and political greatness and wisdom meet in one, and those commoner natures who pursue either to the exclusion of the other are compelled to stand aside, cities will never have rest from their evils — no, nor the human race, as I believe — and then only will this our State have a possibility of life and behold the light of day[2].

ፈላስፎች ንጉሶች ካልሆኑ፣ ንጉሶች እና ልዑላንም የፍልስፍና ኃይል እና መንፈስ እስካልተቀዳጁ፣ የፖለቲካ ኃያልነት እና ጥበብም በአንድ እስካልተገናኙ፣ የሌላኛውን መገለል የሚሹ ተራ ማንነቶችም ዳር እንዲቆሙ እስካልተገደዱ ድረስ የሰው ዘርም ሆነ ከተሞች ከክፋታቸው ፋታ አያገኙም። አፍላጦን ነገሥታት ፍልሰፍና ይማሩ ወይም ፈላስፎች ይንገሱ ያለው ያለምክንያት አይደለም። *የህሊናን መሪነት፤ ይህንን የእውቀት የጥበብ ችሎታ ከከፍተኛ የርቀት ደረጃ ያደረሱ የነገሮች ባህርይ በግልጽ የሚታያቸው ፈላስፎች ይባላሉ። ለፊ ወለፊ ሳይመለከቱ ከህሊናቸወ በሰረፀው የእውቀት ብርሃን ማናቸውንም የሚመለከቱ፤ በስሜት ከሚመራው ከተራው ከድምሩ ሕዝብ የላቁ፤ ሀብት ንብረት የሚያስገኘውን ቅጽበታዊ ደስታ የናቁ የሚገባውን ፍርድ የሚሰጡ ናቸው።* በፕላቶን አስተያየት እንዲህ ያሉ ሰዎች የመሪነት

2 Plato, The Republic, Book Five, Benjamin Jowett (3rd edition = 1892)

ቦታ ሊኖራቸው ይገባል[3]። ሌላኛው የአፍላጦን ድርሳን “Laws” ሲሆን ሦስት በእድሜ የገፉ ግሪካውያን ስለ ሕግጋት አመሰራረት፤ ሕግጋቱን ማን ሊያወጣቸው ይገባል ? የሕግጋቱ ምንጭ ምንድነው? መለኮታዊ ሕግጋት ምንድናቸው? የተፈጥሮ ሕግ ምን ማለት ነው በሚሉ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት ሲያደርጉ ያሳያል። ይሁን እንጂ በዚህ ድርሳን ሶቅራጥስ በገፀ ባሕሪነት አልተሳተፈም። እነዚህ ሦስት ሽማግሌዎች ማግኒሻ ለምትባል ሀገር ጥሩ ሕገ መንግስት ለማርቀቅ በማሰብ ይነጋገራሉ።

ሪፐብሊክ እና ሎውስ የተባሉት ሁለቱ ድርሳናት አንድነትና ልዩነት አላቸው። ሪፐብሊክ በሥነ-ጽሑፍ ውበቱ እና ሐሳብ ፍሰቱ ከሎውስ እጅግ የተሻለ ሲሆን ሕግጋት የሚወጡበትን ጥቃቅን መስፈርቶች ከመለካት ይልቅ አጠቃላይ በሆነ ፖለቲካዊ ባህል እና ሥነ-ምግባር ላይ ያተኩራል። ሎውስ የተሰኘው ድርሳንን አፍላጦን በእድሜ ከሸመገለ በኋላ ጽፎታል ተብሎ ስለሚታሰብ የቃላት አመራረጡም ሆነ የሐሳብ ፍሰቱ ብዙም አይስብም።

ሪፐብሊክ በተባለው ድርሳን ፍጹም የሆነች “ካሊፖሊስ” በተባለች ከተማ ሦስት ሕዝባዊ መደቦች ሲኖሩ እነዚህም ሰራተኛው መደብ፤ የሪፐብሊኩ ጠባቂ ወታደሮች እና በፈላስፋ ንጉስ የሚመሩ ፈላስፋ ገዢ መደቦች ናቸው። በዚህ ድርሳን ይህ አይነቱ ክፍፍል የለም። በአጠቃላይ በሁለቱም ድርሳናት ሆነ በሌሎቹ ሶቅራጥስ እንደተናገሪ አፍላጦን እንደ ጸሐፊ ሰፊ የሆኑ ጥያቄዎችን ስለሕግና ፍትሕ አንስተዋል። ምንም እንኳን የሚሰጡት መልስ አንዳንዴ ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ማኅበረሰብ የማይመጥኑ ቢመስሉም ያነሷቸው ጥያቄዎች ግን ዛሬም ድረስ ዕውቅ በሆኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚወሱ ናቸው። አፍላጦን ከእነዚህ እና መሰል ዘመን አይሽሬ የፍልስፍና ሥራዎቹ ሊመሰገን ይገባዋል። የአፍላጦን “ሪፐብሊክ” የተሰኘ ድርሳን ፍትሕ በግለሰብ ደረጃ እና በ*ሀገር* ደረጃ ምን እንደሚመስል ለማሳየት የተጻፈ ነው።

3 እጓለ ገብረ ዮሐንስ፤ የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1956 ፤ ገጽ 102

ግሪክ የተመሰረተችው በሆሜር የሥነ-ግጥም ታሪካዊ ዘገባ ላይ እነደሆነ የምናውቀው “ኢሊያድ እና ኦዲሴ” በተሰኙት የሆሜር ግጥሞች እና በሌሎችም ግሪካዊ እሴት ጦረኛነት እና ጀብደኝነት ተደርጎ በመወሰዱ ነው፤ ፕሌቶ ይህንን የጀብደኝነት ታሪክ በመፈተሽ ግሪካዊነትን በፍልስፍና፤ ፍትሕ እና አመክንዩ ላይ ለመመስረት ጥረት አድርጓል። በዚህ ምክንያት ፕሌቶ ሥነ-ግጥም እና ተውኔት ሰዎች የሕይወታቸውን እውነተኛ አላማ እንዳይፈትሹ ስለሚያደርጋቸው ነው። በተጨማሪም በወቅቱ አቴንስ ውስጥ የነበረው ቀጥተኛ ዴሞክራሲ ዜጎች በከተማ ጉዳይ በቀጥታ እንዲሳተፉ ስለሚያደርጋቸው በአደባባይ በሚናገሩ ሰዎች የከተማዋ አስተዳደር ከፍተኛ ተፅዕኖ ላይ ይወድቅ ነበር። በዚህም ምክንያት የአቴንስ የሕዝብ አስተዳደር በብጥብጥ፣ ሁከት እና ለመረጋጋት የተሞላ በመሆኑ ሕዝብ በቀጥታ ከሚሳተፍበት ዴሞክራሳዊ አመራር ይልቅ አሪስቶክራቲክ ሆነ አስተዳደር የተሻለ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ ነበር።

በዚህም ምክንያት “ሪፐብሊክ” የተሰኘውን መጸሐፍ ሲያዘጋጅ የድሮ አስተማሪውን ሶቅራጠስን ዋና ገፀ-ባህሪ በማድረግ ተጠቅሞበታል። በርግጥ ሶቅራጠስ በሕይወት እያለ በሪፐብሊክ ውስጥ የተዘረዘሩትን ንግግሮች አድርጓል ወይ? የሚለው ጉዳይ አሁንም አከራካሪ ነው። ሶቅራጠስ በመጸሐፉ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ የመንግስት ባለስልጣናት እና ግለሰቦችን በጠንካራ አመክንዮ እየፈተሸ በግልፅ ያሳፍራቸው ስለነበር ብዙ ጠላቶችን ሊያፈራ ችሏል። ፍትሐዊነት በግለሰብ እና በመንግስት ደረጃ ምን እንደሚመስል ለማሳየት በመሞከሩ ሞራላዊነትን እና ፖለቲካን ለማስታረቅ ሞክሯል።

መጸሐፉ ሲጀመር ሶቅራጠስ ከወዳጃቹ ጋር እየተወያየ ነው። “ፍትሕ ምንድነው/” ሲል ይጠይቃቸዋል፤ አንደኛው “ፍትሕ ማለት እውነት መናገር እና የተዋሱትን እቃ መመለስ ነው።” ሲል ሌላኛው ደግሞ “ፍትሕ ማለት ባልንጀራን መርዳት እና ጠላትን ማጥቃት ነው።” ይላል። በዚህ ጊዜ ሶቅራጠስ ጣልቃ ይገባና “እውነተኛ ባልንጀራችንን እንዴት እናውቃለን?” ሲል ይጠይቃቸዋል። እውነተኛ ወዳጆቻችንን ለማወቅስ ቢሆን “አመክንዮን

መጠቀም የለብንም? ሲል መልሶ ይጠይቃቸዋል። አያይዞም “ጠላቶቻችን ወይም ክፉ ሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት የላቸውም ወይ? ምክንያቱም እኩይ ሰዎች ላይ ተጨማሪ ቅጣት የምንሰነዝርባቸው ከሆነ ይበልጥ ክፉ እና እኩይ ሊሆኑ አይችሉም ወይ?” ሲል ይሞግታቸዋል። በዚህ ጊዜ ሌላኛው ግለሰብ ጣልቃ ገብቶ “ፍትሕ በዓለም የለም፤ ጉልበተኞች ለራሳቸው የሚመቻቸውን ሕግ አውጥተው ብዙኃኑን ይበዘብዛሉ እንጂ” ሲል ውይይቱን ይቀላቀላል። ይህ እንግዲህ በመጸሐፉ በሙሉ የሚቀጥል የውይይት ዘይቤ ነው። በመጨረሻም ሶቅራጠስ ጣልቃ ገብቶ አንድ ግለሰብ ፍትሐዊ የሆነ ሕይወት ለመኖር በመሞከሩ ውስጣዊ ሀሴት እና እርካታ ያገኛል እንጂ ከቁሳዊ ነገሮች በመጉደሉ ሕይወቱ ሊዛባ አይችልም ሲል የተለያዩትን ሀሳቦች ሊያስታርቅ ይሞክራል።

ለሶቅራጠስ ፍትሕ የሰዎችን የነፍስ ጥማት ታረካለች። በመሆኑም በፍትሐዊ ግለሰብ እና ፍትሐዊ ከተማ መካከል ተመሳሳይነት መኖሩን ይጠቁማል። አንዲት ምናባዊ እና ፍትሐዊ የሆነች ከተማ ኗሪዎቿን በሦስት መደብ የምትከፍል ሲሆን እነዚህም ፈላስፋ መሪዎች፣ የከተማዋ ጠባቂዎች እና አምራች ሰራተኞች ናቸው። ፈላስፋ መሪዎች ረዥም ዓመት በትምህርት ማሳለፍ ሲጠበቅባቸው፤ የግል ሀብት እንዲያፈሩ አይፈቀድላቸውም። እንደ መነኩሴዎች በጋራ ገዳማዊ ሕይወት እንዲኖሩ ይገደዳሉ። የሚለብሱት፣ የሚበሉት እና የሚጠጡት በሙሉ በሰራተኞቹ መደብ እየቀረበላቸው ከዓለማዊ ክፋት፣ ሐሜት እና ሙስና ርቀው ይኖራሉ። ወታደሮች እና ቀስተኞች የሚባሉት የከተማዋ ጠባቂዎች የከተማዋን ነዋሪ ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ ሲኖርባቸው አምራቾቹ ደግሞ የከተማውን የኢኮኖሚ እና የምርት ሂደት ያስጠብቃሉ። በከተማው ውስጥ የሚካሄዱ የጣዖት አምልኮዎች የአማልክቱን ሥራ እና ገድል እያጋነኑ በመተረክ የከተማዋ ዜጎች ወሬኞች እና ሥራ የሚጠሉ እንዲሁም ልቅ በሆነ የፍትወት ስሜት የሚቃጠሉ ስላደረጋቸው ስለ አማልክቱ የሚነገር ታሪኮች በሙሉ ግብረገባዊ እና ስርዓት ያለው መሆን አለበት። በመሆኑም ተውኔቶች እና ሙዚቃዎች በሙሉ በጥንቃቄ የተለቀሙ እና የተደረሱ መሆን አለባቸው። በተለይ

በሥነ-ግጥም እንደ ሆሜር ያሉት ገጣሚያን የሰዎችን ስሜት እያነሆለሉ ያልተገባ ተምኔታዊ ዓለም ውስጥ በመክተት ከአመክንዮ እና ተግባራዊ ትምህርቶች የሚያስቀራቸው በመሆኑ በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባል።

በአጠቃላይ ፍትሐዊ ከተማ ለመገንባት እንዲቻል ሁሉም ዜጋ በተመደበበት የሙያ ዘርፍ በልህቀት ሊሰራ ይገባል። ይህ እንዲሆን ዜጎች ከህፃንነታቸው ጊዜ ጀምሮ በከተማዋ ውስጥ ስላለው የመደብ ልዩነት እና የሥራ ክፍፍል ሊማሩ እና ሊሰለጥኑ ይገባል። መሠረታዊ የሆነው አስተምህሮም ፈላስፋ መሪዎች ወርቃማ ነፍስ ሲኖራቸው ጠባቂዎቹ እና አምራቾቹ ደግሞ የብር እና የነሀስ ነፍስ አላቸው። ፈላስፋ መሪዎቹ እንደያዳብሩት የሚመከረው ምግባር ጥበብ ሲሆን ጠባቂዎቹ ደግሞ ጀግንነትን፣ አምራቾቹ ደግሞ ታታሪ ሠራተኝነትን ነው። ፍትሕ እንግዲህ ሁሉም የከተማዋ ዜጋ የተማረውን እና የተመደበበትን የሥራ ድርሻ በአግባቡ ሲወጣ የምናገኘው ስጦታ ነው።

ለአፍላጦን አንዲት ከተማ በመደብ ተከፋፍላ በስርዓት እንደምትመራ ሁሉ ግለሰቡም ቢሆን ማንነቱ በሦስት ደረጃዎች የተከፋፈለ ነው። አንደኛው የአመክንዮ እና የጥበብ ክፍል የያዘው ሲሆን ሁለተኛው መንፈስ እና ነፍሳችንን ያለበት መንፈሳዊ ማንነታችን ሲሆን ሦስተኛው ደግሞ ስጋዊ ፍላጎታችንን የምናረካበት የማንነታችን ክፍል ነው። አንድ ዜጋም ቢሆን እነዚህን ማንነቱን ክፍሎች በሚገባ አቻችሎ ሲኖር ህይወቱ ትርጉም ይኖረዋል። ፈላስፋ መሪዎች አስር ዓመት ሒሳብ፣ አምስት ዓመት ፍልስፍና በትንሹ መማር ስላለባቸው እውነቱን ከሕዝባዊ አስተያየት መለየት ይችላሉ። እውነትን ከሕዝቡ በተሻለ መንገድ መለየት የሚችሉት ፈላስፎቹ መሪዎች በመሆናቸው ሕዝቡን የመምራት መብት እና ግዴታ አለባቸው። እንደ እነዚህ ሰዎች በዚህ ዓለም ያለውን ያልተጣራ እና የተዛባ ህላዌ ፍጹም እና ጥራት ካለው ህላዌ ለመለየት አንደ ፈላስፋ መሪዎች ከልጅነታችን ጀምሮ የሰለጠንን መሆን አለብን።

የተፈጥሮ ሕግ ፅንሰት- አሪስጣጣሊስ

“ሰናይ ምግባር የሁለት ኣኩይ ጽንፎች መሀከለኛነት ነው”

አሪስቶትል/አሪስጣጣሊስ (384-322) ከአፍላጦን ተለይቶ የራሱን የፍልስፍና ትምህርት ቤት ከፍቶ ማስተማር ከጀመረ በኋላ ኒኮሚኪያን ሥነ- ምግባር (Nichomichean Ethics)የሚል ድርሳን ጽፏል። በዚህ ድርሳኑ ረቂቅ የምግባራዊ ሞራል ፍልስፍና አቀንቃኝ መሆኑን አሳይቷል። ሕግ ፍጹም ማኅበረሰብን ለመገንባት እንደሚያገለግል በመጠቆም ጠቅላላ ፍትሕንም ለሁለት ከፍሎታል። አንደኛው ተፈጥሮአዊ ፍትሕ ሲሆን ሌላኛው መደበኛ ፍትሕ ነው። ተፈጥሯዊ ፍትሕ ለሰዎች የማይነጠል እና የማይገረሰስ መብትን የሚያጎናጽፍ ሲሆን መደበኛ ፍትሕ ደግሞ ሰዎች የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያወጡት ነው። ለአሪስቶትል በአንድ ሀገር ሰላም እና ስርዓት ለማስፈን ለአንባገነናዊ አገዛዝ እና ለዲሞክራሲ መሀከለኛ የሆነ ሚዛናዊ አስተዳደርን መገንባት ያስፈልጋል።

አሪስቶትል የዲበአካላዊነት ትምህርት ጠንሳሽ ነው። ሜታፊዚክስ የሚለው ድርሳን በዚህ የእውቀት ዘርፍ ቀዳሚ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሜታፊዚክስ (ዲበአካላዊነት) የሚለው ቃል ራሱ የተፈጠረው በአሪስቶትል ሰበብ ነው። ይህ ጽሑፍ ስለ ፊዚክስ ከጻፈው መጽሐፍ ቀጥሎ ስለተገኘ በተለምዶ ከፊዚክስ ቀጥሎ ያለው መጽሐፍ ለማለት ሜታፊዚክስ የሚለው ቃል በሌሎች ሰዎች ተፈበረከ እንጂ በራሱ ምንም ትርጉም የለውም። የምናየው ዓለው ከየት መጣ፤ ከምን ተሰራ፤ መጨረሻው ምንድነው፤ ደግሞስ በምን ይንቀሳቀሳል የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመልስ የጥናት ዘርፍ ሲሆን አሪስቶትል First Philosophy ወይም Theology በማለት ይጠራዋል።

> Aristotle, as a philosopher, is in many ways very different from all his predecessors. He is the first to write like a professor: his treatises are systematic, his discussions are divided into heads, he is a professional teacher, not an inspired prophet.[4]

አሪስቶትል በመሀከለኛው ዘመን በተነሱ የካቶሊክ እምነት ፍልስፍናዎች እና አስተምህሮቶች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። ካቶሊኩ ፈላስፋ ቅዱስ ቶማስ አኩይናስ ይህንን የተፈጥሯዊ ፍትሕ ሐሳብ ወስዶ በማዳበር የተብራራ የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍናን በተዋቂውና Summa Theologica በተሰኘው ድርሳኑ በሰፊው ጽፎታል። በዚህም ምክንያት አንዳንዴ ጸሐፊያን አሪስቶትል የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና ጠንሳሽ እንደሆነ ሲጽፉ ሌሎች በበኩላቸው ይህንኑ በመቃወም አሪስቶትል የዚህ ፍልስፍና ጀማሪ እንዳልሆነና እርሱ ለማብራራት የሞከረው ሌላ ጽንሰ ሐሳብ ነበር በማለት ይከራከራሉ። ይሁን እንጂ ከሕግ ፍልስፍና ውጪም ቢሆን የአሪስቶትል አሻራ በቀላሉ የሚደበዝዝ አይደለም።

አሪስቶትል “Man is a political animal”- ”ሰው ፖለቲካዊ እንስሳ ነው” በሚለው ጥቅሱ በስፋት ይታወቃል። የሰው ልጅ በማኅበር ሲኖር እውነተኛ የሕይወት ትርጉም የሆነውን እውነት “Eudominia” ያገኛል። በማኅበር የማይኖር ሰው አውሬ ወይም አማልክት “Either a beast or a god” እንደሆነ ይገልፅና አንዲት ከተማ በፅኑ መሠረት ላይ የምትመሠረተው በጠንካራ ምግባራዊ የሞራል አስተምህሮ የታነፁ ዜጎቿ በጋራ ተሰባስበው የጋራ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ መንግስት ሲመሰርቱ ነው። ምክንያቱም ዜጎች በቀጥታ በመንግስት ጉዳይ መሳተፍ ይኖርባቸዋል። በፖለቲካ ውስጥ ያለመሳተፍ ከመሃይምነት ወይም ከስንፍና የሚመነጭ ነው። ለአመክንዮ የታደሉ ጎልማሳ ወንድ ዜጎች ከሴቶች፣ ህፃናት እና ባሮች በስተቀር

4 Bertrand Russell, A History of Western Philosophy (1945), Book One, Part II, Chapter XIX, Aristotle’s Metaphysics, p. 161

በመንግስታዊ አስተዳደር ውስጥ የመሳተፍ ግዴታ አለባቸው። አሪስቶትል “Politics” በተሰኘው ድርሳኑ ይህንን ፅንሰ ሐሳብ ጥልቀት ያብራራው አስተማሪው የነበረውን የአፍላጦንን ዲበአካላዊ አመለካከት ማለትም ምንታዊነት በመተቸት ነው።

ዓለማችን ፍጹም እና ንፁህ በሆነው የላይኛው ዓለም እና ባልጠራው እና በተደበላለቀው ይህች የምንኖርባት የታችኛው ዓለም የተከፈለች ናት በሚል ህላዌን መፈረጅ እንደሌለብን በመግለፅ አፍላጦንን ተቃውሟል። በመሆኑም ፈላስፎች መንገስ አለባቸው ወይም ንጉሶች ፍልስፍና ሊማሩ ይገባል በሚል መሪነትን እና የፖለቲካ ተሳትፎን ንፅህት የሆነችውን የላይኛውን ዓለም በአመክንዮ እና በነፍሳቸው ልትገልፅላቸው ለምትችል ጥቂት ሰዎች መተው ስህተት እንደሆነ በመግለፅ ሁሉም ዜጋ በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍ አለበት በማለት ተከራክሯል። ከዚህ በተጨማሪ የመንግስት አገዛዝ ዓይነቶችን በስድስት የከፋፈላቸው ሲሆን እነዚህም Monarchy,Aristocracy,Polity,Tyranny,Oligarchy እና Democracyናቸው። ከዚህ ውስጥ የተሻለው አመራር Polity ማለት የውክልና ሪፐብሊካዊ አስተዳደር እንደሆነና የኦሊጋርኪ እና የዴሞክራሲ ድብልቅ መሆኑን ያስረዳል። ከዚህ ሁሉ እጅግ እኩይ የሆነው የአስተዳደር ዓይነት ዴሞክራሲ ሲሆን ሴቶች፣ ህፃናት፣ የውጪ ሀገር ዜጎች እና ባሮች በአቴንስ የመንግስት አስተዳደር ውስጥ እንዲሳተፉ መፍቀድ አደገኛ መሆኑን ይገልፃል። የአሪስቶትል የመንግስት አስተዳደር የአከፋፈል ስርዓት እስከአሁን ድረስ ቢያገለግልም ስለ “ዴሞክራሲ” ያለው አስተሳሰብ ኋላቀር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ሕግ እና የሞራል ፍልስፍና

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ግለሰባዊ ሞራል የማኅበረሰባዊ ሞራል ነጸብራቅ ሆኖ ቆይቷል[5]። ይሁን እንጂ ይህ የሁለትዮሽ ጉድኝት ስብስብ በድህረ ዘመናዊነት እየተዋጠች ባለችው ዓለማችን እየተቀየረ ይገኛል። ለዘመናት የግለሰቡ ማንነት የማበረሰባዊ እሴት ውጤት እንደመሆኑ ማኅበረሰቡ ያከበረውን ግለሰቡ ያከብራል፤ ማኅበረሰቡ ያዋረደውን ግለሰቡም ይንቃል ያዋረዳል ተብሎ ይታመን ነበር። ይህም ሆኖ ቡድናዊ የሞራል እሴት በአንድ ቦታ ብቻ ረግቶ አልያም በተለያየ ጊዜ የተለያየ መልኮችን ይዟል። ማኅበረሰባዊ ሞራል በአንድ ቦታ ረግቶ በቆየባቸው ጊዜያቶች በሙሉ ግን ወደ ማኅበረሰብ ዓቀፍ ሕግነት ተቀይሯል። በዘመነ ብሉይ የፍትሕ ተቋማት፣ የተጻፉ የሕግ ድርሳናት፣ የሰለጠኑ የሕግ ባለሙያዎች፤ የሕግ ትምህርት ቤቶች እና መሰል ኩነቶች ባይኖሩም ልማዳዊ ሕግ እና ፍልስፍናዊ የእውነት ጥማት ነበር። በጊዜ ሂደት ዘመናዊ ሕግጋት ከማኅበረሰባዊ ሞራል እና ልማዳዊ ሕግጋት መፍለቅ ጀመሩ፡ የተጻፉ ዘመናዊ ሕግጋት ዕንሰት ሮማውያን የጠንካራ ውትድርና፣ ምህንድስናና የፖለቲካዊ ባህል መሥራች ናቸው። በዚህ ዘመን የአብዛኛው አውሮፓ እና የኮንቲኔንታል የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት የሚከተሉ ሀገራት በሙሉ ስር መሠረታቸው የጥንታዊ ሮማውያን ሕግ የፍትሕ አስተዳደር፤ ባህልና ፍልስፍና ነው።

---

5 'የሰው ሀልዮታዊ ጥረት ሁለት ዓላማዎች አሉት። አንደኛው በውስጡ በፊቱ የተደቀነውን የሥነ ፍጥረት ውስብስብ ሥርአት ለማወቅ ለመተርጎም ነው። ይህንን ፍካሬ አለማት እንበለው። ሁለተኛው 'እንዴት ልኑር ምን ብሠራ ይበጀኛል' የሚለውን የሥነምግባር ጥያቄ ነው። ይህንን ፍኖተ ሕይወት እንበለው። ለሁለቱም እኩል ማሰብ እንደሚገባ አያጠያይቅም። የሩቁን እና የቅርቡን ዓለም በረቂቅ ሕሊናው መጥቆ ቢቃኘው፣ ቢጎበኘው ሕይወቱ ግን በጠብ፣ በጥላቻ፣ በትንቅንቅ፣ በዛቻ ተወጥሮ መላወሻ ቢያጣ ለሰው የምን ይበጀዋል። ከእንዲህ ያለ ውጥረት ነፃ የሚያወጣው እውነተኛ የሥነ ምግባር ዕውቀት ነው። ይህንን ከኬላው ለይቶ፣ ፈልፍሎ ማውጣት መብራቱን መቅረዝ ላይ ማኖር ማለት ነው።

(አጓለ ገ/ዮሐንስ ፣ ብፁዓን ንጹሐነ ልብ፣ ገፅ 19-20)

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ሕግና ሞራሊቲ የሚመነጩት ከማኅበረሰቡ ባህል ወግና ታሪክ ውስጥ ነው። ይሁንና በሕግና በማኅበረሰባዊ ሞራል መሀከል አንድነት እና ልዩነት አለ። መንግስታት በሚያወጧቸው ሕግጋት እና በማኅበረሰባዊ የሞራል ሕግ መሀከል ያሉትን መጠነኛ ልዩነቶች ማብራራት ይገባል። የመንግስታት ሕግጋት በአብዛኛው የተጻፉ እና የታወጁ ናቸው። አዋጆች፤ ደንቦች እና መመሪያዎች በሙሉ በነገስታት ፣ በፓርላማዎች እና ካቢኔዎች ከጸደቁ በኋላ በወረቀት ታትመው ለሕዝብ ይሰራጫሉ። ዘመናት ካለፉ በኋላ ሲሻሩ እና ሲሻሻሉም እንዲሁም ታትሞ በሚሰራጭ ሕግ ነው። ማኅበረሰባዊ የሞራል ሕግ በወረቀት ወይም ድርሳን ታትሞ ለሕዝቡ የሚሰራጭ አይደለም።

ማኅበረሰባዊ የሞራል ሕግ በታሪክ ውስጥ ቀን በቀን አድጎ በሕዝቡ ሕሊና እና ባህል ውስጥ የሚሰርፅ አስገዳጅነት ያለው የሕይወት ዘይቤ ነው። ሌላው የመንግስት ሕግ ተቋማትን ይፈጥራል ፤ ሕጉን የማያስፈጽሙ፤ የሚያስተምሩ፤ የሚተረጉሙ፤ የሚያረቅቁ፤ የሚያጸድቁ፤ የሚያሻሽሉ እና የሚሽሩ ሰዎች እና ተቋማት በግልጽ እና በዝርዝር ተለይተው በእነዚያው ሕግጋት ይቀመጣሉ። በማኅበረሰቡ የሞራል ሕግ ግን እነዚህ ሰዎች እና ተቋማት በዝርዝርና ግልጽ በሆነ መንገድ ተለይተው ባይቀመጡም የሉም ማለት ግን አይደለም፤ እንደ ሁኔታው ይቀያየራሉ፣ ይለዋወጣሉ ሆኖም የማኅበረሰቡን ሞራል ጠባቂ የሆኑትን ሰዎች እና ተቋማትን ግን ሕዝቡ ለይቶ ያውቃቸዋል። ሌላው የመንግስት ሕግ ሲጣስ የሚጣለው ቅጣት እና የቅጣት ዓይነት አስቀድሞ በሕግ የተደነገገ እና የታወቀ ነው። ቅጣቱን የሚያስፈጽሙ ተቋማት እና ግለሰቦችም ይታወቃሉ።

በማኅበረሰባዊ የሞራል ሕግ ግን የቅጣቱ ዓይነት እና ደረጃ በግልጽ የተቀመጠ ባይሆንም ሊገመት የሚችል ዓይነት ነው። ቅጣቱን የሚጥሉት ሰዎችም አንዳንዴ የታወቁ አንዳንዴም የማይታወቁ በመሆኑ ግልጽ አይደለም። ለምሳሌ አንድን ግለሰብ በድርጊቱ ምክንያት ከማኅበረሰቡ ማግለል ቅጣት ከሆነ ፈጻሚው ማኅበረሰቡ ራሱ መሆኑን ልብ ይሏል።

በርግጥ አንዳንድ የልማድ ሕግጋት ዘመናዊ ከሚባለው የመንግስት ሕግ እኩል ተቋማትን መስርተውና ሕጎቻቸውን የሚያስፈጽሙ ሰዎች ሰይመው ይንቀሳቀሳሉ፤ ከመንግስት ሕግ የሚለያቸው ያልተጻፉ በመሆናቸው ብቻ ነው።

> *ቨርቹ ኢቲክስ ካሉት ሦስት ትላልቅ የሥነምግባር ንድፈ ሐሳቦች መካከል አንደኛውና ቀዳሚው ነው። ቨርቹ የሚለው ቃል ወደ አማርኛ ሲተረጎም ሰናይ ምግባር ነው። ኢቲክስ ማለት ደግሞ ሥነምግባር ነው። በዚህም መሠረት ቨርቹ ኢቲክስ በሰናይ ምግባር ወይም ባህሪ ላይ የሚያተኩር የሥነ ምግባር ንድፈ ሐሳብ ወይም የጥናት መስክ ነው። ሌሎች የሥነምግባር ንድፈ ሐሳቦች ለምሳሌ ኩዊንስኩዊንሻል ሥነምግባር ድርጊትን ወይም ውጤትን መሠረት የሚያደርግ ነው፤ የዲአንቶሎጂካል ሥነ ምግባር ደግሞ ግዴታን መወጣት ነው። ለኩዊንስኩዊንሻል ሥነምግባር የአንድ ሰው ድርጊት ግብረገባዊ ይዘት የሚመዘነው በድርጊቱ ውጤት ጥሩነት ወይም መጥፎነት ነው። ለዲአንቶሎጂካል ሥነምግባር ግን የድርጊት ግብረገባዊ ይዘት የሚገመገመው አድራጊው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ግብረገባዊ ግዴታውን ለመወጣት ከሚኖረው ቁርጠኝነት አንፃር ነው[6]።*

በዓለማችን ላይ ብዙ የሥነ-ምግባር ንድፈ ሐሳቦች ቢኖሩም በግንባር ቀደምትነት የሚታወቁት ሦስት ናቸው። እነዚህ ሦስት አስተምህሮዎች የተለያየ ንዑስ ክፍልፋይ ቢኖራቸውም መሠረታዊ ውቅራቸውን በመረዳት የሥነ-ሕግ ተመራማሪዎች እንዴት እና ለምን እነዚህን አስተምህሮዎች እንደተቃወሟቸው ወይም እንደ መሠረት ተጠቅመው የራሳቸውን አስተምህሮ ሊገነቡ እንደቻሉ መረዳት አያዳግትም።

---

6 ዶ/ር ጠና ደዎ፤ ሰው ግብረገብና ስነምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች፤ አአዩ ፕሬስ፤ 2008፤ ገፅ 101

ሕግ በመንግስታት ተረቅቆ እና ጸድቆ በመጽሐፍትም ለሕዝብ ከመድረሱ በፊት መሠረታዊ የሆነው ባህሪው አስቀድሞም ቢሆን በማኅበረሰቡ ልማድ እና የኑሮ ዘይቤ ውስጥ የሚገኝ ነበር። በአብዛኛው ጊዜ ሞራል ሕግን የሚፈጥር ቢሆንም ሕግ ሞራልን አይፈጥርም ለማለት አይቻልም። በሁለቱ መሀከል ለዘመናት የቆየ የምክንያትና ውጤት ግንኙነት አለ። በዚህም ምክንያት በታሪክ ውስጥ የሕግ ፍልስፍናዎችን፤ አስተምህሮዎችን፤ መርሆዎች እና ጽንሰ ሐሳቦችን ውልደት፣ እድገትና ሞት ከመመርመራችን በፊት ለእነዚህ የሕግ ፍልስፍናዎች መሠረት የሆኑትን የሞራል ፍልስፍናዎች በጥቂቱም ቢሆን መዳሰስ ይኖርብናል።

ሞግባራዊነት

"ሰናይ ምግባር በሞኁል ትምህርት ይገኝል"

ምግባራዊ የሞራል ፍልስፍና (Virtue Ethics) ከባህሪ ልዕቀት ጋር የተቆራኘ ነው። ለጥንታዊ ግሪኮች የሰው ልጅ ዋነኛ የሕይወት ጥረት በጤና፤ በስልጣን፣ በእውቀት እና በሀብት ልዕቀትን ማግኘት ነበር። የሰው ልጅ በሌሎች የሕይወት ክፍሎች ልቀትን ለማግኘት እንደሚተጋው በሞራላዊ ሕይወቱም ይህንኑ የሞራላዊ ልዕቀት ለማግኘት መጣር እንዳለበት እና ለዚህ ደግሞ ሞራላዊ ልዕቀት የሚያስገኙለትን የግል ባህሪያት አውቆ ሊያዳብራቸው እንደሚገባ አስተምረዋል።

የሞራል ልዕቀት የሚያስገኘውን ምግባር በምን እናውቃለን? እንዴትስ ልናዳብረው እንችላለን? ሰናይ ምግባር እና እኩይ ምግባር በምን ይገለጻል ግለሰቡስ አንደኛውን ሸሽቶ ሌላኛውን ሊያዳብር የሚችለው እንዴት ነው? "ምግባረ ሰናይነትን" መለኪያው እና ማወቂያው መንገዱ ምንድነው? የሚሉትን ጥያቄዎች የግሪክ ፈላስፎች በልዩ ልዩ መንገዶች መርምረዋቸዋል። ለታዋቂው ፈላስፋ ሶቅራጥስ ምግባረ ሰናይነት ከሞራል እውቀት ይመነጫል ምግባረ ብልሹነት ደግሞ የሞራል እውቀት ከማጣት

የሚመነጭ ችግር ነው፡ ለሶቅራጥስ ሰዎች በአስከፊ እና አስነዋሪ ድርጊት ውስጥ የሚሰማሩት ተገቢውን የሞራል ትምህርት ስላላገኙ ነው። በተቃራኒው ሰዎች በበጎ ተግባር የሚሰማሩት እና ቅን ባህሪ የሚያሳዩት ትክክለኛ የሞራል ትምህርት ስላገኙ ነው። ምክንያቱም ሥነ-ምግባር የሞራል ትምህርት ውጤት ነው። ይሁን እንጂ ሶቅራጥስን ሰዎች ትክክለኛውን የሞራል ትምህርት አግኝተውም ቢሆን ምግባረ ብልሹ ሊሆኑ አይችሉም ወይ? በሚል ለሚቀርብለት ጥያቄ የሚሰጠው መልስ እነዚህ የሞራል ትምህርት ተሰጣቸው እንጂ የሞራል እውቀት አላገኙም፤ የሞራል እውቀት ያለው ሰው ምግባረ ብልሹ ሊሆን አይችልም ሲል ይመልሳል።

የሞራል ትምህርት አግኝተው ቢሆን ምግባረ ብልሹ የሚሆኑ ሰዎች ምግባራቸው መጥፎ ሆኖ ሳለ ጥሩ እየመሰላቸው የሚያደርጉት ናቸው፤ ይህ ሁኔታ "**የሶቅራጥስ አያያዝ**" ተብሎ ይጠራል። ሶቅራጥስ ስለምግባረ ሰናይነት ሲያስተምር የሶቅራጥስ ምልልስ በሚል የሚታወቀውን የራሱን የማስተማር ዘዴ ይጠቀም ነበር። በመሆኑም ሰዎች የሚከተሏቸው ምግባራዊ የሞራል ፍልስፍናዎች በሶቅራጥስ የጥያቄ ብዛት ይፈተኑ ስለነበረ በሶቅራጥስ የተማረ ሰው ተገቢውን የሞራል እውቀት ማግኘቱ አያጠራጥርም።

ለአሪስቶትል መልካም ምግባር ማለት በሁለት ጽንፍ ባህሪያት መሀከል ያለ ባህሪ ነው። ይህ **"የመሀከለኛነት መርህ"** በሚል የሚታወቀው የአሪስቶትል አስተሳሰብ ምግባረ ሰናይነትን ለማግኘት የሚረዳ ዘዴ መሆኑ በስፋት ተብራርቷል። ለምሳሌ ጀግንነት የሚባለውን ባህሪ ለመቀዳጀት በፈሪነት እና በጀብደኝነት መሀከል ያለውን አማካይ ስፍራ ማግኘት ይኖርብናል። ይህ መርህ በተለምዶ "ወርቃማው መሀከለኛ" በመባል ይታወቃል።

Virtue is the golden mean between two vices, the one of excess and the other of deficiency[7]

አሪስቶትል ሰዎች ትክክለኛ ምግባራዊ ሕይወት ሲኖራቸው ኢዶሚኒያ (Euidominia) ወይም እውነተኛ ደስታን ሊያገኙ እንደሚችሉ ያምን ነበር። እንግዲህ የምግባራዊ ሞራል ፍልስፍና ሰዎች ምግባረ ብልሹ ከመሆን ተቆጥበው በሥነ-ምግባር ታንጸው ግብረ- ገብነት ያለው ሕይወት እንዲመሩ የሚያስተምር ነው። በዚህም ምክንያት ሰዎች፤ መንግስታት፤ ሃይማኖቶች እና ልዩ ልዩ ተቋማት ትክክለኛውና ለእውነት የቀረበው ሞራላዊ ምግባር ወይም ባህሪ ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ኖረዋል። ይሁን እንጂ ይህ ባህሪ በጊዜ፤ በቦታ፤ በባህል፤ በትምህርት ሁኔታ፤ በመደብ እና መሰል ሁነቶች የሚለያይ በመሆኑ ዘላቂነት ያለው የሞራል ፍልስፍና አድርጎ ለመውሰድ አስቸጋሪ ነው።

ምግባራዊ የሞራል ፍልስፍና ሰዎች ምግባረ ሰናይ የሚሆኑት ግዴታ ስለሆነባቸው ወይም የተለየ ግላዊ ጥቅም ስለሚያገኙ ሳይሆን መልካምነት የግለሰባዊ ልዕቀት ማሳያ በመሆኑ ሰዎች ከግሪኩ ቃል “Arete” ወይም “Excellence” ያለው ሕይወት ለመኖር ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል። ይህ አመለካከት ከአፍላጦን የዲበ አካላዊ አስተሳሰብ ጋር ይገናኛል። ለአፍላጦን ምንታዊነት(dualism) የፍልስፍናው ማዕከላዊ ሐሳብ ነው። ህላዌ በሁለት ይከፈላል አንደኛው ፍጹም፣ ንፁህ እና ያልተቀየጠው በማይታየው ዓለም ያለው እውነታ ሲሆን ሁለተኛው የተበረዘ፣ የቆሸሸ እና የተቀየጠው የምንኖርበት ይህ ዓለም ነው። ይህንን በምሳሌ ሲያስረዳ የምንኖርበት ዓለም በድቅድቅ ጨለማ የተዋጠ ዋሻን ይመስላል። የዚህ ዓለም ሰዎች በዚህ ዋሻ ውስጥ ሲኖሩ ከዋሻው ውጪ ያለ ብርሃን የሚፈጥረውን ጥላ በዋሻው ግድግዳ ላይ እየተመለከቱ ይኖራሉ እንጂ እውነተኛ ብርሃን የሞላበት ዓለም ምን እንደሚመስል አያውቁም።

7 Ross, David , *Aristotle The Nicomachean Ethics: Translated with an Introduction*. Oxford: Oxford University Press,1925

ሲኒማ ቤት ቁጭ ብለህ ፊልም እያየህ ፊልሙ ከተጀመረ በኋላ ወደ ጨለማው አዳራሽ እየተደናበሩ የሚገቡ ታዳሚዎችን ስታይ ልትስቅ ትችላለህ። ግርግዳውን ይታከካሉ፣ ወንበር በዳበሳ ይፈልጋሉ፣ ሰው ያለበት ወንበር ላይ ለመውጣት ይታገላሉ፣ ጫማህ ላይ ይወጣሉ፣ እግራቸውን እያንፏቀቁ ይሄዳሉ። ዓይናቸው ጨለማውን አልለመደውም፣ አንተም አይናማ፣ እነሱም ዓይናማ። አንድ ጨለማ ውስጥ ተቀምጣችሁ ግን ቀደም ብለህ ጨለማውን ስለተላመድክ ብቻ ከአዲስ ገቢዎቹ ይልቅ አንተ በጨለማ የቆየኸው በደንብ መመልከት ትችላለህ። እነሱም ሲቆዩ ግን ልክ እንዳንተ ዓይናቸው ጨለማውን ይላመደዋል። የሀገራችን ጨለማ አልገፈፍ ስላለ እንደ አፍላጦን የዋሻ እስረኞች ከጨለማው ከማምለጥ ይልቅ እንደ ሲኒማው ቤት ተመልካቾች ሁሉም ዓይኑ ጨለማውን ለምዶ በቅጡ ለመመልከት እየተጣጣረ ነው። The Cinema hall allegory ማለት ይቻላል።

በመሆኑም ትክክለኛውን የዚህ ዓለም ገፅታ ለማወቅ ከዚህ በጨለማ የተዋጠ ዋሻ ማምለጥ ይኖርባቸዋል። ይህ ምሳሌን ወደ ነባራዊ የዓለም ሕይወት ስንለውጠው፤ለምሳሌ “ፍቅር” የተሰኘውን ዕንሰ ሐሳብ እውነተኛ ቅርፅ እና ይዘት በማይታየው የላይኛው ዓለም (the world of being/ Nuomos) የሚገኝ ሲሆን በዚህ ዓለም (The world of becoming/ Phenomenon) ያለው ፍቅር የተበረዘ እና ያደፈ በመሆኑ እውነተኛ ይዘቱን እንዲያገኝ ወደ እውነተኛው የላዕላይ ዓለም ፍቅር መጠጋት ወይም መሳተፍ አለበት።

በመሆኑም መልካም ምግባር በሙሉ ወደ እውነተኛው ዓለም የሚደረግ የልዕቀት ጉዞ ወይም የፍጹምነት ተሳትፎ ነው። በተመሳሳይ ለአሪስጣጣሊስ ሰዎች እውነተኛውን የሞራል ፍጽምና ሕይወት ሲኖሩ “Eudaimonia” ያገኛሉ፤ ይህ ቃል “ፍስሃ” ወይም “ፍካት” ሊባል ይችላል። ምግባረ ሰናይ ሕይወት የሚሰጠው “ፍስሃ” አለ፤ ይህ ቃል “Flourishing” በሚልም ይገለፃል። ሞራላዊ ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች ያብባሉ፣ ይፈካሉ፣ ሀሴትን ይጎናፀፋሉ ወዘተ። ይሁን እንጂ ሞራላዊ የሚሆኑት ሀሴትን ለማግኘት ሳይሆን፤ ሞራላዊ በመሆናቸው ሀሴትን እንደሚያገኙ ሊሰመርበት ይገባል።

ጠቀሜታዊነት

‘‘መጠኑ ሰፌ ዴስታ ፤ ሉብዙ ቁጥር ሕዝብ’’

የዚህ ፍልስፍና አባት ታዋቂው እንግሊዛዊ ፈላስፋ ጀርሚ ቤንታም(1747-1832 GC) ነው። ቤንታም ለእንግሊዝ ሕግና ፖለቲካዊ ፍልስፍና ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። የጀርሚ ቤንታም ተጽዕኖ ጥልቅ ከመሆኑ የተነሳ አፅሙ ደርቆ ሕዝብ እስከ ዛሬ እንዲጎበኘው ተደርጓል። በሕይወት ዘመኑ ሲኖር ግን በራሱ እጅ ያረቀቀው የወንጀለኞች እስር ቤት ዲዛይን ጸድቆ እንዲገነባ ከፍተኛ ውትወታ ሲያደርግ ቢኖርም የዚህ ማረሚያ ቤት ያለመገንባት ቅስሙን እንደሰበረው ብዙዎች ይስማማሉ። ቤንታም በተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና የሚስማማ ከመሆኑም ባሻገር ኢ-አማኝ (Atheist) ነበር። ከእርሱ ጎልፈት በኋላ የእርሱ ደቀመዝሙር የነበረው ስቲዋርት ሚል የእርሱን መሠረታዊ ፍልስፍና ደግፎ አንዳንድ ትንታኔዎቹን በመንቀፍ የጠቀሜታውያን (Utilitarian) የሞራል ፍልስፍና ይበልጥ እንዲስፋፉ አድርጓል።

> Nature has placed mankind under the governance of two sovereign masters, *pain* **and** *pleasure.* **It is for them alone to point out what we ought to do, as well as to determine what we shall do.** On the one hand the standard of right and wrong, on the other the chain of causes and effects, are fastened to their throne. They govern us in all we do, in all we say, in all we think: every effort we can make to throw off our subjection, will serve but to demonstrate and confirm it. In words a man may pretend to abjure their empire: but in reality he will remain subject to it all the

> while. The *principle of utility* recognizes this subjection, and assumes it for the foundation of that system, the object of which is to rear the fabric of felicity by the hands of reason and of law. Systems which attempt to question it, deal in sounds instead of sense, in caprice instead of reason, in darkness instead of light[8].

ለቤንታም የሰው ልጅ በሁለት ጌቶች ስር ይገዛል፤ ደስታና ሐዘን/እርካታ እና ስቃይ። በቅድሚያ ሰዎች በእነዚህ ሁለት ጌቶች እየተገዙ እንደሚኖሩ ማመን ይጠበቅባቸዋል። የጠቀሜታዊን የሞራል ፍልስፍና መሠረት ይህ እሳቤ ነው። እያወቅነውም ሆነ ሳናውቀው፤ ፈልገንም ሆነ ሳንፈልግ እነዚህ ሁለት ጌቶች ሕይወታችንን ይገዙታል። ለዚህ የሞራል ፍልስፍና መዳበር ከጀርሚ ቤንታም ቀጥሎ የተነሳው የቤንታም ወዳጅ ስቱአርት ሚል ጠቀሜታዊ የሞራል ፍልስፍና እንደሚያትተው የሰው ልጆች ተግባር ወይም ባህሪ ሞራል መሆን ወይም አለመሆኑን ማወቅ የምንችለው በሚሰጠው ተጨባጭ ጥቅም ነው። አንድም ምግባር ለአድራጊው ወይም ከዚያ ተርፎ ላሉ ሰዎች ምንም ዓይነት ጥቅም የማያስገኝ ከሆነ ሞራላዊ ተግባር አይደለም።

የጠቀሜታዊ የሞራል ፍልስፍና ሲጠቀለል **"መጠነ ሰፊ ደስታን ለብዙ ቁጥር ሕዝብ የሚሰጥ"** በሚል ነው። ምክንያቱም ደስታ መልካምና በራሱ የሰው ልጆች ግብ ሊሆን የሚገባ ጉዳይ ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ ግለሰብ ተግባሩን መመዘን ያለበት በዚህ ድርጊት ከፍተኛ ደስታን ላገኝበት እችላለሁ ወይ? በሚል መለኪያ ብቻ ነው። ሰዎች በዚህ ድርጊታቸው ደስተኛ እየሆኑ ሲሄዱ የእነሱ ደስታ ተደምሮ ማኅበረሰባዊ ደስታን ይፈጥራል።

---

8 Jeremy Bentham, *An Introduction to the Principles of Morals and Legislation* (1823), Ch. 1 ; Of the Principle of Utility, London: T. Payne and Sons, p.6

"Extracts from Bentham's Commonplace Book", in *Collected Works*, x, p. 142; He credits Priestley in his *Essay on the First Principles of Government* (1768) or Beccaria with inspiring his use of the phrase, often paraphrased as «The greatest good for the greatest number", but the statement "the greatest happiness for the greatest number" actually originates with Francis Hutcheson, in his *Inquiry concerning Moral Good and Evil* (1725) [9]

ቤንታም በዚህ ፍልስፍና የሚያምነው በጥብቅ ከማመኑ የተነሳ "መጠነ ሰፊ ደስታ ለብዙ ቁጥር ሕዝብ" የሚለው ፍልስፍናውን ለመለካት "Felicific Calculus/ፌሊሲፊክ ካልኩለስ" የተባለ የሒሳብ ቀመር አዘጋጅቶ ነበር በዚህም መሠረት አሥራ ሁለት የስቃይ አይነቶችን እና አሥራ አራት የደስታ /እርካታ አይነቶችን የለየ ሲሆን እያንዳንዱ ድርጊት በተለያዩ ሁኔታዎች የሚያስገኘውን የስቃይ ወይም እርካታ ደረጃ ለመለካት የሚቻልበትን አሠራር ዘርግቷል። ከዚህ የምንረዳው ቤንታም ይህንን አስተሳሰቡን የምር ይከተል እንደነበር ነው፤ ምክንያቱም ይህ መርህ በተለያዩ መንግስታዊ የሕግ ማዕቀፎች እንዲካተት ከፍተኛ ጥረት ያደርግ ነበር።

በኋላ ላይ የሚል ጠቀሜታውያንን "የመርህ ጠቀሜታዊነት" እና " የድርጊት ጠቀሜታዊነት" በማለት ለይቷቸዋል። መርህ ጠቀሜታውያን አንድ ድርጊት ምንም እንኳ ከፍተኛ ደስታን የሚያስገኝ ቢሆንም በመርህ ደረጃ ኢ- ሞራላዊ ከሆነ ጥቅም አልባ እንደሆነ ሲያስረዱ የድርጊት ጠቀሜታ ግን ድርጊቱ ከፍተኛ ደስታ / እርካታ እስካስገኘ ድረስ አድራጊው ድርጊቱ ኢ-ሞራላዊ ስለመሆኑ መጨነቅ እንደሌለበት ያስረዳል። ለሚል ትክክለኛው መንገድ መርህ ተኮር ጠቀሜታዊ የሞራል ፍልስፍና ነው። እነዚህ

9 *The Collected Works of Jeremy Bentham: Deontology,* Amnon Goldworth(ed), (1983) p. 309

ፍልስፍናዎች በአውሮፓ ውስጥ በተነሱ የሕግና የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ላይ ቀላል የማይባል ተፅእኖ ያሳረፉ እንደመሆናቸው እንደ ዋዛ ልናያቸው አይገባም።

ጠቀሜታዊ የሞራል ፍልስፍና ዘመናዊ ወይም በቅርብ ግዜ ከተፈለሰፉት አስተምህሮዎች አንዱ ነው። ጠቀሜታዊ የሞራል ፍልስፍና ግላዊ፣ ቡድናዊ እና መንግስታዊ ገፅታዎች ሊኖሩት ይችላል። እንደ ግለሰብ አንድ እናት በእርግዝናዋ ወቅት በውስ ያለው ህፃን የማይድን በሽታ ካለበት ልታስወርደውና የህፃኑን የወደፊት ስቃይ እና የራሷንም ድካም ልታስወግድ ይገባል ወይስ ወልዳው የህይወቱ ፉርቱና የሚሰጠውን መጠበቅ ይገባታል? በመኪና አደጋ ምክንያት ራሱን ስቶ ለአንድ ዓመት አልጋ ላይ የዋለን ሰው የምህረት እረፍት እንዲያደርግ የሕይወት መስመሩን መቋረጥ ሞራላዊ ነው? መንግስት በሽብር የሚጠረጥራቸውን ሰዎች በቁጥጥር ስር አውሎ መረጃ ለማግኘት ሲል ኢ-ሰብዓዊ በሆነ መንገድ ቢደበድባቸው የአብዛኛውን ሰው ሕይወት ለማትረፍ እስከሆነ ድረስ የመንግስት ድርጊት ኢ-ሞራላዊ ሊባል ይችላል ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ።

በአሁን ዘመን ያሉ መንግስታዊ አስተዳደሮች በአብዛኛው የሚከተሉት ይህንኑ የሞራል ፍልስፍና መሆኑ አያጠረጥረም። ይሁን እንጂ ሰዎችን ሁልጊዜም ቢሆን እንደ መንገድ እና ሂደት (Means) እንጂ ራሳቸውን የቻሉ የመጨረሻ ግብ አድርጎ አለማየት አሁን የምንኖርበት ካፒታሊስታዊ ዓለም የሚዳክርበትን የሞራል፣ የአካባቢ ብክለት፣ አስከፊ ድህነት፣ ሽብርተኝነት፣ ርሃብ እና ፖለቲካዊ አለመረጋጋት ፈጥሯል ወይም እንዲፈጠር አግዟል ሊባል ይችላል። ሰዎችን ለተወሰነ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግብ መጠቀሚያ ማድረግ ምናልባት በእጅ ያለውን አጣዳፊ ተግዳሮት ለመወጣት ሊረዳ ይችል ይሆናል፤ በረዥም ጊዜ ሂደት ግን ማኅበረሰብን የሚበዘብዝ ስርዓት ከመፍጠር ወደኋላ አይልም። በዓለማችን የምናየው አብዛኛው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ቀውስ መሠረቱ ጠቀሜታዊ የሞራል ፍልስፍና ከሚገባው በላይ በመለጠጥ ጥቅም ላይ

ከማዋል የመነጨ ነው። ምናልባትም የዚህ ሞራል ፍልስፍና መሥራች እና አቀንቃኝ የነበሩት ቀደምት ምሁራን ካሰቡት እና ካለሙት በላይ ተለጥጦ በተግባር ላይ እየዋለ ስለመሆኑ አያጠራጥርም። በመሆኑም ሁሉም አካል የሚከተለውን የሥነ-ምግባር መርህ በጥልቀት የሚፈተሽበት ዘመን ላይ መሆናችንን መገንዘብ ይኖርብናል።

ግዴታዊነት

"ውጤት ከሚደት አይበልጥም"

ኢማኑኤል ካንት (1724-1804) የዚህ ሞራል ፍልስፍና መሥራች ነው። ካንት በአውሮፓ የፍልስፍና ታሪክ ውስጥ ጉልህ አሻራ የጣለ ከመሆኑ የተነሳ አንዳንዶች የአውሮፓ ፍልስፍና ታሪክን ቅድመ ካንት እና ድህረ ካንት በሚል ይከፍሉታል። ካንት በዲበአካላዊነት፣ በትምህርት፣ በአብርሆት በእውቀት ፍልስፍናዎች የራሱን አሻራ ለማሳረፍ ችሏል። በወቅቱ ውስብስብ እና ከባድ ከተባለው የዲበአካላዊ ፍልስፍና ድርሳኑ እስከታችኛው ማኅበረሰብ ድረስ የተነበበለትን "አብርሆት ምንድነው?" የሚለውን ታዋቂ ጽሁፉ ድረስ ጠቃሚ ሐሳቡን ለዓለም አበርክቷል።

በዚህ ክፍል ስለሞራል ፍልስፍናው ለማንሳት እንሞክራለን። ለካንት የሞራል ሕይወት የምክንያት እና ግዴታዊ ኃላፊነትን የመወጣት ጥምረት ነው። ሁሉም ሰዎች የኃላፊነት ግዴታቸውን ሲወጡ ምክንያታዊ በሆነ የሕይወት መስመር እንደሚመሩ ይጠቁማል፡ ምክንያቱም እንስሳት ተግባራቸውን በደመነፍሳዊ ስሜት እንጂ በአመክንዮ እና የግዴታ ስሜት አያስደግፉም። የሰው ልጅ ግን በአንድ ዓይነት የሞራል ግዴታ ስር ነኝ ብሎ ራሱን በፍላጎት የሚያስገዛ ብቸኛ ፍጡር ነው። እውነተኛ የሞራል ሕይወትን መምራት ማለት ሞራላዊ ግዴታን መውጣት ማለት ነው።

በመሆኑም የሞራል ግዴታ(Categorical Imperative) ሁሉን

አቀፋዊና አጠቃላይ መሆን አለበት። አንድ ሰው ተግባሩን ሲፈጽም ዓለም ዓቀፋዊ የሆነ ሕግ አውጭ አካል መሆኑን እያሰበ እና ይህ ተግባር በሁሉም ሰው እና በሁሉም ቦታ ተፈጻሚ ሊሆን መቻሉን እየመረመረ መሆን አለበት። ይህም ማለት ራሱን የሚያስገዛበት የሞራል መርህ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የሰው ልጅ የሚስማማ እና በሁሉም የሰው ልጅ ያለምንም ችግር ሊፈጸም የሚችል መሆኑን እርግጠኛ መሆን መቻል አለበት።

ለካንት ሰዎች እና የሚፈጽሙት ሞራላዊ ተግባሮች በራሳቸው እንደግብ ሊታዩ ይገባል እንጂ ወደ ግብ ሊያደርስ የሚችሉ መንገዶች መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ ልንከውናቸው አይገባም። ሰዎችን ስንቀርብ እና ከእነርሱ ጋር ልዩ ልዩ የሕይወት መስተጋብር ስንፈጽም በራሳቸው ፍጹም የሆኑ ግቦች እንደሆኑ እያሰበን እንጂ እነሱን በመጠቀም አንድ ዓይነት ትርፍ አገኛለሁ ብሎ ማሰብ ኢ-ሞራላዊ ምግባር ነው።

> It is possible that whilst you have honestly answered Yes to the murderer's question, whether his intended victim is in the house, the latter may have gone out unobserved, and so not have come in the way of the murderer, and the deed therefore have not been done; whereas, if you lied and said he was not in the house, and he had really gone out (though unknown to you) so that the murderer met him as he went, and executed his purpose on him, then you might with justice be accused as the cause of his death. For, if you had spoken the truth as well as you knew it, perhaps the murderer while seeking for his enemy in the house might have been caught by neighbours coming up and the deed been prevented[10].

10 Immanuel Kant, Metaphysics of Morals, 1797, Translated by Mary J. Gregor, Cambridge University Press, 1991

ኢማኑኤል ካንት ምሳሌ ያቀርባል፤ በርህ ላይ ቆመህ ደጆን እና ወጪ ወራጁን እየታዘብክ ሳለህ ድንገት አንድ ነፍሰ ገዳይ ቆንጨራውን እያወዛወዘ አጠገብህ ይድርስና ከቤትህ ውስጥ በእንግድነት ያሳደርከውን ሰው ለመግደል እያፈላለገው መሆኑን ይነግርሃል። በመቀጠልም ሊገድለው የሚያፈላልገውን ሰው ካየኸው እንድትተባበረው ይጠይቀሃል። በመደበኛው ቀን ቢሆን ከቤትህ ያረፈን እንግዳ አውጥቶ ለነፍሰ ገዳይ መስጠት ተገቢ አይሆንም፤ ግን ደግሞ መዋሸትም ቢሆን እንደ ዓለም ዓቀፍ የሕግ አውጪ ሲታይ ሁልጊዜ ሊፈጸም የሚገባ ተግባር አይደለም። ለነፍሰ ገዳዩ ዋሽተህ እንግዳህ ድንገት ሲወጣ ተገናኝተው ነፍሰ ገዳዩ ጉዳት ቢደርስበት፤ ዋሽተህም የሰው ነፍስም እንዲጠፋ ከማድረግ ያልተቆጠብክ በመሆኑ ሁለት ጥፋት ፈጽመሃል። እውነቱን ተናግረህ ቢሆን ግን ነፍሰ ገዳዩ ቤትህ ውስጥ ገብቶ እንግዳውን እየፈለገ ሳለ በጎረቤቶችህ ትብብር በቁጥጥር ስር ሊውል ይችል ነበር።

በመሠረቱ ከመልካም ምግባሮች ሁሉ ተቀዳሚ የሚሆነው ቅን ሐሳብ (good will) ነው፤ ሌሎች ምግባሮች መልካም ቢሆኑ እንኳ ለክፉ አላማ ልንጠቀማቸው እንችላለን ለምሳሌ "ታታሪነት" መልካም ባህሪ ቢሆንም ሰዎች ለተሳሳተ አላማ ታታሪ ከሆኑ የምግባራቸው ውጤት ኢ-ሞራላዊ መሆኑ የማይቀር ነው። ቅን አሳቢነትን ግን ለክፉ አላማ ማዋል የማይቻል በመሆኑ በራሱ እንደ ግብ ሊታይ ይችላል። በመሆኑም ሞራላዊ ተግባሮች በሙሉ በቅን አሳቢነት ላይ ከተመሠረተ ግዴታ ሊመነጩ ይገባል። የሞራል ግዴታዎችም ቢሆኑ ለሁለት መከፈላቸው አልቀረም። ምናባዊ የሞራል ግዴታ እና ፍጹማዊ የሞራል ግዴታዎች ናቸው።

ምናባዊ የሞራል ግዴታ (Hypothetical Imperative) አንድ ሰው ግዴታውን ለተመረጡ ሁኔታዎች ሲል ቢቀይር ሊፈቀድለት ይገባል የሚል ሲሆን ከድርጊቱ ጀርባ ግዴታ ሳይሆን ፍላጎት ብቻ በመኖሩ አድራጊው ካሰኘው ሊተወው ይችላል።

ፍጹማዊ የሞራል ግዴታዎች ሁልጊዜም ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው እና በሁለቱ መሀከል ግጭት ቢነሳ እንኳን ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ካንት ይገልጻል። በመሆኑም ለካንት መልካምነት እራሱን በፍቃድ እና በቅን አሳቢነት ፍጹማዊ ለሆነ የሞራል ግዴታ ማስገዛት ነው። ይህ የሞራል ግዴታም ሁሉንም ሰዎች እኩል የሚያይ፤ ሁሉንም ሰዎች እንደ ግብ የሚገነዘብ ነው። በዚህ የሞራል ፍልስፍና የሚገዛ ሰው ሁልጊዜም ቢሆን የኔ ድርጊት ለሰው ልጆች ሁሉ ሕግ ሊሆን ይችላል ወይ? ብሎ ራሱን መጠየቅ ይኖርበታል።

ታላቁ የጀርመን ፈላስፋ አማኑኤል ካንት የሚታወቀው በዲበአካላዊነት እና በሞራል ፍልስፍናው ቢሆንም ከዚሁ በተጨማሪ ስለ ሕግ እና የሞራል እሳቤዎች ልዩነት በሰፊው ዕፏል። ካንት ማኅበረሰባዊ ድንጋጌዎችን በሁለት ይከፈላቸዋል። የሕግ ድንጋጌዎች እና ሞራላዊ ድንጋጌዎች የሚባሉት ናቸው። ሞራላዊ ድንጋጌ አንድን ድርጊት አስገዳጅ የሚያደርገው የአድራጊው ምክንያት- ድርጊት (Motive) ግዴታ ሳይሆን ፍላጎት ሲሆን ነው፤ ምክንያቱም ሰዎች በሞራል ተነሳስተው አንድን ድርጊት የሚያደርጉት ተገደው ሳይሆን ፈልገው ነው።

ከዚሁ በተቃራኒ የሕግ ድንጋጌዎች (Legal legislations) ላይ የተመረኮዘ ድርጊት ምክንያት የሚያደርገው ፍላጎት ሳይሆን ቅጣትን ነው። በመሆኑም በሕግና በሞራል መሀከል ያለውን ልዩነት ሲያስረዳ መሠረት የሚያደርገው ምክንያተ- ድርጊትን (Motive) ነው። የሕግ ምክንያተ- ድርጊት ቅጣት ሲሆን የሞራል ግን የራስ ተነሳሽነት እና ፍላጎት ናቸው። ይሁን እንጂ ከዚህ አጠቃላይ ከሆነ መስፈርት በተጨማሪም አንድ የሕግ ስርዓት ሊያሟላ ይገባቸዋል የሚላቸውን ምክንያቶ በዝርዝር አስቀምጧል። ሕግጋት ማለትም ከላይ የሕግ ድንጋጌዎች (Legal legislation) ያልናቸው በቅድሚያ ታሳቢ የሚያደርጉት በሁለት ሰዎች መሀከል ያለን ተነፃፃሪ የሕግ ግዴታን መሆን አለበት ይህ ተነፃፃሪ የሕግ ግዴታ ከውል ወይም ከሕግ ሊመነጭ ይችላል። ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የውል ሰጪና ውል ተቀባይ ወይም የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ነው።

በሁለተኛ ደረጃነት ያለው መስፈርት በዚህ ተነፃፃሪ ግዴታ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ዓለም አቀፋዊ ከሆነ መርህ ጋር እሰካልተጋጨ ድረስ ያሻቸውን የማድረግ ሙሉ ነፃነት አላቸው፤ ይህ ማለት በዚህ ግዴታ ተይዘው እስካሉ ድረስ ከዚሁ ተነፃፃሪ ግዴታም ጋር ሆነ በተለየ ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑ ድርጊቶቻቸው ላይ ማንኛውም ወገን ተፅዕኖ ሊያሳርፍባቸው አይችልም ይህንን ስንል ግን የነሱም ድርጊት ቢሆን ዓለም አቀፋዊ እና አጠቃላይ (Universal) ከሆነ ተፈጥሯዊ ሕግ እና መርህ ጋር መጋጨት የለበትም እዚህ ጋር ካንት የተፈጥሮ ሕግን እንዴት ከሕግ ፍልስፍናው ጋር እንዳዋሃደው መገንዘብ ይኖርብናል። በስተመጨረሻ እነዚህ በተነፃፃሪ ግዴታ ውስጥ ያሉ ሰዎች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ አንደኛው ተዋዋይ ወገን ሌላኛውን ተዋዋይ ወገን በሕግ የማስገደድ መብት ይኖረዋል። በመሆኑም ከሕግ የሚመነጨው ቅጣት ወይም ግዴታ እንዲሟላ እነዚህ መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል።

ለሞራል ግዴታ ግን እንደዚህ ዓይነት ግዴታ ሳይሆን ቀደም ብለን ስለ ግዴታዊ የሞራል ፍልስፍና የጠቀስነውን መስፈርት መሟላት በቂ ነው። ይህም ማለት ሰዎች ሌሎች ሰዎችን ጥቅማቸውን የሚያሟሉባቸው መሣሪያዎች አድርገው ማየት ሳይሆን በራሳቸው ፍጹም የሆኑ ግቦች እንደሆኑ በማሰብ እንዲሁም ድርጊቶቻቸው በሁሉም ቦታ ለሁሉም ሰዎች እኩል ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በማሰብ ሊፈፅሙ ይገባል። በጠቃላይ ለካንት ሕግ በተነፃፃሪ የሕግ ግዴታ እና ግንኙነት ውስጥ ያሉ ሰዎች አንደኛው ወገን ሌላኛውን ወገን አጠቃላይ ከሆነ የተፈጥሯዊ ሕግ (Universal Law) አንፃር በመመርኮዝ የሚያስገድድበት ስርዓት እና የሁሉም ሰው ድርጊት በዚህ መርህ እስከተመራ ድረስ እኩል የሆኑ የነፃነት መብቶች (Freedom of equal rights) ተጠቃሚ እንደሚሆን የሚደነግግ ስርዓት ነው።

ሕግ እና ፍትሕ

“ሕግ ፍትሕን የምናገኝበት መሣሪያ ነው”

በሕግና ፍትሕ መሀከል የምክንያት እና ውጤት ግንኙነት መኖሩን ልንዘነጋ አይገባም። ፍትሕ የሕግ ውጤት እና አላማ ሲሆን ሕግ ደግሞ ፍትሕን የምናገኝበት ምክንያት እና መንገድ ነው። ይሁን እንጂ ሁሉም ሕጎች ወደ ፍትሕ አይወስዱም አንዳንድ ሕግጋት ከፍትሕ እና ርትዕ ጋር ይጋጫሉ። በዚህ ጊዜ ሰዎች መንግስት ለሚያወጣቸው ሕግጋት ባለመገዛት አመጽ እና አብዮት ያስነሳሉ። በመሆኑም “ፍትሕ” የሚባለውን ጽንሰ ሐሳብ መተርጎም እና መበየን ይኖርብናል። ፍትሕን መተንተን እና ማስረዳት ፍልስፍና ከተጠነሰሰበት ቀን ጀምሮ የሚያከራክር እና የሚያጨቃጭቅ ጉዳይ እንደሆነ አለ።

ፍትሕን ለሁሉም ሰዎች ባህል፣ ቋንቋ እና ዘመን በሚመች መልኩ መተርጎም እጅግ ከባድ ተግባር ነው። ለዚህም ምክንያት አፍላጦን የጻፈው ታላቅ ድርሳን “ሪፐብሊክ” የሚጀምረው ሶቅራጥስ ከሁለት ወዳጆች ጋር ከአንድ ስርዓተ አምልኮ እየተመለሱ ሳለ በነፋሻማ የባህር ዳርቻ አጠገብ እየተጓዙ “ፍትሕ” ምን ማለት እንደሆነ ሲጠይቃቸው ነው። ይህም የሆነው ፍልስፍና ትክክለኛውን መልስ በማግኘት ሳይሆን ትክክለኛውን ጥያቄ በመጠየቅ የሚገኝ ሐሳብ በመሆኑ ነው። ፍትሕን የሚቃረኑ ሕግጋትን መቃወም ፍትሐዊ ነው? ፍትሕን የሚቃረኑ ሕግጋትን በምን እናውቃለን?

ፍትሕን የሚቃረኑ ሕግጋት የምን ያህሉን ሕዝብ መብት ሲጥሱ ኢ- ፍትሐዊ ሊባሉ ይችላሉ? የፍትሕ ምንጭ እና ተርጓሚ ማነው? ለተማረው፣ ለባለሀብቱ እና ለፍትሕ መገዛት ማንን ይጠቅማል? እነዚህን መሰል ጥያቄዎች መንግስት እና የሕግ እና ፍትሕ አስተዳደር ከተቋቋመ

ዘመን ጀምሮ እየተጠየቁ እስከ ዛሬ ድረስ ዘልቀዋል። ለምሳሌ በግሪክ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ንጉስ ድራኮን የሚባል መሪ ለመጀመሪያ ጊዜ የአቴንስን ሕግጋት በጽሑፍ አስፍሮ በእንጨት ጣውላዎች ላይ በማስቀረጽ የአቴንስ ዜጎች ሁሉ የሚያውቋቸው ቦታዎች ላይ እንዳሰቀላቸው ይነገራል። ይሁን እንጂ እነዚህ ሕግጋት በጣም ከፍተኛ እና አስፈሪ ቅጣት የሚጥሉ ከመሆናቸው የተነሳ በስርቆት ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎችን ሁሉ በሞት የሚቀጡ ነበሩ። በመሆኑም አስከ ዛሬ ድረስ ለተፈጥሮ እና ሰብዓዊነትን የማይመጥኑ ኋላ ቀር ሕግጋት ሲያጋጥሙ የድራኮን ሕግጋት ይባላሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በመሀከለኛው ዘመን የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የክርስትና እምነትን ቀኖና እና ዶግማ ያፋለሱ መናፍቃን እና በጥንቆላ እና መተት ሥራ ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎችን በአደባባይ በንጉሶቹ ትእዛዝ ታቀጥላቸው ነበር፤ የሚገርመው ነገር ግን እነዚህ በጥንቆላ የተጠረጠሩ ሰዎች እና "መናፍቃን" ተብዬዎች ለዚሁ ጉዳይ በተቋቋመ የፍርድ ጉባኤ ፊት ቀርበው ራሳቸውን መከላከል ነበረባቸው።

እነዚህ የጠቀስናቸው ሕግጋት እና የፍርድ ሂደቶች አሁን በ21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ሆነን ስንመለከታቸው አሰቃቂ እና አስነዋሪ ቢመስሉም በዚያ ዘመን ለሚኖሩ የፍትሕ አካላት እና ሕጎች ግን መደበኛ የመንግስት አሠራር ነበሩ። በዚያን ዘመን የሚኖር አንድ በመናፍቅነት ተጠርጥሮ የተያዘ ግለሰብ ባልተቀበለው ሕግ እና የፍርድ ሂደት ፊት ቀርቦ ራሱን እና ቤተሰቡን ከአሰቃቂ ፍርድ ለማዳን ሲል ክሱን ተቃውሞ መከላከል ይጠበቅበት ነበር። ከእነዚህም የሩቅ ዘመን ትውስታዎች እና ታሪኮች ወደ ቅርቡ ብንመለስ እንኳ በተለያዩ የአፍሪካ ሃገራት የነበሩ የቀኝ ግዛት ሕጎች ነጮች እና ጥቁሮች ፤ጥቁሮች እና "የተለዩ" ጥቁሮች የሚለያዩበት እና አንዱን ከአንደኛው የተሻለ መብት በመስጠት የተከፋፈለ የአኗኗር ስልት አስፍነው ነበር።

እነዚህ ከፋፋይ ሕግጋት ከብዙ ትግል በኋላ በመላው ዓለም ኢ-ሰብዓዊ እንደሆኑ ዛሬ ቢታወቅም በዚያ ዘመን ግን ነጩም ጥቁሩም እውነት እና

ትክክል እንደሆኑ አድርጎ ይቀበላቸው ነበረ። ከዚህ የምንረዳው አንድ ትልቅ ቁም ነገር ሕግጋቱ በተለይም ሰው ሠራሽ ሕግጋት በዘመን እና በሳይንስ እድገት እየተሻሩና እየተለወጡ እንደሚሄዱ ነው። ፍትሕ ግን ዘመን አይሽራ ፅንሰ ሐሳብ ነው። በዚህ ዘመንም መንግስት ሕገ-ወጥ እና ወንጀል ብሎ የፈረጃቸው ተግባራት ከሃምሳ እና መቶ ዓመት በኋላ ግን የሚፈቀዱ እንዲያውም የሚበረታቱ ተግባራት ሊሆኑ ይችላሉ። በመሆኑም በሕግ እና ፍትሕ መሀከል ያለውን ግንኙነት ጥርት ባለ መልኩ አብራራቶ መበየን የሁላችንም ኃላፊነት ሊሆን ይገባል።

ፍትሕን ዘመን ተሻጋሪ በሆነ መንገድ ለመረዳት ልንተረጉመው የሚገባው ከሕግጋት ጋር በማያያዝ ሳይሆን ከእውነት ጋር በጥልቀት በማገናዘብ ነው፤ ምክንያቱም እውነት የሆነው ነገር ምን ጊዜም ፍትሐዊ ነው። እውነት ደግሞ ዲበአካላዊ የሆነ ይዘት እና ትርጉም አለው። እውነት ስለዲበአካላዊነት ካለን አመለካከት ይመነጫል። ሰውን መግደል የተሳሳተ እና እውነት አልባ ተግባር የሚሆነው ከዚሁም ጋር ተያይዞ ኢ-ፍትሐዊ እንደሆነ በማሰብ የምንከራከረው "ግድያ" የተሳሳተ ተግባር መሆኑን የምንከተለው ዲበአካላዊ ፍልስፍና የሚያመላክተን ከሆነ ብቻ ነው። አንዳንዶች እውነት የማይለወጥ እና የማያረጅ እንደሆነ ሲያስረዱ አንዳንዶች ደግሞ እውነት በጊዜ እና በዘመን የሚቀያየር እንደሆነ በማመን ይከራከራሉ። እውነት የሆነውን ነገር የምናውቅበት ፍልስፍና ደግሞ የእውቀት ፍልስፍና ይባላል።

በመሆኑም ፍትሕ በዓለም ዓቀፍ የሕግ ስርዓት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ይገለጻል። እነዚህም የሀብት ክፍፍል ፍትሕ ፤ሥነ-ስርዓታዊ ፍትሕ; የእርምት ፍትሕ ፤ የተሃድሶ ፍትሕ; የተፈጥሮ ሀብትና ጥበቃ ፍትሕ እና የመሳሰሉት ናቸው። ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ለአያሌ የፖለቲካ አብዮቶች ምክንያት የሆነ ነው። ጥቂቶች በብዙኃኑ ሀብት እና ጉልበት ተጠቅመው እየተንደላቀቁ ሲኖሩ ሰፊው ሕዝብ ደግሞ በድህነት አረንቋ ውስጥ ሊዘፈቅ ስለማይገባው መንግስት በሀብት ክፍ ካሉት በግብር፤

መዋጮ እና ቅጣት ሀብት እየሰሰበሰበ ለብዙኃኑ ሊያከፋፍል ይገባዋል በማለት ያስተምራል። ሥነ-ስርዓታዊ ፍትሕ በአብዛኛው የሚገለጸው በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ቢሆንም ለፍትሐብሔር ጉዳዮችም ጠቃሚ ነው።

በመሠረታዊነት ሕግ ከግቡና ውጤቱ ይልቅ ሂደቱ ፍትሐዊ ሊሆን እንደሚገባና በሀገርኛ አባባል "የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው" የሆነ አሠራር ኢፍትሐዊ መሆኑን ያስረዳል። በመሆኑም በወንጀል ሂደቱ አንድ ተጠርጣሪን በመደብደብ እና በመግረፍ የሚገኝ የእምነት ቃል በፍትሐዊ ሂደት ያልተገኘ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል። ፈረንጆቹ ይህንኑ ሐሳብ Due process of Law በማለት ይገልጹታል፤የፍትሕ ስርዓት ተገቢውን ሂደት ማለፍ ስለሚገባው በዚሁ መልክ የተገኙ ማስረጃዎችና ፍርዶች ብቻ ፍትሐዊ ናቸው ብለን ማመን አለብን። የእርምት ፍትሕ ከጉዳት እና ካሳ ጋር እንዲሁም ከወንጀል እና ቅጣት ጋር የሚገናኝ ነው። አንድ ሰው በእውቀትም ሆነ በቸልተኝነት በአንድ ሰው ላይ የወንጀል ድርጊት ከፈጸመ ተገቢ እና ተመጣጣኝ የእርምት እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል። ይህ እርምት የእርምት አላማ ማስተማርና ማረም ፤ መቀጣጫነት ፤ በቀል ወይም ማቀብ ሊሆን ይችላል። ሌላው በቸልተኝነት የተፈጸመ ጉዳት ቢሆንም እንኳ፣ በአንድ ግለሰብ ላይ የአካል ጉዳት ያደረሰ ሰው ለዚሁ ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ለተጎጂው ወይም ለቤተሰቡ መክፈል ይኖርበታል። በመሆኑም የእርምት ፍትሕ በወንጀል ወይም በጉዳት አማካኝነት የተዛባውን ማበረሰባዊ ሚዛን መልሶ ማቀናት ነው። የተሃድሶ ፍትሕ ግን ሰዎች ባደረሱት ጉዳት ልክ ቅጣት ሊደርስባቸው አይገባም ምክንያቱም ይህ የፍርድ ሂደት የአሸናፊ እና ተሸናፊ ስነ-ልቦና የሚፈጥር በመሆኑ ዘላቂ የሆነ ሰላም እና ፍትሕ ለማጎበረሰቡም ሆነ ለባለ ጉዳዮች አያመጣም።

በመሆኑም በእርቅ እና ድርድር ባለጉዳዮቹን በተቻለ መጠን ወደነበሩበት አኗኗር ልንመልሳቸው ይገባል ሲል ይከራከራል። የተፈጥሮ ሀብትና ጥበቃ ፍትሕ በበኩሉ ፍትሕ ለሰዎች ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮ ለሚገኙ እንስሶች፣

እጽዋት እና ግዑዛን ሁሉ ሊሠጥ እንደሚገባው ያስተምራል። በመሆኑም ሰዎች የአካባቢያቸው አስተዳዳሪ እንጂ ገዢዎች እና ባለመብቶች አይደሉም፤ ምክንያቱም ሰዎች ራሳቸው የተፈጥሮ አካል በመሆናቸው ተፈጥሮን የመበዝበዝ መብት የላቸውም። ይህ አይነቱ የገዢነት እና የበዝባዥነት አስተሳሰብ ሰው የዓለም ማዕከላዊ እንደሆነ አደርጎ ከሚያስብ አስተምህሮ የመነጨ በመሆኑ አሁን የምናየው አካባቢያዊ ብክለት ሊያስከትል ችሏል። ይሁን እንጂ ሰዎች የተፈጥሮ አካል እንደመሆናቸው ለተፈጥሮ ሕግጋት መገዛት አለባቸው። ምክንያቱም በአካባቢያቸው ያለውን የተፈጥሮ ሀብት በባለ አደራነት መጠበቅ ይገባቸዋል፣ የመንግስት ሕግጋትም ይህንኑ ሊያጸኑ አንደሚገባ አስተምህሮው ያረጋግጣል።

ምዕራፍ ሁለት

የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና

"ሕግ ተፈጥሯዊ ነው"

የሰው ልጆች መንግስት መስርተው በሕግ መተዳደር ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ የሚያወጧቸው ሕግጋት መሠረታቸው ተፈጥሮ ነው። ተፈጥሮ ስንል ግዑዙን እና ሕይወት ያለውን ሁሉ የሚያጠቃልል ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ እነዚህን ፍጥረታት ከሰራው ልዕለ-ኃያል ፈጣሪ ጋርም ይገናኛል። በመሆኑም ሰዎች በመንግስታቸው ውስጥ ወንጀልን ለመቆጣጠር፤ ንግድን ለማበረታታት እና የግለሰቦችን መስተጋብር ለማሳለጥ ከሚያወጧቸው ሕጎች ጀርባ ያለው እሳቤ እና የሞራል መርህ የተገኘው አስቀድሞም ቢሆን በተፈጥሮ ውስጥ በተቀመጠ ስርዓት ወይም ይህን የተፈጥሮ ስርዓት ከፈጠረው አምላክ እንደሆነ ፍልስፍናው ያትታል። በርግጥ የዚህ ፍልስፍና ተከታዮች በአብዛኛው አማኞች ቢሆኑም በአምላክ የማያምኑ ጥቂት የማይባሉ ሰዎች የተጥፈሮ ሕግ ከፈጣሪ የተሰጠ እንደሆነ አድርጎ ማሰብ እንደማይገባ ተናግረዋል፤ ጽፈዋል፤ አስተምረዋል።

> *እንስሳት እና አራዊት እኮ ሃይማኖት አያስፈልጋቸውም፤ አስርቱ ቃላት አይጸፍላቸውም፤ ገሃነመ እሳት አያስፈራቸውም፤ የመንግስተ ሰማያት ተስፋ አያስፈልጋቸውም። የተፈጥሮን ሕግ አፈረሱ ተብሎ ሲከሰሱና ሲወቀሱ ኸዶ ሰምተን አናውቅም። ግን እስቲ ወደ ሰው ልጅ ሕይወት አተኩረን እንመልከት። ከሁሉ አስቀድሞ የሰው ልጅ*

ክፉ እና በጎ ለይታ የምታውቅ ነፍስ አለችኝ ብሎ ይኮራል። ከዚያ በላይ ደግሞ ይቺ አዋቂ ናት የተባለችው ነፍሱ እንዳትሳሳትና ከትክክለኛው የእውነት መንገድ እንዳትወጣ አስርቱ ቃላት፤ ስድስቱ ቃላት፤ ቁራን፤ ቬዳ፤ ጊታ ተጽፎላታል። ግን ይህ ሁሉ ጥንቃቄ ሳለ የሰው ልጅ ታሪክ ከአዳምና ሄዋን ጀምሮ የሕግ አፍራሽነት ታሪክ ነው[11]።

ይህ የሕግ ፍልስፍና የሰው ልጅ በቅድሚያ ከመሠረቱት የሕግና የፖለቲካ ፍልስፍናዎች ስር የሚመደብ ነው። የሰው ልጅ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ታግዞ እንደዛሬ ተፈጥሮን በክፉም ሆነ በደግ ለመቀየር እንደሚችል ሳያስብ እና ሳይችል በፊት በተፈጥሮ ሕግጋት ስር እንደሚገዛና ከዚያም አልፎ ይህንን የተፈጥሮ ሕግ የፈጠረ እና የሚዘውር አንድ ሚስጥራዊ ኃይል መኖሩንም ጭምር ያምን ነበር። በመሆኑም ተፈጥሮን እና ተፈጥሯዊ ነገሮች ማምለክ እና መማፀን እንደልማድ ሆኖ ዛሬም ድረስ በ21ኛው ክፍለ ዘመን በአንዳንድ ባህሎች ይስተዋላል። ይህ የሕግ ፍልስፍና ሕግጋት በተፈጥሮ የተሰጡ በመሆናቸው ከሰው ልጆች ሊነጠሉ የማይችሉ እና ሊገረሰሱ የማይገባቸው ውስጣዊ ባህሪያት እንደሆኑ ይገልጻል። በመሆኑም የሰው ልጆች የሚያወጧቸው ሕግጋት ከእነዚህ የተፈጥሮ ባህሪያት ጋር ሊጣረሱ አይገባም። የመንግስት ሕግጋት የተፈጥሮ ሕግጋት ነፀብራቅ መሆን አለባቸው። የተፈጥሮ ሕግጋት በሰው ሠራሽ ስርዓተ መንግስት ውስጥ የማይተካ ሚና ሊኖራቸው እንደሚገባ ያሳየው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እና ያስከተለው የሰብዓዊ መብት ቀውስ ነበር። በጀርመን ሀገር የመንግስት ስልጣንን የተቆጣጠረው ሂትለር መራሹ የናዚ ፅንፈኛ ቡድን በጀርመን እና በአውሮፓ የሚገኙ "አናሳ" ህዝቦችን ማጥራት የጀመረው ስልጣን መቆጣጠር ከመጀመሩ ነበር። ለዚህ የዘር ማፅዳት አጀንዳው እንዲያግዘው በሀገሪቱ ያሉ ሕግጋትን በሙሉ አናሳ ህዝቦችን የሚያጥላሉ እና ለዘር ማፅዳት የሚያዘጋጁ አድርጓቸው ነበር።

---

11 ብርሃኑ ድንቄ፤ አልቦ ዘመድ -ታሪካዊ ፈጠራ ፤ የህትመት ዓመት አልተጠቀሰም፤ ገጽ 18

በዚህም መሠረት መንግስታዊ ድጋፍ ባለው ጭፍጨፋ አይሁዶች፣ ጥቁሮች፣ ጂፕሲዎች፣ ኮሚዮኒስቶች እና ካቶሊኮች መጠኑ ይለያይ እንጂ "እንዲፀዱ" ተደርገዋል። ሰው ሠራሽ የመንግስት ሕግጋት ከተፈጥሮ ሕግጋት ጋር ሲጋጩ የመንግስት ሰራተኞች እና ተራ ዜጎች ምን ማድረግ አለባቸው? ይህንን ጥያቄ በጥልቀት የመረመረው ጉስታቭ ራድብሩክ (Gustav Radbruch) ሲሆን ሂትለር ወደ ስልጣን ከመምጣቱ በፊት በጀርመን የፍትሕ ሚኒስተር ሆኖ ይሰራ ነበር። ከናዚ መውደቅ በኋላ ባለስልጣናቶቹ በኑረንበርግ ችሎት (Nuremberg trials) ሲዳኙ አይቶ አንዲት በጣም አጭር ግን አነጋጋሪ ጽሑፍ[12] ለሰፊው ሕዝብ አቅርቧል። ለመሆኑ በናዚ ጀርመን የነበሩ ዳኞች ሰዎች የዘር ማፅዳት ሕጉን ተቃርነው እና ተከሰው ሲቀርቡላቸው ምን ማድረግ ነበረባቸው? ሲል ይጠይቃል።

የአንድ ሀገር ፍትሕ ስርዓት በሙሉ በመሠረታዊነት ከተፈጥሮ ሕግ ጋር ሲጋጭ ሕጋዊ መርህ አልባነት (Statutory Lawlessness) የሚከሰት በመሆኑ ዳኞች የተፈጥሮ ሕግን በመጥቀስ ቢቃወሙት ፍትሐዊ እንደሆነ በመጥቀስ ሞግቷል። አንድ የሕግ ስርዓት ለሕዝብ ጠቃሚ(Utility) ፣ ተፈፃሚነት (Certainty) እና ተፈጥሯዊ ፍትሕ (Justice) ሊኖረው ይገባል፣ እነዚህ ሦስት ነገሮች ካልተሟሉ አንድ የፍትሕ ስርዓት በበቂ ሁኔታ ተሟልቷል ሊባል እንደማይቻል አስረድቷል። በፍትሕ ስርዓት ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁልጊዜ የእነዚህ ሦስት ነገሮች (The Radbruch Formula) በስርዓቱ ውስጥ እንደተመሰሉ ሊመረምሩ ይገባል።

ይህ አመክንዮ የኑረንበርግ ችሎት መርህ በመሆን አገልግሏል፣ ምክንያቱም ከዚያ በፊት በዘር ማጥፋት ወንጀል ተከሰው ዓለም ዓቀፍ ፍርድ ቤት የቆሙ ግለሰቦች ባለመኖራቸው ችሎቱ በምን ሕግ እንደሚዳኛቸው ግራ ተጋብቶ ነበር። ከ1948 በኋላ ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ

12 Radbruch, Gustav (2006). Translated by Litschewski Paulson, Bonnie; Paulson, Stanley. "Five Minutes of Legal Philosophy (1945)". *Oxford Journal of Legal Studies*

(UDHR) የተፈጥሮ ሕግጋት በየሀገሩ የፍትሕ ስርዓት ውስጥ እንዲሰርፅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

ሶፊስቶች እና አንጻራዊነት

"ሰው የነገሮች ሁሉ መለኪያ ነው"

ሶፊስቶች የሶቅራጥስ ዘመን ተጋሪዎች ነበሩ። በእነሱ እና በሶቅራጥስ መሀከል የከረረ ጥላቻ እንደነበር ሶቅራጥስ በሚሰነዝርባቸው ዱላ ቀረሽ ትችት መገመት ይቻላል። ሶፊስቶች ፍልስፍና ወይም ትምህርት በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ላይ የሚጠቅም ክህሎት ሊሰጠን ይገባል እንጂ እንደ ሶቅራጥስ እና ተከታዮቹ ውስብስብ የሆኑ ሐሳቦችን በመመርመር ሊጠመድ አይገባም ይላሉ። በተጨማሪም በዓለም ላይ ያሉ ነገሮች በሙሉ ለሰው ልጅ ሕይወት ጥቅም እንዴት ሊሰጡ እንደሚችሉ በማሰብ ሊሰሩ እንደሚገባ ለማሳየት እንደ ፕሮታጎረስ ያሉ ስቶይኮች "ሰው የነገሮች ሁሉ መለኪያ ነው" (Man is a measure of all things) በማለታቸው ይታወቃሉ።

በመሆኑም የተለያዩ ክህሎቶችን ለማስተማር ከተማሪዎቻቸው ገንዘብን ይቀበሉ ነገር፤ ይሁን እንጂ ገንዘብ ተቀብሎ ማስተማር ለሶቅራጥስ ፍልስፍናን እንደመሳደብ ያህል ነበር። በመሠረቱ ሶፊስቶች ለሰው ልጆች ጥቅም የሚሰጡ እንደ የንግግር ክህሎት፤ ጂኦሜትሪ፤ ሒሳብ፤ ሕግ፤ ፍልስፍና እና መሰል ትምህርቶችን እና ዘርፈ ብዙ ክህሎቶች (polymath) ስለሚያስተምሩ በሁሉ ነገሮች ውስጥ ገብተው መፈትፈታቸውን እና ሁሉን አዋቂ ነን ባይነታቸውን ሶቅራጥስ ይጠላው ነበር። ይሁን እንጂ የንግግር ክህሎት የሕግ አዋቂ ወይም ፖለቲከኛ ለመሆን እጅግ አስፈላጊ ስለነበር የሚሰጡት ስልጠና እጅግ አስፈላጊ ነበር።

> Each of these private teachers who work for pay, whom the politicians call sophists and regard as their rivals, inculcates nothing else than these opinions of the multitude which they opine when they are assembled and calls this knowledge wisdom. It is as if a man were acquiring the knowledge of the humors and desires of a great strong beast which he had in his keeping, how it is to be approached and touched, and when and by what things it is made most savage or gentle, yes, and the several sounds it is wont to utter on the occasion of each, and again what sounds uttered by another make it tame or fierce, and after mastering this knowledge by living with the creature and by lapse of time should call it wisdom, and should construct thereof a system and art and turn to the teaching of it, knowing nothing in reality about which of these opinions and desires is honorable or base, good or evil, just or unjust [13]

ሶፊስቶች በቁጥጥሩ ስር ያዋለውን አውሬ እንደሚያጫውት ግለሰብ ናቸው ይላቸዋል ሶቅራጠስ። አውሬውን እየነካኩ እና እየጎነተሉ ሲላቸውም እያጫወቱ እና እያታለሉ ምን እንደሚያስቆጣው፤ ምን እንደሚያስፈራው፤ ምን እንደሚሸውደው፤ ምን እንደሚያስደስተው የሚመዘግቡ ናቸው። ይሁን እንጂ አውሬው ምን እንደሚያስደስተው ማወቅ አውሬውን ማወቅ ማለት አይደለም፤ የሕዝቡን ሰሜት የሚቀሰቅሱ ነገሮች ማወቅ ማለት ሕዝቡን ማወቅ ማለት አይደለም።

አቴንስ የንግድ እና የባህል ከተማ እንደመሆኗ ብዙ ዓይነት የኑሮ አይነቶች፤ ፍልስፍናዎች እና ስርዓተ አምልኮዎች ይካሄዱባት ነበር። በመሆኑም ያልተገደበ የብዝሃ ሕግ ስርዓት ይፈጸምባት ነበር። በመሆኑም

13 Socrates in Plato, *The Republic*, 493, Translated by Jowett Benjamin.

የማይቀየሩ እና የማይለወጡ የተፈጥሮ ሕግጋት የአቴንስ የሕግ ስርዓት መሠረት ነበሩ ለማለት አይቻልም። ሕግ እና ሞራል የሚመነጨው በባህል ሕግ ውስጥ በመሆኑ ግሪኩም መጤውም የሚተዳደረው በዚሁ ስርዓት ነበር። ለሶፊስቶች በተፈጥሮ እና በማይዳሰሰው የሐሳብ ዓለም መሀከል ልዩነት መኖሩን ያምናሉ። በመሆኑም ፍልስፍናቸውን ከባድ አንጻራዊነት ተጭኖት ነበር።

ለእነርሱ እውነት አንጻራዊ በመሆኑ የተፈጥሮ ሕግጋት የማይቀየሩ እና የማይለወጡ መሆናቸውን አይቀበሉም ነበር። የፍልስፍናቸው ማዕከላዊ ሰው እንጂ የማይዳሰሱ ሐሳቦች አልነበሩም። ለሰው ልጆች ጥቅም እስካገለገለ ድረስ ሁሉም ነገር ሊለውጥ እና ሊስተካከል ይገባል። ሶፊስቶች የቅድመ ሶቅራጠስ ዓለምን የሚወክሉ በመሆኑ ሶቅራጠስ ለማይዳሰሱ ውስብስብ ሐሳቦች ቋሚ ብያኔ እና ትርጉም ለመስጠት ሲሞክር ምን ያህል ከእነርሱ አስተሳሰብ እንደራቀ መገመት እንችላለን። በአጠቃላይ የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና እንዲህ ዓይነቱን ተግዳሮት ተቋቁሞ ዛሬ የደረሰበት ከፍታ ላይ ሊደርስ ችሏል።

በምዕራቡ ዓለም "ሶፊስት" የሚለው ቃል በተለምዶ ግልብ እና ጥራዝ ነጠቅ እውቀት ያለውን ሰው ለመወከል ዛሬም ድረስ ጥቅም ላይ ይውላል። ሶፊስቶች የሚጠሉትን ያህል አስከፊ አስተምህሮ አልነበራቸውም። ተግባር ተኮር እውቀት ማስተማርም ሆነ ለትምህርት ማስከፈል በዚህ ዘመን የተለመደ እንዲያውም የሚበረታታ ጉዳይ ቢሆንም በአሁን ወቅት በዘመናችን የሚሰጥ ትምህርት እና አስተማሪዎች ሁሉ ሶፊስት እንደሆኑ አድርጎ ማሰብ አይቻልም። አብዛኞቹ ሶፊስቶች በገንዘብ እና በዝና የደለቡ እጅግ ተፈላጊ ሰዎች በመሆናቸው ብዙዎች ሶቅራጠስ ራሱ ከፍተኛ ታዋቂነት ሊያገኝ የቻለው ሶፊስት በመሆኑ እንደሆነ ያስቡ ነበር። ሶፊስቶች ከሚሰጡት ተግባር ተኮር ስልጠና አንዱ እና በወቅቱ እጅግ ተፈላጊ የነበረው የሙግት ጥበብ ነበር።

በወቅቱ በአቴንስ የሚኖሩ ዜጎች ልዩ ልዩ ክስ ተመስርቶባቸው በችሎት ፊት ሲቀርቡ የፍርድ ሸንጎውን ወይም የዳኛውን ቀልብ እንዴት መሳብ እንደሚችሉ ለማወቅ ስለሚችሉ ከፍተኛ ገንዘብ እየከፈሉ ከሶፊስቶች ተከታታይ ስልጠና ይወስዱ ነበር፤ አልያም ደግሞ ለሕዝብ አስተዳዳሪነት የሚወደዳሩ ሰዎች ሕዝቡን በንግግር ችሎታቸው ምን ያህል አሳምነዋል ወይም ምን ያህል ሰፊ ተወዳጅነት አትርፈዋል በሚለው ነጥብ በመሆኑ ብዙዎች የንግግር ችሎታቸውን ለመሳል ሶፊስቶችን ያፈላልጉ ነበር። በዚህም ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ እውቀትን ከሚሹ ፈላስፎች ይልቅ "ፀጉር ሰንጣቂ" ተከራካሪዎች እና በአፍቅሮተ-ንዋይ የነሆለሉ ተደርገው ይወሰዱ ነበር። ሶፊስቶች ክህሎትን እንጂ እውቀትን የማይሰጡ በመሆናቸው አፍላጦን የተደባለቀው እና ያልፀዳው የታችኛው ዓለም (The world of becoming) ወኪሎች አድርጎ ሲስላቸው፤ ፈላስፎች ግን እውቀት እና እውነት የሚሹ በመሆናቸው ንፁህ እና ላዕላይ የሆነውን ዓለም ለማወቅ የሚጥሩ አድርጎ ይስላቸዋል።

በዚህም ምክንያት የሚያራምዱት የአንፃራዊነት አመለካከት ሶቅራጠስ ከሚፈልገው እና አላማ አድጎ ከተነሳው ፍጹም የሆነውን እውነት እና እውቀት መፈለግ ጥረት ጋር የሚጋጭ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ሶፊስቶች ከቅድመ ሶቅራጠስ ፈላስፎች የሚለዩበት ነጥብ ደግሞ ዓለም ከምን ተሠራች? መጨረሻዋስ ምንድነው? በሚሉት ጥያቄዎች ባለመጨነቃቸው ነው። የቅድመ ሶቅራጠስ ፈላስፎች የምድር ስሪት ከውሃ፣ እሳት ወይም ሌላ ውህድ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ማጣራት የምርምራቸው ማዕከል አድርገው ይወስዱት ነበር። በዚህም ምክንያት ለሶፊስቶች "ፍትሕ ምንድነው?" የሚለው ጥያቄ ጉንጭ አልፋ ክርክር ነበር።

ስቶይኮች እና የተፈጥሮ ሕግ

"ዮምግባር ልዕቀት ስሜት አልባነት ነው"

ስቶይኮች የሮም ስልጣኔ ውጤቶች ናቸው። ፈጣሪ ወይም አምላክ ከተፈጥሮ ተለይቶ የሚገኝ ቢሆንም የዚህ መለኮት ፍንጣቂ በእያንዳንዱ ሰው ነፍስ ውስጥ የሚበራ እንደመሆኑ ሰዎች ሁሉ የመለኮትነት ተካፋይ መሆናቸውን ያምኑ ነበር። ይህ ከሩቅ ምሥራቅ ሃይማኖቶች ጋር መጠነኛ በሆነ መንገድ የሚመሳሰል አስተሳሰብ ስቶይኮች ለሰው ልጆች የሚሰጡት ክብር ምክንያት ነው።

ሰዎች ውስጥ የመለኮት ፍንጣቂ ስለሚገኝ ሰዎች መለኮት ካቋቋመው የተፈጥሮ ሕግ ጋር ለመስማማት አይቸረጉም፤ እንዲያውም ፈጣሪ ሕይወት ባላቸው ነገሮች ሁሉ ውስጥ ይኖራል የሚለው ፍልስፍና (pantheism) መነሻ እነርሱ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ ይገመታል። ስቶይኮች የሰው ዘር በሙሉ እኩል ክብር እንዳለው ከማመናቸው የተነሳ ሰፊ የወንድማማቾች ማኅበር ለመመስረት ያስቡ ነበር። በዚህም ምክንያት የስቶይኮች ቤተ አስተምህሮ እንደ ኢፒክቲተስ ዓይነት ባሪያ እና እንደ ኦሪሊየስ ዓይነት ንጉስ የሚከተሉት ፍልስፍና ነበር።

በመሠረቱ ምግባራዊ የሞራል ፍልስፍና ተከታዮች ቢሆኑም የሞራል ፍልስፍናቸው መሠረት የተለየ ነው። የፍልስፍናው መሠረት ሰዎች በደስታም ሆነ በመከራ ለሚመጣ ስሜት ተገዢዎች መሆን የለባቸውም፤ በመሆኑም ከስሜት የራቀ የሞራል ሕይወት ሊመሩ ይገባቸዋል ሲል ሰዎችም ቢሆኑ ከገንዘብ ፣ ሀብት፣ ስልጣን እና መሰል አላፊ የሰው ልጆች ፍላጎት ርቀው የሞራል ልዕቀት ለማግኘት መጣር እንደሚገባቸው ያስተምራሉ። ይህ ስሜት አልባ ምግባራዊ የሞራል ፍልስፍናን **አፓቲያ (Apathea)** በሚል ይገልፁታል።

> There goes with this a certain coldness in the Stoic conception of virtue. Not only bad passions are condemned, but all passions. The sage does not feel sympathy: when his wife or his children die, he reflects that this event is no obstacle to his own virtue, and therefore he does not suffer deeply. Friendship, so highly prized by Epicurus, is all very well, but it must not be carried to the point where your friend's misfortunes can destroy your holy calm. As for public life, it may be your duty to engage in it, since it gives opportunities for justice, fortitude, and so on; but you must not be actuated by a desire to benefit mankind, since the benefits you can confer — such as peace, or a more adequate supply of food — are no true benefits, and, in any case, nothing matters to you except your own virtue. The Stoic is not virtuous in order to do good, but does good in order to be virtuous. It has not occurred to him to love his neighbour as himself; love, except in a superficial sense, is absent from his conception of virtue[14].

ባጠቃላይ ምንም እንኳ ብዙ ድጋፍ እና ትችት ቢያስተናግዱም መለኮት ሕይወት ባለው ነገር ሁሉ ውስጥ እንደሚኖር ማመናቸው ለተፈጥሮ ሕግ የሚሰጡትን ከፍተኛ ቦታ ያሳያል። የተፈጥሮን ሕግ ማክበር ማለት ሰዎች በውስጣቸው ያለውን "ንዑስ-መለኮታዊነት" መቀበላቸውን እና ማክበራቸውን የሚያሳይ ነው። በመሆኑም ሰዎች ሁሉ አውቀውም ሆነ

14 Bertrand Russell, in *A History of Western Philosophy* (1945), Book One, Part III, Chapter XXVIII, Stoicism, p. 255-256

ሳያውቁት የተፈጥሮ ሕግ አካል ናቸው። መልካም ተግባር የሚያደርጉት ውስጣቸው ካለው የመለኮት ፍንጣቂ በመነሳት አንጂ መልካም አድራጊ ለመባል ወይም ሰናይ ምግባራቸው የሚያስገኝላቸውን ጥቅም ለመቋደስ አይደለም።

ከታላላቅ ስቶይኮች አንዱ የሆነው ሲሴሮ በሮም ሴኔት በሕግ ባለሙያነት እና ፈላስፋነት ረጅም ዘመን አገልግሏል። የግሪክ ፍልስፍናዎችን በጥልቀት በማጥናት ወደ ላቲን እንዲተረጎም ከማድረጉም አልፎ የላቲን መዝገበ ቃላትን አሰናድቷል። ከእርሱ በኋላ የላቲን ቋንቋ አጻጻፍ ስልትና የፍልስፍና ጦማር ዛሬም ድረስ በሕግና ፖለቲካ ዓለም ላይ ተፅዕኗቸው የጎላ ነው። ሲሴሮ የተፈጥሮ ሕግ ደጋፊ ከመሆኑም በላይ የስቶይክ ፍልስፍና እና የሕይወት ዘይቤ አራማጅ ነበር።

ስቶይኮች የሰው ልጅ ሕይወትን ደስታና ሐዘን/ ስቃይ እና እርካታ ከሚያደርሱበት የስሜት መዘበራረቅ እና የመንፈስ መታወክ ነጥሎ በእርጋታና በምን ይገደኝነት ተረጋግቶ ሊያጣጥማት ይገባል ብለው እንደሚያስቡ ቀደም ብለን አይተናል። የሲሴሮ የሕግ የፖለቲካ ጽሑፎች ከትምህርታዊ የምርምር ጽሑፍነታቸው በላይ ስነ-ጽሑፍዊ ውበታቸው አስደማሚ ነበር። በሚያሳዝን ሁኔታ ሲሴሮ የማርክ አንቶኒን ዲክታተር የመሆን ፍላጎት በመቃወሙ አንገቱ ተቀልቶ ተገድሏል።

የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍናን ለመጀመሪያ ጊዜ አብራርቶ የጻፈው ሲሴሮ ሲሆን ለእርሱ ሕግ ማለት አመክንዮ ከተፈጥሯዊ ሕግ ጋር ሲጣመር የሚሰጠን ውጤት ነው። የተፈጥሮ ሕግ የሰው ልጆች ሕግጋትን ማወጅ ከመጀመራቸው እና መንግስት የሚባል ነገር ከመፈጠሩ በፊትም እንደነበር እና ይህ ሕግም የማይለወጥ እና ዘላለማዊ እንደሆነ ያስብ ነበር። የዚህ ሕግ ባለቤት፤ ፈጻሚና ተርጓሚ የሆነ ልዕለሰብዓዊ አካል እንዳለና ይህም አካል ፈጣሪ ወይም አምላክ በሚል የሚታወቅ መሆኑን ጽፏል።

> There is a true law, a right reason, conformable to nature, universal, unchangeable, eternal, whose commands urge us to duty, and whose prohibitions restrain us from evil. Whether it enjoins or forbids, the good respect its injunctions, and the wicked treat them with indifference. This law cannot be contradicted by any other law, and is not liable either to derogation or abrogation. Neither the senate nor the people can give us any dispensation for not obeying this universal law of justice. It needs no other expositor and interpreter than our own conscience. It is not one thing at Rome and another at Athens; one thing to–day and another to–morrow; but in all times and nations this universal law must for ever reign, eternal and imperishable. It is the sovereign master and emperor of all beings. God himself is its author,—its promulgator,—its enforcer. He who obeys it not, flies from himself, and does violence to the very nature of man. For his crime he must endure the severest penalties hereafter, even if he avoid the usual misfortunes of the present life.[15]

ሲሴሮ ከተፈጥሯዊ ሕግ እኩል ሁሉን ዓቀፍ እና ገዢ መሆን እንዳለበት የሚገልጸው ቀና አመክንዮን (right reason) **ነው። ትክክለኛና ቀና አመክንዮ ከእውነተኛውና ከማይለወጠው የተፈጥሮ ሕግ ጋር ሲዋሃድ ፍትሕ እና ርትዕ ለሰው ልጆች ሁሉ ይደርሳል። በተጨማሪም መንግስት የግል ሀብትን መጠበቅ እንዳለበት እና መንግስት ከተቋቋመባቸው አላማዎች አንዱ መሆኑንም ጽፏል።**

---

15 Cicero, *De Re Publica* [*Of The Republic*], Book III Section 22; as translated by Francis Barham

ስቶይሲዝም ስሜት አልባነት ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባለፈ አሉታዊ ስሜት ማስወገድን እና በመከራ እና ሃዘን የማይናወጥ የሕይወት መንገድን ያስተምራል። የዚህ አስተምህሮ ዋነኛ እሳቤ የሚመነጨው ህዋ የማይታይ ግን መሠረታዊ የሆነ ስርዓት (Cosmological order) አለው ከሚለው እይታ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሰዎች ሁሉ የአንድ ትልቅ ቤተሰብ አባላት እንደሆኑም ያምናል። ይህ የተፈጥሮ ፍትሕ በሕግ ፍልስፍና ላይ ያላቸውን አስተሳሰብ ያሳያል። ሲሴሮ የሮም የሕገ-መንግስታዊ ታሪክን በሦስት ደረጃ ይከፍለዋል። የግለሰብ አገዛዝ፣ የጥቂቶች አገዛዝ እና የብዙኃኑ አገዛዝ የሚሉት ናቸው። ሮም ከንጉሳዊ አገዛዝ ወደ ሴኔታዊ አመራር በሂደት መለወጣ እና ሪፐብሊኩም በሁለት ኮንሱሎች እንጂ በንጉስ መመራት ማቆማቸው ለሕገ-መንግስታዊ እድገት መሠረት መጣሉን ያምናል። ይህንንም ከሦስተኛው እና ሕዝቡ በተለያዩ ሕዝባዊ ተቋማት ተወክሎ ድምፁን ከሚያሰማበት የብዙኃኑ አገዛዝ ብሂሎች ድብልቅ መሆኑን ያስተምራል።

ዘመናዊ መንግስታዊ አስተዳደር ከንጉሳዊ፣ መሳፍንታዊ እና የብዙኃኑ አገዛዝ የሚሻሉ ሐሳቦችን እየነቀሰ ጥቅም ላይ ማዋል ይገባዋል። ሲሴሮ በግሪክ ሀገር ለዓመታት ከተዘዋወረ እና ባህላቸውን ካጠና በኋላ የግሪክ ፍልስፍናን ወደ ላቲን በመቀየር የሮም ሪፐብሊክ መሠረት እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ሲሴሮ የምግባራዊ የሞራል ፍልስፍና ተከታይ በመሆኑ ሰናይ ምግባር የልዕቀት ውጤት በመሆኑ ግለሰቡን ጥረት እንደሚፈልግ ያስረዳል። ለሲሴሮ ፍትሕ ማለት በቅድሚያ ሰዎችን አለመጉዳት፣ የንብረት መብታቸውን ማክበር፣ የራስን ቃል ማክበር እና ለሰዎች እንደየምግባራቸው እና እንደ አቅምህ መልካምነትን ማሳየት ነው። ለሲሴሮ ይህን ፍትሐዊ አስተዳደር ማስፈን የሚችለው የተሻለ አገዛዝ መሳፍንታዊ አስተዳደር መሆኑን ያስረዳል፣ ሲሴሮ የሕግ ምሁር ከመሆኑም ባሻገር የሮም ሴኔት አባል ነበር።

የሮም ሕገ-መንግስት በተፈጥሮ ሕግ፣ በቀደሙት አባቶች አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ እና ከትውልድ ትውልድ እየተሻሻለ የመጣ መሆኑን ስለሚያምን ረቂቅ በሆነ የመናገር ችሎታው ይህንኑ ከመስበክ አልቦዘነም። ለሲሴሮ አንድ ሴናተር ሊኖረው የሚገባ ክህሎቶች Sapientia,prudentia,Autocritas እና Oratory ናቸው። ሴናተሩ ሕግ እና ሕገ-መንግስታዊ ስርዓቱን መፈፀም ብቻ ሳይሆን መጠበቅ እና ማስጠበቅ አለበት። በምዕራባዊ የሕገ-መንግስት ስርዓት ውስጥ እጅግ የሚወደድ የመጻፍ እና የመናገር ክህሎት ያለው ፖለቲከኛ እና የሕግ ባለሙያ በመሆኑ ለዘመናዊ የሕግ ምሁራን ልዕቀት ያለው አብነት ሆኗል።

ሲሴሮ ሮማዊ ዜግነቱን ያገኘው በትውልድ አልነበረም፤ ሲሴሮ ሮም ከወረረቻቸው ቦታ ተግዞ ከመጣ ቤተሰብ የተወለደ በመሆኑ በትውልድ ሮማዊ አለመሆኑን ብዙዎች ሴናተሮች እያነሱ ይወርፉት ነበር። በደም ሮማዊ ሳይሆን ለሮም የሕግ ስርዓት ከፍተኛ አገልግሎት በሮም ሴኔት ውስጥ በነበረ የስልጣን ሽኩቻ በጠላቶቹ ሊገደል ሲል የተላከበትን ነፍሰ-ገዳይ " የምታደርገው ነገር ትክክል ባይሆንም ሰይፍህን በአግባቡ ሰንዝረህ አንገቱ ቶሎ እንዲቀነጠስ ብታደርግ የተሻለ ነው። " ሲል ሞቱን በጀግንነት የተቀበለ ነው።

ሌላኛው ስቶይክ ሴኔካ ግን የሴኔቱን የሞት ትእዛዝ በተደጋጋሚ አምልጣል፤ ራሱን ለማጥፋት ብዙ ቢሞክርም እንኳ አልቻለም። የስቶይክ አስተሳሰብ ከብዙ ዘመናት በኋላ ባለንበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን በተለያየ መንገድ ተመልሶ እየተሰበከ ይገኛል፤ ምናልበትም ያለንበት ዓለም ያለመረጋጋት የጥንቱን የኑሮ ሁኔታ ውስጥ በራስ መተማመን እና መረጋጋት ለማግኘት እንዲችሉ እነዚህን ጥንታዊ አሳቢያን እና ሥራዎቻቸውን መልሰው እየመረመሩ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ ወደ ተፈጥሮ ሕግ የሚደረገው እንቀስቃሴ መንግስታዊ እና ማኅበረሰባዊ ድጋፍ እያገኘ መሆኑን መረዳት ያሻል።

የአምላክ ከተማ - ቅዱስ ኦግስቲን

‘‘እያመንኝ እናስብ’’

ኦግስቲን (354-430) የተወለደው በሰሜን አፍሪካዋ የዛሬይቷ አልጄሪያ ከተማ ሲሆን በልጅነቱ የክርስትና እምነት ተከታይ የነበረችው እናቱ ከፍተኛ የእምነት እና የመልካም ባህሪ ተጽእኖ ያሳደረችበት መሆኑን ሁሌም ይናገር ነበር። ከሰሜን አፍሪካዊቷ ግዛት ወደ ሮም፤ ካርቴጅ፤ ሚላን መሰል ከተሞች ለትምህርት የተላከው ኦግስቲን፤ ወጣትነቱ ከሮም የድሎት እና ስጋዊ እርካታዎች ጋር ተደምሮ መንገዱን አስተውት እንደነበር በኂላ ላይ “ኑዛዜ” በተባለው ድርሳኑ አመልክቷል።

> A Berber, born in 354 at Thagaste (now Souk-Ahras) in Africa... The exceptional brilliance of his works (*The City of God*, *The Confessions*), his contradictory nature, his desire to bring together faith and intelligence, classical and Christian civilization, the old wine and the new — these deliberate efforts made him in some ways a rationalist. For him, faith came first: but he nevertheless declared ‹Credo ut intelligam› — ‹I believe in order to understand.› He also said ‹Si fallor, sum› — ‹If I am mistaken, I exist› — and ‹Si dubitat, vivit› — ‹If he doubts, he is alive’... Posterity undoubtedly concentrated its attention on St Augustine as a theologian, and on what he wrote about predestination. But Augustinianism gave Western Christianity some of its colour and its ability to adapt and debate — if only by insisting on the vital need to embrace the faith in full awareness, after deep personnal reflection, and with the will to act accordingly[16].

16 Fernand Braudel, *A History of Civilizations* (1963), Penguin Books (1995 edition), p. 335

የአምላክ ከተማ የተሰኘው ድርሳኑ በወራሪዎች የፈረሰችው የሮም ከተማ ሁኔታ የዜጎቹን ሥነ-ልቦና ክፉኛ የጎዳ በመሆኑ እንደማጽናኛ የተደረሰ ነው። የሮም ነዋሪዎች ሮም የወደቀችው የጥንቶቹን አማልክት በመተው ክርስትናን በመከተሏ ከአማልክቱ ቁጣ የተነሳ መሆኑን በተደጋጋሚ ይናገሩ ነበር። እርሱ ግን በዚህ ድርሳን የአምላክ ከተማ (City of God) እና ምድራዊዋ ከተማ በማያቋርጥ ጦርነት ውስጥ እንደሆኑና የማታ የማታ የጽድቅ እና ፍትሕ ምልክት የሆነችው የአምላክ ከተማ እንደምታሸንፍ ለማስረዳት ሞክሯል።

በዚሁ ድርሳን የአምላክ ፍቃድ ዘላለማዊ ሕጋግትን ለማወቅ እንደሚጠቅም እና ሰው ሠራሽ ሕግጋት ሁሉ ዘላለማዊ ከሆነው የአምላክ ፍቃድ ጋር ሊሰምሩ የተገባ መሆኑን አመልክቷል። በመሆኑም ኢ-ፍትሐዊ ሕግ ማለት ዘላለማዊ ከሆነው ከአምላክ ፍቃድ ጋር የሚጣረስ መሆኑን አመልክቷል። ስለዚህም ከተፈጥሮ ሕግጋት ጋር የሚጋጭ ሕግ ኢ-ፍትሐዊ ሕግ ነው። ኢ-ፍትሐዊ ሕግ ደግሞ ሕግ አይደለም ፤ ስለሆነም ሰው ሠራሽ በሆነችው ከተማ የሚኖሩ ዜጎች እነዚህን ኢ-ፍትሐዊ ሕግጋት ሊቃወሙ ይገባል። ቅዱስ አግስቲን **እያሰብን እንመን ፤ እያመንን እናስብ** በሚለው አቋሙ ይታወቃል። በርግጥ አግስቲን በሥነ-መለኮት፤ ትምህርት፤ ሳይንስ፤ ሞራል እና መሰል ጉዳዮች ላይ በሰፊው ተመራምሯል። እንዲያውም ስለ ድህነት፤ ጸጋ እና ቀዳሚ ኃጢያት ላይ ያቀረባቸው የሥነ-መለኮት ሐሳቦች ዛሬም ድረስ በካቶሊኮቹም ሆነ በፕሮቴስታንቶቹ እኩል የሚጠቀስ መሠረታዊ ሥራ ነው።

አግስቲን በምዕራቡም ሆነ በምሥራቁ የክርስትና ዓለማት፣ በካቶሊኮቹም ሆነ በተሃድሶ አቀንቃኞች እኩል የሚወደስ መንፈሳዊ አባት እና ፈላስፋ ሊሆን የቻለው ያለምክንያት አይደለም። ከቀደሙት የቤተ-ክርስትያን አባቶች መሀከል እንደ እርሱ ከፍተኛ ምርምር ያደረገ እና ሥነ-መለኮታዊ አስተሳሰቡም ተራማጅ የሚባል መንፈሳዊ አባት ለማግኘት ይከብዳል። አግስቲን ወይም በኢትዮጵያኖች አጠራር አገስጢኖስ ከፃፋቸው

ፅሁፎች መሃል “On Trinity” የተሰኘው የካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን ቋሚ ዶግማ እስከመሆን የደረሰ ሲሆን “Confessions” የተሰኘ ድርሳኑ ደግሞ በወጣትነት ዘመኑ የሰራቸውን ኀጢያቶች አንድም ሳያስቀር የተናዘዘበት እንደመሆኑ በዘመኑ ያልተለመደ ድፍረት ሲሆን እስካሁን ድረስ ባሉ የወንጌላውያን አማኞች የሚደነቅ ሥራ ነው።

አገስቲን ተራማጅ መንፈሳዊ እና ዓለማዊ ሥራዎችን ሊያበረክት የቻለው ከወጣትነት ዘመኑ ጀምሮ በተለያዩ ፍልስፍናዎች ተፅዕኖ ስር ወድቆ ስለነበር ነው። ለምሳሌ “Manicheanism” የተባለው የምንፍቅና አስተምህሮ በወጣትነት ዘመኑ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳሳደረበት እና አብዛኛውን የወጣትነት ዘመኑን ከዚህ ፍልስፍና ጋር እየታገለ እንደኖረ በ”ኑዛዜው” ሳይደብቀን ይነግረናል። እንደዚህ ዓይነት የኑፋቄ አስተምህሮዎች ታግለው እየጣሉት ከዛም እየተነሳ መኖሩ መንፈሳዊነቱን ብቻ ሳይሆን ጥልቅ አሳቢነቱንም ጭምር ሊያዳብሩት ችለዋል። አገስቲን በዛሬው የሰሜን አፍሪካ አካባቢ “በርበር” ከሚባል ጎሳ የተወለደ ሲሆን ቤተሰቡ የሮማ ግዛት ዜግነትን ያገኙት በውልደት ሳይሆን በሕግ ነበር። በወጣትነት ዘመኑ ክክርስትና እምነት ርቆ የኖረ ቢሆንም እናቱ ቅድስት ሞኒካ በተደጋጋሚ በምታደርግለት ፀሎት እና ምክር ወደ አውሮፓ ሄዶ የምንኩስና ሕይወቱን ሊጀምር ችሏል። አገስቲን ጥንተ አብሶ (Original sin) የተባለውን ሐሳብ ያፈለቀ እና ያዳበረ በመሆኑ በካቶሊኮች ሲወደድ በጸጋ ድህነት (Salvation through Grace) ላይ በሰፊው በመፃፉ እንደ ማርቲን ሉተር ዓይነቶቹ የተሃድሶ አቀንቃኞች “የጸጋ አባት” እያሉ ያደንቁታል።

የሥነ-ሕግ ፍልስፍናው ከሁሉ አስቀድሞ ፍትሐዊ ጦርነት “Just War” የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ ያፈለቀ ሲሆን ይህንን ቃል “የአምላክ ከተማ” በተባለው ድርሳኑ ላይ ካሰፈረው በኋላ በሰፊው ሊታወቅ ችሏል። ክርስትያኖች ሰላም ፈላጊ ሊሆኑ የሚገባ ሲሆን በእብሪት የተሞላ ጦርነት የመከላከል ክርስቲያናዊ ኃላፊነት እንዳለባቸው የራስን ቤተሰብ ሕይወት እና ቤተ-ክርስትያን ከጥቃት መከላከል ተገቢ መሆኑን አስረድቷል። ከእርሱ

በኋላ እንደ ሁጎ ግርሺየስ ያሉ ፈላስፎች ይህንኑ ሐሳብ ከተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና ጋር አይይዘው አብራርተዋል።

አገስቲን በወጣትነት ዘመኑ እንደ ሲሴሮ ዓይነት ጸሐፊዎችን በማንበቡ በእነሱ የአጻጻፍ ስልት ስር ተፅዕኖ ወድቆ እንደነበር ለተለያዩ ሰዎች በጻፋቸው ደብዳቤዎች ለማወቅ ተችሏል። በዚህ ወይም በክርስትናው ሊሆን ይችላል አገስቲን የተፈጥሮ ሥነ-ሕግ ፍልስፍና አቀንቃኝ ለመሆኑ ጥርጥር አያሻም። በዚህም ምክንያት "city of God" በተሰኘው ድርሳን በወቅቱ በሮማ ግዛት ተንሰራፍቶ የነበረውን የባሪያ ስርዓት ተቃውሟል፤እንዲያውም ባሪያ አሳዳሪ የነበሩ ክርስትያኖች በቤታቸው ያሉ ባሮችን ነፃ እንዲያወጡ ይመክር ነበር። ይህንኑ ሲያብራራ የባሪያ አሳዳሪ ስርዓት የሰው ልጆች ከክብራቸው በኃጢያት ምክንያት የመውደቃቸው አንድ ማሳያ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠረው አንድ ሰው በሌላ ሰው እንደ እቃ እንዲሸጥ እንዲለወጥ አስቀድሞ ሊያስብ አይችልም። በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ሰዎች ፍጹም ስልጣን የተሰጣቸው በእንስሶች እና እፅዋት ላይ እንጂ በሌሎች ሰዎች ላይ አይደለም። የባሪያ ስርዓት የሰው ልጆች በኃጢያት በመውደቃቸው ምክንያት እንደ ቅጣት በላያቸው ላይ ያመጡት ዕርግማን በመሆኑ የእርግማኑ ሰለባ ከባሮቹ ይልቅ ባርያ አሳዳሪው ነው። እንግዲህ እንዲህ ዓይነት አብዮታዊ አስተሳሰብ እርሱ ዘመን መጻፍ እና ማስተማር እንደ እብደት ካልተቆጠረ በስተቀር በራስ ላይ አደጋ የመጥራት ያህል ነው። አገስቲን የራሱም አፍሪካዊነት ስለሚጫነው በአውሮፓዊ ሕይወት እና ፍልስፍና ራሱን እንደ ባዕዳ ከመመልከት አልቦዘነም። የሚገርመው እስከዛሬ እንደ ታላላቅ የምዕራቡ ዓለም ፈላስፎች የሚታዩት ሲሴሮ እና አገስቲን እንኳ በሕግ እንጂ በደም ሮማዊ ያልነበሩ መሆናቸው ነው።

መነኩሴው ፈላስፋ- ቅዱስ ቶማስ አኩይናስ

"የተፈጥሮ ሕግ መሐኮታዊ ኑው"

አኩይናስ (1225-1274) ከልጅነት ዘመኑ ጀምሮ የዶሚኒካን የምንኩስና ማኅበር ባሳደረበት ልዩ ተፅዕኖ የካቶሊክ ሃይማኖት መነኩሴ ለመሆን ባሳየው ተነሳሽነት ቤተሰቦቹ ሐሳቡን ለማስተው እንዲታሰር አድርገውት ነበር። ይሁን እንጂ ከብዙ ጥረት በኋላ ተሳክቶለት በምንኩስና ትምህርቱ ቢቀጥልም ትምህርቱ ብዙም ሊዘልቀው ስላልቻለ ጓደኞቹ "ደደቡ በሬ" እያሉ ይሳለቁበት ነበር። እየቆየ ሲሄድ ባሳየው ልዩ የምርምር እና ጥናት ብቃት የግሪክ ፍልስፍናን ከሃይማኖት አስተምህሮ ጋር በማዋሃድ የሃይማኖት እውቀትና መገለጥ ከአመክንዮ የተፃረረ እንዳልሆነ እንዲያውም አጋዥ መሆኑን ለማሳየት ብዙና ታላላቅ ድርሳኖችን አሰናድቷል። አኩይናስ በፅውቀተ ፍልስፍና፤ በዲበአካላዊነት፤ በስነ-መለኮት፤ በስልተ-ምርት፤ በፖለቲዊ ርዕዮተ ዓለም እና በሕግና አስተዳደር ዙሪያ ብዙ ጽሁፎችን አበርክቷል። ከሞቱ በኋላ የካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን አብዛኞቹን ድርሳናቱን ለመማሪያነትና ለስርዓተ አምልኮ መገልገያነት እንዲውሉ ስታደርግ እርሱ ደግሞ "የቅዱስነት" ማዕረግን ተጎናፅፏል።

> St. Thomas exalted God without lowering Man; he exalted Man without lowering Nature. Therefore, he made a cosmos of common sense; *terra viventium*; a land of the living. His philosophy, like his theology, is that of common sense. He does not torture the brain with desperate attempts to explain existence by explaining it away. The first steps of his mind are the first steps of any honest mind; just as the first virtues of his creed could be those of any honest peasant.[17]

17 G. K. Chesterton, *The Spectator* (27 February 1932)

አኩይናስ ከግሪክ ፈላስፎች መሀከል ለአሪስቶትል ከፍተኛ አድናቆትና ክብር ከማዳበሩ የተነሳ “ፈላስፋው” ብሎ የሚጠራው ብቸኛ የግሪክ አሳቢ አሪስቶትልን ነበር። የካቶሊክ መነኩሴ እንደመሆኑ ሕግ ከፈጣሪ የተሰጠ እና በተፈጥሮ ውስጥ የሚገኝ ስርዓት መሆኑን ማመኑ ብዙ ሊደንቀን አይገባም ይሁን እንጂ ሕግ የሚባለውን ሐሳብ ራሱ ለአራት ዋና ዋና ርዕስ ክፍሎች በማብራራቱ ሐሳቡን በሚገባ ልናጤንለት ይገባል።

እነዚህም ዘላለማዊ ሕግ፤ የሰዎች ሕግ፤ መለኮታዊ ሕግ እና የተፈጥሮ ሕግ የሚባሉት ንዑስ ክፍሎች ናቸው።

ዘላለማዊ ሕግ ዘላለማዊ እንደመሆናቸው በዘላለም ውስጥ ያሉ የማይቀየሩ እና የማይለወጡ እንደሆኑ አድርጎ ፈጣሪ የደነገጋቸው ሕግጋት ናቸው። እነዚህ ዘላለማዊ እና የማይቀየሩ ሕግጋት ለሰው እና ለተፈጥሮ በሚችሉት እና በሚረዱት መልኩ ይገለጻሉ። ዘላለማዊ እና ፍጹም የሆነው ሕግ ለሰዎች የአእምሮ ብቃት እንዲመጥን ተደርጎ ሲተላለፍ እና ሰዎችም ይህንኑ ሲረዱት የተፈጥሮ ሕግ ይባላል።

የተፈጥሮ ሕግ ማለት ሰዎች በተረዱት እና በገባቸው መጠን በዘላለማዊ ሕግ ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፎ የሚወሰን ስርዓት ነው። የሰው ልጅ በተፈጥሮ ከተሰጠው ባህሪያት እና ችሎታዎች አንዱ አመክንዮ እንደመሆኑ ዘላለማዊ እና ጥልቅ የሆነ ነገሮችን በምክንያታዊነት መርምሮ ራሱን ወደ ፍጹማዊነት ሊያስጠጋ እንደሚገባ ይታመናል ይህ ሰብዓዊ እና ምክንያታዊ የሆነ ፍጽምና የተፈጥሮ ሕግ ይባላል። በመሆኑም ምክንያታዊ የሆኑ ሰዎች ሁሉ በየትኛውም የዓለም ክፍል ሆነው በአንድነት የሚረዱት እና የሚያውቁት የራሳቸውንም ሆነ የሌላ ሕይወት ያለው ፍጥረትን ህላዌ ሊያዳብሩ የሚችሉበት መንገድ ነው። ይህ ሕግ ምክንያታዊ ለሆነ ሰው በተፈጥሮ የተገለጠ ነው።

መለኮታዊ ሕግ ግን በምክንያት ለሚመሩ ሰዎች በተፈጥሮ የተገለጠ ባለመሆኑ የሚታወቅ አይደለም። በመሆኑም መለኮታዊ ሕግን ለመረዳት ሰዎች ከምክንያታዊነት ባሻገር መለኮታዊ ድጋፍ እና ጣልቃገብነት ያስፈልጋቸዋል፡ መለኮታዊው ሕግ በልዩ መለኮታዊ መገለጥ ዘላለማዊ የሆነውን ሕግ የሚያስረዳ እና የሚያስፈጽም ሲሆን ዋንኛ ግቡም የሰው ልጆች ዘላለማዊ ግባቸው የሆነውን መለኮታዊ ሕይወት እንዲያገኙ የሚያግዝ ነው። መለኮታዊ ሕግ ምድራዊ የሆነውን ሕይወታችንን ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ የሆነውን ሕይወት የሚገዛና ለዚሁ የሚያዘጋጀን ነው።

የሰዎች ሕግ ወይም ሕገ-ሰብዕ የምንለው ሰዎች ማኅበራዊ ሕይወታቸውን ለማቃናት የተፈጥሮ ሕግን በአዋጆች እና መመሪያዎች ውስጥ አካተው ሲያጸድቁ የምናገኘው ነው። በመሆኑም የሰዎች ሕግ ከተፈጥሮ ሕግ ጋር መስማማት ያለበት ብቻ ሳይሆን የሞራል መስፈርት ሆኖ ሊያገለግል ይገባል። የሰው ልጆች ሕግጋት ከቦታ ቦታ ሊለያዩ እና ሊሰዋወጡ ይችላሉ።

በመሀከለኛው ዘመን በነበረው ምሁራዊ ባህል መሠረት አኩይናስ አስቀድሞ ታዋቂ ሐተቶችን ያስቀምጥና የራሱን ተቃውሞ እንደመልስ ይሰጣል። ለምሳሌ ሕግ ሰዎችን መልካም ያደርጋልን; ብሎ ከጠየቀ በኋላ በአሉታዊው መልስ ይሰጣል። የሰዎች መልካምነት የሚገኘው በሕግ ሳይሆን አስቀድሞም ቢሆን በሰዎች ውስጥ የተቀመጠ መልካምነት በመኖሩ ሕግ ያንን ተፈጥሯዊ መልካምነት ታሳቢ በማድረግ ትእዛዝ እንደሚሰጥ ያትታል። ይሁን እንጂ ሰዎች በውስጣቸው መልካምነት ቢኖርም ይህንኑ ላለማድረግ አልፎ አልፎ ቢያፈነግጡ እንኳ ሕጉ በቅጣት ወደ መልካምነታቸው ሊመልሳቸው እና ሊያለማምዳቸው እንደሚገባ ተገልጿል። እንደሚታወቀው አኩይናስ የአሪስቶትል ፍልስፍና አድናቂ እና ተከታይ እንደመሆኑ ልክ በሶቅራጥስ እና አፍላጦን መሀከል የነበረው የሐሳብ መወራረስ በእነርሱም ዘንድ ይታያል።

አሪስቶትል የሰው ልጅ “ፖለቲካዊ ፍጡር” እንደሆነ እና በዚህ ባህሪው የተነሳ በማኅበር ለመኖር እንደተገደደ እና ማኅበሩ በጥቅል የሚያነሳው እና የሚያሳየው ባህሪ በማኅበሩ አባላት ላይ እንደሚንጸባርቅ ያስባል። ይህም ማለት ግለሰቡ የሕይወት ትርጉም እና አላማውን የሚያገኘው በቀጥታ ከማኅበሩ አላማ ነው። በመሆኑም ሕግ የማኅበሩን ጥቅል ደህንነት (common good) ማስጠበቅ እንዳለበት እና ግለሰቡም በተመሳሳይ ይህንኑ እንደሚከተል ተናግሯል። አኪይናስ ይህን ሐሳብ የሚስማማበት ሲሆን የአሪስቶትልን ፍልስፍና በሙሉ በማጥናት “ክርስቲያናዊ” መልክ እና ጣእም እንዲኖረው ከማድረግ ውጪ ብዙም እንዳልጨመረበት ይስማማሉ። ይህ ጥንታዊ የግሪክ ፍልስፍናን ከክርስትና ጋር እያዋሃዱ የማጥናት ስልት በወቅቱ scholasticism በመባል ሲታወቅ ብዙ ድጋፍ እና ነቀፋ ነበረው። አኪዮናስም ቢሆን እንዴት የአንድን አረማዊ ፈላስፋ ፍልስፍና ታስፋፋለህ በሚል ብዙ ትችት ደርሶበት ነበር።

ማኅበረ-መንግስታት - ሁጎ ግሮሺየስ

“ፍትሐዊ ጦርነት ሞራላዊ ነው”

ምንም እንኳ ከፍተኛ እውቀት ያተረፈው የዓለም ዓቀፍ ሕግን በስፋት በማጥናት እና በማስተዋወቅ ቢሆንም ከዚሁ ጋር በተያያዙ የተፈጥሮ ሕግ ላይ በመመራመሩ ይታወቃል። ሁጎ ግሮሺየስ (1583-1645) ማርቲን ሉተር ባስነሳው የተሃድሶ ቀውስ በምትናጠው አውሮፓ ውስጥ እየኖረም ቢሆን የተለያዩ የክርስትና ሃይማኖት ዘርፎችን ለማስታረቅ ከፍተኛ ጥረት አድርጎ ነበር። ፍትሐዊ ጦርነት (Just war) በዓለም ዓቀፍ ሕግጋት እና ልማድ አንጻር በምን መንገድ መተርጎም አለበት?ለሚለው ጥያቄ በሰጠው መልስ የተፈጥሮ ሕግን አስታራቂ ፍልስፍና እንደ ማስረጃነት አቅርቧል። የዚህ አስተምህሮው ምንጮች ሲሴሮ እና የስቶይክ ፍልስፍና መሆናቸውን ከጽሑፎቹ መረዳት እንችላለን።

> Fully convinced...that there is a common law among nations, which is valid alike for war and in war, I have had many and weighty reasons for undertaking to write upon the subject. Throughout the Christian world I observed a lack of restraint in relation to war, such as even barbarous races should be ashamed of; I observed that men rush to arms for slight causes, or no cause at all, and that when arms have once been taken up there is no longer any respect for law, divine or human; it is as if, in accordance with a general decree, frenzy had openly been let loose for the committing of all crimes[18]

የፍትሐዊ ጦርነት ምክንያቶች የተፈጥሮ ሕግ እና ዓለም ዓቀፍ የማኅበረ-መንግስት ልማድ ናቸው። በጦርነት ሕግ መሠረት ማንኛውም ሀገር የራሱን ልዑላዊነት የማስጠበቅ ተፈጥሯዊ መብት ስላለው ራሱን ከማንኛውም ዓይነት ጥቃት ለመከላከል የሚገባበት ጦርነት ፍትሐዊ ነው። ይህ ማለት አንድ መንግስት ራሱን ለመከላከል፤ የተዘረፈበትን ሀብት ለመስመለስ እና በደረሰበት ጥቃት ልክ ተመጣጣኝ የቅጣት እርምጃ በመውሰድ የሚያስችል ተፈጥሯዊ መብቶች በተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ሀገር የውስጥ ሕግጋትም የሚገኙ እንደመሆናቸው በማኅበረ-መንግስታት ጸድቀው ዓለም ዓቀፋዊ ሕግጋት መሆን ይገባቸዋል ሲል ጽፏል።

ሁጎ ግሮቲየስን የዓለም ዓቀፍ ሕግ አባት እንደሆነ አድርገው የሚያቀርቡ ሰዎች ሉዓላዊና ሰላማዊ ሀገራትን ማኅበረ- መንግስታት በሰላምም ሆነ በጦርነት ወቅት ሊያስማማቸው የሚችል አንድ የተጻፈ ወይም የልማድ ሕግ መኖሩ አስፈላጊ እንደሆነ በተደጋጋሚ ጊዜ መጻፉን

18 Hugo Grotius, *The Law of War and Peace*, trans. Francis Kelsey (Carnegie edition, 1925), Prol. sect. 28.

ያነሳሉ። የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና አብዛኛውን ከሰብዓዊ መብቶች አፈጣጠር ጋር የሚገናኝ በመሆኑ ከዓለም ዓቀፍ የጦርነት ሕግጋት ጋር አያይዞ ሐሳብ መፍጠር አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

ሁጎ ግሮሺየስ (Hugo Grotius) ዓለም ዓቀፍ ማኅበረሰብ (International Society) የሚባለውን ፅንሰ ሐሳብ ቅርፅ እና ደርዝ ያለው በሚታወቁ እና ተቀባይነት ባላቸው ሕግጋት እና መርሆዎች ላይ እንዲፀና ከፍተኛ አስተዋፅጾ አድርጓል። “The Free Sea” በተሰኘው ድርሳኑ ባህሮች እና ውቅያኖሶች ከሃገራት ሉዓላዊ ግዛት ውጪ በመሆናቸው ሁሉም ሰዎች እና ሀገራት በጋራ ሊጠቀሟቸው እንደሚገባ በመግለፅ የእንግሊዝ ግዛት በሜድትራኒያን ባህር ላይ የሚያሳድረውን ጫና ተቃውሟል። ውቅያኖሶች እና ባህሮች ለሰው ልጆች ሁሉ የታደሉ ጸጋዎች መሆናቸውን በመግለፅ የሚከራከረው ከነበረው ጥብቅ የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና በመነሳት ነበር።

በተጨማሪም በወቅቱ በአውሮፓ ውስጥ ሃገራት በፕሮቴስታንት እና ካቶሊክ ዕምነት ደጋፊነት ተከፋፍለው የሚያደርጉትን ረብ የለሽ እና አስከፊ ጦርነት በመቃወም በተከታታይ ከመጻፉ የተነሳ እስከዛሬ ድረስ የምንገለገልባቸውን የጦርነት ሕግ መርሆዎች(The Laws of War) ሊያረቅ ችሏል። ግሮሺየስ በ 17ኛው እና በ18ኛው ክፍለ ዘመን ለተነሱ የሃይማኖት እና የፖለቲካ አብዮቶች መንፈሳዊ አባት ተደርጎ ይወሰዳል ምክንያቱም የሕግ እና የስነ-መለኮት ምሁር በመሆኑ በሁለቱም ዘርፍ ከፍተኛ ተዕዕኖ የሚያሳድሩ የምርምር ትሩፋቶች ለዓለም አቅርቧል።

ለእርሱ ተፈጥሮ እና የተፈጥሮ ሕግጋት በሙሉ በእግዚአብሔር ቅድመ ዓለም ሐሳብ ውስጥ የነበሩ እና በእውቀት ለሰዎች እና በሰዎች መሃል የተቀመጡ ዘመን አይሽሬ መርሆዎች ናቸው። በመሆኑም የተፈጥሮ ሕግጋት እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያጣጣምን መተርጎም ይኖርብናል። የዓለም ዓቀፍ ሕግ አባት ለመባል ያደረሰውን ድርሳን “De Jure Belli ac Pacis/on the Law of War and Peace” ያዘጋጀው በኔዘርላንድ እና

በስፔን መሀከል የነበረውን የብዙ ዓመታት ጦርነት ከኔዘርላንድ መንግስት የታሪክ ጸሐፊ እና ተመራማሪ በመሆን በቅርበት የመረመረ እና የታዘበ በመሆኑ ነበር። ሁጎ የስፔን እና የፖርቱጋል መንግስታት ሃገሩ ሆላንድ ነፃ ግብይት እንድታደርግ የባህር ላይ ነፃ የንግድ ቀጠናውን ኢ-ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተቆጣጥረው የሚተላለፉ መርከቦችን የሚቀርጡበት እና የሚወርሱበት ስርዓት እጅግ ከመቃወም አልፎ ተፈጥሮን የሚፃረር እንደሆነ ያምን ነበር። ከልጅነቱ ጀምሮ የላቲን ቋንቋን አቀላጥፎ ይጽፍ እና ይናገር ስለነበር የስቶይክ ፈላስፎች በሥራው ላይ ተፅዕኖ እንዳሳደሩበት ሳይገልፅ አላለፈም።

ይህንን የስቶይኮች ፍልስፍና ከክርስትና መሠረታዊ መርሆዎች ጋር በማቀናጀት አውሮፓ ውስጥ የነበረውን የማያባራ ጦርነት ለመፍታት ሞክሯል። ለዚህም ካቶሊኮች እና ፕሮቴስታንቶች እና ሌሎች ዓይነት የክርስትና ዘርፍ ተከታይ ሃገራት እና ቡድኖች በሙሉ የሚስማሙበት የሕግ ፍልስፍና ለመቀመር ባደረገው ጥረት የተፈጥሮ ሕግጋትን መሠረት ያደረገ ዓለም ዓቀፍ ሕግ እንዲፈጠር አስችሏል። በእርሱ ዓለም ዓቀፍ ተፈጥሯዊ ሕግ መሠረት ሃገራት ወደ ጦርነት ሊያመሩ የሚችሉት ጦርነቱ ፍትሐዊ ከሆነ ብቻ ነው።

ጦርነቶች ፍትሐዊ ሊሆኑ መቻላቸውን ልንረጋግጥ የምንችለው የጦርነቶቹ ምክንያቶች ተፈጥሯዊ መብትን ከመከላከል የመነጨ ከሆኑ ብቻ ነው። እነዚህም ራስን የመከላከል መብት፣ የደረሰ ጉዳትን ለመተካት ወይም ለማካካስ እንዲሁም ተመጣጣኝ እና ተገቢ የሆነ ጥቃት ማድረስ ናቸው። ገጣሚ እና ፀሀፊ ተወኔት የሆነው ግሮሺየስ የፃፋቸው መርሆዎች በፖለቲካው ዓለም “West Phalia” ስምምነት መሠረት ሲሆኑ በስነ-መለኮት ደግሞ የአርሜኒያ-ካልቪን (Arminian-Calvinist Debate) ረዥም ዘመን የቆየ የስነ-መለኮት ክርክርን ከአርሜኒያ ቤተ-አስተምህሮ በኩል ጠንካራ ድጋፍ እንዲያገኝ ረድቶታል።

መሠረታዊ እሴቶች - ጆን ፊኒስ

"ሕይወት ቀዳሚው የተፈጥሮ ስጦታ ነው"

ጆን ፊኒስ (1940-) የሕግ ፍልስፍና ተመራማሪ እና ለሀገሩ የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አማካሪ፤ ጠበቃ እና የሕግ ባለሙያነትን ደርቦ የሰራ ሲሆን በአሁን ወቅት በማስተማር ላይ ይገኛል። ፊኒስ ዘመናዊ የተፈጥሮ ሕግ ተከታይ ቢሆንም ጥንታዊ የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና አሻራዎች በሥራዎቹ ውስጥ ማየት ይቻላል። ፍልስፍናው ሰባት ተፈጥሯዊ የሆኑ መሠረታዊ መልካም እሴቶች እንዳሉ ይጠቅሳል። እነዚህም ሕይወት ፤እውቀት፤ መዝናኛ፤የስነ-ውበት አድናቆት፤ ወዳጅነትንና ጓደኝት፤ተግባራዊ አመክንዮ እና ሃይማኖት ወይም እምነት ናቸው[19]።

ሕይወት ቀዳሚው የተፈጥሮ ስጦታ ሲሆን የመኖር እና የመሥራት ጉልበት ምንጭ ነው። ሌላኛው እውቀት ብቻ ሳይሆን የማወቅ ጉጉትንም ይጨምራል ይህን ስንል እውቀትን ለማወቅ እና እውነትን ለማግኘት ጥማት ስንል ብቻ የምንፈልገው መሆን አለበት። መዝናናት ከእውቀት ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በራሱ የሚቆም እሴት ሲሆን እውነተኛ ደስታን እና መዝናናት የሚያመጣ እንዲሆን ለመዝናናት ስንል ብቻ ልንተገብረው ይገባል። ውበትን ማድነቅም እንዲሁ ምንም ዓይነት ውጤት ሳንጠብቅ የስነ-ውበት እሴቶችን ለመፍጠር የምንተገብረው ነው።

ማኅበራዊ ግንኙነት የሚፈጠረውና እውነተኛ ጓደኝነትን እና ወዳጅነትን በመፍጠር ሲሆን ከእነዚህ ጉድኝቶች ውስጥ ፈልቆ የሚገኘው ስሜትም የእውነተኛ ደስታ ምክንያት ነው። ተግባራዊ አመክንዮ ሰዎች እና ማኅበራት የግልና የጋራ ዕጣ ፈንታቸውን የሚወስኑበት መሣሪያ ሲሆን የመጨረሻው መልካም እሴት ሃይማኖት ደግሞ ከላይ የተጠቀሱት መልካም እሴቶች በሙሉ ስርዓት እና መልክ የሚይዙበት ማጠቃለያና መደምደሚያ እሴት

19 John Finnis, *Natural Law and Natural Rights,* Oxford: Clarendon Press, 1980

ነው። እነዚህ እሴቶች በተፈጥሮ የተገኙ ሲሆኑ በምድር ላይ የሰው ልጅ ሕይወት ትርጉም እና አላማ የሚያገኝባቸው መንገዶች ናቸው። እነዚህ መሠረታዊ **የመልካምነት እሴቶች (basic goods)** የማይበላለጡ እና የማይወዳደሩ በራሳቸው የሚቆሙ ናቸው።

ጆን ፊንስ በ1962 የካቶሊክ እምነትን ተቀብሎ ጠንካራ እና ወግ አጥባቂ ሊባል የሚችል ፍልስፍና ሊያራምድ በቅቷል። በተለይም የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻን በመቃወም በተደጋጋሚ ግዜ የፃፈ ሲሆን መንግስት የእምነት ተቋማትን ተመሳሳይ ጋብቻን እንዲቀበሉ ሊያስገድዳቸው አይችልም ሲል ተከራክሯል። ለፊንስ ሃይማኖት ከተራ ማኅበር አባልነት ያለፈ የሕይወት አላማ የምናገኝበት መንገድ ነው። ፊንስ የገለፃቸውን የተፈጥሮ ሕግ መሠረታዉያን በሚገባ ያብራራቸው ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አንዱ"Practical reasonableness"(ተግባራዊ አመክንዮ) አንዱ ነው።

ተግባራዊ አመክንዮ የተፈጥሮ ሕግ መሠረታዊ አሃድ እንደመሆኑ እውነተኛው እና ትክክለኛው ተግባር ለመምረጥ ይረዳናል። ሕይወታችንንም በአግባቡ እንድንመራ እና እንድናቅድ ያደርጋል ምክንያቱም በዚህ መርህ ሕይወቱን የሚመራ ሰው ተራ እና ድንገተኛ የሆኑ የሆነ የሕይወት ምርጫ አያደርግም። አንድ ሰው ህይወቱን በዚህ መንገድ ሲመራ የህይወቱን ዕቅድ በሚገባ እንዲያቅድ ብቻ ሳይሆን በአትኩሮት እንዲፈፅም ያግዘዋል።

ተግባራዊ አመክንዮን ከሐሳባዊ አመክንዮ(Theoretical reasoning) መለየት እንደሚገባን ሲያስረዳ ተግባራዊ አመክንዮ ወደ ሰናይ ተግባር በቀጥታ የሚያመላክት እና ማድረግ ያለብንን ተግባር የሚጠቁመን ሲሆን ሐሳባዊ አመክንዮ ግን የተለያዩ ተግባራትን ብንፈፅም የሚያመጡብንን አዎንታዊ እና አሉታዊ ዉጤቶች የሚተነትን ነው። በመሆኑም እነዚህ የስነ-ምግር መሠረታውያን(Basic goods) ለመፈፀም የሰው ልጆች ሊታጠቁ እና ሊሠለጥኑበት የሚገባው አመለካከት አቅጣጫ ተግባራዊ አመክንዩ ነው። መሠረታዊ ምግባራት የስልጣን ተዋረድ የሌላቸው እና እኩያ ናቸው። ራሱን የሚያውቅ እና ከሕፃንነት ዓለም የወጣ ሰው ሁሉ

በተፈጥሯዊ ደመ-ነፍስ የሚያውቃቸው ከመሆናቸው የተነሳ የሚጥሷቸው ሰዎች እንኳ በቅድሚያ በደመ-ነፍሳቸው የሚረዷቸው ናቸው።

እያንዳንዱ ግለሰብ እነዚህን ምግባራዊ መሠረታውያን ወይም መሠረታዊ ምግባራት (Basic good) ለመፈፀም ሲተጋ እንደ ማኅበረሰብ ደግሞ የወል ጥቅም (Common good) በተያያዥነት ወይም በጥቅል ሊሳካ ይችላል። እነዚህ መሠረታዊ ምግባራት በሰዎች ሁሉ የሚፈፅሙ እንዲሆኑ በአግባቡ በመንግስት ሊደገፍ ይገባል። ፊኒስ የካቶሊክ እምነት ተከታይ እንደመሆኑ የቅዱስ ቶማስ አኩይናስን የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍናዎች የሚቀበል ቢሆንም፤ አሁን ያለው ዘመናዊ ማኅበረሰብ በመካከለኛው ዘመን ከነበረው እጅግ ሃይማኖተኛ ማኅበረሰብ የተለየ በመሆኑ የተፈጥሮ ሕግ ዘመኑን እንዲዋጅ አድርገን መተርጎም አለብን ብሎ ያምናል።

የተፈጥሮ ሕግጋት የመለኮት ትእዛዝ ስለሆኑ ብቻ ልንገዛላቸው የምንገደድ ሳይሆን ከሃይማኖት ግዴታ በተነጠለ መልኩም ቢሆን የሰው ልጆች ሕይወት በምድር ላይ እንዲያብብ የሚረዱ ናቸው። በዚህም ምክንያት ፊኒስ የቶማስ አኩይናስን “Primary Precept” በራሱ በመተርጎም ወደ መሠረታዊ ምግባራት (basic good) ሊቀይራቸው ችሏል። በመሆኑም እነዚህ ምግባራት ከፈጣሪ እና ሃይማኖት ተለይተውም ቢሆን በራሳቸው ሊቆሙ እንደሚችሉ በመጠቆም ተከራክሯል። እነዚህ መሠረታውያን የሞራል ፍልስፍና ጠቋሚዎች ስለሆኑ የራስን ወይም የሰውን መሠረታዊ ምግባራት የሚጎዱ ነገሮች በሙሉ ኢ-ሞራላዊ ሲሆኑ፤ የሚጠቅሙ እና የሚደግፉ ነገሮች ደግሞ ሞራላዊ ናቸው።

ፊኒስን የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና (New classical natural law) አቀንቃኝ አድርገው ይስሉታል፣ ሌሎች ደግሞ Neo-Thomism የአዲሱ የቶማስ አኩይናስ ተንታኝ የሚሉትንም አይቀበልም። ጆን ፊኒስ እ.ኤ.አ እስከ 2010 ድረስ የሕግ ፍልስፍናን ካስተማረ በኋላ በጡረታ ሊገለል ችሏል።

ከኢ-አማኒነት ወደ አማኝነት- ሲ ኤስ ሉዊስ

“ተፈጥሯዊ የሞራል ሕግ እና ክርስትና”

“ክርስትና ለጠያቂ አእምሮ” በሚል ወደ አማርኛ የተቀየረው ይህ ድርሳን ከኢ-አማኒነት ወደ አማኝነት ውጣ ውረድ የበዛበት ጉዞ ያደረገው የሲ ኤስ ሉዊስ (1898-1963) ግለሰባዊ እና አመክንዮአዊ ትንታኔ ነው። ሉዊስ መጸሐፉን አጠቃላይ በሆነው የተፈጥሮ ሕግ እና በክርስትና አስተምህሮቶች መሀከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩን ለማስረዳት የተጠቀመበት ዘዴ ነው። በርግጥ አንድን የማያምን ግለሰብ መጽሐፍ ቅዱስን ሳይጠቅሱ በተፈጥሮ በተሰጠ ሞራሊቲ(Natural morality) እና በክርስትና መሀከል ያለን ግንኙነት ማሳየት እጅግ ከባድ ተግባር ነው። ሉዊስ ከተፈጥሮ ሕግ(Natural Law) የተነሳው ማንኛውም ግለሰብ በውስጡ እና በአካባቢው ያለውን የተፈጥሮ ሕግ መካድ ስለማይችል ከእነዚህ የተፈጥሮ ሕግ ቀላል እና ሁሉም ሰው ሊረዳው ወደሚችለው የክርስትና ዶግማ አንባቢዎቹን ለማሻገር ስለፈለገ ነው።

ለሉዊስ ክርስትና እንደ ተፈጥሮ ሕግጋት ሁሉ ግልጽ እና ሁሉም ሰው ሊረዳው የሚችል ሐሳብ ነው። ለዚህ ይመስላል መጽሐፉን /ሚር ክርስቲያኒቲ/(Mere Christianity) ሌጣ ክርስትና ወይም ቱባ ክርስትና አልያም በተለምዶ አባባል ክርስትናን “እንደወረደ” ፤ ሳይወሳሰብ እና ሳይጠላለፍ ለተራው ምእመን ለማስረዳት የሚጥረው፤የተሳካለትም ይመስለኛል። በእግዚያብሔር የማያምን የነበረ ሰው እንደመሆኑ ክርስትናን ከውጭ እንደ ባይተዋር ተመልክቶ የጻፈው ይህ ትንታኔ ለሚያምኑም ለማያምኑም ግልጽ መልስ አለው።

ሉዊስ፤ ሰዎች ሁሉ የትም ቢኖሩ ወይም በየትኛውም ክፍለ ዘመን ቢወለዱ ትክክለኛውን ነገር ከስሕተት መለየት እንደሚችሉ ይጠቅስና አንዳንዶች ግን ይህ *ተፈጥሯዊ የሞራል ሕግ እንደሌሎቹ ደመነፍሶቻችን ሲዳብር የኖረ ጋርዮሻዊ ደመ ነፍሳችን አይደለምን* ብለው እንደሚጠይቁ

ይናገራል። ቀጥሎም ይህ የሞራል ሕግ የምትለው በትምህርት የተቀረጸብን አንዳች ማኅበራዊ ስምምነት አይደለምን የሚሉት እንዳሉም ይጠቅሳል። እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ብዙ ኢ-አማንያን የሚያነሷቸው መሆኑ ግልጽ ነው። የሞራል ሕግ እንደማንኛውም ባህል ሁሉ በዝግመታዊ ለውጥ እየተቀየረ የሚሄድ ማኅበራዊ ስምምነት (Social contract) መሆኑን አብዛኞቹ ኢ-አማንያን የሚጋሩት ነው። እንደነሱ አባባል ይህ ማኅበራዊ ስምምነት አብዛኞቻችን ላይ ያለፍቃዳችን የተጫነ (Involuntary indoctrination) መሆኑን ከሰብዓዊ መብት ጥሰት ጋር የሚያያይዙትም አልጠፉም። ምዕራፍ አንድ እና ሁለት በእነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው።

በርግጥ ከሶቅራጠስ እሰከ ኒቼ ድረስ የምዕራቡ ዓለም የሞራል ፍልስፍና ለብዙ ዓመታት እነዚህን ጥያቄዎች ሲጠየቅ የኖረ ነው። መልካሙ ነገር ምንድነው፤ እንዴትስ እናውቀዋለን፤ አውቀነውስ እንዴት እንተገብረዋለን የሚሉት ጥቂዎች Virtue Ethics የሚያጠናቸው የሞራል ፍልስፍና ጥያቄዎች ናቸው። ለሶቅራጠስ ሞራሊቲ በትምህርት የሚገኝ ባህሪ ሲሆን ክፋት ደግሞ ትክክለኛውን የሞራል ትምህርት ያለማግኘት ውጤት ነው። አንድ ግለሰብ ሶቅራጠስን በጎውን ነገር እያወቁ ክፋት የሚሰሩትንስ ምን ትላቸዋለህ ቢለው "እነዚህ ሰዎች ትክክለኛውን የግብረገብ ትምህርት ያገኙ የመሰላቸው ግን የሌላቸው ናቸው" ይላል። ሉዊስ ግን ከላይ የተቀመጡትን ጥያቄዎች ሲመልስ እንዲህ ይላል።

> *አደጋ ውስጥ ካለ ሰው የድረሱልኝ ጥሪ ሰማህ እንበል። ሁለት ግፊቶች ሊሰሙህ ይችላል- አንዱ እንድትረዳው ይገፋሃል (ከጋርዮሻዊ ደመነፍስ የተነሳ)፤ ሌላው ደግሞ አደጋውን ሸሽ ይልሃል (ራስን ከመጠበቅ ደመ ነፍስ የተነሳ) ነገር ግን ከእነዚህ ከሁለቱ ሌላ በውስጥህ፤ የመሸሹን ግፊት ተጭነህ የመርዳቱን ግፊት እንድትከተል የሚነግርህ ሦስተኛ ነገር ታገኛለህ*[20]

20 አዲስ አሰፋ፤ ክርስትና ለጠያቂ አእምሮ፤ ሮሆቦት አታሚዎች፤ 2006፤ ገፅ 23

እንደ ሉዊስ አመለካከት ይህ ሦስተኛ ነገር ተፈጥሯዊ የሞራል ሕግ ነው። ይህ ሦስተኛ ሕግ ስሜቶቻችንን አንዳንዴ እያፈነ ሌላ ጊዜ እያበረታታ ራሳችንንም ጭምር ለአደጋ እያጋፈጠ ይመራናል። በተጨማሪም እነዚህን ሕጎች ከማጎበረሰቡ ልንማራቸው የምንችል ቢሆንም በዓለም ላይ ያሉ የተገቢ ምግባር ሕጎች እምብዛም አይለያዩም ሲል ሉዊስ ይከራከራል። እዚህ ጋር ሉዊስ ሁለት ያላሰባቸው ነገሮች ያሉ ይመስለኛል። አንደኛው ይህ ሦስተኛ ድምፅ በራሱ በዝግመታዊ የሞራል እድገት ሊዳብር የመቻሉን አጋጣሚ ነው። የሰው ልጆች በአንድ የዝግመታዊ ለውጥ ሂደት አደጋ ሊያስከትል የሚችል ቢሆንም እንኳ ለደካሞች የማዘን ወይም ወንድምን የመርዳት ጋርዮሻዊ ደመነፍስ አዳብረው ሊሆን ይችላል። ሌላው ያልተረጋገጠ ድምዳሜ ደግሞ በዓለም ላይ ያሉት እና ከአንድ ሕዝብ አንድ ሕዝብ የምናያቸው የሞራል ሕጎች ልዩነት *"የሚታሰቡትን ያህል ሰፊ አይደሉም"* የሚለው ድምዳሜ ሲሆን በእኔ አመለካከት በዚሁ ሀገራችን እንኳ ይህ መርህ እንደማይሰራ እጠረጥራለሁ።

ሌላው መጽሐፉ ከሚያጎላቸው ነገሮች አንዱ ሰዎች በውስጣቸው የተቀመጠ አንዳች የመልካምነት ጠቋሚ ጉልበት ቢኖርም ገቢራቸው ግን ያንን ኃይል የሚቃረን መሆኑን ነው። ይህ አስገራሚ ግጭት ነው ይልና ከዚህ የተፈጥሮ ሕግ ጀርባ አንዳች እኛ *ያልፈጠርነው ግን ልናከብረው የሚገባ* ኃይል እንዳለ ይጠቁማል። ከዚህ ሕግ በስተጀርባ ያለው ኃይል ይህንን አጽናፈ ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ ነው። ሉዊስ ስለዚህ ዩኒቨርስ አመጣጥ ቁሳዊ፤ሃይማኖታዊ እና የሕይወት ኃይል የሚባሉ ፍልስፍናዎች በዋነኝነት ተጠቃሽ እንደሆኑ ይገልጽና የዚህን ጉልበት ትርጉም እና አላማ ለመረዳት ግን ሰውን እንደ ጥናታችን ናሙና ልንወስድ እንደሚገባ ያትታል። ምክንያቱም በመላው ዩኒቨርስ ከውጭ በማየት ልንማርበት ከምንችለው በላይ ልናውቀው የምንችል አንድ ነገር ብቻ አለ። ያም አንድ ነገር ሰው ነው። ሰዎችን ከውጭ ከማጥናት እናልፋለን፡ እኛ ራሳችን ሰዎች ነን። ሰውን በተመለከተ ውስጣዊ መረጃ አለን፤ የማወቅ እድሉ አለን[21]

21 ዝኒ ከማሁ፤ ገፅ 33

በርግጥ ሐሳቡ እንደዚህ የቀለለው ለዘመናት የሚያከራክሩትን እና ለፈጣሪ መኖር የሚነሱት ሐሳቦች ታልፈው ነው። እነ Cosmological argument, Design argument, Fine tuning argument እና Ontological argument ብዙም ሳይብራሩ ተድበስብሰው እንደውም ሳይጠቀሱ ተዘለዋል ማለት ይቻላል። ለደራሲው ከዩኒቨርሱ ጀርባ ያለውን ኃይል ለማወቅ ተራሮችን፤ ወንዞችን እና ተክሎችን ማጥናት አስፈላጊ አይደለም። እነዚህ ነገሮች በዚህ ኃይል ቢፈጠሩም ከውጭ ሆነን እንጂ ልክ እንደ ሰው ልጅ ከውስጥም ልናጠናቸው አንችልም። በመሆኑም ለፈጣሪ መኖር አመርቂ ምላሽ አይሰጡንም።

ልከፍተው የተፈቀደልኝ ብቸኛ ፖስታ ሰው ነው። ሰውን፤በተለይም ደግሞ እኔ የተባልኩትን ሰው ስመለከተው፤በራሴ እንደማልኖርና በአንድ ሕግ ስር እንዳለሁ አንዳች ኃይል ወይም ነገር በተወሰነ መልኩ እንድኖር እንደሚፈልግብኝ ተረዳሁ[22]።

ከዚህ የምንረዳው ሉዊስ ከመለኮት ጋር ያደረገው ግላዊ እና ልዩ ተራክቦ (Personal and subjective experience) ለዚህ መጽሐፍ መሠረት መሆኑን ነው። በርግጥም እሱ ባለፈበት የህይወት ተሞክሮ ውስጥ ያለፈ ወይም ሊያልፍ ያለ አልያም እያለፈበት ያለ ግለሰብ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ሰው ይህ መጽሐፍ ላይገባው ይችላል። ለምሳሌ በጣም ሃይማኖተኛ ለሆነ ሰው መከራከሪያ ሐሳቦቹ ሊቀሉበት ይችላሉ፤በጣም ኢ-አማኒ(Anti-theist) ወይም አላማኝ(Atheist) ለሆነ ግለሰብም እንዲሁ ላይዋጥለት ይችላል። ልክ እንደ ሉዊስ ከኢ-አማኒነት ወደ አማኝነት የመጡ ሰዎችም ቁርጥ ያለ እና ላደረጉት ለውጥ ቅልብጭ ያለ የአመክንዮ ቀመር አያቀብሉንም። ለዚህም ይመስላል ደራሲው በምእራፍ 5 መግቢያ ላይ አንባቢው ሽር እንደተሰራበት እንዳይቆጥር የሚያስጠነቅቀው፤ ምክንያቱም እሱ ራሱ የፍልስፍና ተማሪ የነበር እንደመሆኑ ከተፈጥሮ ሕግ ወደ ፈጣሪ መኖር የሄደበት አካሄድ አመክንዮው ብቻ ለሾለ ግለሰብ ሊዋጥለት እንደማይቻል

22 ዝኒ ከማሁ ፤ ገፅ 34

ስለተገነዘበ ይመስለኛል። አንድ ግለሰብ ከተፈጥሮ ሕግ ጀርባ አንድ ኃይል እንዳለ ካወቀ ፤ይህም ኃይል የዚህ ዩኒቨርስ ፈጣሪ እንደሆነ ካወቀ እና ከዚህ ኃይል ጋር ቅራኔ ውስጥ እንዳለ ከተገነዘበ መድሃኒት ያስፈልገዋል ይልና በመጸሐፍ ሁለት ወደ ተካተተው የክርስትና አስተምህሮ ይሻገራል።

በምእራፍ ሦስት "አስደንጋጩ አማራጭ" በሚል ርእስ ስር የቀረበው እና ብዙ ምሁራን "The Lewis Trilemma" በማለት የሚጠሩትን ነው። በእኔ አመለካከት የመጸሐፉ አስኳል ያለው በዚህ ክፍል ውስጥ ነው። አንድ አንባቢ ደራሲው እስካሁን ያለው ነገር ባይገባው ወይም ባይጥመው እንኳ በዚህ ክፍል ስለ ክርስቶስ ማንነት ያስረዳበትን መንገድ ሳያደንቅ ማለፍ አይችልም። ቃል በቃል ባቀርበው የተሻለ ይመስለኛል።

> *ማንም ሰው፤ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ብዙ ጊዜ የሚሉትን የጅል አባባል እንዳይል ለመከላከል እየጣርኩ ነው ያለሁት፡- "ኢየሱስን እንደ ታላቅ የሞራል መምህር ለመቀበል ዝግጁ ነኝ፤አምላክ ነኝ የሚለውን ግን አልቀበልም።" ይህ ከቶ ልንለው የማይገባ ነገር ነው። እንደ ሰው እንዲሁ ሰው ብቻ ሆኖ ኢየሱስ የተናገራቸውን ዓይነት ነገር ቢል ፈጽሞ ታላቅ የሞራል መምህር ሊሆን አይችልም። ወይ አእምሮው የተቃወሰ መሆን አለበት- "ቅቅል እንቁላል ነኝ" ከሚለው ሰው የሚደመር- አሊያም የገሃነመ ዲያብሎስ መሆን አለበት። መምረጥ አለብህ። ይህ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፤ነውም- ካልሆነ እብድ ወይም ከዚያ የከፋ ነው። እንደ ጅል ቆጥረህ ፊትህን ልታዞርበት ትችላለህ፤ እንደ ጋኔን ቆጥረህ ልትተፋበት እና ልትገድለውም ትችላለህ። ወይም እግሩ ስር ወድቀህ ጌታ እና አምላክ ብለህ ልትጠራው ትችላለህ። ሆኖም "ታላቅ መምህር የሆነ ሰው ነው" የሚለውን የማይረባ መጃጃል ይዘን አንቅረብ። እንዲህ የሚያስብል ክፍተት አልተወልንም። ሐሳቡ ያ አልነበረም[23]።*

23 ዝኒ ከማሁ ፤ ገጽ 54 እና 55

እውቁ ደራሲ ጆሽ ማክዶዌል “More than a carpenter” በተሰኘው መጻሐፋቸው ይህንን ሐሳብ ብቻ ወስደው አንድ መጽሐፍ ሙሉ አብራርተውታል። በእኔም አመለካከት ክርስቶስ ከተናገራቸው ነገሮች በመነሳት በክርስቶስ ላይ ልንይዘው የሚገባ አቋም ከዚህ የዘለለ ሊሆን እንደማይችል ነው።

በርግጥ ሀገር በቀል እና በኩር ምሁራን ከሆኑት ኢትዮጲያውያን መካከል አንዱ የሆኑት ልዑል ራስ ካሳ ኃይሉ ፍኖተ-አእምሮ በተሰኘ ድርሳናቸው በፈጣሪ ጉዳይ ላይ ሁሉም ሰው የተለያየ አመለካከት የመያዙን ምክንያት የሚያስረዱበት ሃተታ ልብ ልንል ይገባል።

> *ሰዎች የጌታቸውን መልክ በሩቅ ሆነው ሲመለከቱ አንዱ እንዲያ ያለ ነው ሁለተኛው እንዲህ ያለ ነው ብለው ባንድ ሰው መልክ ላይ ቢስራከሩ ጌትነቱን አምነው ስልጣኑን ፈርተው ከተገዙለት ጌትየው ከነሱ ላይ የሚፈልግባቸውን የጌትነቱን መጠን እና የትእዛዙን መፈጸም ብቻ ነው እንጂ በመልኩ ቅርጽ ላይ የሚከራከሩት ግን ርቀው በሚመለከቱበት በየዓይናቸው ብርሃን መጠን በሚያዩት የመሰላቸውን ብቻ የሚያወሩ ስለሆነ አለቆች ህጻናት እንደሚጫወቱበት ቃል እያደረገ ንግግራቸውን እየናቀ ያልፈዋል እንጂ የሚከራከሩበት ምክንያት በቅናት ለኩራት ካልሆነ በእውነት በልባቸው ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን እየመሰላቸው የሚነጋገሩበትን ማየት የማይችሉትን መልኩን ማወቅ የማይችሉትን ጠባዩን ካላወቁ ብሎ አይፈርድባቸውም*[24]።

ራስ ካሳ ይህን ቢሉም ክርስቶስ ታላቅ የሞራል አስተማሪ ነበር እያሉ የሚያጭበረብሩት እና ጌትነቱን ክደው ካለበት ደረጃ ቀስበቀስ ሊያወርዱት የሚጥሩት በዘመናችን ያሉት ተደናብረው የሚያደናብሩት እነ ዲፓክ ቾፕራ፤ ኤካርት ቶል እና በእነርሱ የሂዩማኒዝም ትምህርት እየተፍገመገመች ካለችው የዛሬይቷ ቤተ-ክርስቲያን የምንረዳው የሉዊስን

24 ልዑል ራስ ካሳ ሃይሉ፤ ፍኖተ አዕምሮ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1953፤ ገፅ 16

የሦስትዮሽ አጣብቂኝ በግድም ቢሆን የትውልዱ የመወያያ ርእስ ማድረግ እንዳለብን ነው። በርግጥ ይህ ሂደት ወጣቱን ወደ አስጨናቂ እና አስደንጋጭ ጽንፍ የሚገፋ ቢመስልም ዘመኑ የጋረጠብን ምርጫ የሌለው ጉዳይ ነው።

በዚህ መጽሐፍ የተነሳው ሌላው ወሳኝ የፍልስፍና ጥያቄ የሞራል ፍልስፍና ሐሳብ ነው። በደራሲው እይታ ሞራል ሦስት ነገሮች ይዳስሳል። በመጀመሪያ፤በግለሰቦች መሀከል ያለ ፍትሐዊነትና ስምምነትን ይመለከታል። ሁለተኛው፤በእያንዳንዱ ግለሰብ ውስጥ ያሉ ነገሮችን ማጽዳት ወይም ስምሙ እንዲሆኑ መቻልን ይመለከታል። ሦስተኛ፤የሰው ልጅን ሕይወት አላማ ባጠቃላይ-ሰው ለምን እንደተሰራ፤የመርከቦቹ ጉዞ ወዴት እንደሆነ፤የሙዚቃ ቡድኑ መሪ እንዴት ያለ ዜማ እንዲፈልቅ እንደፈለገ-ይዳስሳል።

በርግጥ ይህ አንቀጽ የሞራል ፍልስፍናን ብቻ ሳይሆን ደራሲው በክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር ዙርያ በሚቀጥሉት ገጾች ያተታቸውን ሐሳቦች በሙሉ እንደ መልህቅ የያዘ እና የአሪስቶትልን አራቱን የዲበአካላዊነት ምሶሶዎችንም ጭምር የተንተራሰ ነው። መጽሃፉ ስለ መልካም ምግባር እና ባህሪ ፤ ማኅበራዊ ሞራል፤ወሲባዊ ሞራል፤ክርስቲያናዊ ምግባር፤ ይቅርታ፤ ፍቅር፤ ተስፋ እና እምነት በታላቅ ሥነ-ጽሑፋዊ ውበት በታጀቡ አንቀጾች የታጨቀ ነው። ከዚህም የተነሳ የቱን ጥሎ የቱን ማንሳት እንደሚቻል ግራ ያጋባል። ከዚህም የተነሳ መጽሐፉ ሦስት ራሱን የቻለ መጽሐፍ ሆኖ ቢቆም እና ራሱን ችሎ ሊገመገም ይችላል ብዬ አስባለሁ።

በርግጥ ዓለማችን በአሁን ሰአት ከNormative Moral Philosophy ወደ Non-normative moral philosophy እየሄደች ይገኛል። ይህ ማለት ደግሞ በድሮ ዘመን የነበሩት እንደ መልካሙ ተግባር (The ultimate Good) ምንድነው? እንዴትስ እናውቀዋለን? የሚሉት መሠረታዊየሞራል ጥያቄዎች እየተዘነጉ መልካምነት (Goodness) ራሱ ምንድነው፤መጀመሪያ እሱን ልንተረጉም እና ልንስማማበት ይገባል ወደሚል ክርክር ውስጥ

ከገባን ቆይተናል። ለአንድ ማኅበረሰብ መልካም የሆነ ተግባር ለአንድ ማኅበረሰብ ደግሞ መልካም አይሆንም። ክርስትና ግን አጠቃላይ የሆነ ግለሰባዊ እና ማኅበረሰባዊ ሞራል እንዲኖረን ያመላክታል። በርግጥ በአንድ የዙሉ ክርስቲያን እና የእንግሊዝ ክርስቲያን መሀከል የማይናቅ የአኗኗር ዘይቤ እና ማኅበረሰባዊ ግብረገብ ልዩነት መኖሩ የማይካድ ነው። ሆኖም ክርስትና እነዚህን ማኅበረሰባዊ ልዩነቶች የሚያልፍ እና የሚያቅፍ የሞራል ፍልስፍና አለው። ደራሲውም ይህንን አስረግጦ ይናገራል። **ይህ የሞራል ፍልስፍና ጥያቄ ከሌላ የዲበአካላዊነት ፍልስፍና ጥያቄ ጋር ይገናኛል። ምክንያቱም** *መልካሙ ተግባር (ultimate Good) ምንድነው?* **ከሚለው ጥያቄ ጀርባ** *ብቸኛው እና ጠቅላዩ እውነት(Objective and Universal Truth)* **ምንድነው? የሚለው የዲበአካላዊነት ፍልስፍና ጥያቄ ይገኛል።**

በመጀመሪያ ደረጃ ሉዊስ ሁልጊዜም ቢሆን የክርስትና እምነት ዐቃቤ አለመሆኑን አበክሮ ይናገር እንደነበር ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም የጻፋቸው መጻሐፍት በሙሉ ከመለኮት ጋር ካደረገው ልዩ እና ግላዊ ተራክቦ(Personal and Subjective experience) የመነጩ እንደመሆናቸው ጽሑፎቹ በሁሉም ጊዜ እና ቦታ የክርስትናን ዶግማ በሙሉ ደግፈው ሊከራከሩ ይችላሉ የሚል እምነት አልነበረውም። ይህ ብቻ ሳይሆን ከዋናው የክርስቲያኖች ዶግማ ጋር ሊጋጩ የሚችሉ የግል ሐሳቦቹን በመጥቀሱ ጭምር ነው። እንደ እኔ አመለካከት ግን እነዚህ አንቀጾች ሁላችንም የምንናፍቀውን ኢኩሚኒዝም ያፋጥናሉ እንጂ ሌላ ችግር የሚፈጥሩ አይመስለኝም።

ለማንኛውም አንድ ሁለት አንቀጾችን ለማሳያነት እንመልከት፦

ክርስቲያን ከሆንክ፤ ሌሎች ሃይማኖቶች ሙሉ ለሙሉ ተሳስተዋል ብለህ ልታምን አያስፈልግህም። አምላክ የለም ብለህ የምታምን ከሆንክ በመላው ዓለም የሚገኙ ሃይማኖቶች ሁሉ ያላቸው ማዕከላዊ ነጥብ ስህተት ነው ብለህ ማመን አለብህ። ክርስቲያን ከሆንክ ሃይማኖቶች ሁሉ ስለ

እውነቱም ቢሆን ትንሽ ፍንጭ አላቸው ብለህ ለማመን ነፃ ነህ[25]።

ስለስላሴ ትምህርት በሚለው የመጽሐፉ ክፍል ደግሞ እንዲህ ይላል።

ሌሎች ሃይማኖቶች ውስጥ ሆነው እግዚአብሔር በምስጢራዊ ተጽእኖ ከክርስትና ጋር ስምም የሆኑ የሃይማኖታቸው ክፍሎች ላይ እንዲያተኩሩ እየመራቸው የሚገኙ እና ከዚህ የተነሳ ሳያውቁት የክርስቶስ የሆኑ አሉ። ለምሳሌ ቅን የሆነ የቡድሂዝም እምነት ተከታይ፤ ሃይማኖቱ ስለ ምህረት ያለው አስተምህሮ ላይ ይበልጥ እንዲያተኩርና ሌሎች የተወሰኑ ነጥቦች ላይ ቡድሂዝም የያዛቸውን አስተምህሮዎች(አሁን አምንባቸዋለሁ ቢልም) ችላ እንዲላቸው ሊሆን ይችላል[26]።

ይህ እንግዲህ ዛሬ ብዙ ቱባ ቱባ የሚባሉ የቤተክርስቲያን መሪዎች ድህረ-ዘመናዊነት (Post- modernism), አንጻራዊነት (Relativism) የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ (New ageism), (Humanism) ወይም (Secularism) እያሉ የተለያየ ቁንጥ የሚያወጡለትን አስተሳሰብ ሊመስል ይችላል።

ሁላችንም እንደምናውቀው የአንድ ክርስቲያን ዐቃቤ እምነት ዋነኛ ተግባር (ሌሎች እንዳሉ ቢሆንም) ክርስትና ጠቅላይ እና ብቸኛ እውነት (Universal and Objective Truth) መሆኑን ማስረዳት ነው ብለው የሚከራከሩ አያሌ የሥነ-መለኮት ተመራማሪዎች አሉ። ይህ ተግባር እጅግ ከባድ በመሆኑ በብዙ ሃይማኖቶች መሀከል ለረጅም ዘመናት ሲያከራክር የኖረ ነው። ምክንያቱም አብዛኞቹ ሃይማኖቶች በተለይም ሦስቱ ከመካከለኛው ምሥራቅ የፈለቁቱ ማለትም ክርስትና፤እስልምና እና አይሁዲነት Mono-theistic (አሃዳዊ) እንደመሆናቸው የየግላቸው ሃይማኖታዊ ምልከታ ጠቅላይ እና ብቸኛ እውነት (Universal and Objective Truth) እንደሆነ ያስረዳሉ።

25 ክርስትና ለጠያቂ አዕምሮ ፤ ገፅ 43

26 ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 178

ይህ አመለካከት አካታች እና አንጻራዊ (Inclusive and Relative) ከሆኑት የሩቅ ምሥራቅ ሃይማኖቶች በእጅጉ የራቀ ነው። ለአንድ ቡድሂስት ወይም ሂንዱ የእሱ ሃይማኖት ወይም አምላክ በዚህ አጽናፍ ዓለም ላይ ያለ ብቸኛ እና ገዢ አመለካከት መሆኑን ማስረዳት አይጠበቅበትም። አንድ Analytic Philosopher የContinental Philosophy አርቲ ቡርቲ እንደማይወጥለት ሰው ክርስቲያን ባይሆን እንኳ በሕይወት እያለ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥለት ሐሳብ በምድር ላይ አንድ ጠቅላይ እና ብቸኛ እውነት (Universal and Objective Truth) መኖሩን ማስረዳትን ነው። በዚህ ምክንያት አብዛኞቹ Analytic Philosophers አማኝም ሆኑ ኢ-አማኒ በዚህ ዩኒቨርስ ከብዙ ምርምር በኋላ ሊደረስበት የሚችል አንድ እና ብቸኛ የሆነ ዲበአካላዊ እውነት መኖሩን ያምናሉ።

እንደ እነርሱ አባባል አንጻራዊነት የፍልስፍና ቀዳሚ ኃጥያት (Original sin of Philosophy)ነው:: ይህም ማለት ዲበአካላዊነትን ከእውቀት ፍልስፍና ጋር በማደባለቅ የመከሰት ጠንቅ ነው። ሰዎች አንጻራዊ የሚሆኑት በራሳቸውም ሆነ በሌሎች ሃይማኖቶች ላይ ያላቸው እውቀት አነስተኛ ወይም የማያስተማምን ሲሆን ነው። እንደው እንደ ድንገት ክርስትናም ሆነ ቡድሂዝም የሚያስረዱት ትምህርት እውነት ወይም ውሸት መሆኑን የምናውቅበት የምርምር ደረጃ ላይ ብንደርስ እና ሁለቱንም ወገኖች የሚያሳምን አካላዊ ማስረጃ (Empirical Evidence) ቢገኝ በርግጥ ትክክል ሆኖ የሚገኘው የአንደኛው ሃይማኖት አስተምህሮ ነው።

ከዚህ አመለካከት በተቃራኒ የቆሙት አንጻራዊያን ደግሞ እንዲህ ሲሉ ይከራከራሉ። ለክርስቲያኑም ሆነ ለቡዲሂስቱ እኩል አሳማኝ የሆነ አካላዊ ማስረጃ (Empirical evidence) ቢገኝ እንኳ እውነቱ ከሁለቱም ሃይማኖቶች የተለየ እና የገዘፈ ግን በሁለቱም ሃይማኖቶች በተለያየ መንገድ የተገለጸ ሊሆን የመቻሉን እድል ነው። እንደነሱ አመለካከት እነዚህ እምነቶች አንዱን እውነት ከተለያየ አንጻራዊ ምልከታ ገለጻውት ይችላል የሚል ነው። የሰው ልጅ እውቀት እጅግ ውስን በመሆኑ ትልቁ እውነት በአንድ

ሃይማኖት ውስጥ ብቻ ሊገለጽ አይችልም የሚል ነው። ከዚህም ለጠቅ ያደርጉና ሁሉንም ሃይማኖቶች ወይም ዲበአካላዊ አስተሳሰቦች የሚያስረዳ እና በሁሉም ወገኖች ተቀባይነት ያለው ማስረጃ እስካላቀረበ ድረስ እኔ ብቻ ነኝ ትክክል ለዚህም የሚያስረዳ እኔ ብቻ የምቀበለው ማስረጃ አለኝ ብሎ ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት ምንም አይፈይድም በማለት ክርክራቸውን ያሳርጋሉ።

እንደእኔ አመለካካት የትኛውም ዐቃቤ እምነታዊ እንቅስቃሴ ከላይ ከተገለጹት ሁለት ጽንፎች ላይ የተንጠለጠለ ነው። ሉዊስ ይህን ክርክር አልፎታል ባልልም ከሁለቱም ወገን እየረገጠ የሚሄድበት አካሄድ ይታያል። ከዚህ የምንረዳው ነገር ቢኖር ለደራሲው የሕይወት ለውጥ አመክንዮአዊ ክርክር ብቻ አለመሆኑ ነው። ከአመክንዮ በላይ የሆነ እና በቃላት ሊያሰፍረው ያልቻለ አንድ ዓይነት እውነታ እንዳለ መረዳት እንችላለን። በርግጥ አብዛኛው የዐቃቤ እምነት ተከራካሪዎች የክርክራቸው መሠረት ያሉበትን ቡድን የግነት ተጽእኖ(Hegemony) ማስጠበቅ እና ከተቀናቃኝ ተጽእኖ(Counter Hegemony) መከላከል ነው።

ምዕራፍ ሦስት

የሕገ - ሰብዕ ፍልስፍና

የሰው ልጅ ከቅድመ -መንግስት ታሪክ ተላቅቆ ራሱ በመረጣቸውም ሆነ ባልመረጣቸው መንግስታት መመራት ሲጀምር የዕለት ተዕለት ሕይወቱን የሚገዙ ሕግጋት ማስፈለጋቸው አልቀረም። ከዚህም በላይ መንግስታት እና መሪዎች መንግስታዊ መዋቅሮችን የሚያስተዳድሩበት ሕግ አበጅተው ለረዥም ዘመናት እየተገለገሉበት ኖረዋል። ይሁን እንጂ ሕጎች እንዴት ይፈጠራሉ? ማን ለምን እና እንዴት ያውጃቸዋል በሚሉት ነጥቦች ላይ ዛሬም ድረስ መግባባት ላይ ባለመድረሳችን ብዙ ሰዎች የተለያዩ ፍልስፍናዎችን እና አስተምህሮችን ዛሬም ድረስ ይሠነዝራሉ።

የሕገ ሰብዕ ፍልስፍና (Positive Legal Theory) ከእነዚህ ፍልስፍናዎች መሃል አንዱ ሲሆን በአጭሩ የሰው-ሕግ የሚል ትርጉም አለው። የእዚህ ፍልስፍና አቀንቃኞች ሕግ በመሠረቱ ሰው-ሠራሽ ግኝት እንደሆነ ያስተምራሉ። ከዚያ አልፈው ሕግ ሰው ሠራሽ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በሰው ሠራሽነቱ የመቀጠሉንም አስፈላጊነት በአጽንኦት ያረጋግጣሉ። ሕግ ሃይማኖታዊ፤ መንፈሳዊ፤ ትውፊታዊ፤ ዲበአካላዊ እና መሰል ተጨባጭነት ከሌላቸው መነሻዎች እና ትርክቶች ፍጹም የጸዳና የተለየ መሆን አለበት፤ በመሆኑም ሕግ አውጪዎች አስፈጻሚዎች እና ተርጓሚዎች ይህን እውነታ አውቀው ሊጠቀሙበት ይገባል።

ሕግ ማለት የሰው ልጆች ለአንድ የተለየ አላማ ብለው የሚፈጥሩት ስርዓት እንጂ በተፈጥሮ የተገኘ ወይም ከፈጣሪ የተሰጠ ትእዛዝ አይደለም። በዚህም ምክንያት ማንኛውም የሕግ ስርዓት በወቅቱና በጊዜው በስርዓቱ

ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን እንዲያገለግልና እንዲጠቅም ሊታወጅ ፤ ሊሻሻል እና ሊሻር ይገባል። ይህ ፍልስፍናም ቢሆን በውስጡ ልዩ ልዩ ንዑስ ክፍሎች እና ተቃራኒ ሐሳቦችን እና ፈላስፎችን አፍርቷል።

የሕገ-ሰብ ፍልስፍና መሰረቱን ያደረገው በተለምዶ የቪየና ክበብ (vi-ena circle) የሚባለው የፈላስፎችና ሳይንቲስቶች ስብስብ ባስቀመጠው አቅጣጫ ነው። በ19ኛው ክ/ዘመን የነበሩ የተፈጥሮና የማኅበረሰባዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች ፍልስፍና እንደ ጥናት ዘርፍ እየሄደበት ያለውን አቅጣጫ እና አዝጋሚነት ለመገምገም ተነስተዋል። በዚህም መሠረት ፍልስፍና ከሌሎች የእውቀት ዘርፎች ሁሉ ቀድሞ ተነስቶ እያደር ግን የእድገት ደረጃው እየቀነሰ ሄዶ በመቆሙ ምክንያት ይህን የእድገት መቀጨጭ ለመመርመር የተሰበሰቡት ምሁራን በየቅዳሜው ጠዋት ተሰብስበው በሚያደርጉት የሐሳብ ፍጭት የተነሳ ለፍልስፍና አዲስ አካሄድ አስቀምጠዋል። በዚህም መሠረት ፍልስፍና ከዚህ ቀድሞ ራሱን ያለአግባብ ሲያስጨንቅበት ከነበረው የዲበአካላዊነት (metaphysical)፤ የኑባሬአዊነት (existentialism): ሞራላዊ ፍልስፍና ጥያቄዎች እና መልስ የፍልስፍና ተግባራት በሙሉ ተቆጥቦ ዋንኛ ሥራው አመክንዮ እና ቋንቋን ካላስፈላጊ ሐሳቦች ማጥራት መሆን እንዳለበት አስተምረዋል።

ምክንያቱም በቋንቋችን ውስጥ የማይጨበጡ እና የማይዳሰሱ ለሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ሕይወት ምንም የማይፈይዱ ሀሳባዊ ኮተቶችን ካስወገድን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ መነጋገር እንችላለን። የዚህ ፍልስፍና አቀንቃኞች በኋላ በእንግሊዝና አሜሪካ ከተፈጠረው analytic philoso-phy ዘርፍ ጀማሪዎች በመሆን አገልግለዋል። ሁሉም የዚህን ክበብ ዋነኛ መርህ በመውሰድ በየዘርፉ ተግብሮታል። በሕግ ፍልስፍናም የሆነው ይኸው ሲሆን የሕግ አስተምህሮ በእጅጉ ዲበአካላዊ፤ መንፈሳዊ እና ሞራላዊ የሆኑ የቋንቋ ጭነቶች የተከመሩበት እንደመሆኑ የሕግ ጥናትን እና ልምምድን ከእነዚህ ሸክም የሆኑ ሀሳቦች ለማጥራት በሚል የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና ሊመሠረት ችሏል።

የቪየና ክበብ ከመመስረቱ ዓመታት ቀደም ብሎ እምብዛም የማይታወቅ አንድ ኦስትሪያዊ የፍልስፍና እና የሕግ ሊቅ ነበር። ይህ Ludwig Wittegnstein የሚባል የአመክንዮ እና የሒሳብ ጥናት ዘርፍ ሊቅ ያነሳው ጥያቄ የቪየና ክበብ ያነሳውን ጥያቄ ነበር። በመጀመሪያ ያዘጋጀው "Tractatus Logicus" የተሰኘው አነስተኛ ድርሳን መሠረታዊ በሆነ መንገድ የዘመኑን የፍልስፍና ጉዞ አካሄድ የቀየረ ነበር። በአሁኑ ወቅት አብዛኛው ሰው እንደሚስማማው ይህ ሰው በእንግሊዘኛ ተናጋሪው ዓለም ያለውን Analytical Philosophy መሠረት የጣለ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ ማለት የ Positivism ወይም የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና ቅድመ አያት መሆኑን ያሳያል።

ይህ ሰው ከሀብታም ቤተሰብ ቢወለድም ያለውን ሀብት ለጓደኞቹ እና ወንድሞቹ ሰጥቶ በአንደኛው የዓለም ጦርነት በወታደርነት ከተሰማራ በኋላ ታዋቂ ፈላስፋነቱን ሁሉ እርግፍ አድርጎ በመተው በማይታወቁ የኦስትሪያ ገጠራማ መንደሮች ውስጥ ህፃናትን ሒሳብ ያስተምር ነበር። በሕይወት እያለ ያሳተማት ብቸኛዋ እና አነስተኛዋ ድርሳን "Tractatus Logicus" ብቻ ስትሆን ከህልፈቱ በኋላ በእጁ የከተባቸው ጦማሮች ተሰብስበው ሲታተሙ የአውሮፓ ሊቀ-ሊቃውንት ሊያስብሉት ችለዋል። ቪገንሽታይን በዚህ ድርሳን እንዳብራራው የሰው ልጅ ሐሳብ እና ፍልስፍና የቋንቋውን ስፋት እና ጥልቀት ያህል ብቻ ይጓዛል፤ልናውቀው እና ልንረዳው የምንችለው ነገር የምንናገረው ቋንቋ እስካበጀው ድንበር ድረስ ብቻ ያለውን ነው። በመሆኑም ቋንቋ በአመክንዮ እና ሳይንስ ልናስረዳው እና ልናረጋግጠው እስከምንችለው የእውቀት አድማስ ድረስ ብቻ መጓዝ ይኖርበታል። ከዚያ በላይ ያለው ሃይማኖታዊ፣ ሞራላዊ፣ ዲበአካላዊ እና የባህላዊ ልማድ ኮተት በሙሉ ከቋንቋችን ውስጥ ተጠርጎ መውጣት ይኖርበታል። እንዲህ ሲሆን በቋንቋ እና አመክንዮ ልንስረዳው የማንችላቸውን ሐሳቦች እና ቃላት በቋንቋችን ውስጥ መጨመር የአስተሳሰብ አድማሳችንን ከመከለል ውጪ ትርጉም አይኖረውም። በመሆኑም ይህ ቋንቋን የማዕዳት አላማ የመጨረሻ ግብ አድርጎ የሚወስደውን ፍልስፍናን በዕኑ መሠረት ላይ ማቆም ነው። ምክንያቱም ቋንቋ የሐሳብ መገንቢያ ጡብ ነው።

የሂዩም መቀስ - ዴቪድ ሂዩም

“ልማድ የሰው ልጆች ሕይወት አቅኚ ነው”

ተግባራዊነት (Empircism) መሠረታዊ የእውቀት ፍልስፍና ነው። የሰው ልጆች ተወልደው ወደዚህ ምድር ከመጡ ወዲያ በሚያዳብሩት ተግባር እና ተሞክሮ አማካኝነት እውቀታቸውን ያከማቻሉ እንጂ አስቀድሞም ቢሆን ሰው በመሆናቸው ብቻ በአእምሯቸው የተጻፉ የቅድመ እውቀት መሰረታውያን እንደሌሉ ያስረዳል። በመሆኑም የዚህ ፍልስፍና አቀንቃኞች ሰዎች ወደ እዚህ ምድር ሲመጡ ታቡላ ራሳ/Tabula Rasa ወይም ነጭ ወረቀት መሆናቸውን ያወሳሉ።

የዚህ ፍልስፍና ዋንኛ አቀንቃኝ የነበረው ዴቪድ ሂዩም (1711-1776) እስከዛሬ ድረስ የሚታወስበትን የውጤት እና ምክንያት ግንኙነትን በመጠቀም ከላይ የተገለጸውን የልማዳዊነት ፍልስፍና ለማብራራት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

> Custom, then, is the great guide of human life. It is that principle alone which renders our experience useful to us, and makes us expect, for the future, a similar train of events with those which have appeared in the past. Without the influence of custom, we should be entirely ignorant of every matter of fact beyond what is immediately present to the memory and senses. We should never know how to adjust means to ends, or to employ our natural powers in the production of any effect. There would be an end at once of all action, as well as of the chief part of speculation.[27]

27 David Hume, An Enquiry Concerning Human Understanding (1748)

በምድር ላይ በተፈጥሮ በምናያቸው ድርጊቶች መሀከል ያለውን የምክንያት እና ውጤት ግንኙነት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ማስረዳት ወይም ማረጋገጥ አንችልም ይልና ለምሳሌ ጠዋት ከእንቅልፋችን ስንነሳ ፀሐይ በምሥራቅ እንደምትወጣ ወይም መሸቶ እንደሚነጋ ልናውቅ የቻልነው ይህ የድርጊት ቅደም ተከተል ለረዥም ዘመን ሳይዛነፍ በመቀጠሉ እንጂ በርግጥም በመምሸት እና በመንጋት መሀከል ያለውን የምክንያት እና ውጤት ግንኙነት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ስላረጋገጥን አይደለም በማለት ይከራከራል።

ለሂዩም ሰዎች ያለማቋረጥ በተደጋጋሚ ስህተት የሚሰሩት የሆነውን ነገር አይተው መሆን ስለሚገባው ነገር ወይም ስለሚሆነው ነገር የማውራታቸው አባዜ ነው። ለእርሱ በሆነው (what is) እና ሊሆን በሚገባው(what ought to be) መካከል ምንም ዓይነት ሳይንሳዊ ግንኙነት ከሌለ ይህንን ጉድኝት ልንበጥሰው ይገባል በማለት ይከራከራል። ይህም ሳይንሳዊ እና አመክንዩአዊ አካሄድ የሂዩም መቀስ በመባል ይታወቃል።

ይህ የሂዩም መቀስ የሕግ-ሰብዕ ፍልስፍና በሃያኛው ክፍለ ዘመን በሚያንሰራራበት ወቅት እጅግ ከፍተኛ በሆነ መንገድ አገልግሏል። ምክንያቱም የሕግ-ሰብዕ ፍልስፍና አቀንቃኞች ሕግን ከሞራል ፤ ከመንፈሳዊ እና ከዲበአካላዊ ግሳንግሶች እናጸዳለን ብለው ሲንቀሳቀሱ የተጠቀሙት ይህንኑ የዴቪድ ሂዩም መቀስን ነው።

ዴቪድ ሂዩም የሚታወቀው ከእነ ጆን ሎክ እና ፍራንሲስ ቤከን ጋር በመሆን በEmpiricism ቤተ-አስተምህሮ መሥራች በመሆኑ ይታወቃል። ኢምፒሪሲዝም የሚስተምረው እውቀት የሚገኘው በተግባራዊ ተሞክሮ ሲሆን የስሜት አካላቶቻችን መረጃ እና እውቀት የምንቃርምባቸው መንገዶች ናቸው። የሥነ-እውቀት (Epistemology) አስተምህሮች ብዙ ዓይነት ሲሆኑ ኢምፒሪሲዝም አቀንቃኞች ማስረጃ እና መረጃ መገኘት የሚገባው ከሳይንሳዊ ቤተ-ሙከራዎች እና ልምምዶች እንጂ ከባህል እና

ልማድ ባገኘነው እውቀት መሆን የለበትም። በመሆኑም ማንኛውም እውቀት ጊዜያዊ እና ተለዋዋጭ በመሆኑ በየጊዜው በሚደረግ ሳይንሳዊ ምርመራ የሚከለስ ወይም የሚረጋገጥ ነው። ጆን ሎክ እንደሚታወቀው የሰው ልጅ ሲወለድ "Tabula Rasa" ወይም "ንፁህ ወረቀት" ሲሆን በእድሜ ከፍ እያለ ሲሄድ በተሞክሮ በሚገኙት መረጃ እውቀት እና ማንነታቸው እየዳበረ ይሄዳል፤ዲቪድ ሂዩም ይሄንኑ ደግፎ ተከራክሯል።

ጆን ሎክ፣ ፍራንሲስ ቤከን እና ዴቪድ ሂዩም ሦስቱ የእንግሊዝ ኢምፒሪሲስቶች ተብለው ይታወቃሉ። ዴቪድ ሂዩም አመክንዮ ብቻ የእውቀት መሠረት ሊሆን እንደማይችል በመግለፅ "The problem of induction" በራሱ "circular fallacy" ያለበት በመሆኑ ሊታመን እንደማይገባ በመግለፅ በትላንት ድርጊቶች እና በዛሬ ሁነቶች መሀከል ያለው ግንኙነት በ"Inductive reasoning" የሚመሠረት ከሆነ ለብዙ ዘመናት ፀሐይ በምሥራቅ ስለወጣች ብቻ ነገም በምሥራቅ ትወጣለች ብሎ ማሰብ ያለተጨባጭ ሳይንሳዊ ማስረጃ ግልፅ ተፋልሶ ስለሆነ ሊታረም ይገባል[28]። የሂዩም አስተሳሰብ በእርግጥ "መቀስ" መሆኑ ለሥነ-ሕግ ፍልስፍና እና ታሪክ ምን ፋይዳ እንደነበረው ልናስብ ይገባል በማለት ተከራክሯል።

የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና በራሱ ሕግን ከልማድ፣ ባህል፣ ወግ፣ መንፈሳዊ ትርክቶች ለመነጠል ጥረት እንዲደርግ ግፊት የሰጠው የእነዴቪድ ሂዩም የስነ-እውቀት አስተምህሮ ለመሆኑ ብዙም ምርምር አይጠይቅም። ሕግ

---

28 ተስፋዬ ሮበሌ ስለ Circular fallacy ወይም ሙሻ ዘር ተፋልሶ እንደሚያብራራው ሙሻ ዘር ፤ በጠመንጃ ወይም በሽጉጥ ቧንቧ ወስጥ የሚገኝ ከፍል ነው። መሳሪያው ሽከርከሪትን ፤ ኡደትን፤ ዙረትን፤ ድብልብልነትን አመላካች ስለሆነ በእንግሊዘኛው Circular የሚባለውን ቃል ይወክላል ፤ ይህ ተፋልሶ በሙግቱ ድምዳሜና በሙግቱ ነጥብ መሃል አንዳችም የይዘት ልዩነት በማይኖርበት ወቅት እና ተሟጋቹ የሙግቱን ጭብጥ መልሶ እንደ ማስረጃ ሲጠቀምበት የሚከሰት የተፋልሶ ዓይነት ነው። Inductive argument መሰተጋብአዊ ሙግት ሲባል በግዕዝ መስተጋብአዊ ማለት የሚሰበስብ ፤ ሰብሳቢ ማለት ነው። በስነ አመክንዮ አንድ ሙግት ነጥቦቹ ድምዳሜውን መቶ በመቶ ማጽናት የማይችሉ ሙግቶችን የሚያመላክት ነው። (ዶ/ር ተስፋዬ ሮበሌ፤ ሥነ አመክንዮ የሙግት አደረጃጀት፤ አገማገምና አሰናዘር፤ተስፋ ዓቃቢያነ ክርስትና ማህበር፤ 2020

ትላንት በባህል እና ሃይማኖት ላይ ተመስርቶ አንድ ልማድን ከደነገገ ይኸው ልማድ ወደፊት ለሚመጡ ትውልዶች ሕግ ሆኖ የሚቀጥልበት የሥነ-ሕግም ሆነ ሥነ-እውቀት ምክንያት የለም።

የሉዓላዊው አካል ትእዛዝ -ጆን ኦስቲን

"ሕግ ማለት በቅጣት የተደገፈ የኡዓላዊ አካል ትእዛዝ ነው"

እውቁ የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና አቀንቃኝ ጆን ኦስቲን (1790-1859) በሕይወት እያለ በሕመም ሲሰቃይ እና በጠበቃነት ኑሮውን ለመግፋት ሲውተረተር ኖሮ ብዙም ሳይሳካለት አልፏል። በሚገርም ሁኔታ የጀርሚ ቤንታም ወዳጅ በመሆኑ በእርሱ በኩል በያኔው የሎንዶን ዩኒቨርሲቲ የማታ መርሃግብር በአስተማሪነት ተቀጥሮ የሕግ ፊልስፍና ለማስተማር ቢሞክርም ብዙም ተደማጭ አልነበረም። ደራሲ እና ተርጓሚ የነበረችው ሚስቱ በምታገኘው አነስተኛ ገቢ ቀሪዎቹን የሕይወቱን ዘመናት ለመግፋት ተገዷል። ከእርሱ ህልፈት በኋላ ሚስቱ ሳራ ኦስቲን በድጋሚ መጽሐፍቱን ማሳተም ስትጀምር ስራው ተነባቢነትን ሊያገኝ ችሏል።

ጆን ኦስቲን የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና እንዲታወቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በማጥናት በአግባቡ እንዲደራጅ አደርጎታል። ለኦስቲን ሕግ ሰው ሠራሽ ግኝት ሲሆን በሕግና ሞራል መሀከል ምንም ዓይነት ግንኙነት የለም። እናም ባለቤቱ ለሁለተኛ ጊዜ ባሳተመችው ድርሳን "የትእዛዝ መርህ" በመባል እስከዛሬ የሚታወቅለትን መርህ መስርቷል። በዚህም መሠረት ሕግን ከሃይማኖት እና ሞራል እንዲሁም በወቅቱ በሰፊው ይራመድ ከነበረው "የተፈጥሮ ሕግ" ፍልስፍና በመነጠል ብቻውን ለማጥናት ጥረት አድርጓል። እንደ ኦስቲን አስተሳሰብ **"ሕግ የአንድ ሉዓላዊ አካል ትእዛዝ ነው"** ይህ ትእዛዝ ደግሞ በቅጣት መደገፍ ይኖርበታል።

የጀርሚ ቤንታም የቅርብ ወዳጅ እና ጎረቤት ስለነበር የጠቀሜታውያን ፍልስፍና ተጽእኖ ሳያሳድርበት አልቀረም። ለእርሱ ሕግ ማለት ከአንድ ሉዓላዊ አካል ለሌላ በስልጣን የሚያንስ አካል ከቅጣት ማስፈራሪያ ጋር ተደግፎ የተሰጠ ትእዛዝ ነው።

> The central feature of Austin's map of jurisprudence, is ofcourse, the notion of law as the command of the sovereign.Anything that is not a command is not a law.Only General commands count as law. And only commands emanating from the sovereign are positive laws[29].

ይህ ማለት ኦስቲን የፈጣሪ ሕግን ይቃወማል ማለት አይደለም። የፈጣሪ ሕግ ከሰው ሕግ በላይ በመሆኑ መለኮታዊ ጉዳዮችን ብቻ እንደሚያስተዳድር ከሰው ሠራሽ ሕግጋት ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ይገልጻል። ሕግን ለበታች አካላትና ሕዝቦች በትእዛዝ መልክ የሚያስተላልፈው ይህ "ሉዓላዊ አካል" ግን በሕግ ሊገዛ አይችልም። ሉዓላዊው አካል የሚሰጠው ትእዛዝ ከማኅበረሰባዊ ሞራል ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም፤ ሉዓላዊው አካል ማኅበረሰባዊ ሞራልን አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ሊያማክር እና ሊጠቀም ይችላል እንጂ ሊገደድባቸው አይችልም። ኦስቲን ከቤንታም ፍልስፍና በመውረስም ሕግጋት ለሰፊው ሕዝብ መጠነ ሰፊ ደስታና ጥቅም የሚያስገኝ መሆን እንዳለባቸው ያስረግጣል።

በተጨማሪም የሕግ ፍልስፍና ሥራ መሆን ያለበት ሕግ ራሱን የቻለ እና በራሱ አመክንዮ የሚመራ ደረቅ ሳይንስ አድርጎ መቅረጽ ነው። ሕግ መረቀቅ እና መጠናት ያለበት "መሆን ስላለበት" ጉዳይ ሳይሆን "ስለሆነው" ማኅበራዊ ሁኔታ ነው። ሕግ መሆን አለባቸው ወይም መደረግ ይገባቸዋል ስለሚላቸው ሐሳባዊ ሞራላዊ የማኅበረሰብ ልማዶች መጨነቅ

29 Raymond Wacks, Understanding Jurisprudence; An Introduction to legal theory,Oxford Universty Press,4th ed,2015,P.81

የለበትም። ሕግ ማለት ከአንድ ሉዓላዊ አካል የመጣን ትእዛዝ ስለመፈጸም እና ስለ ማስፈጸም በማሰብ ስላለው ነባራዊ ሁኔታ ሲባል የሚጠና ነው።

ማኅበራዊ ሞራል "መሆን ስለሚገባው" ሲያስብ ሕግ ግን "ስለሆነው" ነገር ያስባል። የማኅበረሰባዊ ሞራል እና ሕግ ድንበር ፈጽሞ ሊገናኝ አይገባም በሚል በኦስቲን የተራመደው ሃሳብ የጠቀሜታውያን የሞራል ፍልስፍና መሠረት አለው። ሕግጋት በትእዛዝ መልክ ከአንድ ሉዓላዊ አካል ሲወጡ የብዙኃን መብት እና የእርካታ ደረጃ ያስጠብቃሉ ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ ከዚህ ተርፎ ባለ የማይመስጥ እና መሠረት አልባ የዲበአካላዊ እና ሞራላዊ ጥያቄዎች ውስጥ ገብቶ መፈትፈት ለሕግ ስርዓቱም ሆነ ለሕግ ባለሙያዎች እርባናቢስ የሆነ ልፋትን የሚያስከትል ነው።

> (Bentham) attempted to demystify the common law,to expose what lay behind its mask. The law was a perplexing network of technical rules created by lawyers, conveyancers and judges (Judges & Co) which served their usual corrupt interests. Most people were too poor or too ignorant to derive any benefit the process which puprported to be fair and rational[30].

ጀርሚ ቤንተም ራሱም ቢሆን የጠቀሜታውያን ሞራል ፍልስፍና መሥራች እንደሆነ ቢነገርም በሥነ-ሕግ ጥናት እና ምርምርም ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ከማሳረፉ የተነሳ ለቀዳሚው የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና አቀንቃኝ ጆን ኦስቲን መፈጠር ምክንያት ሆኗል። በኦስቲን ሥራዎች ላይ ተጽእኖ ካሳደሩ የቤንታም ሐሳቦች መሀከል ጥቂቶቹን መዳሰስ ይኖርብናል። ቤንታም የእንግሊዝ ዳኛ ሠራሽ ሕግጋት ወይም በኩር ውሳኔዎች (precedents) የእንግሊዝ የፍትሕ ስርዓት ያልተረጋገጠ፤ ወጥነት የሌለውና የማይገመት

30 Ibid, P 71

እንዲሆን ስላደረገው መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እንደሚያስፈልገው አመልክቷል። በመሠረቱ ቤንታም በፈጣሪ መኖር እና በተፈጥሮ ሕግ የማያምን በመሆኑ እንዲፈጠር የሚፈልገው ስርዓት ሰው ሠራሽ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም።

ቤንታም በሕይወት ዘመኑ በሙሉ ሲታገል የነበረው ሕግጋት በዓይነት ተከፋፍለው ወጥነት እና አጠቃላይነት ባለው የሕግ ድርሳን (code) ተሰንደው መቀመጥ እንዳለባቸው ለማስረዳት ነው። በዳኛ ሠራሽ የሕግ ስርዓት ውስጥ እየኖሩ ፍርድ ቤቶች ሊመሩ የሚገባው አስቀድሞ በታወቀ እና በፖርላማ በጸደቀ የሕግ ስርዓት እና የሕግ ድርሳን (code) መሆን እንዳለበት እየጻፉ እና እየተከራከሩ መኖር የቤንተምን ሕይወት እጅግ ከባድ አድርጎት ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ሐሳቡ ከሀገር እንግሊዝ አልፎ እስከ ሩሲያ ድረስ እንዲታወቅለት ከተለያዩ ሀገራት መሪዎች እና ነገስታት ጋር ሲጻጻፍ ኖሯል።

ቤንተም ዳኛ ሠራሽ ሕግጋትን የውሻ ሕግ (dog Law) እስከማለት ድረስ ቢደርስም የእንግሊዝ ሕግጋትን በተጠቃለለ የሕግ ድርሳን (code) የማስቀመጡና የዚህም ድርሳን የፍልስፍና መሠረቱ ጥብቅ የሆነ የጠቀሜታውያን ፍልስፍና እንዲሁም ማስገደድ በብዙዎች ዘንድ የከፋ ትችን እንዲሰነዘርበት አድርጓል። ይሁን እንጂ codification የሚለውን ቃል በማግኘቱ እና በማስፋፋቱ ዛሬም ድረስ የላቀ እውቅና ከማግኘትም አልፎ የእንግሊዝ ሀገር የሕግ ስርዓት ራሱ የተጠቀለሉ የሕግ ድርሳናትን በከፊልም ቢሆን እየተቀበላቸው ይገኛል።

የሕግ ፅንሰ ሐሳብ - ሃርት

"የቅቡልነት ሕግ መሠረታዊ የሕግጋት መርህ ነው"

የሃርት (1907-1992) "የሕግ ጽንሰ ሐሳብ" / The concept of law" በሚል የሚታወቀው ድርሳን በሕግ-ሰብዕ የሥነ-ሕግ ፍልስፍና አቀንቃኞች ዘንድ እንደ መዐዘን ድንጋይ የሚታይ ነው። እንዲያውም ከእነ ጆን ኦስቲን በኋላ በነበረው ዘመን የነበረውን የእንግሊዝን የሕግ ፍልስፍና አነቃቅቶታል። የዚህ ድርሳን ፀሐፊ የሆነው ምሁር ኤች ኤልኤ ሃርት በእንግሊዝ መንግስት ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች የሰራ ሲሆን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የእንግሊዝ የስለላ ድርጅትን በመቀላቀል ለሀገሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ለረጅም ዘመን አብራው የኖረችው ሚስቱ ግን በድብቅ የእንግሊዝ ኮሚኒስት ፓርቲ አባል ነበረች። ከአይሁድ ቤተሰቦች የተወለደው ሃርት በሀገረ እንግሊዝ ለጥቂት ጊዜ በጥብቅና ሙያ ከሰራ በኋላ ወደ ማስተማር ዘርፍ ገብቶ የሕግ ፍልስፍናን ለረዥም ጊዜ በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ አስተምሯል።

በዚህ ንዑስ ርዕስ ለማየት የምንሞክረው "የሕግ ፅንሰ ሐሳብ" በሚል የተሰየመው ድርሳን ውስጥ የተገለጡትን ሐሳቦች ነው። በመሠረቱ ሃርት ቀንደኛ የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና አራማጅ እንደመሆኑ ይህ ድርሳኑም ይህንኑ ፍልስፍና የሚያብራራበት ነው። ሃርት ጆን ኦስቲን በስፋት የሚታወቅበትን "ሕግ የሉዓላዊ አካል ትእዛዝ ነው" የሚለውን አባባል በመተቸት ጽሑፍን ይጀምራል። ለዚህ ደግሞ እንደ ምክንያት የሚያነሳቸው "ፅኑ ጥያቄዎችን" ነው። ሕግ በነገስታት ማስፈራሪያ ከታከለባቸው ትእዛዝ እንዴት እና በምን ይለያል? የሕግ ግዴታስ ከሞራል ግዴታ ጋር ያለው ጉድኝት ምንድነው?

"ሕግ በቅጣት የተደገፈ የሉዓላዊ አካል ትእዛዝ ነው" የሚለው አባባል ለሃርት አልተዋጠለትም። ሕግ ከሉዓላዊ አካል ትእዛዛት በይዘት በምንጭ እና በተዳራሽነታቸው ስፋት እንደሚለዩ በመተንተን ይጀመራል።

ለምሳሌ ሁሉም ሕግጋት ትእዛዝ ላይሆኑ ይችላሉ አንዳንድ ሕግጋት አመቻች ሌሎቹ ፈቃጅ ናቸው። በተጨማሪም የሕግ ሁሉ ምንጭ አንድ "ሉዓላዊ አካል" አንደሆነ አድርገን መደምደም እንደሌለብን እና ሕግጋት የተለያዩ ምንጮች ሊኖራቸው እንደሚችል ብቻ ሳይሆን ሕግጋቱን ያወጡት አካላት ራሳቸው በሕግጋቱ መገዛት እንዳለባቸው ያትታል። ሃርት ሲቀጥል "በማኅበራዊ ልማድ" እና "በማኅበራዊ ሕግጋት" መካከል ልዩነት እንዳለ ይጠቅስና ማኅበራዊ ልማዶች በማኅበረሰቡ በተለምዶ የሚደረጉ ወይም የማይደረጉ ነገሮች እንደሆኑና ቢጣሱም ያን ያህል ችግር እንደማይፈጥሩ ይገልጻል። "ማኅበራዊ ሕግጋት" ግን ከማኅበራዊ ልማዶች ከፍ ባለ መልኩ አስገዳጅነት እንዳላቸው እና ቢጣሱ ከማኅበረሰቡ ቅጣት የሚያስጥሉ ናቸው።

መንግስት የሚያወጣቸው ሕግጋት ከማኅበረሰባዊ ሕግጋት ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው ይጠቅስና ማኅበረሰቡ በሌሎች 3ኛ ወገኖች ሲታይ ሕግጋቱን የሚተገብርበት ሁኔታ ውጪያዊ እይታ እንደሚባል ማኅበረሰቡ ግን በፍላጎት ሕጉን የሚተገብርበት ሁኔታ ውስጣዊ እይታ እንደሚባል ይጠቅሳል። ቀጥሎም አንድ ሕግ ጥራቱን እና ውጤታማነቱን የሚያገኘው ከዚህ ውስጣዊ እይታ እንደሆነ ይገልጻል።

ይሁን እንጂ የሕግ ስርዓትን ለማስፈን አስፈላጊው መስፈርት አንድ ተራ ዜጋ ለሕጉ ያለው ውስጣዊ እይታ ሳይሆን በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያሉ ኃላፊዎች ለሕጉ ያላቸው ውስጣዊ እይታ እንደሆነ ድርሳኑ አበክሮ ያሳስባል። ምክንያቱም ባለስልጣናት ከተራ ዜጋው ይልቅ በሕጉ የመገዛት ውስጣዊ ፍላጎት ከሌላቸው የመንግስት ተጠያቂነትን ማስፈን እንደማይቻልና የራሳቸውንም ሆነ የሌሎች የመንግስት ኃላፊዎችን ድርጊት መቆጣጠር እንደማይችሉ ይጠቁማል።

ሃርት ሕግጋትን በሁለት ይከፍላቸዋል። አንደኛ ደረጃ ሕግጋት እና ሁለተኛ ደረጃ ሕግጋት። አንደኛ ደረጃ ሕግጋት የማኅበረሰቡን ምግባር እና ተግባር የሚገድቡና የሚያርቁ ናቸው። ማኅበረሰቡ ማድረግ የሚገባውን

እና የማይገባውን በዝርዝር ያመለክታሉ። ሁለተኛ ደረጃ ሕግጋት ወይም አስቻይ ሕግጋት የሚባሉት ደግሞ የአንደኛ ደረጃ ሕግጋት የሚቀየሩበትን፤ የሚሻሻሉበትንና የሚፈጸሙበትን አግባብ ይደነግጋሉ። በተጨማሪም ቀዳሚ ሕግጋት /አንደኛ ደረጃ ሕግጋት ግልጽነት፣ ቅልጥፍና እንዲኖራቸው እንዲሁም ተገማች እና ተመሳሳይ እንዲሆኑ ያስችላሉ ወይም ያግዛሉ።

የሁለተኛ ደረጃ ሕግጋት ደግሞ በራሳቸው ለሦስት ንዑስ ሕግጋት ይከፈላሉ፤ እነዚሁም የቅቡልነት ሕግጋት፤የለውጥ ሕግጋት እና የሙግት ሕግጋት ይባላሉ። የቅቡልነት ሕግጋት አንደኛ ደራጃ ሕግጋት ዕውቅና አንዲያገኙና ግልጽነት እንዲኖራቸው ያስችላሉ። በመሆኑም እነዚህ ንዑስ የቅቡልነት ሕግጋት ቀዳሚ ሕግጋት የሚጸድቁበትና ዕውቅና የሚያገኙበት የቅቡልነት መስፈርቶች በዝርዝር ሲያስቀምጡ ከጊዜ እና ሁኔታ ጋር ሊቀየሩ የሚችሉባቸው አግበብን ያስቀምጣሉ። እነዚህ ሕግጋት አንደኛ ደረጃም ሆነ ሁለተኛ ደረጃ ሕግጋት ሊለወጡ እና ሊቀየሩ የሚችሉበትን መስፈርቶች ይዘረዝራሉ። መስፈርቶቹ እንደሁኔታው የሚለያዩ ሲሆን ሕግጋቱን ሲያስቀምጡ እነማን ምን መቀየር እንደሚችሉና የሚቀይሩበትን ስርዓት በዝርዝር ያሳያል፤ የሙግት ንዑስ ሕግጋት አንደኛ ደረጃ ሕግጋት በተጣሱ ጊዜ እነማነ እንዴት ውሳኔ ያስተላልፋሉ የሚለውን የሚደነግጉ ናቸው። በመሆኑም የትኞቹ ቀዳሚ ሕግጋት ሲጣሱ እነማን በእነማን ላይ የመዳኘት ስልጣን ይኖራቸዋል የሚለውን ያብራራሉ።

በአንድ ሀገር የሕግ ፍልስፍና ውስጥ መሠረታዊ የሆነው ጽንሰ ሐሳብ **የቅቡልነት ሕግ** (Rule of Recognition) ነው። ቀዳሚ ሕግጋት ቅቡልነት የሚያስገኙት በዚሁ ሕግጋት ከሆነ ራሱ የቅቡልነት ሕግን እንዴት ልናውቀው እንችላለን? ብሎ ይጠይቅና ይህን ማወቅ የምንችለው የመንግስት እና የማኅበረሰቡ ተለምዷዊ ድርጊት እና ልማድ በማየት መሆኑን ማለትም የመንግስት ተቋማትን፤ ፓርላማ፤ ፍርድ ቤቶች፤ የሕግ ባለሙያዎች አስተያየት እና የሕግ ምሁራን ጽሁፎች በመመርመር ነው። በመሆኑም ይህ የሃርት እሳቤ የማኅበረሰባዊ እውነታ መርህ (social fact theory) በመባል ይታወቃል።

> The rule of recognition providing the criteria by which the validity of other rules is assessed is an important sense; which we shall try to clarify as an ultimate rule[31].

ኬልሰን ይህንን እይታ በመቃወም የሕግ ልማድ እና ማኅበረሰቡ የሚያደርገውን አይተን የቅቡልነት ሕግጋትን መመስረት አንችልም በማለት ንጹህ እና ያልተቀላቀለ የቅቡልነት ሕግ ለመመስረት ጥረት አድርጓል። የሕግ እና ሞራል ግንኙነትን በተመለከተ ከሃርት በፊት የነበሩ የሰው ሠራሽ ሕግ አስተምህሮ አቀንቃኞች ሕግ የሰው ልጅ ግኝት እንደመሆኑ በምንም መልኩ ማኅበረሰባዊም ሆነ ግለሰባዊ ሞራል በሕግ አወጣጥ እና አተገባበር ላይ ተጽእኖ ሊያሳርፍ አይገባም በሚል ተከራክረዋል። ሃርት ግን የቅቡልነት ሕግጋትን በምንለይበት ወቅት ማኅበረሰባዊ ሞራል በራሱ የቅቡልነት ሕግ አካል የሚሆንበትን መንገድ ማስቀመጥ እንደሚቻል ይገልጻል፤ምክንያቱም ሕግ እና ሞራል የተለያዩ መሆናቸውን ሐሳባዊ በሆነ መንገድ መከፋፈል ቢቻልም በልማድ እና በሕግ አተገባበር ወቅት ግን ሁለቱን መለያየት እጅግ ከባድ መሆኑን ያነሳል።

ከዚህ በተለየ መልኩ ጆሴፍ ራዝ የተባለ ፈላስፋ ሃርትን በመተቸት ሞራል እና ሕግ መቼም ቢሆን በሰው ሠራሽ የሕግ ፍልስፍና ውስጥ ሊደባለቁ እንደማይገባ የሕጉን የቅቡልነት መሠረት ማወቅ የምንፈልግ ቢሆን እንኳ ቀዳሚ ሕግጋቱ የወጡባቸውን ምንጮች (sources of Law) በመመርመር በምንናገኘው የትርጉም ሂደት ልንገዛ ይገባል እንጂ ሞራልን በቅቡልነት ሕግጋት ውስጥ ማካተት ተገቢነት የለውም ሲል ሐሳቡን ሰንዝሯል።

ሎርድ ዴቭሊን በበኩሉ የሞራላዊ ሕግ እሳቤ (Legal moralism) አመንጪ ሲሆን አንድ ሕግ የማኅበረሰቡን የቡድን ሞራል (collective

31 H L A Hart , The Concept of Law, Clarendon Press ,Oxford,1961, P. 105

moral) ሊያስጠብቅ እንደሚገባ በማሰብ ተከራክረዋል። የአንድ ግለሰብ ደርጊቶች ምንም እንኳ በማኅበረሰቡ ላይ በቀጥታ የአካልና የሥነ-ልቦና ጉዳት ባያደርሱም እንኳ ከህብረተሰቡ የሞራል መሰረቶች ጋር የሚጋጩ ከሆነ ሕጉ ሊያወግዛው እና ሊገድበው እንደሚገባ ገልጸዋል። በዚህም የስተዋርት ሚልን "የጉዳት መርህ" በመተቸት ማኅበረሰቡ ላይ ጉዳት እስከሚደርስ ድረስ ሕግ በግለሰቦች ደርጊት ጣልቃ ሳይገባ ይቀመጥ ማለት ለማኅበረሰባዊ ሞራል ተገቢውን ክብር ያለመስጠት ውጤት መሆኑን አሳስበዋል። በርግጥ ሃርትም ቢሆን የሕገ-ሰብ ፍልስፍና አራማጅ እንደመሆኑ ሕግ "ስለሆነው" እንጂ "መሆን ስለሚገባው" መጨነቅ እንደሌለበት ይቀበላል ይሁንና በሕግና ሞራል መሀከል ያለው ጽንፍ የረገጠ ልዩነት ጠቃሚ እንዳልሆነ ያትታል።

በሃገረ እንግሊዝ በ1957 የተቋቋመ "ዎልፈንደን ኮሚቴ" "Wolfenden Committee"" ያቀረበው ሪፖርት ለብዙ ዓመታት አነጋጋሪ ሆኖ ነበር። ኮሚቴው ለመንግስት ባቀረበው ምክረ ሐሳብ ሴተኛ አዳሪነት በአደባባይ እስካልተፈፀመ ድረስ ሊያስቀጣ አይገባም እና በሁለት ለአቅመ አዳም በደረሱ ሰዎች መካከል የሚደረግ የተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት በሕግ እውቅና ሊሰጠው እንደሚገባ የሚመክር ነበር። ለኮሚቴው የሕግ አላማ ግለሰቦች ከሦስተኛ ወገን የሚደርስባቸውን ጥቃት መከላከል እንጂ በግለሰቦች ሕይወት ውስጥ ገብቶ መፈትፈት አይደለም፤ ይህ ሲባል ግለሰቦች በገዛ ቤታቸው የሚያደርጉት ድርጊት ትክክል ወይም ስህተት ብሎ መበየን የሕግ አላማ ባለመሆኑ ጣልቃ ከመግባት መቆጠብ ይኖርበታል። ሎርድ ፓትሪክ ዴቭሊን በወቅቱ የእንግሊዝ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ስለነበር የኮሚቴውን ድምዳሜ ክፉኛ ተችቷል። አንድን ማኅበረሰብ በሚያዋቅሩ እና እንደ ማዕዘን ድንጋይ በሚያገለግሉ የሞራል ፅንሰ ሐሳቦች ላይ ማኅበረሰቡንም ሆነ በሕዝብ የተመረጡ እንደራሴዎች ውሳኔ የማሳለፍ መብት አላቸው። ኮሚቴው የተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት እንዲፈቀድ ካቀረባቸው መከራከሪያዎች አንዱ ፍቃድ (Consent) መሆኑ ለዴቭሊን አልተዋጠለትም፤ ወንጀል አድራጊዎች የድርጊታቸው ሰለባ የሆነው ሰው ፍቃድ ሰጥቷናል ብለው መከራከሪያ ሊያቀርቡ አይችሉም። ለምሳሌ አንድ የሰው ነፍስ ያጠፋ ሰው ፍርድ ቤት

ቀርቦ ሚቹ እንድገድለው ፈቅዶልኛል ቢል ተቀባይነት እንደማይኖረው ሁሉ በዚህም ጉዳይ የተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት ወንጀል እና ኢ-ሞራላዊ ሆኖ ሳለ በአድራጊዎች መካከል ፍቃድ መኖሩን በመጥቀስ መከራከር ትርጉም አልባ ነው። ማኅበረሰብ በሐሳብ የተዋቀረ ተቋም ነው በመሆኑም ማኅበረሰቡን ያዋቀሩት ሞራላዊ አስተሳሰቦችን መንካት ማለት ማኅበረሰቡን ከማፍረስ የማይተናነስ በመሆኑ መንግስት ማኅበረሰቡን ለመጠበቅ ሲል ጣልቃ በመግባት በእነዚህ ድርጊቶች ላይ የተጣለውን የወንጀል ሕግ ማስፈፀም ይኖርበታል። ማኅበረሰቡ ያፀደቃቸው ሕግጋት እና የግብረገብነት ሐሳቦች ላይ አመፅ ማስነሳት እንደ ሀገር ክህደት ሊታይ ይገባዋል። ስለ እነዚህ ሕግጋት ስናስብ ከግምት ማስገባት ያለብን ተራውን ዜጋ (Reasonable Person) እንጂ ተመራማሪውን (Rational Person) አይደለም፤ ምክንያቱም ተራው ዜጋ ባህሉ እና ወጉ እንዲጠበቅለት እንጂ የሞራል ፍልስፍና ታሪካዊ አመጣጥ አያንገበግበውም።

ሃርት የዴቭሊንን ሐሳብ የተቃወመው የስቱአርት ሚልን ሐሳብ በማንሳት ሲሆን ለሚል መንግስት በግለሰቦች ሕይወት ጣልቃ መግባት የሚገባው በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ሕይወት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ከሆነ ብቻ ነው። ለሃርት መንግስት በግለሰቦች ሕይወት ጣልቃ መግባት የሚችለው በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ሕይወት ላይ ጉዳት ሲደርስ ብቻ ሳይሆን በራሳቸው ሕይወት ላይም ቢሆን ጉዳት ሊያስከትሉበት የሚችል አጋጣሚ ሲገኝ መሆን አለበት። በመሆኑም ሃርት እንደ ሚል ሰዎች የፈለጉትን የሕይወት ዘይቤ መከተል እንደሚችሉ ቢደግፍም የሕይወት ዘይቤያቸው ለራሳቸው ሕይወት አደጋ የሚጥል ከሆነ በሕግ ሊከለከል ይገባል። ሃርት እንደሚከራከረው በሕዝቡ ዘንድ ኢ-ሞራል የተባሉ የግለሰብ ድርጊቶች ማኅበረሰብን ያፈራርሳሉ የሚለው አስተሳሰብ በማስረጃ ያልተደገፈ ነው። የማኅበረሰቡ የሞራል ውቅር ተነቃንቋል በሚል በግለሰቦች በራሳቸውም ሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት ባላደረሱበት ሁኔታ በህይወታቸው ጣልቃ መግባት የሕግ አላማ አይደለም። ለምሳሌ የአልኮሆል መጠጥ እና ሲጃራ ላይ ከፍተኛ ታክስ መጣል ወይም ጭራሹኑ መከልከል ሰዎች በራሳቸው

ጤና ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ በሚል መንግስት የሚያስቀምጠው ገደብ ቢሆንም የብዙኃኑ ሞራላዊ አስተሳሰብን በግለሰቦች ሕይወት ላይ መጫን ግን ተግባራዊ ሊሆን አይገባም።

ትርጉም እና መርህ- ሮናልድ ደርኪን

"የሕግ እና ሞኩክ አስታኮቂ መርህ ነው"

ሮናልድ ዶርኪን (1931-2013) የሥነ-ሕግ አስተምህሮውን የጀመረው የሀርትን የሕገ-ሰብ ፍልስፍና በመተቸት ነው። ዶርኪን ይህንኑ ትችት ሲጀምር በሕግ እና ሞራል መሀከል ያለውን ልዩነት የሕገ-ሰብዕ ፈላስፎች እጅግ እንደሚያከሩት ሕግ ከሞራል ተነጥሎ የራሱ የሆነ ሕይወት አለው ሊባል እንደማይቻል ይገልጻል። ከዚህም በተጨማሪ ፍ/ቤቶች ውሳኔ በሚሰጡበት ወቅት ከሕግጋቱ ይልቅ አጠቃላይ መርሆዎች ላይ እንደሚያተኩሩ ይህም በሕግ እና ሞራል መሃል ያለውን ልዩነት እንደሚያጠበው ያሳያል። በመሆኑም ከሕግ ይልቅ መርህ ዳኞች በእጃቸው ያለውን ጉዳይ እንዲፈቱ መሣሪያ ይሆናቸዋል።

ምክንያቱም ሰው ሠራሽ ሕግጋቱ ሁሉንም ዓይነት አጨቃጫቂ የፍ/ቤት ጉዳዮች እና ግጭቶች የሚፈቱ ባለመሆናቸው መርሆዎች (legal principles) በተግባር ላይ ይውላሉ። የተደነገጉት ሕግጋት የማይገዟቸው እና ከሕግ አውጪው እይታ ውጪ የሆኑ ጉዳዮች በየእለቱ ለዳኞች እና ፍ/ቤቶች ይቀርባሉ። በዚህ ጊዜ እነዚህን "ብርቱ ገዳዮች" (Hard cases) ለመወሰን ዳኞች የተጻፈ ሕግ ማግኘት ስለማይችሉ ወይ ከዚህ ቀደም የተወሰኑ ጉዳዮችን በማየት ለዚህ ጉዳይ የሚመጥንና ከብዙ ሕጎች በተውጣጣ አዲስ የሕግ ቀመር መሠረት ጉዳዮን ይወስናሉ ወይም አጠቃላይ መርህን መሠረት በማድረግ ውሳኔ ይሰጣሉ። ስለሆነም እነዚህ ብርቱ ጉዳዮች ባጋጠሙ ቁጥር ለጉዳዮ ፍትሐዊ የሚሆነውን ውሳኔ የሚያውቀው ዳኛው ብቻ ይሆናል። ዳኞች እነዚህ ጉዳዮች በሚያጋጥሙበት ወቅት

ምክንያታዊ እና ትክክለኛ መልስ (the right answer thesis)የመሥጠት ሞራላዊ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል ይልና ዳኞች በግሪክ አፈታሪክ ውስጥ ካለና ኃይልነት ከተጎናጸፈ አምላክ (Hercules) ጋር ያዛምዳቸዋል።

ዶርኪን እና ሃርት በምሁራዊ ሥራቸው እና በግል ሕይወታቸው ወዳጆች የነበሩ ቢሆንም ደርኪን የሃርትን ሰራዎች በተደጋጋሚ ከተቹ ሰዎች ተርታ የሚመደብ ነው። ለምሳሌ ሃርት ቀዳሚ ሕግጋት በሚላቸው ድንጋጌዎች መካከል አንዳንዱ ክፍተት ሊፈጠር እንደሚችልና ዳኞች እንደዚህ ዓይነት ክፍተት በሚያጋጥማቸው ወቅት የራሳቸውን ስልጣን (discretion) በመጠቀም ሊሞሉት እንደሚገባና የእነሱ ውሳኔም ሕግ የማውጣትን ያህል ሊቆጠር እንደሚገባ ይገልጻል።

> Discretion, like the hole in a doughnut, does not exist except as an area left open by a surrounding belt of restriction. It is therefore a relative concept. It always makes sense to ask, «Discretion under which standards?» or «Discretion as to which authority?»[32]

ዶርኪን በበኩሉ በእነዚህ ብርቱ ጉዳዮች ወቅት ዳኛው ክፍተቱን በራሱ ስልጣን ተጠቅሞ ይሞላዋል ማለት አግባብነት የሌለው ነው፤ ይልቁንስ ዳኞች እነዚህን ጉዳዮች ሲወስኑ ከራሳቸው ስልጣን ወይም ተለምዷዊው የሕግ አተረጓጎም ይልቅ "መርህ"ን መሠረት ሊያደርጉ እንደሚገባ ይመክራል። ምክንያቱም የሕግ መርሆዎች ምንም እንኳ አጠቃላይ በሆነው የሰው ሠራሽ ሕግጋት ማዕቀፍ ውስጥ የሚካተቱ ባይሆንም የሕግጋቱን አጠቃላይ ፍልስፍና እምቅ በሆነ መንገድ የሚገልጹ ናቸው።

በተጨማሪም የሕግ መርሆዎች እርስ በእርሳቸው የማይጋጩ ሲሆኑ ሕግጋት ግን አንዳንዱም ቢሆን እርስ በእርሳቸው ይጋጫሉ።

32 Ronald Dworkin, Taking Rights Seriously (1978), p. 31

በመሆኑም አንድ ዳኛ የሕግ መርህ መርጦ ሲወስን መርሆው በስርዓቱ ካሉ ሰው ሠራሽ ሕግጋት ጋር የሚጣጣም መሆኑም ሊያረጋግጥ ይገባዋል። በመሆኑም አንድ ዳኛ ይህንን ተግዳሮት ሊፈታ በሚችል መልኩ አንድ ልዩ እና ተገቢነት ያለው መልስ ማግኘት ይጠበቅበታል። እንዲህ ዓይነት መልስ ባያገኝ እንኳ ሊገኝ እንደሚችል ማመን ይኖርበታል። በመሆኑም "ብርቱ ጉዳይ" የምንላቸው እነዚህ ፈታኝ ጉዳዮች በመደበኛ የሕግ ክፍተት ሳቢያ የሚፈጠሩ ፈተናዎች ከመሆናቸውም አልፎ ለዚህ ክፍተት ተገቢውን የሕግ መርህ ለማግኘት በሚደረግ ትግል የሚፈጠሩ ናቸው፡ ዳኞች እነዚህ መሰል ጉዳዮች በምናስበው ሁኔታ እና በግልጽ የዕለት ተዕለት ሥራዎቻቸው ሊያጋጥሟቸው እንደሚችሉ መገመት ያሻል። እነዚህ ፈታኝ ጉዳዮች በተለምዶ በአብዛኛው በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ እንደሚሆኑ ይገመታል።

ምክንያቱም የይግባኝ አቤቱታ ምክንያት የሚሆኑት በአብዛኛው የሕግ ትርጉም ክፍተቶች በመሆናቸው ነው። ዶርኪን ሃርትን መተቸቱን ሲቀጥል ሃርት በተለምዶ የቅቡልነት ሕግጋት የሚላቸው በማኅበረሰባዊ እውነታነት የሚታወቁ ናቸው። ይሁን እንጂ አንድ ዳኛ ከማኅበረሰባዊ እውነታነት (social fact) የተወሃዱ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ በመርህ ላይ ተመስርቶ እንዲወስን ሊጠበቅበት ይችላል። በመሆኑም የዳኛው ወይም በአጠቃላይ የሕግ ስርዓቱ ዋነኛ ሥራ "የሕግ ትርጉም" መስጠት ነው። ዳኛው የሕግ ትርጉም በሚሰጥበት ወቅት በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ህጋዊ አሰራሮችን የሚደግፍ የሕግ መርህ በመምረጥ እና ይህ መርህም ከማኅበረሰቡ ሞራል ጋር ያልተጋጨ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

በመሆኑም የሕግ ትርጉም በሂደቱ እና ይዘቱ የሥነ-ጥበባዊ ወይም የሥነ-ጽሑፋዊ ትርጉም ወይም ሂስ ጋር እንደሚመሳሰል ይገልጻል። አንድ የሥነ- ጥበብ ሥራ በአንድ ሃያሲ ሲተረጎም ደራሲው የጻፈው ቃል እና ነጥብ ላይ ብቻ ባተኮረ መልኩ ሳይሆን ከሃያሲው እይታ አንጻር መርሆዎች ላይ ተመርኩዞ እንደሆነ ሁሉ፤ ከሕግ ስርዓቱ አጠቃላይ ልምድ ጋር

በሚስማማ መልኩ የዳኛው ልዩ የአተረጓጎም ስልት መቼም ቢሆን አይነተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን ያሳስባል፡ በመሆኑም ይህንን የትርጉም ስልት ገንቢ ትርጉም (constructive interpretation) ሲባል ዳኛው የሚሠጠው ትርጉም በእነዚህ ፈታኝ ጉዳዮች ውስጥም ቢሆን ለሕግ ስርዓቱ አጠቃላይ መርሆ እና አሠራር የቀረበ እና ለዚያ ጉዳይ ደግሞ በተናጠል ልዩ እና አርኪ መልስ የሰጠ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል።

ዶርኪን "Law's empire" በተሰኘው ድርሳኑ የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍናን መሠረታዊ አላባውያን ለመተቸት ሞክሯል። ሕግ ማለት ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ትርጉም እንጂ አንድ ሉዓላዊ አካል የሚሰጠው ትእዛዝ ወይም መመሪያ አይደለም። በርግጥ ይህ ፍርድ ቤቶች በኩር ውሳኔ (Precedent) እንደ ሕግ የሚታይባቸው የአሜሪካ እና የእንግሊዝ የሕግ ስርዓት ውስጥ እንጂ እንደ ኢትዮጵያ እና አብዛኛው የአውሮፓ ሀገራት ላለው የፍትሕ ስርዓት የሚሠራ አይደለም። የሕግ ትርጉም የመንግስት ሕግ እና የሕዝብ ሞራልን የሚያገናኝ ሂደት ሲሆን በሁለቱ ምሶሶዎች መካከል እንደ ድልድይ የሚዘረጋው **የሕግ መርህ (Legal principle)** ነው። የዚህን የሕግ ትርጉም ሂደት በምናካሂድበት ወቅት እንደ አላማ መያዝ ያለብን "Law as Integrity" ወይም **"የሕግ ፍትሐዊ ምሉዕነት"** የሚለውን መመሪያ ነው። ዳኞች በታሪክ ማኅበረሰቡ ያከማቸውን ሞራላዊ አስተሳሰብን በሙሉ የሚያውቁ ናቸው፤በሌላ በኩል የመንግስት ሕግጋትን ለማወቅ የሰለጠኑ በመሆናቸው ሁለቱን ዓለማት የማስታረቅ ግዴታ አለባቸው።

ዳኞች "ብርቱ ጉዳይ" ሲገጥማቸው እንደፈለጋቸው የመተርጎም "Discretion" **"ፍቅድ ስልጣን"** ቢኖራቸውም ይህ ፍቅድ ስልጣን በመርህ የተገደበ እንጂ እንዲያው በደፈናው ለዳኞች ምናባዊ ሐሳብ የተተወ መሆን የለበትም[33]። በተጨማሪም ሃርት "የቅቡልነት ሕግ" የሚለው "Rule of rec-

33 ሕግ መተርጎም ማለት ለአንድ ሕግ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ትርጉም መስጠት ማለት ነው። ይህም ዕጣ እንደማውጣት በተምኔት ወይም ዕድል ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ግብዓት፤ ሂደት እና ውጤት ያለው ተግባር ነው። (ተስፋዬ ንዋይ ፤ሕግ እና አተረጓጎሙ፤ 2012፤ ገጽ 14)

ognition" ሁልጊዜ የሚታወቅ እና የማያከራክር ሆኖ ሊዋቀር እንደማይችል እና በእንዲህ ሁኔታ ዜጎች መብት የላቸውም ሊባል እንደማይቻል ያስረዳል። ዳኞች እውነተኛ እና ትክክለኛ ውሳኔ ለሁሉም ብርቱ ጉዳዮች የመስጠት ኃላፊነት እንዳለባቸው ለማስረዳት ምሳሌ ይሰጣል፤ ሕግ አውጪው "ቅድስና የጎደላቸው ውሎች ሕገ-ወጥ ናቸው" የሚል ሕግ ያወጣል፤ ሁለት ግለሰቦች በሰንበት ውል ፈፅመዋል በሚል ተከሰው ፍርድ ቤት ይቀርባሉ። ዳኛው በሰንበት ውል መፈፀም ቅድስና የጎደለው ተግባር ነው ወይ የሚለውን ብርቱ ጉዳይ (Hard case) በመተርጎም እውነተኛ እና ትክክለኛ ውሳኔ ወይም እልባት የመስጠት ኃላፊነት ይኖርበታል። ይህን ለመተርጎም "መርህ" መፍጠር የዳኛው ግዴታ ነው።

ሌላኛው የብርቱ ጉዳይ ምሳሌ እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ለአሜሪካ የእርስ በእርስ ጦርነት መጀመር immediate cause እንደሆነ ይነገራል[34]። ድሬድ ስኮት እና ሚስቱ ሃርየት የሳንፎርድ ባሮች- slaves ሆነው እየኖሩ ሳለ ከዕለታት በአንዱ ቀን ባለቤታቸው በመሞቱ ምክንያት እና ወደ Free state- ከባርነት ነፃ ወደ ሆነ ክፍለ ሀገር በመሄዳቸው ምክንያት ፍርድ ቤቱ በፍርድ ከባርነት ነፃ እንዲያደርጋቸው አቤቱታ ያቀርባሉ። አንዱ ፍርድ ቤት ነፃ ሲላቸው ሌላው ውድቅ ሲያደርግባቸው ቆይቶ ጉዳዩ ከአሥራ አንድ ዓመት ክርክር በኋላ በ 1857 ዓ ም ለአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይቀርባል። ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በ Roger Taney ሰብሳቢነት የሚመራ ሲሆን ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ 7 ለ 2 በሆነ ልዩነት በሰጠው ውሳኔ በአሜሪካ ውስጥ የሚኖሩ ጥቁሮች በሙሉ "Property " እንጂ ሰው ባለመሆናቸው ፍርድ ቤት መቅረብ አይችሉም። በአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፊት ጉዳይ ይዞ ለመቅረብ በቅድሚያ ዜጋ- Citizen መሆን እንደሚገባ እና ጥቁሮች ደግሞ ዜጋ ባለመሆናቸው በፍርድ ቤቱ ፊት መቅረብ አይችሉም፣ በተጨማሪም ጥቁሮች እና ባሮችን በፍርድ እና በሕግ ነፃ ማድረግ የጀመሩ States ሕገ-መንግስቱን እየጣሱ በመሆኑ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አሳስቧል።

34 Dred Scott v. Sandford, U.S. Supreme Court, 393 (1857)

በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት Abolitionist states እንዲያውም በቋፍ ስለነበሩ ወደ እርስ በእርስ ጦርነቱ ሙሉ ለሙሉ ለመሳተፍ ምክንያት አግኝተዋል። ድሬድ ስኮት እና ሚስቱ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ድሬድ ስኮትም የጦርነቱን መጨረሻ ሳያይ አርፏል። Roger Taney ለውሳኔው እንደ ምክንያት ያቀረበው (ቀንደኛ Originalist ነበር) የሕገ-መንግስቱ አርቃቂዎች ራሳቸው ባሪያ አሳዳሪዎች Slave owners ሆነው ሳለ ጥቁሮች የሕገ-መንግስቱ መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ ብለው ሊያስቡ አይችሉም የሚል ነበር። ደግነቱ የአሜሪካ የእርስ በእርስ ጦርነት እንደተገባደደ 13ኛው፣ 14ኛው እና 15ኛው የአሜሪካ ሕገ-መንግስት ማሻሻያ ተደርጓል፤ ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቶቹ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን ብርቱ ጉዳይ በሕገ-መንግስቱ እና በተፈጥሮ መሃል የተዘረጋ አንድ ዘመን ተሻጋሪ መርህ ፈጥሮ ሊፈታው ይገባ ነበር።

ፍጹማዊ የሥነ - ሕግ አስተምህሮ - ሃንስ ኬልሰን

“የአንድ ሕግ ቅቡልነት ከቀዳሚ የበላይ ሕግ ይመነጫል”

በሀገረ- ኦስትሪያ ተወልዶ ያደገው ሃንስ ኬልሰን (1881-1973) በአይሁዳዊነቱ ምክንያት በሂትለር ወደ አሜሪካ ቢሰደድም በዘመኑ ፍጽማዊ የሥነ-ሕግ አስተምህሮን (pure theory of Law) መሬት እንዳይዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ኬልሰን ቀዳሚውን የኦስትሪያ ሕገ መንግስት አርቅቋል በቪየና እንዲሁም በአሜሪካ በማስተማር እና በመመራመር ብዙ እውቀትን አግኝቷል። በአይሁድ ቤተሰብ ውስጥ ቢወለድም ሲያድግ በካቶሊክ እምነት ተከታይነት ከተጠመቀ በኋላ ከሚስቱ ጋር ቆየት ብሎ የሉተራን እምነት ተከታይ ሆነዋል።

ኬልሰን በወቅቱ የነበረው የሕግ አስተምህሮ በፖለቲካዊ ርዕዮቶች፤ በሞራላዊ ስብከቶች እና በማኅበራዊ ሳይንስ ፍልስፍናዎች ተጽእኖ ስር በመውደቁ እንደተበከለ ያስብ ነበር። በመሆኑም የሕግ አስተምህሮን ከእነዚህ

ሁነቶች ማንጻት ያስፈልጋል በማለት ተከራክሯል። የማንኛውም የሕግ አስተምህሮ እና ስርዓት መሰረታውያን የሕግ ልማዶች ናቸው፤ ልማድ ማለት ደግሞ የድርጊት ትርጉም ነው። የሕግ ልማድ ስርዓት ሕግጋት እና መመሪያዎች ሕጋዊ ቅቡልነታቸውን የሚያገኙበት አሠራር ነው።

> Law is an order of human behavior. An "order" is a system of rules. Law is not, as it is sometimes said, a rule. It is a set of rules having the kind of unity we understand by a system. It is impossible to grasp the nature of law if we limit our attention to the single isolated rule[35].

አንድ አዋጅ ሕጋዊ ቅቡልነትና ትርጉም የሚያገኘው በቀደመ እና ከፍተኛ በሆነ የሕግ ስርዓት የጸደቀ ከሆነ ብቻ ነው። ይህ ቀዳሚ እና ከፍተኛ የሕግ ስርዓትም እንዲሁ በቀደመ እና ከፍተኛ ከሆነ የሕግ ስርዓት ቅቡልነትን ማግኘት አለ በመሆኑም ሕግጋት በእዚህ መንገድ የስልጣ ከዋረድ ይመሰርታሉ። ሕግጋት ቅቡልነት እና ሕጋዊነት የሚያገኙበትን መስመር ተከትለን ወደ ኋላ ስንሄድ ሁሉም ሕግጋት እና የሕግ ልማዶች ቅቡልነታቸውን እና ሕጋዊነታቸው ያገኙበትን **አንድ ቀዳሚ እና መሠረታዊ ሕግ** እናገኛለን። ይህ መሠረታዊ የሕግ ስርዓት (Grundnorm) በአንድ ሀገር የሚገኙ አዋጆችና መመሪያዎች በአንድነት የፈጠሩትን የሕግ መረብ እና ሰንሰለት የሚያስጠብቅ እና የሚያቋቁም ነው። በመሆኑም በአንድ የሕግ ስርዓት ወይም በተለያዩ የሕግ ስርዓቶች ውስጥ ያሉ የሕግ አሰራሮች እና ልማዶች የተፈጠሩበት እና ቅቡልነት ያገኙበትን ምክንያት ከአንድ መሠረታዊሕግ የምናገኝ ከሆነ እነዚህ የሕግ ልማዶች ከአንድ የሕግ ስርዓት እንደተፈጠሩ መገመት ይቻላል።

በመሆኑም አንድ ሕግ ቅቡል ብቻ ሳይሆን ውጤታማም መሆን አለበት። ለዚህ ደግሞ ይህ ሕግ የጸደቀበት አካሄድ ቀደም ብለን በጠቀስነው

35 Hans Kelsen, General Theory of Law and State (1949)

መንገድ ተገቢውን የስልጣን ተዋረድ ጠብቆ መሆን አለበት። በዚህም መሠረት "ፍጹም " የሆነ የሕግ ስርዓት ለመመስረት የሕግ ስርዓቱን በሙሉ ከዚህ የሕግ ስልጣን ተዋረድ ውጪ ካሉ አስተሳሰቦች እና አሰራሮች ማንጻት ያስፈልጋል፤ ያን ጊዜ ይህ ንጹህና ፍጹም የሆነው የሕግ ስርዓት ተገቢውን ውጤታማነት ያገኛል። በመሆኑም ይህ ፍጹም የሆነ የሕግ መሠረታዊበሆነ መልኩ በሕገ-ሰብ ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ አንደመሆኑ ሕግ ሰው ሠራሽ መሆኑን ይቀበላል።

> It is called a "pure" theory of law, because it only describes the law and attempts to eliminate from the object of this description everything that is not strictly law: Its aim is to free the science of law from alien elements. This is the methodological basis of the theory.[36]

አሁን ባለንበት ዘመናዊ የሕግ ስርዓት ይህንን የኬልሰንን መሠረታዊ የሕግ ስርዓት ልማድ (Grundnorm) ከሕገ-መንግስት ጋር ልናመሳስለው እንችላለን ኬልሰን ቀዳሚውን የኦስትሪያ ሕገ-መንግስት ማርቀቅ ብቻ ሳይሆን በንጉሱ ቀጥተኛ ትእዛዝ የኦስትሪያ ሕገ-መንግስት ፍርድ ቤት አባል እንደነበር ልብ ይሏል። ይሁን እንጂ ኬልሰን በአንድ ሀገር ውስጥ ከዚህ መሠረታዊ ሕግ ውጪ ሌላ ተደራቢ ወይም አቻ የሕግ ስርዓት እንዲኖር አይፈቅድም በዚህም ምክንያት ባህላዊ ለሆኑ ሕግጋት እውቅና አይሰጥም። ከዚህም በላይ በአንድ የመንግስታዊ መዋቅር ውስጥ የጸደቀ አንድ አነስተኛ መመሪያ ሒሳባዊ በሆነ መንገድ አንድ ሁለት ብሎ ምንጩን ከመሠረታዊው ሕግ ጋር ማገናኘት አለበት። ከዚህ ውጪ በራሱ የሚንሳፈፍ መመሪያም ሆነ አዋጅ ጸድቆ ወደ ሥራ ቢገባ ቅቡልነት የሌለው ሕግ መሆኑን ይጠቅሳል።

ኬልሰን መሠረታዊ ሕግ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በአንድ የሕግ ስርዓት

36 Hans Kelsen, *Pure Theory of Law,* (revised ed., 1960)

ውስጥ በተጻፈና በተለየ መንገድ የሚገኝ ወይም ብዙ ሰዎች እንደሚያስቡት ሕገ-መንግስት ላይሆን ይችላል። ኬልሰን ለመገንባት የሚፈልገው የአንድን የሕግ ስርዓት የቅቡልነት መንገድ ነው። በመሆኑም መሠረታዊ ሕግ (Grundnorm) የተባለው ሕግ የሀገሪቱ መደበኛ ሕጎች አካል አይደለም። እንዲያውም ሕግጋቱ ሁሉ ቅቡልነታቸውን የሚያረጋግጡበት የሕግ አካል እና የአሠራር ዘይቤ ነው። በመሆኑም ለኬልሰን ሰው ሠራሽ ሕግጋት በሙሉ ጥብቅ የሆነ የስልጣን ተዋረድ ሊኖራቸው አንደሚገባ እና ይህ ጥብቅ የሆነ የስልጣን ተዋረድ ደግሞ ሊረጋገጥ የሚችለው ጥብቅ የሆነ የቅቡልነት ሰንሰለት ከታች ወደ ላይ ሲዘረጋ ብቻ ነው።

በመሆኑም በአንድ የሕግ ስርዓት ውስጥ ያሉ ሰው ሠራሽ ሕግጋት በሙሉ ቅቡልነታቸውን ከአንድ የሚታወቅ ሕግ ወይም የሕግ አሠራር ሊያገኙ እንደሚገባና የሰው ሠራሽ ሕግ ፍልስፍና መሠረታዊ ፅንሰ ሐሳብም ይኸው መሆኑን ኬልሰን በተለያዩ ድርሳኖቹ እና ጽሑፎቹ ለማሳየት ሞክሯል። በመሆም "መሠረታዊ ሕግ" የሚለውን ሐሳብ እንደ ሕግ ብቻ ሳይሆን የሕግጋት ቅቡልነት ማግኛ እና ማስጠበቂያ አሠራር እንደሆነ አድርገን ልናየው ይገባል።

ሌላኛው ጥያቄ ሁሉም ሕግጋት ቅቡልነታቸውን ከዚህ መሠረታዊ ሕግ የሚያገኙ ከሆነ ይህ " መሠረታዊ ሕግ" ቅቡልነቱን ከየት ያገኛል? የሚለው ነው። ኬልሰን ሲመልስ ይህ "መሠረታዊ ሕግ" ቅቡልነቱ ቅድመ-ታሳቢ የሚደረግ ነው ምክንያቱም ከዚህ ሕግ በላይ የሆነ የቅቡልነትም ሆነ የስልጣን የበላይነት ያለው ሕግ ሊኖር አይችልም ወይም አይገባም። በመሆኑም ሰው ሠራሽ ሕግጋት ከታች ወደ ላይ የሕንጻን አገነባብ ደረጃ በተከተለ መልኩ የሚገነቡ ናቸው ብንል መሠረታዊ ሕግ ልክ እንደመሠረት የሚያገልግል ነው።

የሕግ ውስጣዊ የሞራል ውቅር - ሎን ፍለር

“የሕገ-ሰብዕ ውስጣዊ የሞሁክ ውቅር ተፈጥሯዊ ሃው”

ፉለር (1902-1978) በሐርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ፍልስፍና እና የውል ሕግ ያስተማረ ሲሆን ከሃርት ጋር በ1958 እ.ኤ.አ ባደረገው ታዋቂ ሙግት ሳቢያ አስከ ዛሬ ድረስ የሚታወቅበትን “ውስጣዊ የሞራል ውቅር” መስርቷል። ፉለር ለሥነ-ሕግ ፍልስፍና እና ለተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና መሀከለኛ የሆነነ መንገድ ለማሳየት ሞክሯል። በቅድሚያ ሕግ ከልዕለ ሰባዊ ኃይል የመነጨ ዲበአካላዊ እና መንፈሳዊ ምንጭ እና ይዘት እንዳለው አይቀበልም ፤ይሁን እንጂ ሕግ ሰው ሠራሽ ቢሆንም የራሱ የሆነ ውስጣዊ የሞራል ውቅር እንዳለው ያምናል።

ይህንኑ ጉዳይ ሲያብራራ በሕግና ሞራል መሀከል ምንም ዓይነት ግንኙነት አንደሌለ እና ፍጹም የማይገናኙ ተደርጎ በቀደምት የሕገ-ሰብ ፍልስፍና አራማጆች የሚሰብከው አስተምህሮ ስህተት እንደሆነና ሕግ በመሠረቱ ሰው ሠራሽ ቢሆንም ሰው ሠራሹ ሕግም ቢሆን ውስጣዊ የሞራላዊ ይዘት እንዳለው እና ሊኖረው እንደሚገባ ያስረዳል።

> The rules must be (1) sufficiently general, (2) publicly promulgated, (3) prospective (i.e., applicable only to future behavior, not past), (4) at least minimally clear and intelligible, (5) free of contradictions, (6) relatively constant, so that they don’t continuously change from day to day, (7) possible to obey, and (8) administered in a way that does not wildly diverge from their obvious or apparent meaning[37]

37 Lon L. Fuller, *The Morality of Law*, rev. ed. New Haven CT: Yale University Press, 1969, pp. 33-38

በዚህም ምክንያት ሕግጋት ሰው ሠራሽ ቢሆንም “ውስጣዊ የሞራል ውቅር” (internal morality of the law) ስላላቸው ሊታለፉ የማይገባቸው እነዚህ መስፈርቶች፡-

1. በቂ በሆነ መልኩ አካታችነት እና አጠቃላይነት
2. በይፋ ለሕዝብ የታወጁ
3. የወደፊቱን ትውልድ /ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገቡ
4. እርስ በእርሳቸው የማይጋጩ እና የማይቃረኑ
5. ግልጽ እና በቀላሉ ለመረዳት የሚቻሉ
6. በየጊዜው የማይለወጡ እና የማይሻሩ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ቋሚነት ያላቸው፤
7. ለመታዘዝ እና ለመተግበር የማያዳግቱ
8. ሲተገበሩም ከታቀዱለት አላማ ውጪ ውጤት የማያመጡ እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ ሕግ በቂ የሆነ የሕጋዊነት ይዞታ ያለው እንደመሆኑ ርትዕ ያለው እና ተገማች ሊሆን ይችላል።

በሎን ፋለር እና ኤች ኤል ኤ ሃርት በ1958 ዓም በሐርቫርድ ሎው ሪቪው የታተሙ ሙግቶች ተካሄደዋል። ከላይ እንደተመለከተው ሃርት ሕግና ሞራል የሚገናኙበትን መንገድ ለማስረዳት ሞክሯል። የሕግ ሥራ የማኅበረሰብን ባህሪ መቅረፅ እና መምራት እንደመሆኑ ውጤት ተኮር ነው። በመሆኑም ሕግ ውጤታማ በሆነ መንገድ ይህንን አላማ ያሳካ ዘንድ እነዚህ ስምንት መስፈርቶች ጥብቅ በሆነ ሥነ-ስርዓታዊ መንገድ መሟላት ይኖርባቸዋል። በዚህ ምክንያት ፉለር ጥናታዊ የተፈጥሮ የሕግ ፍልስፍና ቢቃወምም በተሻሻለ መልኩ የተፈጥሮ ሕግ ደጋፊ እና ተከራካሪ ሆኖ ቀርቧል ሲሉ የሚከራከሩ ሰዎች አሉ። ከዚህ የተነሳ ፉለር ሥነ-ስርዓታዊ የተፈጥሮ- ሕግ አቀንቃኝ (Procedural Naturalist) እንደሆነ ተደርጎ ቢታይም ሃርት ይህንን ሂደት ሲተች ፍለር “ሞራል” እና “ውጤታማነትን”

አምታቶታል፤ ምክንያቱም ሕግ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲተገበር ማድረግ እና የሕግን ሞራል መፍጠር ለየቅል ናቸው፤ ምክንያቱም የፉለር መስፈርቶች እኩይ የሆነ ሕግ ለማውጣት ቢሆን ውጤታማ በሆነ መንገድ ሊያገለግሉ ይችላል ይላል።

ሎን ፉለር አንድ ታዋቂ ጦማር በማበርከቱም ይታወቃል። The Supleccan Explorers (የዋሻው አሳሾች) ታሪክ በሚል ያጻፈው ነቂሳዊ ጽሑፍ ነው። አምስት አሳሾች በአንድ ዋሻ ውስጥ ጉዞ በማድረግ ላይ ሳሉ ዋሻው ይደረመስና፣ እዚያው ዋሻ ውስጥ የራዲዮ ግንኙነት ተቋርጦባቸው ቀናት ያልፋሉ። በሀያ ሦስተኛው ቀናቸው ከአምስቱ አሳሾች አንዱ ዕጣ አውጥተው የአንዳቸው ስጋ እንዲበላ ሐሳብ ያቀርባል። ሐሳቡን ካቀረበ በኋላ በዕጣው እንደማይሳተፍ ቢገልፅም አራቱ አሳሾች እሱንም ጨምረው ዕጣውን ሲያወጡ እርሱ ላይ ይወድቃል። አራቱ አሳሾች የአንደኛውን አሳሽ ስጋ ቀርጥፈው ከበሉ በኋላ በሰላሳኛ ቀናቸው ይደረስላቸዋል። እነርሱን ለመፈለግ በተካሄደ አሰሳ አስር ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል። በሕይወት ከወጡ በኋላ የሰው ነፍስ በማጥፋት ይከሰሳሉ የሞት ፍርድም ይጣልባቸዋል። ይህንኑ ተቃውመው ይግባኛቸውን አምስት ዳኛ ላለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀርባሉ፣ በዚህን ጊዜ ዳኞቹ በአቋም ይለያያሉ። በመሀከላቸው የሚደረገው ክርክር በተለያዩ የሕግ ፍልስፍናዎች መሀከል የሚደረግ ክርክርን በአጭሩ ለመገንዘብ ይረዳል።

አንደኛው ዳኛ የስር ፍርድ ቤት ቅጣት ሊፀና ይገባል ለሕጉም ምንባባዊ ትርጉም (Textual interpretation) ልንሰጥ ይገባል በማለት ወግ አጥባቂ የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና(Positive Law) ያራምዳል። ሌላኛው ዳኛ እነዚህ ሰዎች በሕገ-አራዊት (state of nature) ላይ እንደሚገኙ ቆጥረን ተግባራቸው ተፈጥሯዊ በመሆኑ ራሳቸው መጠበቃቸው (self preservation) ራስን ከጥቃት እንደመከላከል (self defense) ተቆጥሮ ይቅር ሊባሉ ይገባል ይላል። ሦስተኛው ዳኛ ራሱን ከጉዳዩ ያገላል። ሌሎቹ ዳኞችም የሕጉን አላማ ከግምት በማስገባት አራቱን ለማዳን አስር ሰው

አጥተን እነሱን መግደል ምክንያታዊ አይሆንም እና የሕዝቡም ስሜት ዘጠና በመቶ በላይ ይፈቱ በመሆኑና የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት የሞት ቅጣቱን እንደሚያነሳ መሰማቱን ከግምት አስገብተው በመቃወም እና በመደገፍ መሃል በመሆናቸው የስር ፍርድ ቤት የሞት ቅጣት ፀንቷል። ይህ ምናባዊ ጽሑፍ ከታተመ ጀምሮ ባሉት ሃምሳ ዓመታት ከፍተኛ መነጋገሪያ ሆኗል። የተለያዩ የሕግ አስተምሮቶች በራሳቸው መነፅር ጉዳዩን በመተንተን ከሕገ ሰብዕ አስከ ተፈጥሮ ሕግ፣ ከነቂሳዊ የሕግ አስተምህሮ እስከ ነባራዊ ሥነ-ሕግ፣ ከምግባራዊነት እስከ ጠቀሜታዊነት ድረስ ሁሉም ተመራማሪ በዳኞቹ ፈንታ እየገባ የራሱን ምናባዊ ትንታኔ ፅፏል።

በሃርት እና ፉለር መካከል ስለ ሕግ እና ሞራል የተካሄደው ክርክር በHarvard law review ላይ ታትሞ ከፍተኛ መነጋገሪያ ሆኖ ነበር። ለክርክሩ መነሻ የሆነው የፍርድ ቤት ጉዳይ ሲሆን ይኸውም በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወቅት አንድ በናዚ ጀርመን ጦር ውስጥ የሚያገለግል የጦር መኮንን ቤቱ ውስጥ ሂትለርን ይሳደባል። ይህንን የሰማች ሚስቱ በታላቁ መሪያችን እና መንግስት ለይ ስድብ እን ክብርን የሚያዋርድ ቃላት ሰንዝሯል ብላ ለፖሊስ ታመለክታለች፤ ተከሶ የቀረበበት ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በነበረው ሕግ መሠረት የሞት ቅጣት ይጥልበታል። ይህንኑ የሞት ቅጣት እየተጠባበቀ ጦርነቱ እየተፋፋመ ስለሄደ ወደ ጦር ግንባር ተልኮ በመዋጋት ላይ እያለ የሂትለር ጦር ይሸነፋል። ከጦርነቱ በኋላ በተቋቋመው አዲሱ የጀርመን ፍርድ ቤት የሞት ቅጣቱን የፈረደውን ዳኛ እና የጦር መኮንኑ ሚስት ተከሰው ሲቀርቡ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ዳኛው በወቅቱ በነበረው የናዚ ሕግ መሠረት ሥራውን ያከናወነ በመሆኑ ጥፋት የለበትም ብሎ በነፃ ሲያሰናብተው ሚስትየውን ግን ምንም እንኳ በሂትለር ላይ የስድብ ቃል መሰንዘር ወንጀል ቢሆንም ከሕግ በላይ ባሉ የህሊና እና የሞራል ሕግጋት እንዲሁም ከናዚው ሕግ በፊት ተደንግጎ በነበረው የወንጀል ሕግ መሠረት ጥፋተኛ ብሏታል። በወቅቱ የነበረው ፍርድ ቤት ሀተታውን ሲያቀርብ የናዚ ጀርመን ሕግጋት “Contrary to sound conscience and all sense of justice/ከህሊና እና ከፍትሕ ፅንሰ

ሐሳብ ጋር የሚቃረኑ" በመሆናቸው ሚስትየው እነዚህን የናዚ ሕግጋት የመቃወም ሞራላዊ ግዴታ ነበረባት።

ራሰር የድህረ-ናዚ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመቀበል፤የናዚ ሕግጋት ሰው ሠራሽ ሕግጋት ቢሆኑም "የሕግ ውስጣዊ የተፈጥሮ ስርዓትን" የሚያሟሉ በመሆኑ በዜጎቹም ሆነ አዲስ በተቋቋመው ፍርድ ቤት ውድቅ መደረጋቸው ህጋዊነትን የተከተለ መሆኑን አስረድቷል። ራሰር በዚህ አያያዝ ሃርት የሰው ሠራሽ ሥነ-ሕግ አቀንቃኝ እንደመሆኑ የናዚ ሕግጋት ቅቡልነት አላቸው ብሎ ስለሚያምን የሚስትየው ድርጊት ሊኮንን አይችልም ብሎ ይኮንነዋል። ሃርት ለዚህ ምላሽ ሲሰጥ በሕግ ስርዓት "The core and penumbra" የሚባል ፅንሰ ሐሳብ እንዳለ በማስረዳት ይጀምራል። "Core" የምንላቸው ሕግጋት በቅድሚያ ሕጉ ሊሸፍናቸው ያሰባቸው እና ብዙም አሻሚ ያልሆኑት ናቸው። በአንድ ሰው ሠራሽ ሕግ ውስጥ ያረጀ፣ ጊዜው ያለፈበት ወይም ትቅም ላይ ሊውል የማይችል፣ የተፈጥሮ ሕግን የማይጋፉ የሕግ ቃል ወይም ፅንሰ ሐሳብ ሲገኝ ያንን ቃል የምንተረጉመው በህብረተሰቡ ሞራል ከሆነ ሕግን ለሞራል በማስገዛት መተርጎም ከሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና ጋር አይቃረንም ወይ/ እያሉ ብዙዎች ይጠይቃሉ።

ይሁን እንጂ ይህንን ሕግ ሳንተረጉመው ሞራልን ከሕጉ አላማ ጋር በማነፃፀር እንጂ ደስ ባለን የሞራል መርህ አይደለም፤ሰው ሠራሽ ሕግም ቢሆንም ቢያንስ አነስተኛ የማኅበረሰባዊ የሞራል ደረጃን ማሟላት ይኖርበታል። ራል ይህንን የሃርት አነስተኛ የሞራል ደረጃ "minimum requirement of morality" ራሱ ከየት እና ለምን እንደመነጨ እንመርምር ይላል። የሰው ሠራሽ ሕግ ፍልስፍና አቀንቃኞች አነስተኛ የሞራል ደረጃ ወደ ሕግ ስርዓቱ እንዲገባ የሚፈቅዱት ሕግጋቱ እርስ በእርሳቸው እንዳይጋጩ እና ለሚያገለግሉት ሕዝብ ትርጉም እንዲኖራቸው ነው። ይሁን እንጂ ይህ ትርጉም እና ዓላማ ያለው ሰው ሠራሽ የሕግ ስርዓትየመገንባት ፍላጎት በራሱ ከሰው ሠራሽ ሕግጋቱ ማዕቀፍ ውጪ ያለ ፅንሰ-ሐሳብ "Fidelity to the Law" ሲሆን፤ ይህ ፍላጎት ራሱ ተፈጥሯዊ የሞራል ሕግ ነፀብራቅ ነው።

በመሆኑም የሰው ሠራሽ ሕግ አቀንቃኞች ራሳቸው ይህንን የሕግ ውስጣዊ የሞራል ደረጃ ይቀበሉታል። አንድ ዳኛ በራሱ ጉዳይ መዳኘት የለበትም የሚል ሥነ-ስርዓታዊ ሕግ ታሳቢ የሚያደርገው ሞራላዊ ደረጃን እንጂ ተራ የሕግ ተጠያቂነትን ብቻ አይደለም። በአንድ ፓርክ ውስጥ "ተሽከርካሪ ወደ ፓርኩ ማስገባት አይቻልም!" የሚል ሕግ ቢፃፍ፤ ሳይክልን እንደማይጨምር ግልፅ ነው፤ ምክንያቱም መመሪያው ሞተር ያላቸውን ተሽከርካሪዎች እንጂ ሳይክልን እንደማያካትት አያከራክርም። በመሆኑም "Penumbra" ወይም ግልፅ ያልሆነ ወይም አሻሚ ሕግጋት ሲገኙ ሁልጊዜ ሕግና ሞራል እንደተጋጩ እሰብን ማደናበር ሳይሆን የሕጉን አላማ እያስተዋልን መንቀሳቀስ ይኖርብናል ሲል ሃርት ለፉለር መልስ ሰጥቷል።

ታሪካዊ የሕግ ፍልስፍና ፍሬድሪክ ቮን ሳቭኒ

"ሕግ የሕዝባዊ መንፈስ ነጸብሁቅ ነው"

በሕግ ተመራማሪነት ዘመኑ ረዥም ጊዜውን ያሳለፈው የጥንቷ ሮም ስልጣኔን ሕግ እና ቋንቋ በማጥናት ነው። በሕግ እና በማኅበረሰባዊ ታሪክ ወይም ስነልቦና መሀከል ያለው ግንኙነት ምን አንደሆነ ለማጥናት ጥረት አድርጓል ቮን ሳቭኒ። ሳቭኒ ሕግን ከሚሰጠው ጥቅም እና ተግባር ጋር አቆራኝቶ አይመለከትም። ይልቁንም በሕግ እና በማኅበረሰቡ ታሪክ ወይም ሥነ-ልቦናጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለ ለማሳየት ሞክሯል። በርግጥ ታሪካዊ የሥነ-ሕግፍልስፍና የተመሰረተው ጉስታቭ ሁጎ በሚባል ጀርመናዊ ተመራማሪ ሲሆን ሳቭኒም ከዚህ ግለሰብ በተሻለ የዚህን ቤተ አስተምህሮ እንዲስፋፋ አድርጓል።

ለሳቭኒ ሕግ የማኅበረሰቡ ሥነ-ልቦና ውጤት ነው። ይህ ማኅበረሰባዊ ስነልቦና ደግሞ በማኅበረሰቡ ታሪክ ውስጥ የሚገኝ ነው። በመሆኑም ሕግ **የሕዝባዊ መንፈስ** (Volkgeist/ Popular spirit) ነጸብራቅ ነው። በመሆኑም ልክ እንደ ቋንቋ፤ ባህል እና ሃይማኖት ሁሉ የአንድ ማኅበረሰብን ሕግ በማየት ስለማኅበረሰቡ ማንነት መናገር ይቻላል። እንደ አስተምህሮው

ከሆነ ጠበቆች ፤ዳኞች እና የሕግ ተመራማሪዎች የዚህ ሕዝባዊ መንፈስ አስጠባቂዎች ናቸው፤ምክንያቱም ሕግ የዚህ ሕዝባዊ መንፈስ ውጤት ነው። ፍልስፍናው በራሱ በሁለት የተከፈለ ሲሆን ቀዳሚው እና ሳቭኒ ያለበት ቡድን እውነተኛው የአውሮፓ ሥነ-ሕግ መሠረት እና ሥነ-ልቦና ያለው ወይም ደግሞ የአውሮፓ ሕግ ሕዝባዊ መንፈስ የሚገኘው በሮም ሕግጋት ውስጥ እንደሆነ ሲያስረዳ ሌላኛው ደግሞ የጀርመን ሥነ-ሕግ መሆኑን በመጥቀስ ይከራከራል።

ይህን የሕግ ፍልስፍና የሚተቹ ሰዎች ይህ ፍልስፍና አንድ ታሳቢ የሚያደርገው ነገር የዚህ ሕግ ባለቤት የሆነው ማኅበረሰብ የአንድ እና ተመሳሳይ ቋንቋ ፤ ባህል ፤ ሃይማኖት እና ብሄር ባለቤት መሆን አለበት፤ ይሁን እንጂ በዓለማችን ውስጥ በአንድ መንግስት እና ሕግ የሚገዙ ግን በብሄር ፤ በቋንቋ፤ በታሪክ እና ሃይማኖት የሚለያዩ ህዝቦች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ህዝቦች ሳቭኒ እንደሚለው የአንድ ሕዝባዊ መንፈስ ተጋሪ ሊሆኑ አይችሉም ይላል። ሳቭኒ የሮም ስልጣኔን እና ሕግን በሚያጠናበት ወቅት ባደረበት ተጽእኖ ይህን አስተምህሮ አቋቁሞ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ከጀርመን እና የሮም ስልጣኔ ውጭ ይህ ፍልስፍና ሊሰራ መቻሉ አጠራጣሪ መሆኑን ያክላሉ።

በሕግ እና በታሪክ መካከል ያለውን ግንኙነት በአግባቡ ማጥናት አለብን፤ምክንያቱም ሕግ የሚመነጨው በታሪክ ሂደት ውስጥ ነው። የሕግ አውጪው የሚወጣው ከማኅበረሰቡ ውስጥ በመሆኑ ሕግ በሚያወጣበት ወቅት ንጉስም ሆነ ፓርላማ የማኅበረሰቡን ባህል፣ ታሪክ፣ ሃይማኖት፣ ወግ እና ልማድ በሕግ ውስጥ ለማንፀባረቅ ጥረት ያደርጋል። በመሆኑም በዓለም ላይ ብዝሀር እያንዳንዱ የሕግ ስርዓት የሚመስለው የወጣበትን ማኅበረሰብ ሕዝባዊ ማንነት ነው። ይህን ሕዝባዊ ማንነት(Popular spirit) የምናገኘው በሕዝቡ ወግ እና ልማድ ውስጥ ነው። ወግ እና ልማዱን ለማወቅ ደግሞ የሕዝቡን የስልጣኔ ታሪክ ማወቅ አለብን። በዚህም ምክንያት አንዳንድ ሕግጋት ከታወጁ በኋላ ከታተሙበት ወረቀት በላይ ትርጉም መስጠት አቅቷቸው በመደርደሪያ ላይ ሲቀሩ ሌሎች ሕግጋት ግን በቀላሉ በሕዝቡ ተቀባይነት ያገኛሉ።

የሕገ-ሰብዕ አቀንቃኞች ግን ሕግ ማለት ሉዓላዊ አካል የሚሰጠው ትእዛዝ እንደሆነ የሚያቀርቡት መከራከሪያ ኋላቀር ነው። ይህ ሕዝባዊ መንፈስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ እና እየተቀየረ የሚሄድ በመሆኑ ሕግ አውጪዎች ሁልግዜ የሕዝባዊ መንፈስ እንዴት እያደገ እና ወደ ምንነት እየተቀየረ እንደሆነ በጥልቀት ማጤን ይኖርባቸዋል። ሕግ አውጪው ሕግ በሚያረቅበት ወቅት በታሪካዊ ሁነት ውስጥ እየተሳተፈ እንደሆነ ሊገነዘብ ከዚህም አልፎ ታሪክን እንደሚፅፍ ሰው በከፍተኛ ኃላፊነት ግዴታውን ሊወጣ ይገባል።

ማኅበረሰብ በየወቅቱ የሚያድግ እና የሚለወጥ በመሆኑ ሕግም የሚያድግ እና የሚለወጥ መሆን አለበት፤ በዚህም ምክንያት ሕገጋት በድርሳን (Code) ተሰንደው ሊጠቀልሉ አይገባም፤ የአንድ ማኅበረሰብ እድገት ካለቀ ያን ጊዜ ምናልባት ሕገጋቱን Codify ማድረግ እንችላለን። ሕግ ማለት የማኅበረሰቡ ነፀብራቅ በመሆኑ ሕገጋት እንደሚገኙበት ልዩ ልዩ ማኅበረሰቦች የተለያዩ መሆናቸው አይቀሬ እንደመሆኑ አጠቃላይ (universal) እንደሆኑ አድርጎ ማሰብ የሕግጋቱን እድገት መቀልበስ እና ያሉበትን ማኅበረሰብ አለማወቅ ነው።

ሳቭኒ ሕግ አውጪው ሕግጋትን ያገኛል እንጂ አይፈጥራቸውም (Laws are found not made) በማለት ተከራክሯል። በ1814 ጀርመን የናፖሊዮን ወረራን መክታ ነፃ ከወጣች በኋላ ሕግጋቶቹን አጠቃሎ የመሰነድ (Codification) ሂደት በመጀመሩ ሳቭኒ ይህንኑ በመቃወም ይህን መርህ ሊቀምር ችሏል። ሕግጋትን አጠቃሎ ለመሰነድ ስለዚያ ማኅበረሰብ ታሪክ፣ ወግ እና ባህል ፍጹም እና ረቂቅ የሆነ መረዳት ላይ መድረስ አለብን። ይህ ደግሞ በአንድ ጊዜ ሊደረስበት የሚችል ደረጃ እንዳይሆን አንደኛ የማኅበረሰብ እድገት ተለዋዋጭ (Dynamic) ሲሆን የማኅበረሰብን ረቂቅ ወግ እና ልማድ ማጥናት ደግሞ እጅግ ከባድ ተግባር ነው።

ሳቭኒ የሕግን እድገት የሚያመሳስለው ከቋንቋ እድገት ጋር ነው። ቋንቋ ሲፈጠር መጀመሪያ አነስተኛ መግባቢያ ቃላት ሲኖሩት እነዚህም ቃላትም በጥቂት የቋንቋው ተናጋሪዎች መሀከል ብቻ የሚዘወተሩ ናቸው። ቀስ በቀስ ግን ቋንቋው ከማኅበረሰቡ ጋር እያደገ ሲሄድ የማኅበረሰቡን ስሜት፣

እውቀት እና ፍቃድ በአመዛኙ ሊገልፅ ይችላል። የሕግም እድገት እንዲሁ በሂደት ጥልቀት እና ምጥቀት እያገኘ ሲሄድ የማኅበረሰቡን የማንነት እና የሥነ-ልቦና ነፀብራቅ እስከመሆን ሊደርስ ይችላል። ሳቭኒ ከአንድ ሉዓላዊ አካል የሚጫኑ ሰው ሠራሽ ሕግጋትን እንደሚቃወም ሁሉ "የተፈጥሮ ሕግ" የሚባለውን አስተሳሰብ መነኩሴዎች የሚያራምዱት መሃይምነት እንደሆነ ይናገር ነበር። የተፈጥሮ ሕግ ሁሉም ማኅበረሰብ ተመሳሳይ እና አጠቃላይ ሕግጋት እንደሚመራ አድርጎ የሚያስብ አስተምህሮ በመሆኑ የተለያዩ ህዝቦች በተለያየ መንገድስላሳለፉት የታሪክ እና የማንነት ገፅታዎች ቦታ የሚሰጥ አይደለም።

በጀርመን ሐሳባዊነት (German Idealism) ጥላ ስር ያደገው የታሪካዊ ሥነ-ሕግ ቤተ-አስተምህሮ በሌሎች ሃገራት ምሁራን ላይም ተፅዕኖውን አሳርፏል። ከእነዚህ ምሁራን መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው ሄነሪ ሜን ነው። የእንግሊዝ ፍልስፍና ሕግ ከጥንታዊ የሕግ ተቋማት ውስጥ የሚፈልቅ ቢሆንም በጊዜ ውስጥ በዝግመታዊ ለውጥ እያደገ የሚሄድ ነው። ይህንን ለማሳየት የሕግ ታሪካዊ እድገት ስድስት ደረጃዎች እንዳሉት ይገልፃል። የመጀመሪያዎቹ ሦስት ደረጃዎች ለውጥ አልባ ቀደምት ማኅበረሰቦች (Static Societies) ሲሆኑ የጽሑፍ ስልጣኔ የሌላቸው በመሆኑ ስርዓተ አምልኳቸው ቀዳሚ የሕግጋት ምንጭ በመሆን ያገለግላል። በእነዚህ ማኅበረሰቦች ዘንድ ዘውዳዊ ውሳኔዎች በአጠቃላይ በንጉሱ ርህራሄ እና ጥበብ ላይ የተመሠረቱ ሲሆን ባህል እና ልማዳዊ ሕግጋት ከዚህ ቀጥሎ ይዳብራል። በመጨረሻም የመሳፍንቱን፣የነገስታቱን እና የሕዝቡን የሥነ-ሕግ ታሪክ በሕግ ድርሳናት ተሰንደው እንዲቀመጡ ያደርጋል። ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ተራማጅ ማኅበረሰቦች ሲሆኑ በሕግ እና ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ ያለው ለውጥ ባልታቀደ መልኩ በሚፈፅም ለውጥ ሳይሆን ታስቦ በሚደረግ ምህንድስና ነው። ሕግ አውጪዎቹ እና ባለሙያዎቹ ፍትሕ እና እኩልነት ለማስፈን በሚል የሚፈጥሩት ስርዓት ነው።

ምዕራፍ አራት

ማኅበረሰባዊ ውል እና የግለሰብ ነፃነት

ሕግ ከማኅበረሰባዊ ሞራል እና ልማድ ጋር የጠበቀ ቁርኝት እንዳለው ሁሉ ከፖለቲካዊ ፍልስፍናዎች ጋርም ትይዩ የሆነ እድገት እና ቅርበት ያለው ድንበርተኝነትን ይጋራል። ከሰው ልጆች የቅድመ ታሪክ ዘመን ጀምሮ ያለው የሕግና ሞራል ትስስር ብንመረምር ማኅበረሰባዊ ሞራል ለመንግሥት ሕግጋት መንገድ ጠራጊ በመሆን አገልግሏል። በዘመናዊ መንግሥታት ምስረታ ደግሞ ፖለቲካዊ ርእዮተ ዓለም እና ፍልስፍና ለሕጎች እና አዋጆች አቅጣጫ ጠቋሚ በመሆን እያገለገለ ይገኛል። አሁን ባለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን የትኛውም መንግሥት የሚያወጣው ሕግ የሚከተለው ፖለቲካዊ ፍልስፍና ነፀብራቅ ነው። ከዚህም አልፎ ሕግጋት የፖሊሲ እና የፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም ማስፈፀሚያ መሣሪያ እንደሆኑ ተደርጎ ይታሰባል። በታሪክ ውስጥ የሁለቱ እድገት አቻነት ያለው በመሆኑ ፍጹም በሆነ መንገድ አንድነታቸውን እና ልዩነታቸውን ሰንጥቀን ማሳየት አንችልም።

በተወሰኑ ሁኔታዎች ፖለቲካዊ ርዕዮት የሆነው ሐሳብ የሕግ ፍልስፍና በመሆንም ሊያገለግል ይችላል። እንደዚህ ዓይነት የጠበቀ ትስስር በሌሎች የፍልስፍና ዘርፎችም መታየቱ የተለመደ ነው። ለምሳሌ በሃይማኖት ፍልስፍና ወይም ሥነ-መለኮት እና በዲበአካላዊነት ፍልስፍና (Metaphysics) መሀከል የሐሳብ መወራረስን ልንገነዘብ እንችላለን። ይህም ብቻ ሳይሆን ስለ ሕግ ፍልስፍና የተመራመሩ ሰዎች እና ስለ ፖለቲካዊ

ፍልስፍና የተመራመሩ ሰዎች በአብዛኛው አንድ ዓይነት ናቸው። የጆን ሎክ ማኅበረሰባዊ ውል (social contract) ፤ የቶማስ ሆብስ ሕገ-አራዊት (state of nature) እና የስቲዋርት ሚል "የነፃነት" ሐሳብ በአብዛኛው እንደ ፖለቲካዊ ፍልስፍና የሚታዩ ቢሆንም ከእነዚህ ፍልስፍናዎች መፀነስ በኃላ የተነሱ የሕግ ፍልስፍናዎች፤ ምርምሮች፤ የታወጁ ሕግጋትን የተላለፉ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች በእነዚህ ፍልስፍናዎች ተዕዕኖ ስር የወደቁ ናቸው።

ሕግና ፖለቲካዊ ፍልስፍናዎች የሚጋሯቸው ባህሪያት እጅግ ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ በዚህ አጭር ፅሑፍ ብቻ ግንኙነታቸውን ሙሉ በሙሉ ማሳየት አንችልም። በመሆኑም አንድ ማነፃፀሪያ መስፈርት ማኅበረሰባዊ ውል (social contract) ነው። በዘመናዊ የመንግሥታት ታሪክ ውስጥ ማኅበረሰባዊ ውል የዜጎችን እና የመንግስታትን መብትና ግዴታ ከመደንገግ እና ከማብራራትም አልፎ እንደ ሕግም እንደ ፖለቲካዊ ሰነድም ሊታይ የሚችል ፅንሰ ሐሳብ ነው። እንደ ፖለቲካዊ ፅንሰ ሐሳብ የሚታየው ዜጎች ከመንግስታቸው የሚፈልጉትን መብት እና ጥቅም እንዲሁም የራሳቸውን ግዴታ አስፍረው የሚተማመኑበት የቃል ኪዳን ሰነድ በመሆኑ ነው። ይህ ውል በአንዳንድ ሁኔታ ሀገረ- መንግስትን የሚመሠርት ሲሆን በሌላ ሁኔታ ደግሞ ሀገረ-መንግስትን የሚያፀና ነው። ስለዚህ በአንድ ሀገር ያሉ ዜጎች እና የፖለቲካ ሃይላት የሚወዳደሩበትን፤ የሚተዳደሩበትን እና መብት የሚፈጥሩበትን ስርዓት ያስቀምጣል።

ይህ ማኅበረሰባዊ ውል ሕግ እንደመሆኑም በሕግ አዋቂዎች እና ምሁራን የሚብራራ፤ የሚተረጎም፤ ተጠቅሶ ውሳኔ የሚሰጥበት የሚሻሻል እና የሚሻር ነው። በተለምዶ ማኅበረሰባዊ ውል እንደሆነ ተደርጎ የሚወሰደው ሕገ-መንግስት እንደመሆኑ እንደ ማንኛውም ሕግ በባለሙያዎች የሚተረጎም እና የሚብራራ መሆን አለበት እንጂ አንዴ ከፀደቀ በኃላ ሳይነካ የሚቀመጥ ቅዱስ መፅሐፍ አይደለም። በመሆኑም የዚህ የማኅበረሰባዊ ውል ፅንሰ ሐሳብ መነሻ የሆኑትን ፈላስፎች ሐሳብ መዳሰስ ያስፈልገናል። ምክንያቱም በዚህ ውል አስፈላጊነት፤ አስገዳጅነት፤

የተዋዋይ ወገኖች ባህሪ፤ አስቻይ ሁኔታዎች እና መሰል ሁነቶች ላይ የተለያዩ ፈላስፎች የተለያየ ዓይነት አመለካከት አዳብረዋል። በመሆኑም የዚህ ውል ይዘት፤ ቅርፅ እና የሚሸፈነው ስፋት በብዙ ይለያያል።

በመሠረቱ ማኅበረሰባዊ ውል (Social contract) የፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም ፅንሰ ሐሳብ ቢሆንም የውል ሕግ አለባውያንም አሉበት። ውል ሲባል በቅድሚያ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው የውል ሕግ፣ ተዋዋይ ወገኖች፣ ምስክር እና ፊርማ የመሳሰሉት ሐሳቦች ናቸው። በፖለቲካው ዓለም ያለው ማኅበረሰባዊ ውልም ቢሆን እነዚህን መሠረታዊ የውል ሕግ ፅንሰ ሐሳቦችን ከግምት ያስገባ ሲሆን በተለያዩ የማኅበረሰባዊ ውል ፅንሰ ሐሳቦች መሀከል ያለው ክርክር ተዋዋይ ወገኖቹ እነማን ይሁኑ? የውሉ ይዘት ምን ይሁን? ቀድሞውንስ ለምን ውል አስፈለገ? በሚሉት ነጥቦች ላይ ነው። ሁሉም ግን ውል እንደሚያስፈልግ ስለሚተማመኑ፣ ውል ምንድነው የሚለውን ጥያቄ መመለስ ግድ ይላል።

ውል በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መሀከል አንድ ግዴታን በመወጣት በተመላሽ የተወሰነ ጥቅም ለማግኘት የሚደረግ ህጋዊ እና ሞራላዊ ስምምነት ነው[38]። በመሆኑም አንድ ውል ማሟላት የሚገባው ነጥቦች አሉ፣ ከእነዚህም አንዱ የውሉ ይዘት ህጋዊ እና ሞራላዊ መሆን አለበት ይህም ማለት ተዋዋዮቹ ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የሚስማሙበት ጉዳይ ከማኅበረሰቡ እና ከተፈጥሯዊ ሥነ-ምግባር ጋር የሚጋጭ መሆን የለበትም። የውሉ ይዘት ከመንግስት ሕግጋት ጋር የሚጋጭ ከሆነ ህጋዊ በሆነ ፍርድ ቤት አቅርቦ ለማስፈፀም የማይቻል ብቻ ሳይሆን የሦስተኛ

38 በጥቅል አነጋገር ውል ስምምነት ቢሆንም ከሌሎች ስምምነት የሚለየው ለአፈጻጸሙ ከበስተጀርባው የህግ ድጋፍ ያለው ስምምነት እመሆኑ ላይ ነው። ተዋዋዮቹ በቅድሚያ አንድ ተለይቶ የታወቀ ፍሬ ነገርን በተመለከተ ሐሳብ ለሐሳብ ይለዋወጣሉ፤ሐሳብ ለሐሳብ ይገናኛሉ፤ በመቀጠልም የተግባቡትን ፍሬ ነገር ለማከናወን ወይም ከማከናወን ለመቆጠብ በመስማማት ውለታ ይፈጽማሉ፤ በዚህ ስምምነታቸውም ይገደዳሉ።
(ረ/ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ፤ የውል ህግ መሰረት ሃሳቦች ፤ አአዩ መጻህፍት ማዕከል ፤ ሶስተኛ ዕትም፤ ዘ1999፤ ገጽ 14)

ወገንን መብት የሚጋፋ በመሆኑ ከጅምሩም ውድቅ መሆን ይኖርበታል። ሌላው ውሉ የሚቻል መሆን አለበት ምክንያቱም አንድ ተዋዋይ ለመፈፀም የሚያዳግት ነገር ለማድርግ ሊስማማ አይችልም።

ከሁሉም በላይ መሠረታዊ የሆነው ነጥብ በተዋዋይ ወገኖች መሀከል ፍጹም ፍቃድ መኖር አለበት። አንዱ ተዋዋይ ወገን በኃይል ተገዶ ወይም በሌላኛው ወገን ተታሎ ወደ ውል መግባት የለበትም። ውሉ በሚፈፀምበት ወቅት ተዋዋይ ወገኖች ውል ለመፈፀም የሚያስችል እድሜ ላይ የደረሱ፣ በህመም ወይም በእርጅና የአእምሮ ብቃታቸው ያልተሰናከለ መሆን ይኖርበታል። በተዋዋይ ወገኖች መሀከል ያለመግባባት ቢፈጠር ውሉ በምን መርህ ይተርጎም? እነማንስ ይተርጉሙት? የሚለው ነጥብም የውል ሕግ ማዕዘን ነው። ከዚህ በተረፈ የውሉ ቅርፅ እና የአፈፃፀም ሁኔታ ለተዋዋይ ወገኖች ነፃነት የተተወ በመሆኑ ከፈለጉ በቃል አልያም በጽሑፍ የስምምነታቸውን ይዘት ሊያሰፍሩት ይችላሉ።

እነዚህ የውል ሕግ መሰረታውያን ሐሳባዊ እና ምናባዊ ለሆነው የፖለቲካል ሳይንስ ፅንሰ ሐሳብ በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ሊውሉ ይችላሉ፣ እንዲያውም የክርክሮቹ ምንጮች እና መዘውሮች በአብዛኛው በእነዚህ ነጥቦች ላይ ያተኮሩ በመሆኑ የተለያዩ የማኅበረሰባዊ ውል ትርክቶችን ስናነብ እንደ ማንፀሪያ ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ለምሳሌ የውሉን ይዘት በተመለከተ ሆብስ ተዋዋይ ወገኖች ፍጹም በሆነ መንገድ የመታዘዝ ግዴታ እንዳለባቸው እና ሌዋታኑም ፍጹም በሆነ መንገድ ሉዓላዊ እንደሆነ ሲገልፅ ጆን ሎክ ግን የተፈጠረው መንግስት ፍጹም ሉዓላዊ ሳይሆን የተዋዋይ ወገኖች ታዛዥ መሆኑን ስለሚገልፅ በሁለቱ መንግስታት መሀከል ያለው የተዋዋይ ወገኖች ግዴታም እንዲሁ እንደሚለያይ መገመት ይቻላል።

ሕገ - አራዊት - ቶማስ ሆብስ

‘‘ የተጎሳቆለ ፤ አስከፊ ፤ ያልሰለጠነ እና እጅግ አጭር ሕይወት ’’

በእንግሊዝ ከነበሩ ታላላቅ ፈላስፋዎች መሀከል የሚመደበው ቶማስ ሆብስ (1588-1679) ዘመን ተሻጋሪ የሆነው ድርሳኑ ለብዙ የማኅበረሰባዊ ሳይንስ ጥናቶች መሠረት ሆኗል። ሆብስ በወቅቱ በእንግሊዝ ሀገር ውስጥ የነበረውን የእርስ በእርስ ጦርነት እና የመንግስት መዳከም ስለተመለከተ የእርስ በእርስ ጦርነትን ከሚጋብዝ መንግሥት የተሻለ መንግሥት ለመገንባት ምን ዓይነት ንድፈ ሐሳብ ያስፈልጋል ለሚለው ጥያቄ የራሱ ፍልስፍናን አስቀምጧል። ሆብስ በቅድሚያ መንግስት እና ሕግ በሰው ልጅ መሀከል ባይኖር ምን ሊፈጠር ይችላል? በማለት ይጠይቅና ራሱ በሚሰጠው መልስ የሚፈጠረው ክፍተት ሕገ-አራዊትን (State of nature) እንደሚፈጥር ያስረዳል።

በዘመኑ- አራዊት ሰዎች ከሰውነት በታች ይወርዳሉ። መንግሥት ባለመኖሩ ሁሉም ደስ ያሰኘውን ያለ ከልካይ ይፈፅማል፤ በሞራል እና ሕግ የማይገዛ ማኅበረሰብ በመፈጠሩ ግለሰቦች በራሳቸው ሕግ ተመርተው ያሻቸውን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ ከመሯሯጥ በስተቀር የሚገዙበት ቆስቋሽ ምክንያት የላቸውም በሕግ የተደራጀ ማኅበረሰብ ባለመኖሩ ባህል፣ ሳይንስ፣ ሥነ-ጥበብ የጊዜ እና የቦታ ንቃተ ህሊና አይኖርም። በመሆኑም የግለሰብ ሕይወት የተነጠለ፤ የተጎሳቆለ፤ አስከፊ፤ ያልሰለጠነ እና እጅግ አጭር ይሆናል።

> Whatsoever therefore is consequent to a time of War, where every man is Enemy to every man; the same is consequent to the time, wherein men live without other

> security, than what their own strength, and their own invention shall furnish them withall. In such condition, there is no place for Industry; because the fruit thereof is uncertain: and consequently no Culture of the Earth; no Navigation, nor use of the commodities that may be imported by Sea; no commodious Building; no Instruments of moving, and removing things as require much force; no Knowledge of the face of the Earth; no account of Time; no Arts; no Letters; no Society; and which is worst of all, continual fear and danger of violent death; **And the life of man solitary, poore, nasty, brutish, and short.**[39]

በዚህ አስከፊ ምናባዊ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የራሳቸውን ጥቅም በጉልበት የሚያስጠብቁ እንደመሆናቸው በማያባራ ጦርነት ውስጥ ለመኖር ይገደዳሉ። በመሆኑም በሕገ-አራዊት ውስጥ ያሉ ሰዎች በጦርነት ውስጥ ለመኖር ከመገደዳቸውም አልፎ ይህ ጦርነት ሁሉም በሁሉም ላይ ያወጀው ጦርነት እንደመሆኑ በቀላሉ ሊገታ የማይችልና አስከፊ እንደሚሆን ያስታውቃል። ሁሉም ሰው የሁሉም ሰው ጠላት ይሆናል። ሰዎች ከራሳቸው ጥንካሬ እና ፈጠራ ውጪ ያለ ምንም ጥበቃ ሲኖሩ የሚመጣውም እንዲሁ ነው። በእነዚህ ሁኔታዎች ለኢንዱስትሪ ቦታ የለም፤ ምክንያቱም ስለ ምርት እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ይህንን ተከትሎም ምድር አትለማም፣ የባህር ኃይልም ሆነ በባህር የሚመጡ እቃዎች አይኖሩም፣ ምቹ የሆኑ ህንፃዎች፣ የመጓጓዣ መሣሪያዎች፣ ስለ ምድር ገፅታ ያለ እውቀት፣ የጊዜ ገላጮች፣ ሥነ-ጥበብ፣ ፊደላትም ሆኑ ማኅበረሰብ በሙሉ አይኖሩም። ከዚህ ሁሉ አስከፊው ግን በማያቋርጥ ፍራቻ እና የአሰቃቂ ሞት ስጋት ውስጥ መኖር ነው። የሰው ልጅ ሕይወትም የብቸኝነት፣ የድህነት፣ የጭካኔ በመሆኑ አጭር ይሆናል። የሉዓላዊው ስልጣን ባለቤት ንጉስም ይሁን

39 Thomas Hobbes, Leviathan, The First Part, Chapter 13, p. 62

ሌላ፤ሉዓላዊ ስልጣኑ በአደራ የተሰጠው የተፈጥሮ ሕግ ግድ የሚለውን የህዝቦች ደህንነት እንዲያስገኝ እንዲሁም ለሕጉ ደራሲ ለሆነው ፈጣሪ ብቻ ተጠያቂነቱን እንዲያሳይ ነው። ደህንነት ስንል ግን አካላዊ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ማንም ሰው ህጋዊ በሆነ ሥራ፣ ሪፐብሊኩ ላይ አደጋ እና ጉዳት ሳያደርስ ለራሱ የሚያካብታቸውን እርካታዎች ያካትታል።

ይሁን እንጂ ሰዎች በሕገ አራዊት ተመርተው ከሰውነት በታች ወርደው ተራቆቱ እንጂ የአመክንዩ ጥበባቸውን ያልረሱ በመሆናቸው አንዳንዶች የሰው ልጆች በሰላም እና በተረጋጋ ሁኔታ መኖር እንዳለባቸው ሰው በመሆናቸው ብቻም በተፈጥሮ የታደሉት የማይገረሰስ፤ የማይነጠል እና የማይለወጥ የከበረ መብት እንዳላቸው ለመገንዘብ ይገደዳሉ። በዚህ አባባሉ ምክንያት ብዙ ሰዎች ቶማስ ሆብስ የተፈጥሮ ሕግ ፈላስፋናን ይደግፋል ወይም ይከተላል በማለት ይከራከራሉ። በሕገ-አራዊት መኖር የሰለቻቸው እነዚህ ሰዎች የራሳችንን መብት እና ጥቅም የሚያስጠብቅ አንድ "ሉዓላዊ አካል" መፍጠር አለብን በማለት መስማማት ላይ ይደርሳሉ። ይህ የጋራ ስምምነት ወይም ማኅበራዊ ውል ይህን ሉዓላዊ አካል ይፈጥራል። በመሆኑም ሉዓላዊነት የተሰጠ እንጂ የተገኘ አይሆንም። ይህን ሉዓላዊ አካል ለመፍጠር ሰዎቹን ያነሳሳቸው ዋነኛ ምክንያት ፍርሃት ነው።

> The office of the sovereign, be it a monarch or an assembly, consisteth in the end for which he was trusted with the sovereign power, namely the procuration of the safety of the people, to which he is obliged by the law of nature, and to render an account thereof to God, the Author of that law, and to none but Him. But by safety here is not meant a bare preservation, but also all other contentments of life, which every man by lawful industry, without danger or hurt to the Commonwealth, shall acquire to himself[40].

40 Ibid, P 178

በዘመነ- አራዊት ውስጥ የሚኖር ሰው ድንገትና ባልጠበቀው ሁኔታ በሌላ ግለሰብ ጥቂት ሊደርስበት እና ጥቀቱን ያደረሰበትም ሰው ያለ ምንም ቅጣት ሊኖር ይችላል። በመሆኑም ይህን "ሉዓላዊ አካል" በስምምነት ወይም ውል የፈጠሩ ሰዎች ራሳቸው በዘመነ-አራዊት ሲኖሩ ከታደሉትና የፈለጉትን ነገር በፈለጉት ሰው ላይ እና በፈለጉት ጊዜ የማድረግ እንስሳዊና ያልተገደበ መብት ቀንሰው ለዚህ በትብብር ለፈጠሩት ሉዓላዊ አካል ይሰጡታል። ይህ ሉዓላዊ አካልም በተራው የእነዚህን ተዋዋይ ወገኖች መብት እና ሕይወት የመጠበቅ ግዴታ ይጣልበታል።

ሆብስ ይህ የተፈጠረውን ሉዓላዊ አካል **"ሌዋታን"** ሲል ይጠራዋል። ሌዋታን በአፈ ታሪክና በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚታወቅ አስፈሪ የባህር ውስጥ አውሬ ነው። ይህንን ስዕል መሳል የፈለገው ይህ ሉዓላዊ አካል ከተፈጠረ በኃላ በተዋዋይ ወገኖች ፍጹም የሆነ ታዛዥነት ሊኖረው እና ስልጣኑም ፍጹም መሆን እንዳለበት ለማሳየት ነው። የዚህ ፍፁማዊ ስልጣን መብት ጉዳይ ብዙ ሰዎችን አያስማማም እንዳንዶች እንዲያውም ሰዎች ሌላ ሰውን በመፍራት በውል የፈጠሩት አካል በሚደርስባቸው ፍርሃት አዘል አገዛዝ ስር ከወደቁ አንድን መጥፎ ነገር በሌላ መጥፎ እንዳመተካት ነው ሲሉ ይከራከራሉ።

ሌዋታኑ "ፍጹም ሉዓላዊ አካል" እንደመሆኑ ሕግ የማውጣት፤ ሕግ የመተርጎም እና ሕግ የማስፈፀም ፍፁማዊ ስልጣን አለው። በመንግስቱ ስር ለሚኖሩ ተዋዋይ ወገኖች የሚሰጠውን ትእዛዝም ዜጎች ፍፁማዊ በሆነ መንገድ ሊከተሉት እና ሊታዘዙት ይገባል። ይህ ጉዳይ ፍልስፍናውን ከሕገ-ሰብ ፍልስፍና ጋር ያመሳስለዋል። ጆን ኦስቲን የዚህን የሕግ ፍልስፍና መሠረት ሲጥል "ሕግ ማለት ከሉዓላዊ አካል የተሰጠ ትእዛዝ ነው" በማለት እንደደመደመ ማስታወስ አለብን። ምንም እንኳ የኦስቲን እና የሆብስ "ሉዓላዊ አካላት" በፍልስፍናዊ የንድፈ ሐሳብ አመሠራረታቸው እና በሚያስገኙት ውጤት እጅግ የተለያዩ ቢሆኑም ሁለቱም ሕግ የሉዓላዊ አካል ትእዛዝ መሆኑን ይስማማሉ። በመሆኑም የሆብስ ፍልስፍና ከተፈጥሮ ሕግ

ፍልስፍና እና ከሕገ-ሰብ ፍልስፍና ጋር የሚጋራው እና የሚያመሳስሉት ነገሮች እንዳሉት መገንዘብ ይኖርብናል።

ከዚህም በተጨማሪ ሆብስ ቀዳሚ የሆነውን የማኅበራሰባዊ ውል (ፍልስፍና) የጠነሰሰ እንደሆነ ይነገራል። ምክንያቱም በሕገ-አራዊት የሚመሩት ሰዎች ሌዊታኑን ወይ ሉዓላዊ አካሉን የሚፈጥሩት በጋራ በሚያደርጉት ስምምነት ነው። ይህን ስምምነት አንድ ማኅበረሰባዊ ውል አድርገን ልንወስደው ይገባል። ሆብስ ያሰበውን መሠረታዊ ውል በኃላ ላይ የማኅበረሰባዊ ውል ፈላስፎች አዳብረው እና አስፋፍተው የዘመናዊ መንግስት መመስረቻ እና መተዳደሪያ ፅንሰ ሐሳብ እንዲሆን አድርገውታል። የአንድ ሀገር ዜጎች በፍርሃት አማካኝነት ለተፈጠሩበት የደህንነት ስጋት መብታቸውን የሚያስጠብቅላቸው አንድ ሉዓላዊ ተቋም ቢፈጠተሩም ይህ አካል የዜጎቹን ደህንነት ከማስጠበቅ በዘለለ በዚያው ውል አማካኝነት ተጨማሪ ግዴታዎች፤ መብቶች እና ኃላፊነቶች ሊጣሉበት ይችላል።

ሕዝባዊ ፍቃድ - ዣን ዣክ ሩሶ

"ሕዝባዊ ፍቃድ የሕዝቡ ኡዓላዊነት መገለጫ ነው"

ሩሶ (1712-1778) የፈረንሳይ አብዮት የመንፈስ አባት፣ ታላቁ የዘመነ አብርሆት ተመራማሪ በመባልም ይታወቃል። የፈረንሳይ አብዮተኞች የእርሱን ፍልስፍናዎች እና አስተምህሮዎች አብዮቱን ለማቀጣጠል ተጠቅመውባቸዋል። ሩሶ ጄኔቫ ውስጥ ተወልዶ ያደገ ቢሆንም የሞተው ፈረንሳይ ውስጥ ነው። ሥራዎቹ ከፖለቲካ ፍልስፍና እስከ ትምህርት ፍልስፍና ፤ ከሙዚቀኝነት እስከ የፈጠራ ጽሁፍ ባለሙያነት ድረስ የተስፋፉ ናቸው። ሩሶ ከደረሳቸው መጻህፍት መሀከል አንደኛው ርዕሱ ራሱ ማኅበረሰባዊ ውል "Social Contract" የሚል ነው።

በዚህ ድርሳኑ ከእርሱ ቀድሞ የነበረውን ቶማስ ሆብስን ክፉኛ ይተቻል። በእርሱ አስተያየት ሆብስ በሕገ አራዊት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን እንደ አረመኔ አራዊት ፤ ማገናዘብ የማይችሉ፤ ራስ ወዳድ እና ጨካኝ አድርጎ መላሉ ስህተት መሆኑን ይጠቅሳል። ሩሶ ይህንን ቅድመ መንግስት ተምኔታዊ ሁኔታ ሕገ-አራዊት የሚሰፍንበት ሳይሆን ሕገ-ተፈጥሮ የሚገዛበት እንደሆነ ይናገራል። በሕገ-ተፈጥሮ ውስጥ ደግሞ ሰዎች ከእውነተኛ ማንነታቸውና ከተፈጥሮ ጋር ሰለሚዋሀዱ ነፃ ፤ አስተዋይ እና ደግ እንደሚሆኑ ይከራከራል። በመሆኑም ለሰዎች የተሻለው ነገር በዚህ ዓይነት ምናባዊ ሁኔታ ውስጥ መኖር ነው።

ይህ በሕገ-ተፈጥሮ ውስጥ የሚኖር ግለሰብ ቀጣዩ ሰብዓዊ የእድገት ደረጃ መንግስት መመስረት መሆኑን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሲረዳ ተሰባስቦ ማኅበረሰባዊ ውል በመመስረት መንግስት ያዋቅራል። ይህ ማኅበረሰባዊ ውል የተዋዋይ ወገኖች አጠቃላይ ስምምነት ያለበት በመሆኑ ሕዝባዊ ፍቃድ (General will) በመባል ይታወቃል። ይህ ሕዝባዊ ፍቃድ የሕዝብ ሉአላዊነት መገለጫ እንደመሆኑ ሕግ አውጪው፤ፈጻሚው እና ተርጓሚው ሳይሸራርፉ ሙሉ ለሙሉ ሊያስፈጽሙት ይገባል።

> Robespierre's ideas were derived from his close study of Rousseau, whose theory of the general will formed the intellectual basis for all modern totalitarianisms. According to Rousseau, individuals who live in accordance with the general will are "free" and "virtuous" while those who defy it are criminals, fools or heretics. Those enemies of the common good must be forced to bend to the general will. He described this state-sanctioned coercion in Orwellian **terms as the act of "forcing men to be free." It was Rousseau who originally sanctified the sovereign will of the masses**

> **while dismissing the mechanisms of democracy as corrupting and profane. Such mechanics -- voting in elections, representative bodies, and so forth -- are "hardly ever necessary where the government is well-intentioned," wrote Rousseau in a revealing turn of phrase**[41].

የሮብስፒር ሐሳቦች የተገኙት የሩሶን የሕዝባዊ ፍቃድ ፅንሰ ሐሳብ በቅርበት በማጥናት ነው። እንደ ሩሶ ከሆነ ከሕዝባዊ ፍቃድ ጋር ስምሙ ሆነው የሚኖሩ ግለሰቦች "ነፃ" እና "ምግባራዊ" ሲሆኑ ሕዝባዊ ፍቃድን የሚጥሱት ግን ወንጀለኞች፣ ሞኞች እና መናፍቃን ናቸው። የጋራ ጥቅም ጠላቶች ወደ ሕዝባዊ ፍቃድ እንዲያዘነብሉ ሊገደዱ ይገባል። ይህንን በመንግስት የተደገፈ ግዳጅ በኦርዌላዊ ንግግር ዘይቤ ሲያስቀምጠው "ሰዎች ነፃ እንዲሆኑ ማስገደድ" ይለዋል። የዴሞክራሲን አሠራር ብልሹ እና የረከሰ በማለት በማጣጣል የሕዝባዊ ፍቃድን ሉዓላዊነት የደገፈው ለመጀመሪያ ጊዜ ሩሶ ነበር። በምርጫ የመምረጥ፣ ተወካይ አካላት የመሳሰሉት አሰራሮች ቀናነት ባለው መንግስት ስር እምብዛም አስፈላጊነት የላቸውም ሲል ይገልፃል። በሕገ-ተፈጥሮ ውስጥ የሚኖሩት ዜጎች ምንም እንኳ የዘመናዊነት ጸጋን ባይታደሉም በተፈጥሮ የተገኙ መልካም ባህሪያት አላቸው። እንዲያውም በተፈጥሮ ሕግ ስር የሚኖር ግለሰብ በቅድመ ሰው ስልጣኔ አረመኔነት እና በዘመናዊ ስልጣኔ የሞራል እና የማኅበረሰብ ግንኙነት ውድቀት መሀከል የሚገኝ እንደመሆኑ ትክክለኛው የሰውነት መለኪያ እንደሆነ አበክሮ አሳስቧል።

ሩሶ ድርሳኑን የሚጀምረው "Man is born free but is every where in chains." /"የሰው ልጅ ነፃ ሆኖ ተወልዶ በየቦታው ግን በሰንሰለት ተጠፍሯል" በሚለው ዘመን ተሻጋሪ ጥቅስ ነው። ለእርሱ "State of na-

41 Jonah Goldberg (2007). *Liberal Fascism: The Secret History of the American Left from Mussolini to the Politics of Meaning*. NY: Doubleday, p. 39

ture" እንደ ሆብስ "ሕገ-አራዊት" ሳይሆን "ሕገ-ተፈጥሮ" ነው። በዚህ ወቅት ሰዎች ሎክም ሆነ ሆብስ ካሰቡት በላይ በነፃነት እና ደስታ ያሻቸውን እና ልባቸው የወደደውን እያደረጉ ስለሚኖሩ ፍጹም በሆነ ሃሴት እና ክብር ያሉ ናቸው። በመሆኑም ወደ ማኅበረሰባዊ ውሉ የሚገቡት ሆብስ እንደሚለው በተፈጥሮ የነበራቸውን ፍጹም መብት እየቀነሱ ለሉዓላዊ አካል በመገበር ሳይሆን ቀድሞም በተፈጥሮ የነበራቸውን ፍጹም ነፃነት ለማስጠበቅ ነው። በመሆኑም መንግስት የሚፈጠረው የዜጎቹን ነፃነት ለመጨመር እና ለማስጠበቅ እንጂ ለመቀነስ አይደለም። ሉዓላዊ አካል ጉልበት (Power) ሳይሆን ስልጣን (Authority) ስለሚኖረው የስልጣኑ ምንጭ ሕዝባዊ ፍቃድ መሆኑን ሁልጊዜም ማስታወስ አለበት። በተጨማሪም ሰዎች ወደ ማኅበራዊ ውል የሚገቡት ከፖለቲካዊ ተሳትፎ የሚገኘውን ማኅበራዊ ጉድኝት ሃሴት እና ጥቅም ለመቋደስ ነው።

በማኅበራዊ ውል የሚፈጠረው ሉዓላዊ አካል በመሆናቸው የሚፈጥሩት ነው። በዚህ ምክንያት ሩሶ **የሕዝባዊ ሉዓላዊነት** (Popular sovereignity) ቀዳሚ አቀንቃኝ እና የፈረንሳይ አብዮት የመንፈስ አባት እንደሆነም ይናገራል። ሕዝባዊ ፍቃድ የሚመሰረተው እያንዳንዱ ዜጋ ተሰባስቦ የጋራ ጥቅማችን (common good) ምንድነው? በማለት በሚያደርገው ውይይት ነው። ሕዝባዊ ፍቃድ ማለት እያንዳንዱ ግለሰብ የግል ጥቅም ተደምሮ የምናገኘው ሳይሆን የማይነጣጠል የጋራ ጥቅም ለመፍጠር የሚደረግ ጥረት ነው። በመሆኑም በሕዝባዊ ፍቃዱ የማይገዛ በሙሉ በጉልበት ሊገደድ ይገባል። ሕግ አውጪው በሕዝቡ ልማድ እና ወግ ላይ የተመሠረተ ሕግ ሊያወጣ እና ከዚያም በኋላ ከፖለቲካ ተሳትፎ መታቀብ ይኖርበታል። ለሩሶ ዴሞክራሲ ልክ እንደ አቴንስ በህዝቦች ቀጥተና ተሳትፎ የሚመሠረት የሕዝብ አስተዳደር ሲሆን ለሁሉም ህዝቦች ተፈፃሚ ሊሆን የማይቻል የአመራር ዓይነት እንደሆነ ያስገነዝባል።

አሪስቶክራቱ ፈላስፋ- ጆን ሎክ

‘‘የመንግስት ቀዳሚ ተግባር የግል ንብረትን መጠበቅ ነው’’

ጆን ሎክ (1632-1704) በሙያ ክህሎቱ ሃኪም የነበረ ሲሆን ይህንኑ ሙያ በመጠቀም ከእንግሊዝ መሳፍንት እና ንጉሳዊ ቤተሰቦች ጋር በፈጠረው ግንኙነት የመንግስት አሠራርን እና ፖለቲካን በሚገባ ለመገምገም ዕድል አግኝቷል። የጆንሎክ የማኅበረሰባዊ ውል ፍልስፍና ከሆብስ በተለየ ሁኔታ የሰዎችን ባህሪ ይገመግማል። በመንግስት አልባነት ወቅት ሆብስ እንደሚፈራው እና እንደሚተነብየው ሕገ-አራዊት አይሰፍንም፤ ይልቁንም ሰዎች በተፈጥሯቸው መልካም እና በጎ በመሆናቸው መንግስት ባይኖር እንኳ እርስ በእርሳቸው ወደ መጠፋፋት አይሄዱም። ይሁን እንጂ በዚህ ጊዜም ቢሆን በጋራ ወደ መተማመን እና መስማማት በመምጣት መንግስትን ለመፍጠር አይቦዝኑም። መንግስትን ለመፍጠር የሚገቡበት “ማኅበረሰባዊ ውል” ዋነኛ አላማ ግን እርስ በእርስ እንዳይገዳደሉ እና እንዳይጠፋፉ የሚጠብቃቸው አካል ለመፍጠር ሳይሆን ነፃነታቸውን እና ንብረታቸውን የሚያስከብር ከሌላ ሰው ጋር ክርክር ውስጥ ቢገቡ “ነፃና ገለልተኛ ዳኝነት” የሚሰጥ ተቋም ለመፍጠር ነው።

> The state of nature **has a** law **of nature to govern it, which obliges every one: and** reason, which is that law, teaches all mankind, who will but consult it, that being all equal and independent, no one ought to harm another in his life, health, liberty, or possessions[42].

በመሆኑም በዚህ ማኅበረሰባዊ ውል የሚፈጠረው አካል ሆብስ እንደሚለው አስፈሪ “ሌዋታን” ሳይሆን ማኅበረሰባዊ ውሉን የተዋዋሉት ሰዎች ለጋራ ጥቅማቸው ብለው የሚቀጥሩት ሠራተኛ ነው። በመሆኑም

42 John Locke, *Second Treatise of Government*, Ch. II, sec. 6

ምንም እንኳ በተሰጠው ኃላፊነት አማካኝነት ኃይልን የመጠቀም ብቸኛ መብት ቢኖረውም ለሎክ መንግስት ፍፁማዊ አምባገነንነት የተጎናፀፈ አይደለም ሊሆንም አይገባም። በመሆኑም መንግስት ከሕዝቡ በሚሰበስበው ቀረጥ አማካኝነት የሕዝቡን መብት በተለይም የግል ንብረትን የማስጠበቅን የፀና ልዩ እና የማይተካ ሚናውን ሊፈፅም ይገባል ምክንያቱም ንብረት ማፍራት መንግስትን ከመፍጠር ይቀድማል።

ጆን- ሎክ ሰዎች በመሠረታዊነት መልካም እንዲሆኑ ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮ የማይነጣጠሉ እና የማይገረሰሱ መብቶች እንዳሏቸው እና እነዚህም ሕይወት፤ ነፃነት እና ንብረት የማፍራት መብት እንደሆኑ ፅፏል። የጆን ሎክ ጽሑፍ አሜሪካ ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ተላቅቃ የራሷን ሀገረ-መንግስት እና ሕገ-መንግስት እንድታቋቁም ተፅዕኖ አድርጓል ተብሎ ይታሰባል ምክንያቱም የእርሱ ሐሳቦች በአሜሪካ ሕገ-መንግስት ውስጥ ተካትዋል። ጆንሎክ ራሱ የእንግሊዝ መንግስት ባቋቋመው የመሬት ስሪት እና ክፍፍል ኮሚቴ ውስጥ ተሳትፎ መሬትን እየለካ ያካፍል ስለነበረ መንግስት እና ሕዝብ በግል ንብረት ወይም ሀብት ማፍራት እና በማስጠበቅ ላይ ያላቸውን ሚናበግልፅ እና በቅርበት ተመልክቷል። ጆንሎክ ስለ ንብረት የፃፋቸው ሐሳቦች በንብረት ሕግ ፍልስፍና ውስጥ በመርሆነት እና ማስተማሪያነት አገልግለዋል።

> Government has no other end than the preservation of property[43]

ሎክ ሰዎች ንብረት ወይም ሀብት የሚያፈሩት ጉልበታቸውን በተፈጥሮ ከተገኘ ሀብት ጋር ሲያገናኙት እና ሲያዋህዱት መሆኑን ፅፏል። ይህ በተለምዶ The Labor theory of Ownership የሚባል ሲሆን ለሎክ ፈጣሪ የተፈጥሮ ሀብትን ለሰው ልጆ ሁሉ በጋራ እና በእኩልነት የሰጠ በመሆኑ የሰው ልጆች ይህን የተፈጥሮ ሀብት የግላቸው ለማድረግ የግላቸው መሆኑን

43 Ibid, Ch. VII. sec. 94

እርግጠኛ ከሆኑበት የራሳቸው ጉልበት ጋር ሊያዋህዱት ይገባል፤ ሰዎች ወደ ግላቸው ሊያዞሩት የሚገባው ሀብትም ለማኅበረሰቡ አገልግሎት ሠጥቶ ከተረፈው ላይ ብቻ ነው፡፤ በመሆኑም ሰዎች ተሰባስበው የሚፈጥሩት ይህ ማኅበረሰባዊ ውል ሕይወታቸውን እና ነፃነታቸውን ከመጠበቅ አልፎ የልፋታቸው ውጤት የሆነውን የግል ሀብት ሊጠብቅላቸው ይገባል።

> If man in the state of nature be so free, as has been said; if he be absolute lord of his own person and possessions, equal to the greatest, and subject to no body, why will he part with his freedom, this empire, and subject himself to the dominion and control of any other power?[44]

በመሆኑም ሰዎች ማኅበረሰባዊ ውል የሚመሠረቱት ለሕይወታቸው በመስጋትና በፍርሃት በመጠርነፍ ሳይሆን አስቀድሞም ቢሆን በተፈጥሮ ያገኙት የማይነጠል እና የማይገረሰስ መብት የሚጠብቅ ሰራተኛና አገልጋይ ለሥራው ኃላፊ እና ተጠያቂ የሚሆን መንግስት ለመመሠረት ነው።

ጆን ሎክ ሃይማኖተኛ ሰው እንደመሆኑ "ሕገ-አራዊት" የሚለው ሐሳብ "ሕገ-ተፈጥሮ" የሚገዛው የቅድመ ዓለም ዓይነት ቦታ እንጂ ሰዎች እርስ በእርሳቸው የሚባሉበት ዓይነት አይደለም። አዳም እና ሄዋን በገነት ሳሉ የሚኖሩባት ዓይነት ዓለም ሰዎች ሁሉ በእኩልነት እና በነፃነት የሚኖሩባት ዓለም ናት። ለተፈጥሮ ሕግ እና ለአመክንዮ የሚገዙ ሰዎች እርስ በእርሳቸው የማይጎዳዱ እና የሚከባበሩ የጋራ መተማመኛ ሰነድ የሆነ ሕግ ወይም ውል ለማርቀቅ ለምን አስፈለጋቸው/ የመጀመሪያው ሰዎች በራሳቸው ጉዳይ አድሏዊ እንዳይሆኑ ለሁሉም የሚያገለግል ሕግ ያስፈልጋል የሚል ነው። ሎክ የተፈጥሮ ሕግ የሚለው ከመለኮት ሕግ ጋር ተመሳሳይ ለመሆኑ እንደሚያምን የሚያሳየው ከጊዜው አስተሳሰብ ባፈነገጠ

44 Ibid, Ch. IX, sec. 123

መልኩ ባርነትን የሚቃወም በመሆኑ ነበር። ይሁን እንጂ ሎክ ባርነትን እና የባሪያ ንግድን እየተቃወመ ከባሪያ ንግድ ጋር ጥብቅ ግንኙነት ካላቸው ኩባንያዎች ጋር ይሰራ ነበር። በተለያዩ ሰፋፊ እርሻዎች እና ምርቶች ከሚያገኘው ገቢ የተነሳ የግል ሀብት ማፍረትን እጅግ መደገፍ ብቻ ሳይሆን የሕግ ዋነኛ አላማ እንዲሆንም ይፈልግ ነበር።

የሰው ልጆች ሁሉ ጉልበታቸውን በተፈጥሮ ከሚገኝ ሀብት ጋር ሲያዋህዱት የግል ሀብት ያፈራሉ፤ለምሳሌ አንድ ግለሰብ በጫካ ውስጥ እየሄደ ትልቅ ዛፍ ላይ የተንጠለጠለ ፍሬ ሲመለከት እጁን ዘርግቶ ማለትም ጉልበቱን አውጥቶ ሲያወርደው የራሱ የግል ሀብት ያደርገዋል። ይህ እንዲሚላ ግን የተፈጥሮ ሀብቱ እጥረት የሌለበት እና የግል ሀብት የምናደርገውም ተትረፍርፎ የሚበላሽ መሆን የለበትም። ገንዘብ ግን በብዙ ብናከማቸውም የሚበላሽ እቃ ባለመሆኑ የቻልነውን ያህል ልናከማቸው እንችላለን። ማኅበረሰባዊ ውል የሚያስፈልገው ሕጉ የሚታወቅ ቢሆን እንኳ በዚህ ሕግ ያለ አድሎ የሚዳኝ ዳኛ እና ያህንኑ ፍርድም የሚያስፈፅም አካል ባለመኖሩ ነው። በዚህ ውል የሚፈጠረው መንግስት ፍጹም ሉዓላዊ ሊሆን የማይገባው ብቻ ሳይሆን እርሱም እራሱ ከዚህ ማኅበረሰባዊ ውል በታች መሆኑ መረጋገጥ አለበት። ሉዓላዊ መንግስታት በተፈጥሮ ሕግ ላይ የተመሰረተው መንግስት በዝባዥ እና አምባገነን ከሆነ ዜጎች በዚህ መንግስት ላይ የማመፅ ተፈጥሯዊ መብት አላቸው ምክንያቱም አንድ መንግስት ህጋዊ ባልሆነ መንገድ አምባገነን ሲሆን ራሱን ወደ ሕገ-አራዊት ዘመን እየመለሰ በመሆኑ ዜጎች ሚያደርጉት አመፅ ይህንን ወደ ሕገ-አራዊት ዘመን የመመለስ ሂደት የሚቃወም በመሆኑ ህጋዊነት እና ቅቡልነት ያለው ተግባር ነው። ብዙዎች እንደሚምኑት ይህ ሐሳብ የአሜሪካን የነፃነት ትግል የጠነሰሰ ነው።

የፍትሕ ቀመር- ጀን ሮውልስ

‘‘ፍትሐዊ ርትዕ የማኅበረሰባዊ ውል መሠረት ነው’’

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ከተነሱ ጥቂት ፈላስፎች መሀከል ከሮውልስ ጋር በአቻነት የሚቆሙ ጥቂቶች ናቸው። ሮውልስ (1921-2002) በሕግና በፖለቲካ ፈላስፎች የሚታወቀውን የማኅበረሰባዊ ውል (Social contract) ሐሳብ እጅግ ጥልቀት ባለው መልኩ እንዲራቀቅ እና እንዲስፋፋ አድርጎታል። ከ600 ገጽ በላይ በሆነው ድርሳኑ ፍትሐዊ ርትዕ (Justice as fairness) በሚል የሰየመውን የፍትሕ ቀመር ለማብራራት ሞክሯል። ፍልስፍናውን የሚጀምረው የጠቀሜታውያንን የሞራል ፍልስፍና በመተቸት ነው። ጠቀሜታዊ የሞራል ፍልስፍና የግለሰቦችን ልዩ ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ እና ከደስታ በፊት የትክክለኛነትን ጥያቄ የማይመለስ ነው። አንድ ድርጊት ለሰፊው ሕዝብ መጠነ ሰፊ ደስታ ያመጣል ተብሎ ከመታሰቡ በፊት ለአንድ ግለሰብ ደስታ እንደሚያመጣ እርግጠኛ መሆን አለብን። ከዚያም አልፎ ግለሰቡ ደስታን ያመጣው ድርጊት ያስገኘለትን የእርካታ ደረጃ ከመለከታችን አስቀድሞ ትክክለኛነቱንና ቀናነቱን መለካት ይኖርብናል።

> Justice is the first virtue of social institutions, as truth is of systems of thought. A theory however elegant and economical must be rejected or revised if it is untrue; likewise laws and institutions no matter how efficient and well-arranged must be reformed or abolished if they are unjust. Each person possesses an inviolability founded on justice that even the welfare of society as a whole cannot override. For this reason justice denies that the loss of freedom for some is made right by a greater good shared

> by others. It does not allow that the sacrifices imposed on a few are outweighed by the larger sum of advantages enjoyed by many. Therefore in a just society the liberties of equal citizenship are taken as settled; the rights secured by justice are not subject to political bargaining or to the calculus of social interests[45].

እውነት የሐሳብ ስርዓት ምግባር እንደሆነ ሁሉ ፍትሕም የማኅበረሰባዊ ተቋማት ቀዳሚ ምግባር ነው። አንድ ሐሳብ ድንቅ ቢሆን እንኳ እውነትነት ከሌለው አለመቀበል ወይም ማሻሻል ይኖርብናል። ሕጎች እና ተቋማትም እንዲሁ ቀልጣፋ እና በደንብ የተደራጁ ቢሆኑ እንኳ ፍትሐዊ ካልሆኑ ሊከለሱ ወይም ሊሻሩ ይገባል። እያንዳንዱ ግለሰብ ማኅበረሰብ ራሱ በጥቅሉ የማይገረሰሰው በፍትሕ ላይ የተመሰረተ የማይጣስ መብት አለው። ስለዚህም ፍትሕ የአንዳንዶች ነፃነት ማጣት በብዙኃኑ መጠቀም ይካካሳል የሚለውን አይቀበልም፤ በአንዳንዶች ላይ የተጣለ መስእዋትነት ብዙዎች ከሚያጣጥሙት ደስታ በላይ እንዲያመዝን አይፈቅድም። ስለዚህ ፍትሐዊ ማኅበረሰብ ውስጥ የእኩል ዜግነት ነፃነቶች የማይለወጡ በመሆናቸው በፍትሕ የተረጋገጡት መብቶች ለፖለቲካ ቁማር እና ለማኅበረሰብ ጥቅም ስሌት አይውሉም።

የሮውልስ ፍትሐዊ ርትዕ መሠረታዊ በመሆነ መልኩ ከማኅበረሰባዊ ውል ፅንሰ ሐሳብ ውስጥ የሚፈልቅ ነው። ይሁንና የዚህን ማኅበረሰባዊ ውል ይዘትና ቅርፅ ከመወያየታችን በፊት ይህን ውል ከጥንታዊ መሠረቱ ጀምሮ እንዬት፤ ለምን እና እነማን ተዋዋሉት የሚለው ጥያቄ አንገብጋቢ በመሆኑ ሊመለስ ይገባዋል። ይህ ውል ሳይፈፅም በፊት ያለውን ምናባዊ አሰላለፍ **“ቀዳማዊ ሁኔታ”** (orginal position) ብንለው በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ተዋዋይ ወገኖች ያሉበት አቋም እና ማንነትም መታወቅ ይኖርበታል። በዚህ “ቀዳሚዊ ሁኔታ” ያሉ ተዋዋይ ወገኖች ግለሰባዊ የማንነት መሠረታቸውን

45 John Rawls, A Theory of Justice, Chapter I, Section 1, pg. 3-4

እንዳይረዱ “የመርሳት ሽፋን” (veil of Ignorance) በሚባል ተግዳሮት ያታቸውን፤ የማኅበረሰባዊ መደባቸውን፤ ሃይማኖታቸውን፤ ብሔራቸውን እና መሠል ማንነታቸውን ከመገንዘብ ተከልክለዋል።

> First of all, no one knows his place in society, his class position or social status; nor does he know his fortune in the distribution of natural assets and abilities, his intelligence and strength, and the like. Nor, again, does anyone know his conception of the good, the particulars of his rational plan of life, or even the special features of psychology such as his aversion to risk or liability to optimism or pessimism. More than this, I assume that the parties do not know the particular circumstances of their own society. That is, they do not know its particular economic or political situation, or the level of civilization and culture it has been able to achieve. The persons in the original position have no information as to which generation they belong.[46]

ይሁን እንጂ መሠረታዊ የአመክንዩ እድል እና መሠረታዊ የስሌት እውቀት ክምችት አላቸው። በመሆኑም በዚህ የመርሳት ሽፋን ተከልለው በዚህ ማኅበረሰባዊ ውል ወሰን መካተት ስላለባቸው እና ስለሌለባቸውም መርሆዎች እና አንቀፆች ተከራክረው እና ተወያይተው ለእያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን የሚያስማማ እና የተሻለ ሕይወት ለመኖር የሚያስችል ስምምነት ላይ መድረስ ይኖርባቸዋል። እዚህ ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚያደርጉትን ድርድር ሮውልስ ሒሳባዊ በሆኑ ቀመሮች በምናብ ተመርቶ አስቀምጧቸዋል። በመሆኑም ተዋዋይና ተደራዳሪዎቹ በኃላ የመርሳት ሽፋኑ ሲነሳ በውሉ መሠረት የሚደርሳቸውን ዕጣ ስለማያውቁ ድንገት

46 Ibid, p.117

የማያምር ዕጣ ሊደርሰኝ ይችላል ብለው ስለሚሰጉ ለሁሉም ተዋዋይ ወገኖች ሊያስማማ የሚችል መርህ በውሉ ውስጥ እንዲሠፈር ይከራከራሉ ተብሎ ይጠበቃል።

በመሆኑም በድርድሩ ወቅት ያሉ ተዋዋይ ወገኖች በእነዚህ ሁለት የፍትሕ መርሆዎች ይመራሉ ተብሎ ይጠበቃል። አንደኛው መርህ ሁሉም ሰው በእኩልነት እና በነፃነት ማግኘት ይጠበቅበታል። ሁለተኛው መርህ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስክ እኩልነት እንዳይኖር ሊፈቀድ የሚችለው በሚደረገው ውል የአነስተኛ ተጠቃሚነት ዕጣ ለሚደርሰው ወገን ጥቅም ከሆነ እና ይህን የተሻለ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ የማግኘት እድል ለሁሉም ሰው የተሰጠ ከሆነ ብቻ ነው።

> One main problem in Rawl's defense of "justice as fairness" is that Rawls believes that no one can deserve his or her advantages or assets in life—it's all a matter of luck. As he puts it, "No one deserves his greater natural capacity nor merits a more favorable starting point in society." The reason ? Because even a person's character (i.e., the virtues he or she practices that may provide him with ways of getting ahead of others) "depends in large part upon fortunate family and social circumstances for which he can claim no credit"[47]

ሁለተኛው መርህ "የልዩነት መርህ" በመባልም ይታወቃል ምክንያቱም በቀዳማዊ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ተዋዋይ ወገኖች መጨረሻ ላይ አነስተኛ የማኅበረሰባዊ ወለል ላይ የሚገኝ የሕይወት ዕጣ ሊደርሳቸው አንዳንዶች ሃብታም ሊሆኑ የሚገባው አነስተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች ሕይወት የሚጠቅም ቁስ የሚያመርቱ ወይም መሰል አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ ብቻ ነው።

47 Tibor R. Machen, "What is Morally Right With Insider Trading," *Public Affairs Quarterly*, Vol. 10 (April 1996), pp.135-142.

ለምሳሌ ያህል አንድ የልብ ስፔሻሊስት ዶክተር ቅንጡ መኪና እና ሰፊ ቤት ቢኖረው በሙያው እጅግ ብዙ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን የልብ ሕመማን የሚረዳ ከሆነ ብቻ ነው።

ስለ ነፃነት- ስቱአርት ሚል

‘‘የብዙኃኑ አንባገነንነት የነፃነት ፀር ነው’’

ስቱአርት ሚል (1806-1873) በስፋት የሚታወቀው የጠቀሜታውያንን የሞራል ፍልስፍና በማስፋፋት ነው። የሚል አባት ጀሞስ ሚል የጀርሚ ቤንታም አድናቂ እና ተከታይ በመሆኑ ልጁ ስቱዋርት ሚልን የሚቀጥለው የጠቀሜታውያን የሞራል ፍልስፍና አቀንቃኝ እንዲሆን ከልጅነት ጀምሮ ኮትኩቶ አሳድጎታል። ስቱአርት ሚል ገና በሕጻንነቱ ግሪክ እና ላቲን አጥንቷል፤ ይህ ከፍተኛ የጥናት እና ምርምር ሥራው ከቤተሰቦቹ ከፍተኛ ጫና ጋር ሲደመር በሃያ አመቱ የአእምሮ ጤና መታወክ እንዲደርስባት አድርጎታል። በሂደት የረጅም ጊዜ ጓደኛው የሆነችውን ሃሪየት ቴይለር የተባለች እንስት ሲያገባ ግን ሕይወቱ እየተረጋጋ እና የፍልስፍና አስተምህሮቶቹም ቅርፅ እየያዙ ሄደዋል።

ስቱአርት ሚል “ስለነፃነት” ወይም “On Liberty” የተሰኘውን አነስተኛ ጽሑፍ አዘጋጅቶ እንዲጨርስ በብዙ የረዳችው ሚስቱ እንደሆነች ገልጿል። ይህች አነስተኛ ድርሳን በሕግ ፍልስፍና ታሪክ እና በምዕራባዊያን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ፈር ቀዳጅ ሆናለች። ይህች ጽሑፍ እስካሁን ድረስ በሕግ ትምህርት ቤቶችና በአውሮፓ ፓርላማ የሚቀነቀነውን “የግለሰባዊነት” አስተምህሮ ያስጀመረች ናት ቢባል መጋነን አይሆንም። ይህች ድርሳን “ግለሰባዊነት” የሕግ ከለላ እንዲኖረው በጽኑ ትከራከራለች። ግለሰብ የብዙኃኑ አስተሳሰብ ሊጫንበት እንደማይገባና ሕግና መንግስትም የብዙኃኑን መብት ለማስጠበቅ ከመሥራት ይልቅ የግለሰቡን መብት በማስጠበቅ ላይ ቢሰሩ እንደሚሻል ትመክራለች። ሚል “የብዙኃኑ አንባገነንነት” በሚል የሚጠቅሰው

አፈና ግለሰቡ ማንንም ሳይጎዳ በሚያራምደው የሕይወት ዘይቤ ላይ የተቀጣጣ ጥቃት እንደሆነ አበክሮ ይገልፃል።

> Society can and does execute its own mandates: and if it issues wrong mandates instead of right, or any mandates at all in things with which it ought not to meddle, it practises a social tyranny more formidable than many kinds of political oppression, since, though not usually upheld by such extreme penalties, it leaves fewer means of escape, penetrating much more deeply into the details of life, and enslaving the soul itself. Protection, therefore, against the tyranny of the magistrate is not enough: there needs protection also against the tyranny of the prevailing opinion and feeling; against the tendency of society to impose, by other means than civil penalties, its own ideas and practices as rules of conduct on those who dissent from them; to fetter the development, and, if possible, prevent the formation, of any individuality not in harmony with its ways, and compel all characters to fashion themselves upon the model of its own[48].

ለመሆኑ የግለሰብ ነፃነት ማለት ምን ማለት ነው? መንግስትስ ነፃነትን ለመገደብ የሚገደደው መቼ ነው? ግለሰቡም የመንግስትን ጣልቃገብነት መቃወም የሚችለው መቼ ነው? የሚሉ ሐሳቦች በሰፊው ተብራርተዋል። ለሚል በታሪክ ውስጥ በስልጣን እና ነፃነት መሀከል የማይሞት ትግል አለ። በመንግስት ስልጣን እና በዜጎች ነፃነት መሀከል ያለው ቅራኔ በሂደት የዜጎችን ነፃነት እና መብት እያገዘፈ መሄድ አለበት። በሰው ልጅ ቀዳሚ

48 John Stuart Mill, On Liberty, 1859, Chapter 1; Introduction

የመንግስት ምስረታ ዘመናት መንግስት እንዲመሠረት እና ማኅበረሰብ እንዲፀና ነገስታት እና መንግስታት በዜጎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የስልጣን ኃይል ሲያሳርፉ ኖረዋል።

> The only purpose for which power can be rightfully exercised over any member of a civilized community, against his will, is to prevent harm to others. His own good, either physical or moral, is not a sufficient warrant[49].

ዘመናዊ የሆኑ መንግስታት ከተመሠረቱ እና የዲሞክራሲ ስርዓት ከተገነባ በኃላ ግን ዜጎች ራሳቸውን በሕግ ማስገዛት ጀመሩ ይሁን እንጂ በዚህ ዘመንም ቢሆን ከመንግስት አምባገነንነት እና ጭቆና ይበልጥ ለግለሰብ መብት አስፈሪ የሆነው "የብዙኃኑ አምባገነንነት" ነው። ምክንያቱም ሳለው የሕዝብ አመለካከት በሕግ አይመራም፤ የሚታወቅ ተቋም የለውም፤ የተፃፈ ሕግ አይኖረውም። በማኅበረሰቡ ውስጥ የሰረፀው አስተሳሰብ በታሪክ ቀድሞ በብዙኃኑ ተቀባይነት ስላገኘ ብቻ በነፃ ግለሰቦች አስተሳሰብ ላይ ጫና እያሳደረ ይኖራል።

"ስለነፃነት" የተባለው ድርሳን ነፃነትን በሦስት ይከፈላል። አንደኛው የሐሳብ እና የስሜት ነፃነት፤ ሁለተኛው ፍላጎትን የማርካት ነፃነት ሲሆን ሦስተኛው የመሰብሰብ እና የመደራጀት ነፃነት ነው። የሰው ልጅ የፈለገውን ሐሳብ የመያዝ እና ይህንኑንም የማቀንቀን መብት አለው። በተጨማሪም ፍላጎቱን እና ጥማቱን ባሰኘው መንገድ የማርካት ነፃነት ሊኖረው ይገባል። የሰው ልጅ ፍላጎት እና ሐሳብ ከማኅበረሰቡ ልማድ አንፃር ሲታይ ኢ-ሞራላዊ መስሎ የሚታይ ቢሆን እንኳ ሌላ ሰው ላይ ግልፅ የሆነ "ጉዳት" እስካላደረሰ ድረስ ሊታገድ አይገባውም። ሚል **"የጉዳት መርህ"** የሚባል የሞራል መርህም ያስቀምጣል፤ መንግስት በግለሰቦች

49 Ibid

ነፃነት ጣልቃ መግባት የሚገባው ነፃነታቸውን የሚጠቀሙበት መንገድ በሌሎች ግለሰቦች ላይ ግልፅ እና የማያሻማ ጉዳት ሲያደርስ ብቻ ነው።

> If all mankind minus one, were of one opinion, and only one person were of the contrary opinion, mankind would be no more justified in silencing that one person, than he, if he had the power, would be justified in silencing mankind[50].

ከዚህ በተጨማሪ ነፃነታቸው ሊገደብ የሚገባው ሕፃናት እና አንዳንድ "ያልሰለጠኑ ሕዝቦች" ናቸው። በመሰረታዊነት አንድ ማኅበረሰብ "ግለሰባዊነትን" ሊያበረታታ ይገባል "ግለሰባዊነት" እየተበረታታ ሲሄድ ፈጠራ እና ብዙኃንነት እየጨመረ ከመሄዱም በላይ ግለሰባዊነት ሰው የመሆን የመጨረሻ ግብ እና ጥልቅ እርካታን መጎናፀፊያ መንገድ ነው። ግለሰቡ የራሱን ማንነት እና ፍላጎት እስከ መጨረሻው ድረስ በመሄድ እንዲፈለግ እና እንዲያሟላ ሊፈቅድለት ይገባል ሲልም ተከራክሯል።

በተጨማሪም ግለሰቡ የመንግስትን ጣልቃ ገብነት ሊቃወም የሚችልባቸው መስፈርቶች አስቀምጧል። አንድ ግለሰብ በመንግስት ተአቅቦ የደረሰበትን ድርጊት ከመንግስት በተሻለ ብቃት ድርጊቱን የመፈፀም አቅም ሲኖረው ወይም ግለሰቡ ከድርጊቱ ልዩ ጥቅም የሚያገኝ ከሆነ ወይም ድርጊቱ የመንግስትን ስልጣን ያለአግባብ አግዝፎ ግለሰቡን በመንግስት ላይ ጥገኛ የሚያደርግ ከሆነ አንድ ሰው መንግስት በግለሰቦች ላይ የሚያደርሰውን ጣልቃ ገብነት መቃወም ይኖርበታል። የግለሰባዊነት ፅንሰ ሐሳብ በአውሮፓ የዘመናዊ ፖለቲካ አስጀማሪ ከመሆኑም ባሻገር በተለይም "የጉዳት መርህ" ለብዙ የሥነ-ሕግ ፍልስፍናዎች መሠረት ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ በስፋት ተቃውመውት ፅፈዋል። ሚል በጊዜው ሴቶች ከወንዶች እኩል የመምረጥ እና የመመረጥ መብት ሊኖራቸው እንደሚገባ በማሰብ የአያሌ ሴቶችን ፊርማ አስባስቦ ለፖርላማው አቅርቧል።

50 Ibid

ማኅበራሰባዊ ውል እና ግለሰባዊነት

መንግስት የሚፈጠረው እና የሚፀናው በተዛፊም ሆነ ባልተዛፊ ማኅበረሰባዊ ውል አማካኝነት ነው። ማኅበረሰባዊ ውሉ የፊጠረው መንግስትም ሆነ ማኅበራዊ ውሉን ያፀደቀው ማኅበረሰብ ግን የተሠራው ከግለሰቦች ነው። በመሆኑም ውሉን ለማስፈፀም እና ማኅበረሰባዊ ደህንነትን እና ሰላምን ለማምጣት እሠራለሁ በሚለው መንግስትና በግለሰቡ መሃል ሁልጊዜም ቢሆን የማያቋርጥ ትግል አለ። በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ግለሰቦች ከዕለታት በአንድ ቀን ተነስተው ማኅበረሰባዊ ውሉ አይመለከተኝም፤ አይገዛኝም እውቅናም ነፍጌዋለሁ፤ ውሉ ተቋርጦ በራሴ መርህ መመራት እፈልጋለሁ ሊሉ ይችላሉ። ማኅበረሰቡ ሊደግፋቸው ወይም ሊቃወማቸው ይችላል።

በዚህ ጊዜ መንግስታዊ ስልጣንን የያዙ ሰዎች አጣብቂኝ ውስጥ ይገባሉ። በአንድ ወገን ማኅበረሰቡ ድህንነቴን፤ ሰላሜንና ብልፅግናዬን ያስጠብቅልኛል ብሎ ድምፁን ሰጥቷቸዋል። በሌላ ወገን ግለሰቡ ይህ የማኅበረሰቡ ሐሳብ በእኔ ነፃነት ላይ የተቃጣ ጥቃት በመሆኑ የሕዝቡን ሐሳብም ሆነ የመንግስታቱን ፖሊሲ እና ሕግጋት አልቀበልም ሊል ይችላል። ይህ ውጥረት በሰላም ወቅት በነፃ የሚዲያ ተቋማት እየተንፀባረቀ ሲቀጥል የከፋ ቀን ደግሞ አብዮት ወይም መፈንቅለ መንግስትን ሊወልድ ወይም ሊጠነስስ ይችላል። በመሆኑም ሕግ የእዚህ ውጥረት ማርገቢያ፤ ማንፀባረቂያ ወይም ማባባሻ ሊሆን ይችላል። በዚህ ምክንያት ጥሩ የሕግ አርቃቂዎች፤ አፅዳቂዎች፤ አመንጪዎች፤ ተርጓሚዎች፤ አስተማሪዎች እና ተመራማሪዎች በሁለቱ ወገን ያለው ውጥረት ሚዛኑ ተጠብቆ እንዲኖር ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ለዚህ ውጥረት ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆነው “የፀረ ሽብር ሕግ” ነው የፀረ-ሽብር ሕግ ዓለም ዓቀፋዊ በሆነ ደረጃ አከራካሪ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል። የፀረ-ሽብር ሕግ በተለምዶ የፖሊስ እና የድህንነት አካላት

በወንጀል የተጠረጠረ ግለሰብን ከሚመረምሩበት እና ማስረጃ ከሚሰበስቡት መንገድ ለየት ባለ መልኩ ግዙፍ ስልጣን ይሰጣቸዋል። የፖሊስ እና የደህንነት አካላት የግለሰቡን ስልክ፤ ኢ-ሜይል፤ የጽሑፍ ግንኙነቶች ያለግለሰቡ ፍቃድ ሊበረብሩ እና ሊመረምሩ ይችላሉ። በአንድ በኩል እነዚህ አካላት በማኅበረሰባዊ ውሉ አማካኝነት ሕዝቡ የጋራ ድህንነቱን ለማስጠበቅ የሰጣቸው ኃላፊነት አለ፤ በሌላ በኩል ግለሰቡ ነፃነቱን እና የግል ሚስጥሩን የመጠበቅ መብት አለው።

የግለሰብ መብት ተከራካሪዎች ይህ በሕግ የተፈጠረ መንግስት የሚባል አካል ያለምንም ከልካይ በግለሰቦች ነፃነት ላይ እየተረማመደ የሕዝቡን መብት አስጠብቃለሁ የሚል ከሆነ ቀስ ብሎ ደግሞ የማኅበረሰቡን መብት እና ነፃነት የሚጨፈልቅ አገዛዝ ሲፈጥር የሚያስጥለን አይኖርም ይላሉ። የማኅበረሰቡን የጋራ ጥቅም መጠበቅ አለበት በማለት የሚከራከሩ ደግሞ አንዳንዴ የጋራ ጥቅምንና ደህንነትን ለማስጠበቅ የግለሰቡ መብት እና ነፃነት መስዋዕት ሊሆን ይችላል በማለት የጠቀሜታውያን የሞራል ፍልስፍና በማጣቀስ ይከራከራሉ። በአጠቃላይ መገንዘብ የሚኖርብን ጉዳይ ቢኖር ግን የሕግ ስርዓቶች ውጤታማ የሚሆኑት በእነዚህ ሁለት ፅንፎች መሀከል ያለው ውጥረት ሚዛናዊ ሆኖ እንዲቀጥል የሚያስችሉ ሲሆን ብቻ ነው።

ምዕራፍ አምስት

ገሃዳዊ ሥነ - ሕግ

ገሃዳዊ ሥነ-ሕግ(Legal Realism) በመሠረቱ ወግ አጥባቂ የሕግ አስተምህሮን (Legal formalism) በመቃመወም የተጀመረ የሕግ ፍልስፍና ነው። ይህ ፍልስፍና ሕግ ከተፈጥሮ የሚገኝና የማይሻር ወይም ከፍተኛ ስልጣን ባላቸው ሉዓላዊ አካላት የተሰጠ ትእዛዝ መሆኑን አይቀበልም። በመሆኑም በመሠረታዊነት የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍናንም ሆነ የሕገ-ሰብ ፍልስፍና ይቃወማል። አስተምህሮው የአሜሪካ የሥነ-ሕግ ፍልስፍና እና የስካንዲኒቪያ የሥነ-ሕግ ፍልስፍና በሚል በሁለት ንዑስ ክፍሎች ይከፍላል።

በሀገረ-አሜሪካ ያለው የሕግ ስርዓት ሕግ የሚፈጠረው ፍርድ ቤቶች በሚሰጧቸው በኩር ውሳኔዎች አማካኝነት እንደሆነ ያስተምራል። እነዚህ በኩር ውሳኔዎች የስር እና አቻ ፍርድ ቤቶች በተመሳሳይ ጉዳይ ለሚሰጡት ውሳኔ ልክ እንደ ሕግ ተቆጥረው አስገዳጅ ይሆናሉ። በዚህ ምክንያት የሃገረ አሜሪካ ፍርድ ቤቶች ሕግ ተርጓሚ ብቻ ሳይሆኑ ሕግ አውጪም ጭምር ናቸው። በመሆኑም የአሜሪካው ገሃዳዊ ሥነ-ሕግ በፍርድ ቤቶች ውሳኔ፤ በዳኞች የአመክንዩና ባህሪ ጉዳይ እንዲሁም በፍርድ ቤት የአሠራር ባህል ላይ ያተኮረ ፍልስፍና ነው። የዚህ አስተምህሮ ተከታዮች እንደሚሉት ሕግን የሚፈጥሩት ፍርድ ቤቶች ናቸው። ሕግ ማለት ፓርላማው አፅድቆ የላከው ነጭ ወረቀት ሳይሆን ዳኞች እነዚህን ሕይወት አልባ የሕግ አንቀፆችን ከባለጉዳዮች ልዩ የሕይወት ሁኔታ ጋር አጣምረው ፍርድ ሲሰጡ የሚፈጠር ጉዳይ ነው።

ስለሆነም ሕግ ከአንድ ሉዓላዊ አካል ወይም ፓርላማ የሚሰጡትን ወይም በተፈጥሮ አማካኝነት በሰዎች ህሊና ውስጥ የታተመ የማይለወጥ እና የማይገረሰስ ጉዳይ እንደሆነ ተደርጎ ሊቆጥር አይገባም። በዚህ ገዛዳዊ ሥነ-ሕግ ፍልስፍና ከሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና ጋር የሚጋራው ሐሳብ ሕግ ምንም ዓይነት ዲበአካላዊም ሆነ ተፈጥሮአዊ መሠረት የሌለው መሆኑን ነው። በመሆኑን ሕግ ሰው ሠራሽ መሆኑን ይቀበላል። ይሁንና ሕግ ሰው ሠራሽ ቢሆንም የትኞቹ ሰዎች ይፈጥሩታል በሚለው ነጥብ ላይ ልዩነቱን ያስቀምጣል።

የሥነ-ሕግ ፍልስፍና አራማጆች በአብዛኛው ዳኞች፤ ጠበቆች፤ የሕግ አስተማሪዎችና አርቃቂዎች ስለነበሩ ሕግ ሕይወት ኖሮት በውሳኔዎች ውስጥ የሚገለጥ መሆኑን ሙሉ ለሙሉ ይስማማሉ። በዚህም ምክንያት የሕግንና የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ለማጥናት አንደኛው እና ዋነኛው መሠረታዊ ጉዳይ የዳኞችን ግለሰባዊ ባህሪ እና አቋም ማወቅ ነው። ምክንያቱም ዳኞች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በውሳኔዎቻቸው ውስጥ የራሳቸውን ፖለቲካዊ ባህላዊ፤ሃይማኖታዊ እና ግለሰባዊ አቋሞች ያንፀባርቃሉ። በመሆኑም ከዳኞቹ የግል ባህሪ ተነስተን በአንድ ጉዳይ ላይ ምን ዓይነት ውሳኔ ሊሰጡ እንደሚችሉ መገመት እንችላለን።

በተጨማሪም የሕግ ታሪክን ስናጠና የፍርድ ቤቶችን ታሪክን ማጠቃለል የማንችል ከሆነ ተሞክሯችን የተሳካ አይሆንም። ባጠቃላይ ዳኞች ውሳኔ ሲሰጡ ከውስጥም ሆነ ከውጪ በሚመነጩ ተፅዕኖዎች ውስጥ ሆነው መሆናቸውን በመገንዘብ የሚሰጡት ውሳኔ ግለሰባዊ እና ማኅበረሰባዊ ፋይዳ እንዲኖረው ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህ የሕግ ፍልስፍና ዳኛ ሠራሽ የሕግ ስርዓትን ለማይከተሉ ሃገሮች ብዙም ትርጉም ላይሰጥ ይችላል ምክንያቱም ለእነሱ ሕግ የሚፈጥረው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንጂ ዳኛ ወይም ፍርድ ቤቶች አይደሉም። በመሆኑም በአንድ ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ፓርላማው ወይም አንዱ ሉዓላዊ አካል ካወጣው ሕግ የሚያፈነግጥ መሆን የለበትም ዳኛ ሠራሽ ሕግ በሌለበት ሀገር ዳኛ ሕግ ይተረጉማል እንጂ ሕግ አይወጣም/አይፈጥርም።

ሌላኛው ጠንካራ የገሃዳዊ ሥነ-ሕግ አቀንቃኝ ካርል ሌውለን ሲሆን ሰፋ ባለ መልኩ ሊተነትነው ሞክሯል። በ1931(እ.ኤ.አ) በጻፈው “some realism about realism” በሚለው መጣጥፍ የገሃዳዊ ሥነ-ሕግ መሠረታውያን የሚላቸውን ነጥቦች ለይቷል። እነዚህም ፡-

1ኛ ሕግ ምንጊዜም ቢሆን በለውጥ ሂደት ላይ ነው።

2ኛ ሕግ ወደ ግብ የሚያደርሰን መንገድ እንጂ በራሱ ግብ አይደለም።

3. የማኅበረሰብ ለውጥ ከሕግ ለውጥ ይልቅ ይፈጥናል።

4ኛ. “በሆነው” እና “ሊሆን በሚገባው” (ማለትም በሕግ እና ሞራል) መሀከል ያለው ልዩነት ጊዜያዊ እና ለሕግ ጥናት አላማ ብቻ የሚውል ነው።

5/ ሕግጋት የስር ፍርድ ቤቶችን ሥራ/ልምድ አይወስኑም የሚል ጥርጣሬ ተገቢነት።

6ኛ ጠቋሚ እና ገዳቢ ሕግጋት የፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ አናሳነት

7ኛ የፍርድ ቤቶች ውጤቶችን ልዩ እና ጠባብ በሆኑ ፍልስፍናዎች ማስቀመጥ

8ኛ ሕግን ሁልግዜም ቢሆን ከሚያመጣው ውጤት አንፃር መገምገም

9ኛ ከላይ በተዘረዘሩት መርሆዎች የሕግ ጥናትን እና ልምምድን ለመቀየር ጥረት ማድረግ የሚሉት ናቸው።

1. The conception of law in flux. 2. The conception of law as a means to an end and not an end itself. 3. The concept of a society in flux faster than the flux in the law. 4. The temporary divorce of Is and Ought for

> purposes of study. 5. Distrust of traditional rules to describe what courts or people are actually doing. 6. Disbelief that prescriptive rules are the heavily operative factor in producing court decisions. 7. The belief in the worthwhileness (sic) of grouping cases and legal situations into narrower categories than…in the past.19 8. [I]nsistence on evaluation of any part of law in terms of its effects. 9. Insistence on sustained and programmatic attack on the problems of law along any of these lines[51].

የስካንዲኒቪያ የሥነ-ሕግ ፍልስፍና ጀማሪ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ የሆነው ካርል አለቨርኮና 1939 (እ.ኤ.አ) “Law as Fact” በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ድርሳን የማኅበረሰባዊ የስነ- ሕግ ጥናት (sociological Jurisprudence) አስጀማሪ ተደርጎ ይወሰዳል። ለእርሱ “ሕግ ማኅበረሰባዊ እውነታ” ነው “Law is nothing but a set of social facts” በመሆኑም ሕግ የሉዓላዊ አካል ትእዛዙ አይደለም፤ ተፈጥሯዊ፤ መንፈሳዊ ወይም ዲበአካላዊ ይዘት እና ምንጭ የለውም። ሕግጋቱ በራሳቸው የቆሙ አስገዳጅነት ያላቸው አሀዶች “Independent imperatives” ሆነው በዳኞች አእምሮ ውስት ከማኅበረሰባዊ እውነታ ጋር እየተጣጣሙ የሚተረጎሙ ናቸው። በመሆኑም ሕግ በዜጎች አእምሮ ውስጥ ተፅዕኖ ሳያሳድር አስገዳጅነት እና ተቀባይነት የሌለው ከሆነ ዜጎች ምንጊዜም ቢሆን ቅጣት ሳይደርስባቸው ሕጉን የሚያመልጡበትን መንገድ እየፈለጉ ይኖራሉ ሲል ፅፏል።

51 Karl LLwelyn ,Some Realism About Realism,1931

ፈላስፋው ዳኛ - ኦሊቨር ዌንደል ሆልምስ

"የሕግ ሕይወት በአመክንዩ ሳይሆን በልማድ የሚመሩ ነው"

ሆልምስ (1841-1935) የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ከመሆኑ ባሻገር ለየት ባሉ ፍልስፍናዊ አቋሞቹ እስከዛሬ ሲወሳ ይኖራል። የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዘጠኝ ዳኞች ሲኖሩት ከሚሰጡት ውሳኔ ውስጥ የልዩነት ሐሳቦችን በተደጋጋሚ በማቅረቡ የተነሳ **"ታላቁ ተቃዋሚ"** (the great dissenter) በመባል እስከ መጠራት ደርሶ ነበር። በሀገረ-አሜሪካ የተመሠረተውን ገዛዳዊ ሥነ-ሕግ ከጠነሰሱት ሰዎች መሀከል ግንባር ቀደሙ ሲሆን ከእርሱ ሌላ ብዙ ሰዎች አስፋፍተው ፅፈውበታል። ሆልምስ እንደሚለው "የሕግ ሕይወት በአመክንዩ ሳይሆን በልማድ የሚመራ ነው" ሕግ እና የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ደረቅ በሆነ የሕግ እና የአመክንዮ ሰንሰለት እና ቀመር እየተሰሉ የሚፈጠሩ ሳይሆን በወቅቱ ያለው ጠንካራ ማኅበረሰባዊ እና መንግስታዊ ገገር ሐሳብ ውጤት መሆን አለባቸው። ይህ ልንክደው የማንችለው ሃቅ በመሆኑ ዳኞች በዚህ ማኅበረሰባዊ ወይም መንግስታዊ ገገር ሐሳብ ስር አውቀውም ሆነ ሳያውቁት ሊወድቁ ይችላሉ።

> When we study law we are not studying a mystery but a well-known profession. We are studying what we shall want in order to appear before judges, or to advise people in such a way as to keep them out of court. The reason why it is a profession, why people will pay lawyers to argue for them or to advise them, is that in societies like ours the command of the public force is intrusted to the judges in certain cases, and the whole power of the state will be put forth, if necessary,

> to carry out their judgments and decrees. People want to know under what circumstances and how far they will run the risk of coming against what is so much stronger than themselves, and hence it becomes a business to find out when this danger is to be feared. The object of our study, then, is prediction, the prediction of the incidence of the public force through the instrumentality of the courts.[52]

ሕግን ስንመረምር እና ስናጠና የተያያዝነው ጉዳይ ሚስጥራዊ ሙያ አለመሆኑን ልናውቅ ይገባል። ይልቁንም ሰዎች በዳኞች ፊት ሲቀርቡ ምን ማለት እንዳለባቸው የሚረዳቸውን እና ተመልሰውም በከሳሽነትም ሆነ በተከሳሽነት ወደ ፍርድ ቤት የማይቀርቡበትን መንገድ ፍለጋ ነው። አንድ ጊዜ ፍርድ ከተሰጠ ቀጥሎ የመንግስት አጠቃላይ ጉልበት የሚውለው ይህንኑ በማስፈጸም ላይ በመሆኑ አስቀድሞ እንዲህ ዓይነት ተጋላጭነት ላይ ላለመውደቅ ሲባል በሕግ ሙያ ላይ ያሉ ሰዎችን ማማከር አስፈላጊ እና ግዴታ ሆኗል። በመሆኑም ጠበቆቹም ቢሆን ፍርድ ቤቶች ምን ሊወስኑ ይችላሉ የሚል የግምት ተግባር ላይ የሚሳተፉ ናቸው።

ዳኞች ይህን የማያደርጉ ቢሆን እንኳን አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት ራሳቸው በፈጠሩት ግላዊ ተዕዕኖና ሐሳብ ስር የሚወድቁ በመሆኑ በእውቀት የዚህ ገገር ሐሳብ ፈፃሚ መሆን አለባቸው። መንግስታዊ እና ማኅበረሰባዊ ገገር ሐሳብ የምንለው ማኅበረሰቡ በወቅቱ የያዘው የሞራል መርህ፤ መንግስት ያቀደው እና የሚያስፈመው ፖሊስ ወይም ለሕዝቡ አንገብጋቢ የሆነ ጉዳዮችን የሚያካትት ነው።

52 Holmes Oliver Wendell, The Path of the Law, Harvard Law Review,1897

> If you want to know the law and nothing else, you must look at it as a bad man, who cares only for the material consequences which such knowledge enables him to predict, not as a good one, who finds his reasons for conduct, whether inside the law or outside of it, in the vaguer sanctions of conscience[53].

በመሆኑም ዳኛ ውሳኔ ሲፅፍ "የምመራው በሕግ እና አመክንዩ ብቻ እንጂ በሌላ ገፀ ሐሳብ አይደለም" ማለት የለበትም፤ ምክንያቱም "ሕግ ማለት የፍርድ ቤቶች የዕለት ተዕለት ተግባር ነው" በመሆኑም ፍርድ ቤቶች የሕግጋት ሐሳብ እና ውጥን ይሳካ ዘንድ በውሳኔያቸው ከመደገፍ አንስቶ ውሳኔያዊ ተአቅቦ እስከ ማድረግ መሄድ አለባቸው በማለት ተከራክሯል።

ሆልምስ ያደገው በአሜሪካ ሀገር እውቅ ከነበሩ ተመራማሪ እና የኪነ-ጥበብ ሰዎች መሃል ነበር። አባቱ ታዋቂ ገጣሚ እና ደራሲ ሲሆን የቤተሰባቸው ወዳጆች እነ ዋልዶ ኤመርሰን እና ዊሊያም ጀምስ በመሆናቸው ከልጅነቱ ጀምሮ የተወዳጃቸው ሰዎች እና እየሰማቸው ያደጋቸው ክርክሮች ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድረውበታል። ሆልምስ በወቅቱ በአሜሪካ የነበረው የፀረ-ባርነት እንቅስቃሴ እንዲደግፍ ምክንያት የሆነው እናቱ እና በወቅቱ ተራማጅ ሐሳብ የነበራቸው አሳቢያን ስለነበሩ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። በዚህም ምክንያት በአሜሪካ በነበረው የእርስ በእርስ ጦርነት የአንድነት ሃይሎችን ደግፎ አብረሃም ሊንከን ባቀናጀው ጦር ውስጥ ለመመልመል በቅቷል።

በዚህ ጦርነት ከፍተኛ የጦር መኮንን እስከመሆን የደረሰ ሲሆን ጦርነቱ እንዳበቃ የጦር ሜዳል ተሸልሞ ወደ ሲቪል ህይወቱ ተመልሷል።

---

53 Ibid

ከጦርነቱ በኋላ በሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ የሕግ ክፍል ገብቶ የተመረቀ ሲሆን ቦስተን ውስጥ የሕግ ሙያውን መለማመድ ሲጀምር በወቅቱ በተለያየ ቦታ የሚሰጣቸውን የንቃተ-ሕግ ሰበካዎች እና ጦማሮች አሰባስቦ “The common law” የተሰኘ ድርሳን ሊያዘጋጅ ችሏል። ይህ ድርሳን ምናልባትም “ገሃዳዊ ሥነ-ሕግ” መሠረት የያዘበት ቀዳሚ ሥራ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

የሆልምስን ሕይወት ታሪክ ያነሳነው ያለምክንያት አይደለም፤ ከወጣትነት ጊዜው ጀምሮ ከሐሳባውያን ተርታ ከሚመደበው ዊሊያም ጄምስ ጋር የሚያደርጋቸው ክርክሮች እና በእርስ በእርስ ጦርነቱ ወቅት ያስተዋላቸው ጉዳዮች በአስተሳሰቡ ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድረውበታል። ዊሊያም ጄምስ ታዋቂ የሥነ-ልቦና ተመራማሪ እና Pragmatism የተሰኘውን የሥነ-እውቀት መሥራች ፈላስፋ ነበር። ፕራግማቲስም ወይም ተግባራዊነት እንደሚያስተምረው “The truth is what works” እውነት ማለት የሚሰራ ነገር ነው። ይህ አስተሳሰብ ከገሃዳዊነት ጋር ያለው ቁርኝነት ከፍተኛ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም። በዚህም ምክንያት “Common law” የተሰኘውን ድርሳን የሚጀምረው እስከዛሬ ድረስ እጅግ ታዋቂ በሆነበት አባባል ነው፤ ”The life of the law has not been logic, it has been experience. The felt necessities of the time, the prevalent moral and political theories, institutions of public policy, avowed or unconscious and even the prejudices which judges share[54] ” የሕግ ሕይወት አመክንዮ ብቻ ሳይሆን የረኸርም ጊዜ ልማድ ጥርቅም ነው። ዘመኑ የሚጠይቀው ጉዳይ፣ የተስፋፋው የሞራል እና ፖለቲካዊ ጥያቄ፣ የታመኑ እና ያልታወቁ ሕዝባዊ አመለካከቶች እና የዳኞች ድንቅ ዝንባሌ በሙሉ የአንድን ሀገር የሕግ ፍልስፍና የሚቀርፁ ነገሮች ናቸው።

54 Oliver Wendell Holmes Jr, The Common Law. **I**. Boston: Little, Brown and Company, 1881

በወቅቱ የጀርመን ሐሳባዊነት ከአውሮፓም ተሻግሮ በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች እጅግ ተፅዕኖ የሚያሳድር ሐሳብ በመሆኑ ሕግ ተገማች እና ወጥ በሆኑ የአመክንዮ መርሆዎች ብቻ የሚመራ ሒሳባዊ ቀመር(Mathematical formula) አለመሆኑን በተደጋጋሚ ተናግሯል። ሆልምስ ይህንን ሊል የቻለው በወጣትነት ዘመኑ ጊዜውን ከገጣሚያን፣ ደራሲያን፣ ፈላስፎች እና መሰል የጥበብ ሰዎች ጋር ያሳልፍ ስለነበር ይህንኑ ተፅዕኖ መገመት አያዳግትም።

ሆልምስ ዳኞችን ሕግን ለመተርጎም የሚያሳዩት ጥበባዊ ተጋድሎ በሕጉ ላይ ሕይወት የመዝራት ያህል እንደሆነ ያምናል። ወግ አጥባቂ፣ ቀመራዊ እና ሐሳባዊ የሕግ አመለካከቶችን በሙሉ በጥርጣሬ መመልከት ያለብን ሕግ በየጊዜው እና በየዘመኑ የሚነሱ ተግዳሮቶችን ፈጠራ በታከለበት መልኩ እንዳይፈታ ጋሬጣ ስለሚሆኑ ነው። ይህንን ለማድረግ ፍርድ ቤቶች ከቀደሙ በኩር ውሳኔዎችን (Precedents) ከወቅቱ ጋር እንዲስማማ በማድረግ ሊተረጉማቸው እንደሚገባ አውስቷል። ከዚህ በተጨማሪ ሰው ሠራሽ ሕግጋት የተፈጥሮ ሕግ መሠረት የሌላቸው እና ሊኖራቸው የማይችል መሆኑን ሲገልፅ ሕግጋት ከአንድ የማይታይ መለኮታዊ ኃይል ወይም በተፈጥሮ ውስጥ ከሚገኝ ቀመር ይመነጫሉ ማለት የዳኞችን የመመራመር እና አዲስ የሕግ ጥበብ የመፍጠር አቅም ማሳነስ ነው።

የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ከተሾመ በኋላ ሕገ-መንግስቱን በመተርጎም ጉዳይ የተለየ አቋም ነበረው። በወቅቱ Textual Interpretation ወይም ምንባባዊ ትርጉም አቀንቃኞች የሕገ-መንግስቱ ቃላት በቀጥታ እንደወረደ ሊተረጎሙ ይገባል ይህም ለሕገ-መንግስቱ መንፈስ እና ለአርቃቂዎቹ ያለንን ክብር የምናሳይበት መንገድ ነው የሚባል አመለካከት የተንሰራፋበት ጊዜ ነበር። ሆልምስ ይህንን አመለካካት ከጠቅላይ ፍርድ ቤት እስከሚሰናበትበት ወቅት ድረስ ሲተቸው ኖሯል። ሕገ-መንግስቱ እንደ ትንቢት ቃል የማይነካ እና የማይሻሻል ተደርጎ መሳል እንደሌለበት እንዲያውም ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ህያው ሰነድ እንዲሆን ዘመኑን

በሚመጥን መልኩ መተርጎም አለበት። "The provisions of the constitutions are not mathematical formulas that have their essence in form, they are organic, living institutions transplanted from English soil. Their significance is vital, not formal. "የሕገ-መንግስቱ ቃላት ጭብጣቸው በቅርፅ ላይ ብቻ የተንጠለጠሉ ሒሳባዊ ቀመሮች ሳይሆኑ ህያው ተቋማትን የሚገነቡ ህያው ቃላት ናቸው። የአስፈላጊነታቸው ትርጉም ጥቅምን እንዲያበረክቱ እንጂ ለስርዓት አይደለም። በአጠቃላይ ሕግ ማለት ፍርድ ቤቶች ምን እንደሚወስኑ መተንበይ ወይም መገመት ነው።

ይህ የግምት መርህ (Prediction theory of Law) በአንድ ጉዳይ ላይ ለመከራከር የቀረቡ ባላጋራዎች ክርክራቸውን የሚቃኙት ዳኛው ሊወስንልኝ ይችላል በሚሉት የሐሳብ መስመር ላይ እንጂ ሕጉ ምን ይላል በሚለው ሐሳብ ላይ ብቻ አይደለም። ዳኛው ወይም ፍርድ ቤቱ ምን ሊወስን ይችላል የሚለውን ለማወቅ ደግሞ "Bad Man"/እኩይ ግለሰብ መሆን አለብን። ይህ እኩይ ግለሰብ በመሠረቱ ለክፋት የቆመ ሳይሆን መሆን የሚገባውን እና የሆነውን (Is Vs Ought) በሚገባ የለየ መሰሪ እና ተግባራዊ ሰው ነው። በመሆኑም የያዘውን ጉዳይ ለማሸነፍ የሚያደርገው ክርክር ሕጉ ምን ይላል? ወይም መልካም የሆነው ነገር የቱ ነው? በሚሉ ጉንጭ አልፋ ነገሮች ላይ ብቻ አያተኩርም። ሕጉን ለማወቅ እንደዚህ እኩይ ግለሰብ ተግባራዊ መሆን አለብን። ሆልምስ እስከ 90ኛው ዓመቱ ድረስ በአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰራ ሲሆን በእድሜ ትልቁ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆኑና በፈላስፋነቱ ከሕግ ውጪ ባለው ማኅበረሰብም እየተነሳ ይኖራል።

የሕግ ጥርጣሬ - ዠሮም ፍራንክ

"ሕግ ማለት ዳኛው ቁርሱን የበላው ነገር ነው"

በሀገረ- አሜሪካ በሕግ ሙያ ይተዳደር የነበረው ዠሮም ፍራንክ (1889-1957) በገሃዳዊ ሥነ- ሕግ አቀንቀኞች በስፊው ይታወቃል። ፍራንክ ዠሮም የገሃዳዊ ሥነ-ሕግ አቀንቃኞችን በሁለት ይከፍላቸዋል። ቀዳሚዎቹ የሕግ /Rule skeptics) ተጠራጣሪዎች ሲሆኑ ሌሎቹ የፍሬ ነገር (fact skeptics) ተጠራጣሪዎች ይባላሉ። የሕግ ተጠራጣሪዎቹ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሚጠቀሟቸው ሕግጋት ግልፅነት የጎደላቸው እና ግራ የሚያጋቡ እንደሆኑ ይጠቅሳሉ። እነሱም በበኩላቸው ሕግጋት ለሁለት ይከፍሏቸዋል። የወረቀት ሕግጋት እና እውነተኛ ሕግጋት። የወረቀት ሕግጋት በሕግ አውጪ አካል የሚሠጡ ሲሆኑ እውነተኞቹ ሕግጋት ግን ያልተፃፉ እና የዳኛውን ህሊና የሚለውጡ ሲሆኑ እውነተኛ፤ ተገማች እና ወጥነት ያላቸው እንዲሆኑ እነዚህ ያልተፃፉ ሕግጋት መታወቅና መጠናት ይኖርባቸዋል።

> Increasingly constructive doubt is the sign of advancing civilization. We must put question marks along many of our inherited legal dogmas, since they are dangerously out of line with social facts[55].

የፍሬ ነገር ተጠራጣሪዎች በበኩላቸው በስር ፍርድ ቤት ዳኞች ላይ ያተኩራሉ። በእነሱ አመለካከት ዳኞች የሰው እና የሠነድ ማስረጃዎችን ከመረመሩ በኃላ ተገቢውን ሕግ መምረጥ ሲገባቸው ምስክር እየተሰማ ወይም የሰነድ ማስረጃዎችን እንደሚመረምሩ አስቀድመው ለመረጡት የሕግ ማዕቀፍ ይስማማል በሚሉት መልኩ በመሆኑ ማስረጃው ከአድሎ በፀዳ መልኩ መመዘኑ አጣራጣሪ ይሆናል።

55 Jerome Frank ,Law and the Modern Mind ,1930, Page 159,

የስር ፍርድ ቤት ዳኖች “ቅድመ ውሳኔ” ላይ እንዲደርሱ የሚያደርጓቸው ምክንያቶች የሚታወቁና የማይታወቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ ዳኞች ምስክር የሚሰሙበት ወቅት የምስክሩ ልዩ ባህሪ፣ መልክ፣ የንግግር ዘይቤ በሚሰጠው ምስክርነት ላይ ያላቸውን አመኔታ ሊቀንሰው ይችላል። በተያያዘም የባለጉዳዩ ባህሪ፤ ግለ ታሪክ፤ አሳዛኝነት እና መሰል ሁኔታዎች ከዳኛው ቅድመ ታሪክ ጋር በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ መልኩ ተገናኝቶ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሚሠጠው ውሳኔ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

ፍራንክ ጀሮም በሕግም ፍልስፍናም የተመረቀ ተመራማሪ እንደ መሆኑ የአሜሪካን የሕግ ፍልስፍና አንድ ደረጃ ከፍ አድርጎታል። በዳኝነት በሰራባቸው ዓመታት የተመለከተውን በሙሉ ከራሱ አመለካከት ጋር በማዋሃድ “Law and the modern mind” የተሰኘውን ድርሳኑን አሰናድቷል። ይህ መፅሃፍ ለአሜሪካ ገዛዳዊ ሥነ-ሕግ አቀንቃኞች እንደማጣቀሻ ከማገልገሉም በላይ የፍትሕ ስርዓቱን ያነጋገረ ነበር። ፍራንክ ጀሮም ራሱ የአእምሮ ህክምናውን ከተከታተለ በኋላ በሥነ-ልቦና እና በሕግ በተለይም ደግሞ በዳኝነት መሀከል ያለውን ግንኙነት ለማጥናት ጥረት አድርጓል።

እንደ እርሱ አመለካከት የዳኞች ውሳኔ ከሥነ-ልቦና ውቅራቸው የሚመነጭ በመሆኑ ዳኞች በሕግጋቱ መሀከል ክፍተት ሲያገኙም ሆነ በተለመደው የሕግ ትርጉም ሥራቸው በምንም መልኩ የስነ-ልቦና ተፅዕኖች አያድርባቸውም ማለት እንደማይቻል ተከራክሯል። ፍራንክ በኦሊቨር ዌንድል ሆልምስ ተፅዕኖ ስር የወደቀ ለመሆኑ ብዙ ማሳያዎች ከመኖራቸውም በላይ ራሱም በተደጋጋሚ የገለፀው ነው። የሕግ ትርጉም ተገማች እና የተወሰኑ የሥነ-ስርዓት ሂደቶችን የሚከተል ”Mechanical” የሆነ ሂደት እንደሆነ ተደርጎ መቅረብ እንደሌለበት ይህም ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ እንደሆነ ያምናል።

በመጽሐፉ ካቀረባቸው እና የእርሱ ሳይኮ አናሊቲክ አስተምህሮ እና መርህ ተደርጎ የሚወሰደው ይህ ምሳሌ ነው። የሰው ልጆች በእናታቸው ማህፀን ውስጥ ሲኖሩ የተደላደለ፣ ምቹ እና የተጠበቀ ኑሮ እንደሚኖሩ እና ገና "ሽል/Embryo" እያሉ የሚኖሩበት ሐሳብ የለሽ የተንደላቀቀ ሕይወት በኃይለኛው ምጥ ወደዚህ ዓለም ሲቀላቀሉ ይጠፋል። ከዚያ በኋላ በህይወት ዘመናቸው ሙሉ ራሳቸውን ለመቻል ሲታትሩ ይኖራሉ። በህፃንነት እድሜያቸው ከማህፀን ዓለም ከተለያዩ በኋላ በእናታቸው ማህፀን ውስጥ ውስጥ የነበረውን መደላደል እና ምቾት ከአባታቸው ክንድ ከሚሰጣቸው ድጋፍ እና ከለላ ይጠብቃሉ።

ይሁን እንጂ እያደጉ እና በስሜት፣ በእውቀት እና በአካል እየጎለበቱ ሲሄዱ አባታቸው የሚሰጣቸውን ከለላ "Security" ወደ መንግስት ሕግ ያስተላልፉታል። ከዚያ በኋላ የመንግስት ሕግ ልክ እንደ ወላጅ አባታቸው እንዲጠብቃቸው ይጠብቃሉ። ይሁን እንጂ ሕግጋት የሰው ልጆችን ፍጹም በሆነ መንገድ ሊጠበቁ እና ሊከልሉ አይችሉም። በመሆኑም ሰዎች ከዚህ የህፃንነት ዓለም ወጥተው በስሜት ሊጎለብቱ እና የፍትሕ ስርዓቱ እና ፍርድ ቤቶች የማይገመቱ እና የማይጠበቁ ውሳኔዎች ሊወስኑ እንደሚችሉ መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ይህ የፍራንክ ትንተና "Father fixation" በተደጋጋሚ ጊዜ የተገለፀ ሕግን እና ሥነ-ልቦናን በማዛመድ የተገኘ አስተምህሮ ነው።

ማኅበረሰባዊ ምህንድስና - ሮስኮ ፓውንድ

"ሕግ የማኅበረሰባዊ ምህንድስና መሣሪያ ነው"

በገሃዳዊ ሥነ-ሕግ ጥላ ስር በንዑስ ርዕስነት ፓውንድን (1870-1964) ያስቀመጥነው ምንም እንኳ በጎላ ላይ ራሱን ከገሃዳዊ ሥነ-ሕግ እንቅስቃሴ የነጠለ ቢሆንም የገሃዳዊ ሥነ-ሕግ ጠንሳሽ የሚባል ሰው ስለነበር ነው። ፓውንድ በሐርቫርድ ዩኒቨርስቲ አስተምሯል፤ የሕግ ትምህርት ቤቱ ዲንም በመሆን አገልግሏል። ፓውንድ ሕግ የማኅበረሰባዊ ምህንድስና (Social engineering) መሣሪያ እንደሆነ ያምን ነበር። ሕግጋት ሲወጡ እና ሲተገበሩ አንድ የተለየ ማኅበረሰባዊ ፋይዳ እንዲኖራቸው ተደርጎ መቀረፅ ይኖርባቸዋል ሲል አስተምሯል። ከዚህም የተነሳ (Sociological Jurisprudence) ቤተ አስተምህሮ አስጀማሪ እንደሆነ ተደርጎ ይወሳል።

> This somewhat wide list of tasks for the modern sociological jurist is a perfect example of how Pound tended to mix methodological as well as normative approaches to create his new theory. He looked at legal history, surveyed in detail a huge body of legal philosophy, and also discussed real legal problems. His 5 volumes of Jurisprudence provide a vast body of knowledge about a great many things from Comte to Ehrlich, the code of Hammurabi or the Anglo Saxon dooms. In carrying out these studies, Pound reached the conclusion that his sociological jurisprudence would focus more on how law develops due to the link between law and society rather than an analysis and interpretation of statutes and cases[56].

56 Elise Nalbandian, Socioliogical Jurisprudence;Roscoe Pounds Discussions on legal interests and Jural Postulates, Mizan Law Review,Vol 5,No.1,2011

በርግጥ ከገሃዳዊ ስነሕግ እንቅስቃሴ እንዲርቅ ካደረጉት ምክንያቶች አንደኛው ከተዋቂው የገሃዳዊ ስነሕግ አቀንቃኝ ካርል ሌውሊን(Kar LLewiyn) ጋር በተለዋወጠው የጽሑፍ ኃይለ-ቃል አማካኝነት ባሳደረው ቁመኝነት እና ፍራንክሊን ዲ-ሩሰቬልት የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችን ቁጥር ከዘጠኝ ወደ አሥራ አምስት ከፍ ለማድረግ የፍርድ ቤቱን ውሳኔዎች ለ New Deal እንቅስቃሴ ተገገር እንዲሆኑ ለማድረግ ያደረገውን ጥረት በመቃወም ነበር።

ምንም እንኳ ፓውንድ የNew Deal እንቅስቃሴ ደጋፊ የነበረና የእርሱ ፍልስፍናዎችም ለሩዝቬልት እንቅስቃሴዎች መሠረት እንደነበሩ ቢነገርም መጨረሻቸው አላማረም። ፖውንድ የሕግን ወግ አጥባቂነት (Legal formalism) ማለት ሕግጋት የማይቀየሩና የማይለወጡ ስለሆኑ ሊነኩ አይገባም የሚለውን አስተሳሰብ የሚተች ሲሆን ሕግጋቱ የማኅበረሰቡን ሕይወት እና አንገብጋቢ ችግሮች ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መራቀቅ እና መተርጎም እንደሚኖርባቸው እና የሕግ ጥናት እና የማኅበረሰብ ጥናት እጅና ጓንት ሆነው ካልሄዱ የሚፈለገውን የፍትሕ ደረጃ ማምጣት እንደማይቻል በሰፊው ፅፏል።

ሮስኮ ፓውንድ የገሃዳዊ ሥነ-ሕግ ጠንሳሽ ተደርጎ ቢወሰድም ከካርል ሌውሊን ጋር ያደረገው ሙግት ከምሁራዊ ጥናት ዳስሳ ተገልሎ እንዲኖር አድርጎታል። በ 1931 (እ.ኤ.አ) ሌውሊን በጻፈው እና ቀደም ብሎ በተጠቀሰው መጣጥፍ የገሃዳዊ ሥነ-ሕግ ምሁራን ብሎ ከዘረዘራቸው ሰዎች መሀከል ሮስኮ ፓውንድን ሊያካትተው አልፈቀደም። ፓውንድ ግን በሀገረ አሜሪካ በ1920ዎቹና 1930ቹ ከተነሱት ወጣት የገሃዳዊ ሥነ-ሕግ ምሁራን በዕድሜ ገፋ ያለ ከመሆኑም ባሻገር ቀደም ብሎ የሕግ ወግ አጥባቂነትን (Legal formalism) ተችቷል። በሁለቱ መሀከል ያለው ፀብ ግላዊ ቢሆንም ሁለት የተለያዩ የሕግ ፍልስፍናዎች እንዲበለፅጉ ምክንያት ሆኗል።

ሌውሊን በ1931 (እ.ኤ.አ) “Some realism about realism በሚል የጻፈው ጽሑፍ በቀጥታ ለሮስኮ ፓውንድ የተሣፈ ነው። ምክንያቱም ፓውንድ ቀደም ብሎ በጻፈው ፅሑፍ ካርል ሌውሊን እና ፍራንክ ኸርሮሞ የሚጠቀሙት ቃል እና ፅንፈኛ አቋማቸውን በመተቸት ፅፏል። ለዚህ ምክንያት የሆነው ካርል ሌውሊን ጋር አብረው እንዲሠሩ በኮሚሽን በወሰዱት ሥራ ሊስማሙ አለመቻላቸው ነው። አስገራሚ በሆነ ሁኔታ በሁለት ምሁራን መሀከል የተነሳው የግል ፀብ ሁለት ተቃራኒ የሚመስሉ ቤተ-አስተምህሮዎች እንዲፈጠሩ ሰበብ ሊሆን ችሏል። ይሁን እንጂ ገሃዳዊ ሥነ-ሕግ እና ማኅበረሰባዊ ሥነ-ሕግን ቀረብ ብለን ስንፈትሻቸው ከሚለያቸው ይልቅ የሚያቀራርባቸው ጉዳይ እጅግ ብዙ ነው።

ሁለቱም ሕግ ከዲበአካላዊ እና ሞራላዊ ይዘት መላቀቅ እንዳለባቸው ይገልፃሉ፤ ሁለቱም ሕግ መንገድ እንጂ ግብ እንዳልሆነም ይቀበላሉ። ካርል ሌውሊ እና ሮስኮ ፓውንድ ከዓመታት በኃላ የነበረባቸውን ፀብ አስወግደው በጋራ ብዙ ሥራዎችን አበርክተዋል። ይሁን እንጂ ብዙ ሰዎች አሁንም ቢሆን የገሃዳዊ ሥነ-ሕግ የመንፈስ አባት አድርገው የሚወስዱት ኦሊቨር ዌንዴል ሆልሞስን እንጂ ሮስኮ ፓውንድን ያለመሆኑ በሁለቱ መሀከል የነበረው ፀብ ምክንያት እንደነበር ይገልፃሉ።

ለሮስኮ ፓውንድ መብት ማለት ሰዎች በጊዜ ውስጥ የሚያዳብሩት ጥቅም ነው። በመሆኑም እነዚህ ጥቅሞች/መብቶች እውቅና ሊሰጣቸው፣ ሊጠበቁ እና ሊፈፀሙ ይገባል፤ይህንን የሚያደርገው ሕግ ነው። ይሁን እንጂ መብቶች ሁሉ የተወሰነ ገደብ ሊኖራቸው ይገባል። መብቶች የግለሰብ፣ የማኅበረሰብ እና መንግስታዊ (Public interest,social interest and private interest) በሚል ይመደባሉ። የግለሰብ መብት ከግለሰቡ ጋር ብቻ የተያያዘ ሲሆን መንግስታዊ መብቶች ደግሞ መንግስት የሕዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚጎነፀፋቸው ናቸው። ማኅበረሰባዊ መብቶች ለመንግስት በይፋ ያልተሰጡ ግን በማኅበረሰቡ ብቻ የተቀመጡ እና በጥቂቱ ከመንግስታዊ መብቶች የሚለዩ ናቸው። መብቶች ሁልግዜም ተፎካካሪ እና ተወዳዳሪ

መሆናቸው ስለሚታወቅ ዳኞች ራሳቸውን እንደ ማኅበራዊ መሃንዲስ ማየት አለባቸው። በመሆኑም ሕግጋት በሚፀድቁበት በሚሻሻሉበት እና በሚተረጎሙበት ወቅት ማኅበረሰባዊ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ሊገቡ ይገባል።

ሕግ ከመውጣቱ በፊት ማኅበረሰባዊ ሁኔታዎች (Social facts) በአግባቡና ረዘም ላለ ጊዜ ሊጠኑ፤ ሕግጋቱ ከወጡም በኋላ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ተፅዕኖ እና ፋይዳ ያለማቋረጥ የሚመረመር ካልሆነ ሕግጋቱን በማውጣት ልናሳካው ያሰብነው ማኅበረሰባዊ ምህንድስና ሊሳካ አይችልም። በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚመጡ ለውጦች ምክንያታዊ እና ፍትሐዊ መሆን አለባቸው፤ ለዚህ ደግሞ በየሀገሩ ያለ የፍትሕ ሚኒስቴር ይህንን ሊሰራ ይገባል። የሕግ ባለሙያዎች ራሳቸውን እንደ ማኅበራዊ መሃንዲስ የሚያዩ ከሆነ ሕግ ደግሞ የእነሱ የምህንድስና መሣሪያ ነው። ማኅበረሰቡ ተፎካካሪ የሆኑ መብቶች መሃል የሚገኝ መሆኑ ስለሚታወቅ ከእነዚህ መብቶች መሀከል ለማኅበረሰቡ የተሻሉ እና የሚጠቅሙ የምንላቸው ተመርጠው በእነርሱ አላማነት ማኅበረሰቡን ወደ ተፈለገው ግብ እንዲደርስ ልንቀርፀው ይገባል።

የማኅበረሰብ ምህንድስና የሕግ ጥናት (Sociological Jurisprudence) የማኅበረሰብ ጥናት (Sociology) አንደኛው ክፍል አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፤የማኅበረሰብ ጥናት ሰፊ እና ጥልቀት ያለው የጥናት ዘርፍ ሲሆን የፓውንድ ፍልስፍና የሚያጠናው ሕግና ማኅበረሰብ መሃል ባለው ግንኙነት ብቻ ነው። ቀደም ብለን እንዳነሳነው በግለሰብ መብት እና መንግስታዊ መብት መሃል የጥቅም ግጭት ሊነሳ ይችላል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው “The Right to privacy” ነው። ሰዎች ቤታቸው እና ግላዊ ግንኙነታቸው ያለ እነርሱ ፍቃድ እንዳይጣስ እና እንዳይበረበር ይፈልጋሉ፤መንግስት ደግሞ ማኅበረሰቡን ከሽብርተኞች ጥቃት የመከላከል ግዴታ ስላለበት በሁለቱ መብቶች መካከል ሁልጊዜም ግጭት ይኖራል። በዚህ ጊዜ ዳኞች እና ሕግ አውጪዎች ራሳቸውን እንደ ማኅበረሰባዊ

መሃንዲስ የሚመለከቱ ከሆነ ምን ዓይነት ማኅበረሰብ መገንባት እንሻለን የሚለውን ጥያቄ ከማኅበረሰቡ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ መመለስ ይኖርባቸዋል።

በመሠረቱ ገሃዳዊ ሥነ-ሕግ (Legal realism) እና ማኅበረሰባዊ ምህንድስና ሥነ-ሕግ (Sociological Jurisprudence) የሚያመሳስላቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ሁለቱም ወግ አጥባቂ ሥነ-ሕግ (Legal Formalism) ይቃወማሉ፤ ተጨባጭ ማኅበረሰባዊ ሁኔቶች እና ችግሮች ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ያምናሉ እና ሕግ ሁልጊዜ የማይቀየር እና ተገማች መሆኑን ይቃወማሉ። ሮስኮ ፓውንድ ፍራንክ ጄሮም በይፋ ከመታወቁ በፊት ሥራዎቹን መጻፍ እና ማስተዋወቅ የጀመረ ሲሆን ለጥቂት ጊዜም አብረው ሰርተዋል። ይሁን እንጂ ምክንያቱ ምን እንደሆነ በማይታወቅ መልኩ በመካከላቸው በተፈጠረ ፀብ የገሃዳዊ ሥነ-ሕግ አቀንቃኞች ሮስኮ ፓውንድን ክፉኛ በመተቸት አካሄዳቸውን ለይተዋል። ፍራንክ ጄሮም ራሱ ለፓውንድ ብቻ ባዘጋጀው ጽሁፍ ፍልስፍናውን ሊያጣጥል ሞክሯል። ሕግን መለኮታዊ እና ልማዳዊ ከሆነ ተደጋጋሚ እና አሰልቺ አሠራር በመነጠል የማኅበረሰቡን የዳኞችን እና የሌሎች ሕግ ባለሙያዎቹን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ሕይወት ያለው የጥናት እና የምርምር ዘርፍ እንዲሆን ብዙ ጥረዋል። ዛሬ ሕግን ከልዩ ልዩ የማኅበረሰብ ሳይንስ ጥረቶች ጋር እያዛመዱ መመራመር የተለመደ ሆኗል።

ምዕራፍ ስድስት

ነቂሳዊ የሕግ ፍልስፍና

ይህ ፍልስፍና የተለያዩ የሕግ አስተምህሮዎችን ያቀፈ ቤተ አስተምህሮ ነው። ነቂሳዊ የሕግ ፍልስፍና (Critical legal theory) የጀመረው በ1970ቹ (እ.ኤ.አ) በሀገረ-አሜሪካ ሲሆን አጠቃላይ ሀሳቡም የሕግ ስርዓቱ ታሪካዊ ሂደት በግልፅ እና በአፅንኦት ያልተመረመረ በመሆኑ በአንዳንድ ሕዳጣን የማኅበረሰብ ክፍሎች የመገለል እና የመገፋት ስሜትን የሚያሳድር ነው። በመሆኑም በታሪክ ውስጥ የፍትሕ ስርዓቱ በእነዚህ የኅበረተሰብ ክፍሎች ላይ ያሳደረውን ማኅበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተፅዕኖ በማጥናት ለሕዝብ ግልፅ መሆኑ መንገዶች በማሳተም የንቃተ-ህሊናን ደረጃ ከፍ ማድረግ ነው።

አሜሪካኖቹ በየዓመቱ June 12 የሚያከብሩት በዓል አላቸው Loving day ይባላል። በ1967 ዓ.ም የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ፀረ ድብልቅ ጋብቻ ውሳኔ ተከትሎ የሚከበር ነው። ታሪኩ ሲጀምር Richard Loving የሚባል ነጭ ወንድ እና Mildred Loving የምትባል ጥቁር ሴት በቨርጂኒያ ሀገረ ግዛት ትዳር ይመሰርታሉ። በወቅቱ የክፍለ ሀገሩ ሕግ ነጭ እና ጥቁር እንዳይጋቡ የሚከለክል በመሆኑ የአንድ ዓመት የእስር ቅጣት ይጣልባቸዋል። ጉዳዩን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያፀናውም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 14 ኛውን የሕገ-መንግስት ማሻሻያ (the equality right and due process right) የክፍለ ሀገሩ ፍርድ ቤቶች ጥሰዋል

በሚል የእስር ትዕዛዙን አንስቶላቸዋል[57]። የአሜሪካ ታሪክ የዘረኝነት ብቻ ሳይሆን የፍቅር ታሪክም ነው፤ ስማቸው Loving መሆኑ ራሱ ስምን መልአክ ያወጣዋል እንዲሉ ነው፤ነቂሳዊ የሕግ አስተምህሮ እንዲህ ባለ ዘመን የበቀለ ነው።

የዚህ አስተምህሮ የመንፈስ ወላጅ ገሃዳዊ የሕግ አስተሳሰብ (Legal Realism) እንደሆነ ይታሰባል ይሁንና የዚህ ፍልስፍና አራማጆች በ1970 እና 60ቹ በጥቁሮች መብት አንቅስቃሴ፤ በሴቶች መብት እንቅስቃሴ እና የፀረ-ቬትናም ጦርነት እንቅስቃሴ ሳቢያ የተወለዱ ናቸው[58]። በሕግ እና በፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም መሀከል ቀጥተኛ እና ያፈጠጠ ውህደት እያለ ያንን በመካድ የሕግ ስርዓቱን ማስቀጠል ተገቢነት የለውም፤ በስልጣን እና በሕግ አተረጓጎም እና ማርቀቅ መሀከል ያለው ግንኙነት በታሪክ ውስጥ ተገቢውን ስፍራ ላላገኙ እንደ ጥቁሮች ሴቶች፤ ድሃ የጎበረተሰብ ክፍሎች ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት በማለት ተከራክረዋል።

> One of the greatest merits of the critical legal studies movement was to have created an intellectual space in which law and legal thought could be better used to resist the dictatorship of no alternatives. Its limited but important contribution to such resistance was the development of ideas about alternatives, made from the contradictions and variations in established law. The greatest failure of the movement was not to have embraced and executed this task more fully[59]

57 Loving Vs Virginia, 388 US Supreme Court 388 (1967)

58 Duncan Kennedy and Karl E. Klare, “A Bibliography of Critical Legal Studies,” Yale Law Journal, Vol. 94 (1984)

59 Roberto Mangabeira Unger , The Critical Legal Studies Movement: Another Time, A Greater Task (2015), Harvard Press, P.15

በመሆኑም በዚህ አስተምህሮ ስር የሚታቀፉ ምሁራን የራሳቸውን ፍልስፍናዊ አስተሳሰብ የሚፈጥሩ ሳይሆኑ ከእነሱ ቀድሞ የተፈጠረን የሕግ አሠራር እና ጥናት የሚነቅሉ፤ የሚተቹ እና የሚፈትሹ በመሆናቸው አጠቃላይ አስተሳሰባቸው ይህ ነው ብሎ ለመበየን አዳጋች ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ የጋራ የሆኑ ነጥቦች እንደሚያግባቧቸው መገመት አያዳግትም። ለምሳሌ ያህል ሕግ አንዳንዴ ግልፅነት የጎደለው እና አጣራጣሪ እንደሚሆን ይህም የሚፈጠረው በሕጉ ውስጥ ባሉ ክፍተቶች እና ተቃርኖዎች መሆኑ ሁሉም የነቂሳዊ ሥነ-ሕግ አሳቢዎች የሚጋሩት ነው። ለእነሱ ሕጉ አንዳንድ የጎበረተሰብ ክፍሎችን እኩል የማያስተናግድ በመሆኑ ግልፅ ያልሆነና የሆነ አድልዎ ያዘለ ነው። በዚህም ምክንያት ጥቂቶች ስልጣናቸውን እና የበላይነታቸውን የሚያስጠብቁበት መሣሪያ በመሆን እያገለገለ ይገኛል።

ከዚያም በላይ ሕጉ የተረቀቀበት አላማ ግብ ተኮር ያልሆነ እና የተወሳሰበ በመሆኑ ይህንኑ ማጥራት (Demystify) ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል። ይህ አስተምህሮ ረዥም ለሚባል ዘመን በአውሮፓ እና አሜሪካ ባሉ የፍትሕ ስርዓቶች ላይ ያለ ማቋረጥ ብዙ ትችቶን ያቀረበ በመሆኑ አንዳንዶች እንደ አፈንጋጮችና ሰርዓት አልበኞች ሊፈረጁቸው ችለዋል። ሆኖም በዓለም የፍትሕ፤ የኢኮኖሚ እና ፖለቲካ ምህዳር ላይ ያሳረፉት ተፅዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም።

ነቂሳዊ የሕግ ጥናት ግራ ዘመም ቤተ-አስተምህሮ መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ። በመሆኑም በካፒታሊስት ስርዓተ መንግስት ውስጥ ያለውን የመደብ ልዩነት እና ጭቆና በሕግ ስርዓት ውስጥ የሚንፀባረቅ መሆኑን አምርሮ ይቃወማል። በርግጥ ነቂሳዊ የሥነ-ሕግ ምርምር በሕግ ላይ ብቻ ያተኮረ እና ማዕቀፉም ጠበብ ያለ እንቅስቃሴ ቢሆንም በተመሳሳይ ወቅት በአውሮፓ ውስጥ ነቂሳዊ የማኅበረሰብ ጥናት (Critical social theory) የሚባል ቤተ-አስተምህሮ ከፍተኛ ተቀባይነትን አግኝቶ ነበር። እነዚህ ሁለት የጥናት እና የምርምር ዘርፎች እርስ በእርሳቸው ሊደጋገፉ የሚችሉ ቤተ-አስተምህሮዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም።

ነቂሳዊ የማኅበረሰብ ጥናት ዋነኛ አቀንቃኞች ጆርገን ሃበርማስ፣ አንቶንዮ ግራምሺ፣ ኸርበርት ማርኩሰ፣ ቴዎዶር አዶርኖ፣ ማክስ ሆካይመር እና የመሳሰሉት ናቸው። ዋነኛ አላማቸው ማኅበረሰቡ በልማድ እና በአስተሳሰብ ከተጫኑበት ኋላቀር አመለካከቶች ማላቀቅ ነው። እነዚህ እንቅስቃሴዎች በኋላ ላይ በስፋት ለታወቀው የድህረ-ዘመናዊነት እንቅስቃሴ መሠረት የጣሉ ናቸው። በመሠረቱ ዘመናዊው የሰው ልጆች እድገት ክፍል የሚጀምረው ከአብርሆት በኋላ የሰው ልጅ በአመክንዮ፣ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ሒሳብ ተጠቅሞ በመካከለኛው ዘመን ይዳክርበት ከነበረው ጨለማ መላቀቁ ነው።

ይህ የምርምር እና የጥናት ሂደት ለብዙ ዘመናት ከቀጠለ በኋላ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ሲደርስ እንዲቆም ተገዷል። በዚህም ምክንያት አመክንዮ እና ሳይንስ እስከዛሬ ለሰው ልጆች የሰጡት ጥቅም በራሱ መመርመር አለበት፤ ምክንያቱም ሁሉም የተፈጥሮ እና የማኅበረሰብ ሳይንስ ግኝቶች እንደማይነኩ እና የማይቀየሩ አድርገን መሳል የለብንም እንዲያውም የሰው ልጆች "አመክንዮ" ላይ ከፍተኛ እምነት የጣሉ በመሆኑ ሁሉም ማኅበረሰባዊ ተቋማት እና የአስተሳሰብ ውቅሮች በድጋሚ ሊፈተሹ እንደሚገባ አስተምህሮው ያስረዳል። ይህ አስተሳሰብ በመሠረታዊነት የተፈጠሩ የማኅበረሰብ ውቅሮች መንቀስ፣ መፈተሽ፣ ማረጋገጥ እና ሲብስም ማፍረስን እንደ ግብ የያዘ በመሆኑ አመለካከቱ ሁልጊዜ መርማሪ እንጂ ፈጣሪ አይደለም። ከመፈተሽ ውስጥ የሚገኝ እውነታ በመኖሩ ይህንኑ ለማስረዳት ይሞክራል።

ይህ እቅስቃሴ በ1960ዎቹ በአውሮፓ እና አሜሪካ ሲጀመር ብዙዎቹ የተመለከቱት እንደ ማርክሲስታዊ ግራ ዘመም እንቅስቃሴ ሲሆን ኮሚዩኒዝም ከሞተበት አፈሩን አራግፎ መጣ ሲሉ ሌሎች እውነተኛ ማርክሲስት ነን ባዮች ደግሞ እውነተኛውን የማርክሲስት አስተምህሮ የሚከልሱ "ኑፋቄ ማርክሲዝም" አስፋፊዎች አድርገው ይስሏቸዋል። ይሁን እንጂ አብዛኞቹ የዚህ ቤተ-አስተምህሮ አቀንቃኞች ማርክሲስት አስተሳሰብንም በጥልቀት ተችተዋል። ይሁን እንጂ ብዙ ሰዎች ከሚያቀርቡበት የሰላ ትችት አንዱ

ነቂሳዊ የማኅበረሰብ ጥናት “ሳይንስ እና አመክንዮ” የጭቆና መሣሪያ እንደሆኑ በመሳል ክፉኛ ቢተቿቸውም የእነርሱን የሚተካ የተሻለ ስርዓተ-ሐሳብ አላቀረበም። እንዲያውም ሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን ሳይንሳዊ ባልሆነ ስርዓት የሚተች በመሆኑ መርህ አልባ አስተምህሮ እንደሆነ አድርገው ይስሉታል።

እንግዲህ ነቂሳዊ የሥነ-ሕግ አስተምህሮም ከዚሁ አስተሳሰብ ጋር በመንፈስ የሚተሳሰር እንቅስቃሴ ነው። በመሆኑም ሕግ የባለሀብቱ፣ የነጮች፣ የባለስልጣኑ፣ የወንዶች እና የመሰል ጉልበተኞች መጠቀሚያ መሣሪያ መሆኑን አስቀርተን የማኅበረሰባዊ ለውጥ መሣሪያ እንዲሆን እንዴት ማድረግ ይቻላል? የሚለው ነጥብ ሁሉንም የዚህ ቤተ-ጥናት አባሎች ያስማማል። ለዚህ እንቅስቃሴ በፍጥነት ምላሽ የሰጡት ጥቁሮች እና ሴቶች ሲሆኑ በወቅቱ የአሜሪካ የሕግ ስርዓት በአብዛኛው እነዚህን የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚጨቁን ስለነበር በልዩ ልዩ መንገድ ትችት እንዲቀርብበት የሚጋብዝ ስርዓት ነበር። ሕግ እንደሚባለው ተገማች እና ተመሳሳይ ሳይሆን ጉልበተኞችን እንዲያገለግል በቀላሉ ልንጠመዝዘው የምንችል መሣሪያ ነው። ለዚህ ደግሞ በታሪክ ውስጥ ያሉ የኢኮኖሚ እና የመደብ ልዩነቶች በሕግ እንደታገዙ በማሳየት ማኅበረሰቡን ማንቃት እንዳለባቸው ብዙዎቹ የዚህ አስተምህሮ አቀንቃኞች ያምኑ ነበር።

ድህረ- ዘመናዊነት እና ሕግ

“አገጻጹዊነት እና አፍሁሸነት”

ድህረ- ዘመናዊነት በ20ኛው ክፍለ ዘመን ማለቂያ አካባቢ በተለያዩ ፈላስፎች፤ ተመራማሪዎች እና የንባብ ሰዎች በተለያየ መልክ እና ቋንቋ እየተገለፀ እዚህ የደረሰ አስተሳሰብ ነው። ድህረ-ዘመናዊነት ከዘመናዊነት ቀጥሎ ያለ ዘመንን እና ሥርዓትን የሚወክል ቃል ነው። ዘመናዊነት የሰው ልጅ ከመሀከለኛው ዘመን ጨለማ በጠንካራ አመክንዮ፤ በሳይንስ እና

ቴክኖሎጂ ተላቅቆ በመውጣት የፈጠረውን ወቅት ይወክላል። ዘመናዊነት (Modernity) በፍልስፍናዊ ፅንሰ ሐሳብነት ሲመረመር የሳይንስ እና የምክንያታዊነት ፍጹማዊ ገናናነትን ይወክላል፤ ከዘመነ አብርሆት (Enlightenment) ጊዜ ጀምሮ እየተስፋፋ የመጣው ይህ የሳይንስ እና የአመክንዩ ገናናነት ለአንዳንድ የሥነ-ጥበብ እና የሳይንስ ተመራማሪዎች ሊዋጥላቸው አልቻለም።

ለምሳሌ በማኅበረሰባዊም ሆነ በተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፎች መሀከል እና ውስጥ ያለው ድንበር ጠንካራነት እና አይነኬነት እንዲሁም የአንዳንድ ቀመሮች፤ መርሆች፤ ንድፈ ሐሳቦች፤ ሕጎች እና አስተምህሮዎች አይደፈሬነት ለብዙ ሰዎች የሚያጠግብ ሊሆን አልቻለም። በመሆኑም ብዙ ተመራማሪዎች የሥነ-ጥበብ ሰዎች፤ ምሁራን ከተለመደው "ሳይንሳዊ" እና "ምክንያታዊ" ማዕቀፎች ሆነ ብለው በማፈንገጥ የራሳቸው ሥነ-ጥበባዊ እና ሳይንሳዊ ሐሳቦችን ማቅረብ ጀመሩ። ይህ አፈንጋጭነት በሕግ፤ በሳይንስ፤ በስዕል፤በሙዚቃ፤ በሥነ-መለኮት እና በፍልስፍና መታየት ሲጀመር ሰዎች በተለያዩ ዘርፎች ያሉትን እነዚህን መሰል አካሄዶች የድህረ-ዘመናዊነት ውጤት ሲሉ ሰይመዋቸዋል።

በመሆኑም ድህረ-ዘመናዊነት **በአፍራሽነት** (Deconstructionism) **እና በአንፃራዊነት** (Relativism) ይወክላል። አፍራሽነት ቀደም ሲል የጠቀስናቸውን የአስተሳሰብ ዘርፎች ድንበር እና ልዩ ልዩ መርሆች ገናናነት ማፍረስ እንደሚገባ ሲያስረዳ እንደ ጃኪውስ ዲራይዳ ዓይነት ፈላስፎች በብዛት እንዳስፋፉት ይገልፃል። አንፃራዊነት በበኩሉ በእነዚህ ድንበሮች መሀከል ያለው ልዩነት ከፈረሰ እውነትን ፍፁማዊ በሆነ መንገድ ማግኘት አንችልም፤ ፍፁማዊ እውነት (Objective truth) የሚባለው ተምኔታዊ የሆነ የማይጨበጥ ቅዠት እንደሆነ ያስተምራል። ይህ ሰፊ የሆነ አስተሳሰብ በሁሉም የትምህርት ዘርፎች ውስጥ ሰርፆ እንደገባው ሁሉ በሕግ ጥናት እና ምርምር ውስጥም ሰርፆ ገብቷል።

ሕግ ሲረቀቅ እና ሲፀድቅ ከዚህ በፊት ተስፋፍተው በነበሩ ቅድመ እውቀቶች ሳቢያ የሚታወቁ እና የሚገመቱ ሂደቶችን ያልፋል፤ ሕግ ሆኖ ከታወጀም በኃላ በፍርድ ቤቶች ውስጥ ሲተረጎም በማኅበረሰቡ ውስጥ ከነበሩ እና በጥልቀት ከሰረፁ እሳቤዎች ጋር የተያያዘ ነው። በመሆኑም እነዚህን ማኅበረሰባዊ አይነኬ እሴቶች መንግስታዊ አሰራሮች ከሌላ ዕይታ ተመልክተው ሕጉን ሊተገብሩት እንደሚገባ ያስረዳሉ። ድህረ-ዘመናዊ ፍልስፍና ዘር-ተኮር የሕግ አስተምህሮ፤ "ሴታዊ" የሕግ አስተምህሮ፤ የብዝሃ- ሕግ ፍልስፍና እና መሰል የሕግ አስተምህሮዎች እንዲነቃቁ እና እንዲነሱ ከፍተኛ የፍልስፍና ድጋፍ አድርጓል። ለምሳሌ ያህል ዘር-ተኮር የሕግ አስተምህሮ (Racial legal theory) በሀገረ- አሜሪካ ውስጥ ሲያብብ የሀገሪቱ ሕግ በነጮች እና በጥቁሮች መሀከል የተዛባ ግንኙነት እንዲኖር በሚታወቁ እና በማይታወቁ መስኮች ጥቁሮችን እየበደለ ይገኛል በሚል የተነሳው አስተምህሮ በአብዛኛው የድህረ-ዘመናዊ ፍልስፍና ድጋፍ ያለው ነበር። ድህረ-ዘመናዊነት ዛሬም ቢሆን በሕግ ስርዓቱ ውስጥ በልማድ ተይዘው ያሉ አስተሳሰቦችን እና የማይደፈሩ ድንበሮችን ለማፍረስ አዲስ ሕግጋት እና አሠራሮች እንዲመነጩ በማድረግ ላይ ይገኛል።

ጆርገን ሃበርማስ- የግንኙነት መርህ

"ሕግ የተግባቦት መሣሪያ ነው"

ሃበርማስ (1929-) ጀርመናዊ የፍልስፍና እና የኅብረተሰብ ጥናት ተመራማሪ የነበረ ሲሆን የፍራንክፈርት ቤተ-አስተምህሮ ተከታይ ነበር። ሃበርማስ "The Theory of communicative Action" እና "Between Facts and Norms" የተባሉ ሁለት ድርሳናት ሲያዘጋጅ ስለ ሕግ እና ማኅበረሰብ መስተጋብር ሰፊ ዳሰሳ አስቀምጧል። ለሃበርማስ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ቀጣይነት ያለው እና የተረጋጋ ስርዓት ለመፍጠር የማያቋርጥ ግለሰባዊ እና ማኅበረሰባዊ ውይይት ያስፈልጋል። ይህ በአመክንዩ በሚመሩ ዜጎች መሀከል የሚደረገው የተናጥል እና የጋራ ውይይት ቀስ በቀስ ወደ አንድ የጋራ መግባባት ያደርሳል።

ይህ የጋራ መግባባት የሚፈጥረው ማኅበረሰባዊ ሞራል የሥነ-ሕግ ዋነኛ አጀንዳ ነው። ከዚያ በፊት ግን በተደጋጋሚ የሚደረገው ይህ የግለሰብ ከግለሰብ እና የማኅበረሰብ - ከማኅበረሰብ ውይይት አንዳች ገገር ሐሳብ ወይም ተፅዕኖ ይፈጥራል፤ ይህ ገገር ሐሳብ ወይም ተፅዕኖ ደግሞ የግንኙነት ሳይንስን ይወልዳል፤ ይህ የግንኙነት ኃይል በተራው ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እየታገዘ እና እየተመራ አስተዳደራዊ ኃይል ይሆናል። ከማኅበረሰባዊ ውይይት የተለያየ የግንኙነት ደረጃዎችን አልፎ የተፈጠረው ሕግ ሕዝባዊ ቅቡልነት ይኖረዋል። በመሆኑም ሕግ በማኅበረሰብ መሀከል የውህደት እና የተግባቦት መሣሪያ በመሆን ሊያገለግል ይገባዋል። በተጨማሪም የሕገ-ሰብዕ ፍልስፍና ሕግን ከቅጣት እና ትእዛዝ ጋር ብቻ ሲያገናኘው የተፈጥሮ ሕግ ፍልስፍና ደግሞ ሕግን ከልዕለ-ሰብዓዊ የሞራል ምንጭ ጋር ያይዘዋል፤ ይሁን እንጂ ሁለቱም ሕግ በዕለት ተዕለት የሰዎች የተግባቦት ሕይወት ላይ ያለውን ተፅዕኖ ቦታ አልሰጡትም። ሃበርማስ በሌሎች የማኅበረሰብ ሳይንስ አስተምህሮዎች የሚታወቀው "የግንኙነት መርህ" (Discourse principle) የሚለውን አስተምህሮ በማስገኘቱ ነው።

ለሃበርማስ አንድ ድርጊት ሕጋዊነት የሚኖረው በድርጊቱ ወይም በመመሪያው ተፅእኖ የሚደርስባቸው ሰዎች በውሉ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ምክንያታዊ በሆነ ውይይት ከተቀበሉት ብቻ ነው። ይህ እንደሚታወቀው የሕጋዊነት እና የቅቡልነት ጥያቄ እንደመሆኑ አንድ የሕግ ስርዓት የሚያሳየውን የአሳታፊነት እና የአካተችነት ደረጃ ይመረምራል ምክንያቱም የሰው ልጅ ቋንቋ ይመረምራል። ምክንያቱም የሰው ልጅ ቋንቋ በመሠረቱ ትርጉም ያለው ሐሳብ ያዘለ በመሆኑ በውይይት ሁሉ ውስጥ "የተግባቦት አመክንዩ" (Communicative reason) አለ። ይህ የተግባቦት አመክንዩ እንዲዳብር ደግሞ "ሕዝባዊ መድረክ" (Public space) ያስፈልጋል።

ይህ "ሕዝባዊ መድረክ" አካላዊ ሳይሆን ሐሳባዊ ነው። በፊውዳላዊ ስርዓት የባህል ባህሪ የሕዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ የከለከለ እንደመሆኑ

“የውክልና ባህል” ልንለው እንችላለን ምክንያቱም ነገስታቱ እና መሳፍንቱ የሕዝቡን ባህል የሚቀርፁና የሚመሩ ነበሩ፤ ይሁን እንጂ የካፒታሊስቱ ስርዓት የፊውዳላዊውን ስርዓት ሲተካው ይህ የውክልና ባህል ተረስቶ አዲስ “ሕዝባዊ መድረክ” ተፈጠረ። ይህ መድረክ ሀሳባዊ እንደመሆኑ በጋዜጦች፤ መፅሄቶች፤ የውይይት እና የመጻሕፍት ክበባት እና ልዩ ልዩ ማኅበራት እንዲሁም ካፌዎች ሊወክል ይችላል። እነዚህ በሙሉ ለሕዝቡ የውይይት መድረክ በመሆን አገልግለዋል። በመሆኑም ለመጀመሪያ ጊዜ ይህ “ሕዝባዊ መድረክ” መንግስት የማይቆጣጠረው የተፅዕኖ ማዕከል ሆነ። በመሆኑም ቀደም ሲል ያነሳነው ማኅበረሰባዊ ውይይት (public Discourse) እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ መፈጠር እንዳለበት ሃበርማስ አበክሮ ገልፆል።

> As historical and social beings we find ourselves always already in a linguistically structured lifeworld. In the forms of communication through which we reach an understanding with one another about something in the world and about ourselves, we encounter a transcending power. Language is not a kind of private property. No one possesses exclusive rights over the common medium of the communicative practices we must intersubjectively share. No single participant can control the structure, or even the course, of processes of reaching understanding and self-understanding. How speakers and hearers make use of their communicative freedom to take yes- or no-positions is not a matter of their subjective discretion. For they are free only in virtue of the binding force of the justifiable claims they raise towards one another. The logos of language embodies the power of the intersubjective, which precedes and grounds the subjectivity of speakers.[60]

60 Jurgen Habermas , *The Future of Human Nature*, 2003, p. 10

ሃበርማስ ተግባራዊ ተግባቦት በሚለው ፍጹማዊ እና ምናባዊ ግንኙነት ወቅት ሰዎች በእኩልነት እና በቅንነት የሚግባቡበት ሁኔታ ይፈጠራል። በተለምዶ የሰዎች ግንኙነት በስልጣን ግንኙነታቸው ጥላ ስር የወደቀ በመሆኑ ነፃ እና ፍትሐዊ አይደለም። ለምሳሌ አንድ ተማሪ እና ሌክቸረር በአንድ ፅንሰ- ሐሳብ ላይ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ፊት ቢከራከሩ ወይም ደግሞ አንድ የቀበሌ ሊቀመንበር እና የጨረቃ ቤት በቅርቡ በዚያው ቀበሌ የሠራ ሰው ሲነጋገሩ ንግግራቸውን ያሉበት የስልጣን ከፍታ እና ዝቅታ ጫና ስለሚያሳድርበት ነፃ አይሆንም። በመሆኑም በሕግና ማኅበራዊ ውል ስሪት ወቅትም ተዋዋይ ወገኖች በእኩልነት ላይ በተመሠረተ ተግባራዊ ተግባቦት (Communicative action) መሠረት በማኅበራዊ ውሉ ወይም በሚወጣው የመንግስት ሕግ የሚያገኙት እና የሚፈጠርላቸው መብትን አስመልክቶ በሚደረግ ውይይት በእኩልነት የማሳተፍ መብት ሊኖራቸው ይገባል።

ይህም ማለት መብት በሕግ ሲፈጠርላቸውም ቢሆን ይህንኑ መብት እንደያዙ ወይም እንዳላቸው ተደርጎ መታሰብ ይኖርበታል። በመሆኑም ብዙ ሰዎች ሃበርማስ የጆን ሎክን "ሰዎች ከማኅበረሰባዊ ውል በፊትም ቢሆን የሕይወት እና ነፃነት መብት አላቸው" የሚለው እሳቤ እና የነሱን "ዜጎች ማኅበረሰባዊ ውል ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ምንም ዓይነት መብት የሌላቸው እና መብታቸው በማኅበረሰባዊ ውሉ የተፈጠረ ነው" የሚሉት አስተሳሰቦችን ያዛመዳቸው እና የቀላቀላቸው መሆኑን እንረዳለን። ምክንያቱም ሃበርማስ እንደሚለው የሕግ መብቶች ፈጣሪዎች ራሳቸው የመብቶቹ ባለቤቶች ተደርገው መታሰብ ይኖርበታል፤ በዚህም የሕግ መብቶች የመፈጠሩ ጉዳይ በመሠረታዊነት የተዋዋይ ወገኖቹ የፖለቲካዊ ውሳኔ ውጤት መሆኑን ያመለክታል።

አነስታይ የሕግ ፍልስፍና

"አባታዊ ስርዓት የሕግጋት መሠረት መሆን የለበትም"

በዓለማችን ላይ ያሉ ማኅበረሰቦች ከቅድመ ታሪክ ዘመን ጀምሮ አመሠራረታቸው እና ውስጣዊ ውቅራቸው ቢጠና በአብዛኛውና በመሠረታዊነት የተቋቋሙት በአባታዊ (Patriarchal) ጥላ ስር ነው። አባታዊ የሆነው የማኅበረሰብ አመሠራረት ለወንዶች በቤተሰብ፤ በሕዝብ አስተዳደር፤ በሃይማኖት ተቋማት፤ በትምህርት እና መሰል የማኅበረሰብ ዘርፎች ቅድሚያ እና ከፍተኛ ቦታ የሚሠጥ ነው። ይህ ወንድ-መር የኅበረተሰብ አወቃቀር በታሪክ ውስጥ አልፎ አልፎ በሚነሱ ጠንካራ ሴቶች ውግዘት እና ትግል ቢገጥመውም እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በተደራጀ መልኩ ሁሉን ዓቀፍ ውግዘት እና ተቃውሞ አልገጠመውም ነበር። ይህን ትግል የመሩት ሰዎች በተለምዶ አቃፊ ሊባል በሚችል አነስታይ አስተምህሮ (Feminism) ስያሜ ስር ይጠቃለላሉ። ይህ አስተምህሮ ሴቶች በሁሉም እና ማንኛውም መስክ ከወንዶች እኩል እንደሆኑና በሁሉም ረገድ እኩል የሀብት የትምህርት እና የስልጣን ድርሻ ሊያገኙ እንደሚገባ፤ ታሪካዊ በሆነ ሁኔታ የደረሰባቸው ኃላቀርነትም በተጨማሪ ዕድል ሊስተካከል እንደሚገባ ያስተምራል።

የሴት- ተኮር የሕግ ፍልስፍናም በወንዶች እና ሴቶች መሀከል ያለው የተዛባ እና ኢ-ፍትሐዊ የሆነ ግንኙነት በመንግስት ሕግጋት ውስጥ የሚንፀባረቅ በመሆኑ የፍትሕ ስርዓቱን ከአድሎ እና ኢ-ፍትሐዊነት በማፅዳት ለወንዶች እና ሴቶች እኩል ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ ሕግጋት እንዲወጡ ሊደረግ ይገባል በማለት ይከራከራል። ፍ/ቤቶችም ሕግጋትን በሚተረጉሙበት እና ውሳኔ በሚሠጡበት ወቅት በወንዶች እና በሴቶች መሀከል በታሪክ ውስጥ ያለውን የተዛባ ግንኙነት ከግምት ውስጥ

በማስገባት የሴቶችን ጥቅም ከግምት ውስጥ በሚያስገባ መልኩ መሆን አለበት[61]**።**

> In the new Code of Laws which I suppose it will be necessary for you to make I desire you would Remember the Ladies, and be more generous and favourable to them than your ancestors. Do not put such unlimited power into the hands of the Husbands. Remember all Men would be tyrants if they could. If particular care and attention is not paid to the Ladies we are determined to foment a Rebellion, and will not hold ourselves bound by any Laws in which we have no voice, or Representation[62].

ይህ በዋናው የአነስታይ ፍልስፍና ላይ የሚታይ ልዩነት በሕግ ፍልስፍናውም ላይ ይንፀባረቃል። የሴት- ተኮር ፍልስፍና በአብዛኛው "ባደጉት" ምዕራባዊ ሃገራት ውስጥ የሚራመድ እና የተፈጠረ እንደመሆኑ

---

61 በኢትዮጲያ የዳኝነት ስራ የወንዱ ብቻ ስልጣን ሆኖ የኖረ ነው። ለሴት ዳኛ ሆኖ ችሎት ማስቻል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እርም ነበር። "ለሴት ዳኛ ለነብር እረኛ የለውም" ይባላል። ስርዓቱ የወንድ ስለነበር ህግ አውቂውና ዳኛውም እሱ ነበር። ይህም በፍርድ ስራ፤ የፖሊስ ስራ፤ የዓቃቤ ህግ ሰራዎች እና ወዘተ ላይ ተጽእኖ ማድረጉ አይቀርም። በአሁኑ ወቅት ግን ሴቶችም በየፍርድቤቱ ችሎት ተቀምጠው መታየት ጀምረዋል።
(እሸቱ ድባቡ፤ ተባእታይ አገዛዝ በኢትዮጲያ- ችግሩና የመፍትሄው መንገድ፤ አዲስ ጥራት ማተሚያ፤ ሰኔ 1997፤ ገጽ 147)

62 Abigail Adams, in a letter to John Adams (31 March 1776), published in *Familiar Letters of John Adams and his wife Abigail Adams* (1875) edited by Charles Francis Adams, p. 147

የሴቶችን እና የማኅበረሰብን ግንኙነት የሚያየው ከተማረች ነጭ ምዕራባዊ ሴት አንጻር ብቻ እንደሆነና እያደጉ ባሉ ሃገራት ውስጥ ያለውን ባህል ከግምት ውስጥ አያስገባም የሚሉ እንዳሉ ሁሉ በሴቶች ላይ የሚደርሰው ጭቆና ተመሳሳይ እንደሆነና በዓለም ላይ ባሉ ሴቶች በሙሉ ተቀባይነት የሚያገኙ እና የሁሉንም ሴቶች በደል የሚያጎሉ ሐሳቦችን ማፍለቅ እንደሚቻልም የሚከራከሩ አሉ። ይህ ልዩነት ቢኖርም ሁሉም ሴታዊትነትን የሚያቀነቅኑ ሰዎች የሚስማሙበት ነገር ቢኖር አሁን ባለው እና በሚመጣው ስርዓት ሴቶች እና ወንዶች የእኩል ዕድል ተጠቃሚ ሊሆኑ የተገባቸው መሆኑን ነው።

አነስታይ የሕግ ፍልስፍና (Feminist Jurisprudence) የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በ1978 ዓመተ ምህረት በHarvard women's law journal በታተመ የምርምር ጽሑፍ ላይ የዋለ ሲሆን በወቅቱ ከነበረው ነቂሳዊ የሕግ ፍልስፍና እንቅስቃሴ ጋር ቁርኝነት አለው። ብዙ ዓይነት የሴት ተኮር የሕግ ፍልስፍና ዓይነቶች ያሉ ቢሆንም በመሠረታዊነት የሚታወቁት የሚከተሉት The Liberal equality model,the sexual difference model,the dominance model,the anti-essential model and the post-modern model ናቸው። ሊበራል ሞዴል ሴቶች በሥነ-ተዋልዶ፣ በመንግስት ውክልና፣ በማኅበረሰባዊ ውክልና እና መሰል ዓውዶች በሙሉ ያልተገደበ ነፃነት ያስፈልጋቸዋል ሲል የልዩነት ሞዴል በበኩሉ በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለው ልዩነት አካላዊ፣ ማኅበረሰባዊ፣ ስሜታዊ እና ሥነ-ልቦናዊ በመሆኑ በተፈጥሮ የተገኘም ሆነ በማኅበረሰብ የተፈጠረን ልዩነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሴቶችን የማይጨቁን ግን ለሴቶችም የማያደላ የፍትሕ ስርዓት ልንገነባ ይገባል በማለት ይከራከራል። ይህን ሞዴል በመቃወም የሚቀናቀነው ሌላኛው የተመሳሳይነት ሞዴል (Sameness model) የወንዶችን እና የሴቶችን ልዩነት ከግምት ውስጥ እናስገባ የሚለው መከራከሪያ ለዘመናት የኖረው የወንዶች የበላይነት በተለያየ መንገድ እንዲቀጥል የሚያደረግ ሙከራ እንደሆነ ያስረዳል።

የስልጣን ሞዴል (Dominance model) ከሌሎቹ ሞዴሎች በተለየ በወንዶች እና በሴቶች መካከል እኩልነት እንዲመጣ ትግል ማድረግ የችግሩን መንስኤ ካለማወቅ የሚመጣ ነው። በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለው ግንኙነት በታሪክ ውስጥ በሙሉ ለስልጣን የሚደረግ ትግልን የሚወክል ነው። ሴቶች በወንዶች ለረዥም ዘመን ተጨቁነው እና ተረግጠው የኖሩ በመሆናቸው የሚያስፈልገው እኩልነትን ለማምጣት የሚደረግ እንቅስቃሴ ሳይሆን ጭቆናን ለማስወገድ የሚደረግ ትግል ነው። በመሆኑም በሁሉም ዘርፍ ያሉ ሴቶች የወንዶችን የበላይነት ለማስወገድ ስልጣን መጎናፀፍ ይገባቸዋል።

Antiessential model ከቀደሙት ሴት ተኮር ቤተ-አስተምህሮዎች በተለየ መልኩ ትኩቱን በራሱ በሴት ተኮር እንቅስቃሴ ላይ በመሰንዘር ይጀምራል። ሴት ተኮር እንቅስቃሴዎቹ በተለይም እስከ 1980ዎቹ በነበረው ሂደት "ሴት" የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ ሲበይን ነጭ፣ የተማረች እና በመሀከለኛው የሥራና የኑሮ መደብ ላይ የምትገኝ፣ በተቃራኒ ፆታ ግንኙነት ላይ ያለችን ሴት ነው። ይሁንና ጥቁር እና ላቲን የሆኑ፣ በዝቅተኛ የኑሮ መደብ የሚገኙ ያልተማሩ እና በተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን ከግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ ለእኩልነት የሚደረገውን ትግል እንዲያነክስ አድርጎታል በሚል ይከራከራል። በመሆኑም የሕግ ስርዓቱ ሁሉንም ሴቶች እና እናቶች በተመሳሳይ መንገድ አይጨቁንም፤ለአንዳንድ ሴቶች ከሌሎች የባሰ እና የከፋ ጭቆና የሚያስከትል ነው። በመሆኑም ሴት ተኮር እንቅስቃሴዎች የአስተሳሰብ አድማሳቸውን በማስፋት የሁሉንም ሴቶች የሕይወት ገፅታ በሚዳስስ እና በሚያሻሽል መልኩ እንቅስቃሴዎችን ሊቃኙ እንደሚገባ ያስተምራል። የድህረ ዘመናዊ እንቅስቃሴ በበኩሉ የፍትሕ ስርዓቱ ውስጥ ያሉትን እና የተደበቁ አድሎዎችን መታገል የሚቻለው ስርዓቱን ሐሳባዊ በሆነ መንገድ ማፍረስ (Deconstruct) ማድረግ ሲቻል እንደሆነ ያስረዳል።

በዚህ ድርሳን ምዕራባዊ የሥነ-ሕግ ፍልስፍናን ለማብራራት የተፃፈ በመሆኑ ትኩረት ያደረገው በምዕራቡ ዓለም ያለውን የሴት ተኮር የሕግ ፍልስፍና ላይ ነው። ይሁን እንጂ ባደጉ እና በተማሩ ሀገራት እንኳ ይህን መሰል ጭቆና በሴቶች ላይ የሚደርስ ከሆነ በማደግ ላይ ባሉ የአፍሪካ እና የእስያ ሀገራት ሴቶች በሃይማኖት እና በባህል በተቀመጡ ሕግጋት ምን ያህል አስከፊ ጫና ላይ እንደሚገኙ መገመት አያዳግትም። በመሆኑም በእነዚህ ሃገራት የሚቀነቀነው ሴት ተኮር የሕግ ፍልስፍና በገጠር የምትኖረውን አፍሪካዊት ሴት ሕይወት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት። በአፍሪካዊ ሃገራት ውስጥ እንደ Katherine Mackinon ዓይነት ፅንፈኛ የDominance model (የስልጣን ሽኩቻ) ሞዴል አቀንቃኝ መሆን ወይም ደግሞ ድህረ ዘመናዊ ሴት ተኮር የሕግ ፍልስፍናን ማቀንቀን ለሴቶች የሚያስገኘው ትርፍ መኖሩ አጠራጣሪ ነው፡ለዚህ እንደ ጥሩ ማሳያ ልንወስደው የምንችለው ታሪክ ይህ ነው።

በ1970 በቴክሳስ ክፍለ ሀገር አንዲት ኖርማ ኮርቪ (Norma Mac Corvey) የተባለች ወጣት ውርጃ ለመፈፀም ትፈልጋለች፣ ይሁን እንጂ የቴክሳስ የወንጀል ሕግ ውርጃን ስለሚከለክል ግራ ይገባታል። ሁለት ወጣት “ፌሚኒስት” ጠበቆች ደግሞ የክፍለ ሀገሩን የፀረ ውርጃ ሕግ መሞገት እንደሚፈልጉ ትሰማና ታገኛቸዋለች፣ ጉዳይዋን ለዳላስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ያቀርቡታል። የኖርማ ማንነት እንዳይታወቅ ጄን ሮው (Jane Roe) የሚል የሚስጥር ስም ይሰጧታል፣ ባላንጣቸው ደግሞ የቴክሳስ ዓቃቤ ሕግ ሄንሪ ዋድ (Henry Wade) የክፍለ ሀገሩን ሕግጋት ለማስጠበቅ ታጥቆ ፍልሚያ ይጀምራሉ። በማይታወቅ ሰው ተደፍሬ ነበር የሚል አቤቱታ ያቀረበችው ጄን ሕገወጥ ክሊኒክ ሄዳ ለማስወረድ ስትንቀሳቀስ ፖሊስ ክሊኒኩን ይዘጋዋል፣ በቴክሳስ ውርጃ የሚፈቀደው የእናቲቱ ሕይወት አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ ብቻ ነበር።

የቴክሳስ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የክፍለ ሀገሩ የፀረ ውርጃ ሕግ የሕገ-መንግስቱን The right to privacy እና በዘጠነኛው የሕገ-መንግስት ማሻሻያ የተቀመጠውን መብት የሚጥስ ነው ብሎ ይወስናል። ጉዳዩ

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይደርሳል እዚያም ከፍተኛ ክርክር ይነሳል በ 7 ለ 2 የአብላጫ ድምፅ የቴክሳሱን ውሳኔ ያፀኑታል። ጉዳዩ በጣም አንገብጋቢ ከመሆኑ የተነሳ ሀገሪቱን በሁለት ጎራ ይከፈላል። ጄን ሮውን የሚደግፉ Pro-choice ፣ ዓቃቤ ሕጉን የሚደግፉ ደግሞ Pro-life ተብለው እስከዛሬ ጭፍጭፍ ላይ ይገኛሉ። ጉዳዩ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከዓመት በኋላ ሲወሰን "ጄን ሮው " ልጇን ሳታስወርድ በመቅረቷ በሰላም ተገላግላው የጉዲፈቻ አድራጊዎችን እየጠበቀች ነበር፣ ጉዳዩ እንዳለቀ ልጇን በጉዲፈቻ ትሰጣለች።

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጉም እርግዝናን በሦስት ደረጃዎች Trimesters በመከፋፈል የመጀመሪያው ትራይሜስተር ሴት ልጅ ውርጃ የማድረግ ሙሉ መብት ሊኖራት እንደሚገባ፣ በሁለተኛው ትራይሜስተር ግን የባለሙያ ድጋፍ እና ይሁንታ ልታገኝ እንደሚገባ፣ በሦስተኛው ትራይሜስተር ግን ህይወቷ አደጋ ላይ ካልወደቀ በቀር ውርጃ እንደሚከለከል ያትታል[63]። ይህ ውሳኔ ብዙ ሰዎችን እስከዛሬ ያነታርካል፣ ውርጃ እና Right to privacy ምን አገናኛቸው? ይህ የለየለት Judicial activism ነው፣ ሕገ መንግስቱን የሚጥስ ነው ፣ ኢ-ሞራል እና የፅንሱን የመኖር መብት የሚንቅ ነው ወዘተ

ከዓመታት በኋላ በ1994 ዓ ም አንዲት ሴት "I am Roe " የሚል የሕይወት ታሪክ መጽሐፍ ታወጣለች፣ በእድሜ የገፋችው ኖርማ ኮርቬይ ማንነቷን ገልፃ በይፋ Pro-choice ተከራካሪ ትሆናለች። እንዲያውም የውርጃ ክሊኒክ አቋቁማ ብዙ ውርጃ ካስፈፀመች በኋላ ፣ ድንገት ባልተጠበቀ ሁኔታ "ጌታን ተቀበለች " / Pro-life ሆንኩ አለች። ተደፍሬ ነበር ያለችው በጓደኞቿ ግፊት እንጂ ውሸት እንደነበር ገልፃለች። በሥራዋ እጅግ ከመፀፀቷ የተነሳ ትሠራበት ከነበረው እዚያው የውርጃ ክሊኒክ አጠገብ " Rescue lives" የሚል ድርጅት ከፍታ እስከ ዕለተ ሞቷ (2017, Feb) ድረስ ስትከራከር ኖራለች።

63 Roe v. Wade, 410 U.S Supreme court (1973)

የሕግ እና የሥነ-ምጣኔ ጥምረት

“ሥነ-ምጣኔ ሕግን ሲደግፍ ስርዓቱ ውጤታማ እና ቀልጣፋ ይሆናል”

ሕግ እና ሥነ-ምጣኔ በታሪክ ውስጥ የነበራቸው ግንኙነት ረዥም እና ሰፊ ነው። በተለያዩ ጊዜ የተነሱ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ፍልስፍናዎች በሕግ እና ኢኮኖሚክስ መሀከል ያለውን ግንኙነት በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ሊያጠኑ ሞክረዋል። ከአዳም ስሚዝ እስከ ካርል ማርክስ ድረስ የተነሱት ፍልስፍናዎች በሁለቱ መሀከል ያለውን ግንኙነት ሳይጠቅሱ አላለፉም። ይሁን እንጂ በ1961 (እ.ኤ.አ) በአሜሪክ የቺካጎ ኢኮኖሚክስ ቤተ-አስተምህሮ ስር የተሰበሰቡት እንደ ሮናልድ ኮዝ እና ጀራልድ ካላብሬሲ ዓይነት ተመራማሪዎች በሕግና በሥነ-ምጣኔ መሀከል ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለ ለማሳየት ሞክረዋል። በዚህም ኢኮኖሚክስ ለሕግ አውጪዎች እና ተርጓሚዎች ቁልፍ መሣሪያ እንደሆነና አንድ ሕግ በማኅበረሰቡ እና መንግስት ላይ የሚያስከትለው የወጪ መጠን እና በአንድ ሕግ መሠረት ውሳኔ ሲሰጥ በተከራካሪ ወገኖች ላይ የሚያሳድረው ጫና ምን እንደሆነ ከኢኮኖሚክስ ሕግጋት አንፃር መመርመር እንደሚገባን ይገልፃሉ።

ኢኮኖሚክስ የሕግ ስርዓቱን ሲደግፍ ስርዓቱ ውጤታማ እና ቀልጣፋ ይሆናል። በመሆኑም ቅልጥፍና (Efficiency) ያለው የፍትሕ ስርዓት አጠቃላይ ለሆነ የሀገር እድገት ወሳኝ ሚናን ይጫወታል። ይህም ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚክስ አንዳንድ ሕግጋት በግለሰቦችም ሆነ በመንግስት ላይ የሚያስከትሉትን ወጪ እንድንገምት ያግዘናል፤ ለምሣሌ ከውል ውጪ ባሉ ኃላፊነቶች በአንድ ባለጉዳይ ላይ የደረሰውን የጉዳት መጠን (Present and future damage) በትክክል ለማስላት መጠቀም ያለብን መሠረታዊ የኢኮኖሚክስ ሕግጋትን እንደሆነ ፍልስፍናው ያስተምራል።

ዳኞች ዕለት ተዕለት የጉዳት ካሳን በማስላት ሲወስኑ በጣም ኃላ ቀር የሆኑ የስሌት ቀመሮችን እየተጠቀሙ ቢሆን እንኳ ሳያውቁት የኢኮኖሚክስ ሕግጋትን በውሳኔያቸው ውስጥ እየተገበሩ ነው። በተጨማሪ ሕግጋት በዜጎች ላይ የሚያስከትሉት ኢኮኖሚያዊ ተዕዕኖ በመገመት ትንበያውን ለሕግ አውጪዎች እና የፖሊስ አርቃቂዎች ማቅረብ ይቻላል። ይህ ማለት አንድ ሕግ ሲወጣ ከሃያ እና አርባ ዓመት በኃላ በተወሰኑ የኅበረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ እና አዎንታዊ ተዕዕኖ ቀላል ኢኮኖሚያዊ ሕግጋትን በመጠቀም መተንበይ እንደሚችል ምሁራኑ ያስረዳሉ።

አንዳንዶች ኢኮኖሚያዊ የሕግ ጥናትን እስከዕንፍ በመውሰድ የሕግ ዋንኛ አላማው ቅልጥፍና እና ወጪ ቁጠባን በማበረታታት የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ እንዲጎለብት መርዳት እንደሆነ ያትታሉ። ይሁን እንጂ አብዛኞች ሕግ ተርጓሚዎች የኢኮኖሚክስ መርሆዎችን በመረዳት በፍርዶቻቸው ውስጥ መጥቀስ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የተለመደ ተግባር አልነበረም። የዚህ ፍልስፍና አራማጆች ቅልጥፍና (Efficiency) የፍትሕ ስርዓቱን የምንለካበት ዋነኛ መሣሪያ እንደሆነ ከማስቀመጣቸው የተነሳ የተለያዩ የመለኪያ መርሆዎችን ቀይሰዋል።

ምዕራፍ ሰባት

የብዝሃ- ሕግ ፍልስፍና

“የሕግ ብዝሃነት የአንድ ሀገር የፍትሕ ስርዓት ጥንካሬ ነው”

በአንድ ሀገር ውስጥ ከአንድ በላይ የሕግ ስርዓቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ የሕግ ብዝሃነት (Legal pluralism) በምን መንገድ ሊስተናገድ እንደሚገባ ብዙ ሰዎች የተለያየ ዓይነት ሐሳቦችን አቅርበዋል። አፍሪካ ውስጥ ያሉ ባህላዊ እና የልማድ የሕግ ስርዓቶች ተቀራራቢ እና ተወራራሽ በሆነ መልኩ ተያይዘው በአንድ ሃገራት ውስጥ ከመገኘታቸው ባለፈ ከእነዚህ ሕግጋት በተለየ መልኩ መጤ የሆኑ አውሮፖዊ ሕግጋት በውዴታ እና በግዴታ ተጭነውባቸው ይገኛል።

በቅኝ አገዛዙ ዘመነ መንግሥት አውሮፓውያን የራሳቸውን ቋንቋ፤ ባህል እና ሕግ በአፍሪካ ቀዳሚ ባህሎች እና ሕዝቦች ላይ ሲጭኑ ከዚህ ቀደም ከነበሩት ባህሎች እና ልማዶች ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ የደረሰባቸው በመሆኑ ይህንን ተቃርኖ በማስወገድ በሕግ፤ በልማድ ሕግጋት እና በአውሮፓዊ ሕግጋት መሀከል ያለውን ግንኙነት መወሰን ነበረባቸው። በመሆኑም ብዙዎቹ የቀኝ ገዢ ሕጎች በተወሰነ መልኩ ቅኝ በተገዙት ሕዝቦች ላይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚደነግጉ ነበሩ። በዚህም መሠረት ከአውሮፓ የመጡት ሕጎች ሰፊ እና ግዙፍ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ሲሆኑ አነስተኛ እና ግላዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ባህላዊ ሕግጋት ተፈፃሚ ይሆኑ ነበር። ይህ ሁኔታ ልዩ የሆነ የብዝሃ-ሕግ ስርዓት እንዲኖር ያደረገ ሲሆን ሕጋዊ ብዝሃ-ሕግ በመባል ይታወቃል።

ይሁን እንጂ ከዚህ በተለየ መልኩ አንድ ሰው በአንድ ሀገር ውስጥ እየኖረ በአንድ እና ተመሳሳይ ጉዳይ ከአንድ በላይ ለሆኑ ሕግጋት ተገዢ እንዲሆን ሲገደድ የሚፈጠረው ሁኔታ ተግባራዊ የሕግ ብዙኃነት ይባላል። በተግባራዊ የሕግ ብዙኃነት ወቅት ዜጎች በአንድ ሀገር ውስጥ ቢሆንም ከክልል ክልል በሚለያዩ ሕግጋት አማካኝነት በተመሳሳይ ጉዳይ የተለያየ ፍርድ ሊጣልባቸው ይችላል። ይህንን ጉዳይ በማስተዋል ሰዎች የተሻለ ውሳኔ/ ሕግ ወዳለበት ክልል ጉዳያቸውን ይዘው ሲሄዱ የመድረክ ምርጫ ጉዳይ ይከሰታል።

በቀደመው ሕጋዊ የብዙኃ ሕግ አስተምህሮ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ አይከሰትም፤ ምክንያቱም ባህላዊ ሕግጋቱ እና አውሮፓዊ ሕግጋት ጎን ለጎን ሳይገፋፉ በሥራ ላይ ይውላሉ፤ በአንድ ሀገር የተለያዩ የሕግ ብዝሃንነትን ለመፍታት የሚያስችል የሕግ ስርዓት መዘርጋት ግን ግዴታ ነው። በርግጥ አሁን ባለንበት የሉላዊነት ዘመን ባህሎች፤ ሕጎች፤ መንግስታት በሙሉ እየታጠፉ ወደ አንድ ማዕከላዊ ባህል፤ መንግሥት፤ ገንዘብ እና ርዕዮት እየመጣ ቢሆንም ይህ ሂደት ረዥም ጊዜ የሚፈጅ እንደመሆኑ ሃገራት በውስጣቸው ያሉት የተለያዩ የሕግ ምንጮችን በማክበር ጠቃሚ በሆነ ሁኔታ ሊገላገሉባቸው ይገባል።

የብዝሃ-ሕግ ፍልስፍና አጠቃላይ ሐሳብም አፍሪካ ውስጥ ባሉ ሀገራት የተለያዩ የልማድ እና የባህል ሕግጋት ማዕከላዊ ከሆኑት እና ከፖርላማ ከሚታወጁት ሕግጋት ይልቅ ለሕዝቡ ሕይወት የሚቀርቡ በመሆናቸው ኗሪ ሕጎች (Living Laws) ናቸው። በመሆኑም እነዚህን ባህላዊ ሕግጋት እንደ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ፤ ባህልን የማሻገሪያ እና የማስተማሪያ ስርዓት፤ ለማዕከላዊ መንግስት የሕግ ምንጭነት እና መሰል ሁነቶች ላይ በማዋል ሀገርን እና ሕዝብን እንዲጠቅሙ ማድረግ ይገባል።

የሕግ ንቅለ ተከላ (Legal Transplantation)

በማደግ ላይ ያሉ ሃገራት የዲሞክራሲ ተቋማት ግንባታን እንደ ዋነኛ አጀንዳቸው አድርገው መንቀሳቀስ የጀመሩት ሕጎቻቸውን በማዘመን ነው። አብዛኞቹ አፍሪካዊ ሃገራት ዘመናዊነት ወይም ሕግ ማዘመን የሚለውን ቃል የተረዱት ያደጉ ሃገራት ሕግጋትን መቅዳት በሚል ስለሆነ በተለይም ከቀኝ ግዛት ከተላቀቁ በኋላ ከፍተኛ በሆነ መንገድ ከአውሮፓ ሕግ እና ባህል ለመላቀቅ ቢጥሩም አልተሳካላቸውም።

እንደ ኢትዮጲያ ያሉ ሃገራትም ዘመናዊነትን የፈረንጅ ሕግ እና ባህል መቅዳት በሚል የተረዱት በመሆኑ ከፍተኛ ሕግ ከአውሮፓ አስመጥተዋል። ሕጎቹ ሲመጡም የተካሄደው ንቅለ ተከላ ነው። በወቅቱ ማዕከላዊ መንግስቱን የሚያገለግሉ እንደ ፍትሐ-ነገስት ያሉ ሕግጋት ተነቅለው የአውሮፓ ሕግጋት ተተክለዋል። በ1950 ዎቹ አጼ ኃይለስላሴ ይህን ሰፊ የአርቃቂ ኮሚቴ ሲያደራጁ ሀገር በቀል ሕግጋት እንዲታከሉ ትእዛዝ ቢሰጡም ሕግጋቱ በአመዛኙ አውሮፓዊ መሆናቸው አልቀረም። የሃገራችን የፍትሐ-ብሔር ሕግ፤ የወንጀል ሕግ፤ የወንጀል ሥነ-ስርዓት ሕግ፤ የፍትሐ-ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ፤ የንግድ ሕግ እና የባህር ሕግ በሙሉ የተቀዱት ከአውሮፓ ሃገራት እንደመሆኑ እነዚህ ሕግጋት በዚህ ግማሽ ክፍለ ዘመን ለሕዝቡ ያመጡት ጥቅም መጠናት ይኖርበታል።

የሕግ ስርፀት (Legal Penetration)

ከአውሮፓ የመጡት ሕግጋት ወደ ሀገር ውስጥ መጥተው በጥቅም ላይ ሲውሉ የገጠማቸው ተግዳሮት ቀላል የሚባል አይደለም። በፍትሕ ስርዓቱ እና በማኅበረሰቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ለመስረጽ ከፍተኛ የሆነ የተቀባይነት ችግር ለማለፍ ተገደዋል። በመሆኑም እነዚህ ሕግጋት በማኅበረሰቡ ውስጥ ተገቢውን እውቅና እና ተቀባይነት እንዲያገኙ መንግስት ሰፊ የሆነ የንቃተ ሕግ ሥራዎችን መሥራት አለበት በማለት

አንዳንድ ሰዎች ሲከራከሩ የተቀሩት ደግሞ እነዚህ ሕጎች በሂደት እና በጊዜ ቀስ እያሉ ወደ ማኅበረሰቡ መስረጽ አለባቸው እንጂ በቀጥታ በሕዝቡ ላይ መጫን የለባቸውም በማለት ይከራከራሉ። ሌሎች በበኩላቸው ውጤታማ የሆነ የሕግ አሰራጸኑት ተግባር ሊከናውን የሚችለው እነዚህን ሕግጋት ሙሉ ለሙሉ በማስፈጸም ነው። ለምሳሌ የሴት ልጅ ግርዛት በውንጀል ሕጉ የተከለከለ ቢሆነም አሁንም በአብዛኛው የሀገራችን ክፍሎች ይፈጸማል በመሆኑም ይህንን ሕግ በኃይል እንዲፈጸም ካደረግነው ሊሰርጽ ይችላል ብለው የሚከራከሩ ሰዎች አሉ።

የብዝሃ-ሕግ ፍልስፍናም አጠቃላይ የተለያዩ የልማድ እና የባህል ሕግጋት ማዕከላዊ ከሆኑትንና ከፖርላማ ከሚታወጁት ሕግጋት ይልቅ ለሕዝቡ ሕይወት የሚቀርቡ በመሆናቸው ሕይወት ያላቸው ሕጎች (Living Laws) ናቸው። በመሆኑም እነዚህን ባህላዊ ሕግጋት እንደ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ፤ ባህልን የማሻገሪያ እና የማስተማሪያ ስርዓት፤ ለማዕከላዊ መንግስት የሕግ ምንጭነት እና መሰል ሁነቶች ላይ በማዋል ሀገርን እና ሕዝብን እንዲጠቅሙ ማድረግ ይገባል። ባህላዊ ሕግጋት ሕይወት ያላቸው የሆኑት ሕዝቡ እንደ ባእድ ሕግጋት ስለማያያቸው ነው። ለሕዝቡ ሃዘን፤ስሜት፤ደስታእናሞራል በእጅጉ የቀረቡ ብቻ ሳይሆን መለየት እንኳ አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም በማደግ ላይ ያሉ ሃገራት በሕግ ስርአታቸው ውስጥ ከአንድ በላይ የሕግ ስርዓት መኖሩን እንደ መልካም አጋጣሚ ሊያዩት ይገባል።

የአውሮፓ መንፈስ እና ኢትዮጲያዊ ፍልስፍና

"በተዋህዶ ከበረ"

ታዋቂው የታሪክ ፀሀፊ ኤድዋርድ ጊበንስ ስለ ኢትዮጵያ ስልጣኔ ሲፅፍ "The Ethiopians slept nearly a thousand years, forgetful of the world by whom they were forgotten" ኢትዮጵያውያን ለሺህ ዓመታት ያህል ሌላውን ዓለም ረስተው እና በሌላውም ዓለም ተረስተው እንደኖሩ ይገልፃል። ይህ በሌላው ዓለም የመረሳት መዘዝ ሃገሪቷ ለየት ያለ የስልጣኔ መንፈስ እንዲኖራት አስገድዷል። ከሌላው ዓለም ባልተነጠለችበት ወቅት ከልዩ ልዩ ስልጣኔዎች ጋር ልዩ ልዩ ሐሳቦችን በመጋራት የስልጣኔው መንፈስ እንዲያድግ ጥረት አድርጋለች። የኢትዮጵያ የሕግ ፍልስፍና እና የፍትሕ አስተዳደር ታሪክ ከምዕራቡም ከምሥራቁም ዓለም የተለያዩ ፅንሰ-ሐሳቦች እና ሕግጋት ወስዶ የተዋቀረ በመሆኑ ዛሬ ከሕግጋቱ ውስጥ ፍጹም ምዕራባዊ ወይም ፍጹም ምሥራቃዊ የሆኑ ሕግጋት ማግኘት ይቻላል።

ፍልስፍናን በተመለከተ ፍጹም ኢትዮጲያዊ የሆነ የሕግ ፍልስፍና ልናገኝ አንችልም፤ይህንኑ ሐሳብ በሚደግፍ ሁኔታ የፍልስፍና ምሁሩ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ፍልስፍና በኢትዮጲያ ውስጥ "ወንበር የላትም!" በማለት በተደጋጋሚ መናገሩን ልብ ልንል ይገባል። ፍልስፍናን እንደ አፍላጦን እና አሪስጣጣሊስ አንድ ቤተ-አስተምህሮ ከፍቶ የሚያስተምር ግለሰብ ባለመኖሩ የኢትዮጵያ የሐሳብ ዓለም ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ወደ መንፈሳዊነት እና ባህታዊነት ያደላ በመሆኑ "የኢትዮጵያ ፍልስፍና" ነበር ብሎ ለመናገር እንደሚያዳግት ይገልፃል። ይህንኑ ሐሳብ በሚያጠናክር መልኩ ዶ/ሩ "ላሊበላዊነት እና አክሱማዊነት" የሚለውን ሐሳብ ያስተዋውቃል።

ኢትዮጵያዊነት በአክሱማዊነት ዘመን የነበረው ስልጣኔ ከግሪኩ ሄለናዊ ፍልስፍና ጋር እንደሚመሳሰል እና ይህ ስልጣኔ አንገት እና ደረቱን ወደ ሰማይ ቀስሮ እየተንጠራራ የሰውን ሁሉን ቻይነት እና ጥበብ ሲያመላክት ሰዎች በአንድ አላማ እና ሐሳብ ከተሰባሰቡ ታላላቅ ሥራዎችን መሥራት እንደሚችሉ በኩራት ሲናገር፤ ላሊበላዊነት ግን ዝቅ ብሎ ወደ ውስጥ የሚመለከት የሰዎችን ጥበብ እና ሁሉን ቻይነት ከመመስከር ይልቅ ዝቅ ማለትን፣ ትህትናን እና ወደ ውስጥ መመልከትን የሚያመላክት እብራይስጣዊ አመለካከት በመሆኑ ከጀብድ ይልቅ ባህታዊነትን ያበረታታል። በመሆኑም የኢትዮጵያ የስልጣኔ መንፈስ ከአክሱማዊነት ወደ ላሊበላዊነት በመሻገሩ ታላላቅ የስልጣኔ ግኝቶችን ከማቆም ይልቅ ምንኩስናን እና ባህታዊነትን ወደሚያበረታታ ንፅረተ-ዓለም እንደተቀየረ ይገልፃል። ሌላኛው የፍልስፍና ምሁር ብሩህ ዓለምነህ ይህንን አመለካከት በመቃወም ይህንን ሽግግር አረጋግጠን መናገር አንችልም ሲል ተከራክሯል። *"ዘርዓያቆብና ወልደ ሕይወት የባህልና የእምነት ፍተሻ የአብርሆት ዘመንን በማምጣት አጼ ቴዎድሮስ ላይ ለሚጀመረው የዘመናዊነት ፕሮጀክት የባህል መደላደል የመፍጠር አቅም ነበር። የአጼ ቴዎድሮስም ሆነ የአጼ ኃይለስላሴ የዘመናዊነት ፕሮጀክት ያልተሳኩት የተደላደለ የባህል መሠረት ስላላገኙ ነው። ዘርዓያቆብና ወልደ ሕይወትም ይሄንን ነገስታቱ ሲፈልጉት የነበረውን የተደላደለ የባህል መሠረት ነበር ለማምጣት ሲጥሩ የነበሩት"*[64] እነዚህ ሁለት ኢትዮጲያዊ ፈላስፎች አንዱ አስተማሪ ሌላኛው ተማሪ ሲሆኑ በመሀከለኛው ዘመን ካቶሊኮች ወደ ኢትዮጲያ ዘልቀው ሁሉን ባለሀገር ሃይማኖት እያስቀየሩ መንግስታዊ ሃይማኖት እስከመሆን በደረሱበት ወቅት የተነሱ ናቸው። በተለይም ዘርዓያቆብ ወይም ወርቁ ሃይማኖታዊ ሕግጋትን እጅግ የኮነነ እና የተቸ ከመሆኑ የተነሳ አንዳንድ ሰዎች የእርሱ ሐተታዎች ኢትዮጲያዊ ባልሆነ ሰው የተጻፉ መሆናቸውን በመግለጽ ይከራከራሉ።

64 ብሩህ አለምነህ፤ የኢትዮጲያ ፍልስፍና ዘርዓያቆብና ወልደ ሕይወት ሐተታዎች ትንታኔ፤ 2011፤ ገጽ 176

> *የሙሴ መጽሐፍ ከፍጥረት ሕግና ስርዓት እንዲሁም ከፈጣሪ ጥበብ ጋር አይስማም። በውስጡ የተሳሳተ ጥበብ ይገኛል። ለሚመረምር ግን እውነት አይመስለውም፤ በፈጣሪ ፍቃድና በፍጥረት ሕግ የሰው ልጅ እንዳይጠፋ ልጆችን ለመውለድ ወንድና ሴት በፍትወተ ስጋ እንዲገናኙ ታዟል። ይህም ሕግ እግዚያብሔር ለሰው በሕገ ተፈጥሮው የሰጠው ነው። እግዚያብሔር የእጁን ሥራ አያረክስም። እግዚያብሔር ዘንድ እርኩሰት ሊገኝ አይችልም። ሙሴ ይህንን ማለቱ ትክክል ነው አልልም ፈጣሪን ዋሸ እንዳደረገው ልቦናችን ይነግረናል። እንደገናም የክርስቲያን ሕግ ለማስረጃ ተጓምራቶች ከእግዚያብሔር ናት ይላሉ፤ ነገር ግን የወሲብ ስርዓት የተፈጥሮ ስርዓት እንደሆነ ምንኩስና ግን ልጆች ከመውለድ ከልክሎ የሰውን ፍጥረት አጥፍቶ የፈጣሪን ጥበብ የሚያጠፋ እንደሆነ ልቡናችን ይነግረናል*[65]።

የኢትዮጵያን ፍልስፍና ምንነት ለማወቅ ከፈለግን እንደ ጥሩ ናሙና የሚያገለግሉን ሕግጋቱ ናቸው። ሀገሪቱ በግል እና በመንግስት ደረጃ በየትኞቹ ሕግጋት እንደተዳደረች እና እነዚህ ሕግጋት ከየት ሀገር፣ በእነማን፣ ለምን ምክንያት እንደተቀዱ ስንመረምር የኢትዮጵያ የስልጣኔ መንፈስ ምን ዓይነት እንደሆነ በቀላሉ መረዳት እንችላለን። እስከ 1950ዎቹ ድረስ እንደ መንግስት ሕግ በመሆን ያገለገለው ፍትሐ-ነገስት ከሀገረ ግብፅ ከአረብኛ ተተርጉሞ የመጣ ሲሆን ሃይማኖታዊ እና ምድራዊ ጉዳዮችን በመዳኘት ረዥም ዘመን ያገለገለ ሕግ ነው። በመሆኑም የሃገራችን የሕግ ፍልስፍና እና አጠቃላይ የስልጣኔ አቅጣጫ እጅግ ሃይማኖታዊ እንደነበር መረዳት እንችላለን። እንለ ገብረ የሐንስ ይህንኑ ሲያስረዱ ስልጣኔዎች የራሳቸው የእድገት መንፈስ እንዳላቸው እና የአውሮፓ ስልጣኔ ራሱ በታሪኩ ውስጥ ብዙ የእድገት ደረጃ እንዳሳለፈ ይነግሩናል። በተለያዩ ጊዜ የተነሱ ስልጣኔዎችን ምሥራቅ ወይም የምዕራብ፣ አዲስ ወይም አሮጌ እያሉ

65 ዘርዓያቆብ / ወርቁ፤ ሐተታ ዘርዓያቆብ፤ 1640፤ በዳንኤል ወርቁ የተሰናዳ ድርሳን፤ ገጽ 14

በመከፋፈል አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ ማድረግ ምንም ፋይዳ እንደሌለው እና ሁሉን በዘመኑ ዓውድ መረዳት እንዳለብን ይነግሩናል። ይህንኑ ሲገልፁ *"የስልጣኔ መንፈስ ወደፈቀደበት ይነፍሳል። ለመቃወም አይቻልም። የሚገባም አይደልም። ምክንያቱም የስልጣኔ ሀብታት ከሰው የህሊና ጥረት የሚገኙ ስለሆኑ በየትም ቢወለዱ ዘመዳሞች ናቸው። ለመዓት ወይም ለምህረት የሚቸኩል ሰው ሳይሆን እነዚህን ዘመዳሞች የሚያስተዋውቅ ሸማግሌ ያስፈልጋል[66]"* ይህንን ያላደረገ ስልጣኔ ወይም ትውልድ ከሁሉም ተጣልቶ እና ግራ ተጋብቶ መሃል እንደሚቀር ያስረዳናል።

በመሆኑም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ምሁር ሀገራዊ እና ጥንታዊ የሆነውን የኢትዮጵያ ስልጣኔ አውሮፓዊ ከሆነው ስልጣኔ ጋር ማዋሃድ፣ ማዛመድ እና ማገናኘት እንዳለብን ሲገልፁ *"በዘመናችን በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ምሁር ፊት የተደቀነው ሥራ ይህ ይመስለኛል። ሁለቱን ስልጣኔዎች የኢትዮጵያን እና የአውሮፓውያን በገዛ መንፈሳችን ድልድይነት ማገናኘት፣ በጥረታችን ግለት እና ሙቀት እንዲዋሃዱ ለፍሬም እንዲበቁ መድረስ ዋና ሥራ ነው[67]"* ይህንን ለማድረግ ግን መጀመሪያ ሀገራዊ የሆነውን ባህል፣ ትውፊት እና ወግ በሚገባ ጠንቅቆ ማወቅ እና መረዳት ያስፈልጋል። ከዚያ በኋላ አውሮፓዊ የሆነውን ስልጣኔ፣ ፍልስፍና እና ባህል በመመርመር ከራሳችን ስልጣኔ ጋር ወግ እና ደንብ ባለው መልኩ ማዋሃድ ያስፈልጋል፤ በዚህ ጊዜ መንፈስ "በተዋሃዶ ይከብራል[68]" በማለት ከተዋህዶ ክርስትና ዶግማና ቀኖናዎች መሃል ቁልፍ የሆነውን ፅንሰ ሐሳብ በመውሰድ "በተዋህዶ

66 የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ፤ ገፅ 18

67 ዝኒ ከማሁ

68 ዘወትር ስለ ምስጢረ ሥጋዌ ስናነሳ አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ እንላለን። አምላክ ሰው ሆነ ማለት በአካልም በባህርይም በግብርም ነው። ባህርያችንን ገንዘብ አደረገ። ይህ ተዋህዶ ቃል እንበለ ውላጤ(ከአካላዊ ቃልነቱና አምላካዊ ባህርዩ ሳይጎድልና ሳይለወጥ) በአካልም በባህርይም ሰው የሆነበት፤ ሰውም ግዙፉንና ስጋዊ ባህሪዩን ሳያጣ የባህርይ አምላክነትን ያገኘበት ምስጢር መሆኑን አባቶች ይነግሩናል።

(በአማን ነጸረ፤ ጽንዐ ተዋህዶ፤ ብራና መጻህፍት፤ 2012፤ ገጽ 316)

መክበርን" የኢትዮጵያዊና አውሮፓዊ መንፈሶች መዋሃድን የሚወክል ፅንሰ ሐሳብ ያደርጉታል።

እንግዲህ ይህንን በተዋህዶ የመክበርን ፅንሰ ሐሳብ ወደ ኢትዮጵያ የሕግ ፍልስፍና ታሪክ ቀይረን እንመረምረው ዘንድ ይገባል። ኢትዮጵያ የብዙ የባህል እና የልምድ ሕግጋት ሀገር ናት። በእነዚህ ሕግጋት ላይ አዲስ አውሮፓዊ ሕግጋት አምጥተን ደርተንባቸዋል። የሃገራችን የፍትሕ ስርዓት አንዱ ደካማነት የሚመነጨውም እነዚህ አውሮፓዊ ሕግጋት ከሕዝቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር ያልተዋሃዱ እና ባዕድ የሆኑ ሕግጋት መሆናቸው ነው። በተዋህዶ የመክበር አላማ በኢትዮጵያ ሥነ-ሕግ ያልተሳካ እና ወደፊትም የማይሳካ ጉዳይ እንደሆነ እንውሰደው። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁለት ስልጣኔዎች ሲጀመርስ መዋሃድ አለባቸው ወይ? የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ ይገባናል፤ ዘይት እና ዉሃ የሆኑ የስልጣኔ መንፈሶች የማይዋሃዱ ከሆነ ምናልባትም ለማዋሃድ የምናደርገው ጥረት ከጅምሩም የተሳሳተ ሊሆን ይችላል።

የሚሻለው አካሄድ ከሌሎች ስልጣኔዎች እና የፍትሕ አስተዳደር ፍልስፍናዎች የሚጠቅሙ ሐሳቦችን ነቅሰው እየወሰዱ የራስን ስልጣኔ ለማዳበር የሚጠቅሙ ማዳበሪያዎች በማድረግ በዋናነት ግን የራስን ስልጣኔ ማዳበር የሚያዋጣ ተግባር ነው። በተለይ በ1960ዎቹ የተደረጉት የገፍ የሕግ ንቅለ ተከላ ሂደቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ታላቁ የሕግ እና የታሪክ ባለሙያ ዶ/ር አበራ ጀምበሬ *"ከ1940ዎቹ እኩሌታ በኋላ ሀጎጀ በዓለም ላይ ከሚገኙት ሕጎች ጋር በተቻለ መጠን ተመጣጣኝ እንዲሆኑ በማሰብ ከጥንታዊ ወደ ዘመናዊ ሕግ የመሸጋገር እርምጃ በመውሰድ ስድስት ዓበይት ሕግጋት (codes) በውጪ ሀገር ሊቃውንት እና በአገር ተወላጅ ምሁራን አስጠንታ በሀገሪቱ መደበኛ ሕግ ሆነው እንዲሰራባቸው አድርጋለች"*[69] ይሉናል እነዚህ ዓበይት ሕግጋት በአብዛኛው ከአውሮፓ

69 አበራ ጀምበሬ፤ የኢትዮጲያ ህግና የፍትህ አፈጻጸም ታሪክ ከ1426 እስከ 1966፤ ሻማ ቡክስ፤ 2006 ፤ ገፅ 296

በተለይም ከፈረንሳይ ሀገር የተቀዱ ናቸው። ዋንኛው ዓብይ ሕግ "የፍትሐ ብሔር ሕግ" በመሠረታዊነት የፈረንሳይ ሀገር ሕግ ነው። ምናልባትም ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ከልጅነታቸው ጀምሮ በፈረንሳይ መምህራን ተምረው ያደጉ በመሆናቸው በዚህ ተፅዕኖ ስር ወድቀው ሊሆን ይችላል። ይሁንና ሌሎች ሕግጋትም ለምሣሌ እንደ ቀዳሚው የተሻፈ ሕገ-መንግስት ዓይነቶች የተቀዱት ከሀገረ ጃፓን መሆኑን ስንመለከት፤ ፍትሐ-ነገስቱ ከአረብ ሃገራት መወሰዱን ስናጤን የኢትዮጵያ የሕግ ፍልስፍና ከምዕራቡም ከምሥራቁም የተደባለቀ መሆኑን እንረዳለን።

ለዶ/ር አበራ ጀምበሬ እነዚህ ዓበይት ሕግጋት የፀደቁት "ከጥንታዊነት ወደ ዘመናዊነት" የሚደረግ ሽግግርን ለማፋጠን ነው። ይሁንና ይህ ሽግግር ጠቃሚ ስለመሆኑ ወይም የተፈለገው ዘመናዊነትስ ምን ዓይነት እንደነበር በግልፅ የሚታወቅ ነገር የለም። ንጉሰ ነገስቱ ቀዳሚውን ሕገ-መንግስት ለሕዝቡ "ሲሰጡም" የተናገሩት ሕዝቡን ዘመናዊው ዓለም ከደረሰበት ለማድረስ ተብሎ የታቀደ አላማ እንደነበር ነው። ይሁን እንጂ ሕገ-መንግስቱ እንዴት ይህንን ሊፈፅም እንደሚችል የሚታወቅ ነገር አልነበረም። ስለ ዘመናዊ ትምህርት ስናስብ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ "Pioneers of change" በተባለ ድርሳናቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት በኩር ምሁራን ጃፓንን እንደ አብነት ይወስዱ እንደነበር እና ለዚህም ምክንያታቸው ጃፓን የምሥራቁንም የምዕራቡንም ስልጣኔዎች ሳይጋጩ በመያዝ ጥንታዊነት እና ዘመናዊነት ተመጋግበው እና ተደጋግፈው ሀገርን ሊሳድጉ እንደሚችሉ ጥሩ ማሳያ በመሆኗ ነበር። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች ሃገራትም ይህንኑ "በተዋህዶ የመክበር" ስኬት ሊደግሙት አልቻሉም። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ጃፓን ከ"Meiji restoration" በፊት ይህ ተሃድሶ እንዲመጣ መንገድ ጠራጊ የሆኑ ምክንያቶች እንደነበሩ እነዚህም ተመሳሳይ ባህል እና ቋንቋ፣ ከፍተኛ የተማረ የሰው ኃይል፣ ያደገ ከተሜነት፣ ጠንካራ የንግድ ባህል እና የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ናቸው[70]።

70 Bahru Zewdie, Poineers of change in Ethiopia, The Reformist Intellectuals of the Early 20th century,Ohio University Press,2002, p. 5

እንግዲህ ኢትጵያ ዛሬም ባዕድ ሕግጋትን ከባህሏ እና የመንግስት እና ሕዝብ አስተዳደር ጋር የማዳቀል እና የማስረፅ ልምምዷን አጠናክራ ቀጥላለች። እነዚህ ሕግጋት ግን ከሕዝቡ አኗኗር ጋር ያልተገናዘቡ እና ያልተጣጣሙ በመሆናቸው በየጊዜው የሚሻሻሉእና የሚሻሩ በመሆናቸው የተለመላቸውን ያህል ጥቅም እየሰጡ አለመሆናቸው እሙን ነው። ይህ ባህል መቅረት ይኖርበታል፣ ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ የራሷን የሕግ ፍልስፍና በማዋቀር ሕግ ማመንጨት እንጂ ሕግ መቅዳት የለባትም፤ ሕግጋቱ መቀዳት ካለባቸው ሃገሪቷ ውስጥ ካሉት የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ባህል፣ ወግ እና ልማድ እንጂ ከውጪ ሃገራት ባዕድ ልምድ እና ባህል አይደለም። ካደጉት ሃገራት መዋስ ያለብን የሕግ ሐሳቦች እጅግ የተመረጡ፣ አነስተኛ እና ቴክኒካዊ ሆኑ እና ሀገር ውስጥ በሚደረግ ውይይት እና ምርምር ሀገራዊ ከሆኑ እሴቶች ጋር ሊጣጣሙ የሚችሉትን ብቻ መሆን አለበት።

ከጥንታዊነት ወደ ዘመናዊነት

"የበኩር ሕገ-መንግስት ፍጭት"

የዘመናዊነት ፅንሰ ሐሳብን በአግበቡ ሳንረዳ እና ምን እንደምንፈልግ በአግባቡ ሳይገባን የተደረገ ሩጫ በመሆኑ የዶ/ር አበራ ጀምበሬን ቃል ተጠቅመን "ከጥንታዊንት ወደ ዘመናዊነት" ያደረግነው ዝላይ ከፍተኛ ፍጭት ያስተናገደ ነበር። በተዋህዶ የመክበር ፍላጎት ሳይሳካ መና የቀረ መሆኑን ለመረዳት በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የተሻሬ ሕገ-መንግስት ሲረቅቅ እና ሲፀድቅ በተራማጆቹ እና በጥንታዊያኑ መሀከል የነበረውን ፍጭት ማየት ይበቃል። ይህ ሕገ-መንግስት የንጉሰ ነገስቱ "ስጦታ" ስለመሆኑ በመግቢያው ያለ ምንም ርህራሄ ያረዳናል። እንደ ዶ/ር አበራ ጀምበሬ ከሆነ ሁለት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው በሕዝቡ የሚታወቀው ሲሆን 55 አንቀፆች ያሉት፣ 20 በሚደርሱ አርቃቂዎች ንጉሱ፣ መሳፍንቱ እና ጳጳሱ በተገኙበት የተፈረመ ነው። ሁለተኛው ክፍል 85 አንቀፆች ያሉት ሲሆን እንደ ማጣቀሻ እንዲያገለግል ታስቦ ቢፈረምበትም ከዋናው ሰነድ ጋር

አብሮ አልታወጀም። ሁለተኛው እና ያልፀደቀው ሰነድ የተዘጋጀበት ዋነኛ ምክንያት መሳፍንቱ ናቸው። ለዚህም ምክንያቱ ዋነኛው ሰነድ የንጉሱን መለኮታዊ እና ፍፁማዊ ስልጣን ሲያረጋግጥ የመሳፍንቱን መብት እና ስልጣን ሳይገልፅ ያለፈ ነበር። በይፋ ያልታወጀው ሁለተኛው ሰነድ ግን መሳፍንቱ ስላላቸው ስልጣን የሚያብራራ ሲሆን በዘር የሚተላለፍ የርስት መብትን ይደነግጋል።

ለዚህ ምክንያት የሆነው ብዙዎቹ መሳፍንቶች ልጅ እያሱን ከስልጣን ለማውረድ ከተፈሪ መኮንን ጋር ያበሩ በመሆናቸው ተፈሪ ስልጣን ሲይዝ በዚህ እንዲክሳቸው ስለፈለጉ ነው። ይህ ሕገ-መንግስት ኃይለስላሴ ዘውድ በጫኑ ዘጠነኛው ወር የታወጀ ሲሆን፤ዘውዴ ረታ "የቀዳማዊ ኃይለስላሴ መንግስት" በሚለው መጽሐፋቸው በወቅቱ የነበረውን የማርቀቅ ሂደት በዝርዝር አስረድተዋል። አጼ ኃይለስላሴ በአዋጅም በግልም ለመሳፍንቱም ለሕዝቡም በተደጋጋሚ ጊዜ ማንም ሳያስገድዳቸው ለሕዝቡ የሰጡት ሕገ-መንግስት መሆኑን ቢገልፅም ዘውዴ ረታ ግን ዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ ንጉሱ ሀገራቸውን "እንዲያዘምኑ" ከፍተኛ ጫና ያሳድርባቸው እንደ ነበር ያስረዳሉ። በዚህም ምክንያት ዙፋኑን ከተረከቡ ብዙም ሳይቆዩ ሊግ ኦፍ ኔሽን የተሰኘው ዓለም ዓቀፍ ድርጅት ሃገሪቷ በአባልነት እንድትቀጥል የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ አውጥቶ ለንጉሱ ሰጥቷቸው ነበር።

ከእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች መሀከል የባርያ ንግድን ማጥፋት፣ አስከፊ እና ኢ-ሰብዓዊ የሆነ የሞት ቅጣትን ማስቀረት እንዲሁም "ዘመናዊ" የትምህርት ስርዓት እና ሕግጋትን ማስተዋወቅ የሚሉት ይገኙበታል። ዓለም ዓቀፍ ተቋሙ ንጉሱ የባርያ ነጋዴዎችን አድኖ ለሕግ የሚያቀርብ ተቋም እንዲመሰርቱ ሐሳብ እስከማቅረብ ደርሶ ነበር። ሃገሪቷ ሊግ ኦፍ ኔሽንን ከተቀላቀለች ከስድስት ዓመታት በኋላ እንኳን ተገቢውን የዘመናዊነት ደረጃ እንድታሟላ ከፍተኛ ጫና ቢደርስባትም እነ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ እና ንግስት ዘውዲቱ የአልጋ ወራሽ ተፈሪ ተራማጅ አስተሳሰብ የሚጎትቱ ነበሩ።

በዚህም ምክንያት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ንጉሰ ነገስት ተብለው በነገሱ ማግስት መሳፍንቱን፣ ሚኒስትሮችን፣ የጦር መኮንኖችን፣ ጳጳሱን እና የሚመለከታቸውን ጠርተው ሕገ-መንግስት እንዲረቀቅ እና ይህንኑ የሚያስተባብር ኮሚቴ እንዲቋቋም ያዘዙት፤ይህንኑም ሲያብራሩም የተሻለ ሕገ-መንግስት ማወጅ ሀገሪቷን ወደ ዘመናዊ አስተዳደር ለማሻገር ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት እና ሁሉም ባለው አቅም ይህንን ጥረት መደገፍ እንደሚገባው መክረዋል። በዚህ ወቅት መሳፍንቱ በሁለት ይከፈላሉ፤ወግ አጥባቂዎቹ ሕገ-መንግስት እና ፓርላማ የሚባሉ ባዕድ አሰራሮችን ወደ ሃገሪቷ ማስገባት ለረዥም ዘመን የቆየውን ባህል፣ ታሪክ፣ ወግ እና ልማድ የሚጻረር በመሆኑ መቅረት ይገባዋል ሲሉ ተራማጅ የሆኑት መሳፍንት በበኩላቸው ሕገ-መንግስት እና ፓርላማ ስልጣንን በመገደብ የመንግስት ስርዓት እንዲዘምን እንደሚደርግ አሳስበዋል። የወግ አጥባቂዎቹ ቡድን የሚመራው በራስ ካሳ ሃይሉ ሲሆን የተራማጆቹ ቡድን ደግሞ በበጅሮንድ ተክለሐዋሪያት ተክለማርያም እና ራስ እምሩ ሃይለስላሴ[71] ነበር። በሁለቱ ቡድኖች መሀከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት ግን ግልፅ ሲሆን መሳፍንቱ ስልጣናቸው ወደ ልጆቻቸው በዘር እንዲተላለፍ እና በየክፍለ ሀገራቱ ያለው የመሬት ይዞታም እንዲሁ ወደ ልጆቻቸው እንዲተላለፍ በሚፈልጉት ወግ አጥባቂዎቹ መሳፍንት እና ይህ ስርዓት እንዲቀር ሕዝባዊ መንግስት እንዲመሰርት በሚፈልጉት ተራማጆቹ መሳፍንት መሀከል ነበር።

ዘውዴ ረታ እንደጻፉት ንጉሰ ነገስቱ የተራማጆቹን ዘመናዊ አስተሳሰብ ቢደግፉም ወግ አጥባቂዎቹ የታፈሩ እና የተፈሩ መሳፍንት በመሆናቸው

---

71 ነገር ግን በዚያን ጊዜ በኢትዮጲያ ባገራችን የትምህርት ነገር ስላልተስፋፋና የህዝቡም ኑሮ በጥንተ ልማዱ የቆየ ስለሆነ፤ እጅግ የበረታ የንጉስና የባላባት ሹማምንት የካሃናትም ሰልጣን ነበረ። የድሞክራት ኮንስቲቲሲዮን ደህና አድርጎ ለመመስረት አልተቻለም። ቢሆንም መንግስት ከጥንቱ ሲጀመር የተመሰረትው ስለህዝቡ ጉዳይ ስለሆነ እኛ ቁርጥ አሳብ አድርገን የህዝብ ጉባኤ መንግስት እንዲቆም ነበር ፍቃዳችን።

(ልዑል ራስ እምሩ ሃይለስላሴ፤ ካየሁት ከማሰታውሰው፤ አአዩ ፕሬስ፤፤ 2002፤ ገጽ 184)

ሐሳባቸው በሁለት ተጣብቆ ይጨነቁ ነበር[72]። ራስ ካሳ ኃይሉ እና በጅሮንድ ተክለሀዋሪያት በንጉሱ ፊት ዱላ ቀረሽ የሚባል ክርክር ያደረጉ ሲሆን ንጉሱ የሁለቱንም ወገን መከራከሪያ ሐሳብ ካደመጡ በኋላ ወግ አጥባቂዎቹ "ፓርላማ" የሚባል ነገር ጭራሽ አያስፈልግም ሲሉ ያነሱትን መከራከሪያ በማለዘብ ሁለት ፓርላማዎች እንዲቋቋሙ እና የሕግ መመሪያ የተባለው የታችኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕዝብ በተመረጡ እንደራሴዎች እንዲቋቋም እና ሕግ በማርቀቅ ለንጉሰ ነገስቱ የማቅረብ ስልጣን እንዲሰጠው ወስነዋል። ወግ አጥባቂዎቹ እንደተከራከሩት ቢሆን የሕግ ረቂቁን ለመንግስት የማቅረብ ኃላፊነት እና በሕዝብ ድምፅ የመወከል ሂደት ራሱ የተጋነነ ስልጣን በመሆኑ መቅረት እንዳለበት አበክረው አስጠንቅቀዋል። በዚህ ምክንያት ራስ ካሳ እና በጅሮንድ ተክለሀዋርያት በጣም የከረረ እና የግል ስብዕናን የሚነካ ንግግር ይለዋወጡ እንደነበር እና ሕገ-መንግስቱን የማርቀቅ ሂደት የሁለት ሐሳቦች ማለትም የ"ጥንታዊነት" እና "ዘመናዊነት" ከፍተኛ ፍጭት አውድማ መሆኑን ከተክለሃዋሪያት ጠንካራ ቃላት መረዳት ይቻላል[73]።

ይህ ሕገ መንግስት ጃፓንን እንደ ምሳሌ በመውሰድ የተረቀቀ ሲሆን ልክ እንደ ጃፓን ጥንታዊነትን እና ዘመናዊነትን ለማዋሃድ ጥረት ያደረገ

72 ልማዳዊውን የፌውዳል ሥርዓት በሚያምኑት መሳፍንትና፤ ዘመናዊ አስተዳደር እንዲመሰረት በሚደግፉት ሚኒስትሮች መሃከል በተፈጠረው ከፍተኛ የሐሳብ ልዩነት፤ ቀዳማዊ ሐይለስላሴ ለሚሰጡት ውሳኔ ምን ያህል ከባድ እንደሆነባቸው መገንዘብ ይቻላል። ንጉሰ ነገስቱ በዚያን ጊዜ የነበራቸው አስተሳሰብ በፕሮግሬሲስት መንፈስ ላይ የተመሰረት ቢሆንም፤ የዘውዳቸው ምሶሶዎች ከሆኑት ከመሳፍንቱና ከባላባቱ ጋር ቀጥታ የሆነ ጦርነት መግጠም አይችሉም ነበር።
(ዘውዴ ረታ፤ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ መንግስት ከ1923-1948፤ ሻማ ቡክስ፤ 2007 3ኛ እትም፤ ገጽ 33)

73 ላንድ ሰው ንጉስ ለተባለው የተሰጠው ስልጣን ለማስተዳደር አስፈላጊ ቢሆንም እንኳ፤ እብሪቱ እንዳሰኘው ወይም በባለሟሎቹ አዋካቢነት እየተገፋ በህዝቡ ትዳር ላይ አዛኝ መሆኑ ቀርቶ፤ ህዝቡ በፍቃዱ የመረጣቸው ወኪሎቹ በጉባዔ እየተሰበሰቡ፤ እየተከራከሩ ላገር መተዳደሪያ የሚሆኑትን ደምቦቹን ሃሳቦቹን በቃል ብዛት እንዲቆርጡ ማድረግ አስፈላጊነቱ ከሁሉ የባሰ መሰለኝ። ስለዚሁ ሁሉ ኮንስቲቲሲዮኑን የመጻፍ አጋጣሚ ሲፈቀድልኝ እምቢ ማለቱ ትልቅ ስህተት መሆኑን ተረዳሁት።
(ፊታውራሪ ተክለሓዋሪያት ተክለማሪያም፤ የህይወቴ ታሪክ፤ አአዩ ፕሬስ፤ 1998፤ ገጽ 400)

እንጂ በመጨረሻ የታወጀው ሕገ-መንግስት መሳፍንቱ ያላቸውን በዘር የሚተላለፍ የርስት እና የስልጣን መብት በመንጠቅ ስልጣናቸውን በንጉሰ ነገስቱ ፍቃድ የሚፀና አድርጎታል። በዚህ ምክንያት አንዳንዶች ሲከራከሩ ንጉሰ ነገስቱ ዘመናዊነትን በማስተዋወቅ ሰበብ ሁሉን ነገር በሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ስር እንዲሆን የጠቀለሉበት ሕገ-መንግስት መሆኑን ይጠቁማሉ። ሕገ-መንግስቱ ከረቀቀ በኋላ ያለውን መንግስት ታሪክ ስናጠና ሕገ-መንግስት የረቀቀው አስቀድሞም ቢሆን ስልጣንን ለማካበት እንጂ እውነተኛ ዘመናዊነትን ለማስተዋወቅ አልነበረም። የተፈለገው "ዘመናዊነት" ራሱ በውጪ ጫና የመጣ እንጂ ከውስጥ መነጨ ባለመሆኑ ዛሬም ቢሆን የሕግ እና የፍትሕ አስተዳደራችን በልማዳዊ እና ሀገራዊ በሆነው ማንነት እና ምዕራባዊ ወይም ምሥራቃዊ በሆነው የሕግ ፍልስፍና መሀከል ግራ ተጋብቶ የቆመ ነው።

ምሥራቃዊነት ወይስ ምዕራባዊነት

"ነገሊ ፎትሐ ኑገስት"

የሀገራችን የፍትሕ አስተዳደር ስርዓት እና የሕግ ፍልስፍና የታነፀው በምዕራባዊነት ወይም በምሥራቃዊነት የሕግ ፍልስፍና ላይ መሆኑ የተረጋገጠ አይደለም። ምዕራባዊ ስልጣኔ ወይም ፍልስፍና ከፍተኛ አትኩሮት የሚሰጠው ለአመክንዮ እና ተግባራዊ እውቀቶች ነው። ኢማኑኤል ካንት "አብርሆት ምንድነው?" በተሰኘው እና የዘመነ አብርሆትን ፋይዳ በሚመረምርበት ጽሑፍ በአውሮፓ የነበረው አጠቃላይ እንቅስቃሴ እና መሠረታዊ የሆነውን የዘመኑን ፈላስፎች ጥያቄ "የገዛ አመክንዮህን ለመጠቀም ድፈር" በሚል ዓረፍተ ነገር እንደሚጠቃለል ጽፏል። በመሆኑም ምዕራባዊነት ከጥንት እስከዛሬ ለአመክንዮ፣ ለተፈጥሮ ሳይንስ እና ሰው ሠራሽ ግኝቶች ቅድሚያ ስለሚሰጥ መንፈሳዊ የሆኑት ምዕራባዊ ሃይማኖቶች እና የሥነ-መለኮት አቀንቃኞች እንኳን ምርምራቸው በምክንያት እና ምርምራዊ ድርሳናት ላይ እንዲሆን ብዙ ይጥራሉ።

ምሥራቃዊ ስልጣኔ እና ሃይማኖቶች በበኩላቸው ከአመክንዮ እና ተግባራዊ እውቀቶች ባሻገር በተመስጥኦ (Mysticisim) ላይ ይመረኮዛሉ። ምሥራቃዊ ሃይማኖቶች እና ስልጣኔዎች ሁሉን ነገር በአመክንዮና ምርምር ከማስረዳት ይልቅ ወደ ውስጥ በተመስጥኦ የመመልከት፤ አንድ እና ፍጹም የሆነ እውነትን ከመፈለግ ይልቅ ሁሉንም እውነቶች በየዓውዳቸው የመቀበል እና የማስረፅ ባህሪ አላቸው። የኢትዮጵያ የሕግ ፍልስፍና በእነዚህ ሁለት ስልጣኔዎች መካከል ከመሆኑም ባሻገር እነዚህን ሁለት አስተሳሰቦች በአፍሪካ አሕጉር ውስጥ አቻችሎ ለማኖር የሚጥር ነው። አፍሪካዊ የሕግ ፍልስፍና እና ስልጣኔ ደግሞ በመሠረታዊነት አፋዊ እና ማኅበረሰባዊ ነው። ለተመስጦአዊ ልምምድ ወይም ለአመክንዮአዊ ምርምር ሳይሆን ከትውልድ ትውልድ በቃል ሲተላለፍ የመጣ ባህልና ልማድን በማስጠበቅ የሚገለፅ ነው። አፍሪካውያን "Ubuntu" ወይም "I am because We are" "እኔነቱ ከእናንተነት ውስጥ ይገኛል" በሚል ብሂል ስለሚያምኑ በጋራ የመኖር፣ የማምለክ፣ የማምረት እና የመንቀሳቀስ የቆየ ልምምድ አላቸው። እንግዲህ ኢትዮጵያ ሦስት ዓይነት ስልጣኔዎች የሥነ-ሕግ ፍልስፍና መናኸሪያ ናት ብንል የተጋነነ አነጋገር አይሆንም።

ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን ኢትዮጵያ ጥንታዊ የሆኑትን የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖቶች መገኛ ስትሆን ሁለቱም ሃይማኖቶች ያልደረሱባቸው እና በባህላዊ አኗኗር የሚኖሩ ህዝቦችም ያሉባት ናት። እንግዲህ የኢትዮጵያ የሕግ ፍልስፍና እነዚህን ሁሉ የስልጣኔ እና የአኗኗር ዓይነቶች ለማዳቀል እና ለማዋሃድ ጥረት የሚያደርግ ነው። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን ፍትሐ-ነገስት የተባለው የሕግ ድርሳን ታሪክ ነው። ፍትሐ-ነገስት ንጉስ ዘርዓ ያዕቆብ ካሳወጁት የመጀመሪያ አጠቃላይ ሕግ ከሆነው "ፈውስ መንፈሳዊ" ቀጥሎ የታወጀ እና ኢትዮጵያን ለረዥም ዘመን ያገለገለ ነው። ስለዚህ ሕግ አመጣጥ እና ፋይዳ በአግባቡ ብዙ ምንጮችን አጣቅሰው የጻፉልን ዶ/ር አበራ ጀምበሬ ናቸው። *"ፍትሐ ነገስት የኢትዮጵያ ሕግ ሆኖ በሕግ ተቀባይነት ያገኘበት ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ የተዋሃደበት ጊዜ በትክክል ያልታወቀ እንደመሆኑ መጠን*

በፍርድ ቤቶችም የተጠቀሰ ፍርድ መስጠት የተጀመረበት ጊዜ ተረጋግጦ አልታወቀም[74]" ይሉናል። ይህንኑ ሲያብራሩም ሲቸኮንቲ ሮስኒ የተባለ ጣሊያናዊ የታሪክ ተመራማሪ በአጼ ሰርፀ ድንግል(1558-1588) ዘመን ላይ ሥራ ላይ እንደዋለ ሲጠቅስ ከአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን (1426-1460) ጀምሮ በተለያዩ ገዳማት ወደ ግዕዝ ተተርጉሞ በሀገሪቱ ሁሉ ይሰራበት እንደነበር እንደተጣፈም ይነግሩናል። እጅግ የሚገርመው እና አነጋጋሪ የሆነው ጉዳይ ፍትሐ-ነገስት መቼ ወደ ሃገራችን ገባ?የሚለው ሳይሆን በማን ተፃፈ፣ ይዘቱስ ምንድነው የሚለው ነው። ይህ ጉዳይ አከራካሪ በመሆኑ ብዙዎች ወደኋላ እንደተስማሙት "*ፍትሐ ነገስት ከቅዱሳት መፃሃፍት፣ ከሮማውን ሕግና ከጀስቲኒያን ሕግ የተቀዳ ከመሆኑም በላይ በተፃፈበት ዘመን በግብፅ የነበረው አስተሳሰብና የአካባቢ ሁኔታ ያሳደረው ተፅዕኖ ውጤት የሆኑ አንዳንድ የሕግ መሠረታዊሐሳቦች ያሉበት ይመስላል*[75]"። ማለትም ፍትሐ-ነገስት ምዕራባዊም ምሥራቃዊም የሆነ የሕግ ሰነድ ነው።

የፍትሐ-ነገስት ደራሲ መሆኑ የሚነገርለት ግብፃዊው አብን አል አሳል ሕግጋቱን ከሮማዊ ሕግጋት እያጣቀሰ ወደ አረብኛ ቋንቋ ሲፅፍ እርሱ የኖረበት እና የጻፈበት አካባቢ ባህል እና ወግ ማለት የእስልምና ሕግጋት ምንጮች ተፅዕኖ እንዳሳደሩበት ብዙዎች ይስማማሉ። ሌሎች ተመራማሪዎች እንደሚሉት ከሆነ ደራሲው ከሮም ሕግጋት ላይ ተመርኩዞ አብን አል አሳል የጻፈው ሳይሆን የቀደሙ የክርስትና እምነት አባቶች ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን፣ የጳጳሳት ጉባኤ ውሳኔዎች አጣቅሰው የጻፉት እንደሆነ በመጥቀስ ይከራከራሉ። እንግዲህ የኢትዮጵያን ማዕከላዊ መንግስት ከ1426 እስከ 1950ዎቹ ድረስ ለ500 ዓመታት ያገለገለው ዋነኛ መጻሕፍ ይዘቱ እና ምንጩ አከራካሪ መሆኑ እሙን ነው። ከዚህም በላይ ይህ ሕግ የምሥራቁንም የምዕራቡንም ሃይማኖቶች እና ፍልስፍናዎች በሕግጋቱ አንቀፆች ውስጥ ያንፀባረቀ ነው።

74 የኢትዮጲያ ሕግና የፍትህ አስተዳደር ታሪክ ፤ ገጽ 162

75 ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 167

የሀገራችን የሕግ ፍልስፍና እስከዛሬ ድረስ እንደዚህ ዓይነት ግራ መጋባት ላይ የወደቀ በመሆኑ ፍትሐ-ነገስት የኢትዮጵያ ሥነ-ሕግ ያለበት የማንነት ቀውስ ጥሩ ማሳያ ነው። ዛሬም ድረስ ከተለያዩ ሃገራት ልዩ ልዩ አዋጆችን እንቀዳለን፤ይህንኑም በኩራት እንናገራለን። አሁን በሃገራችን ያሉ ሃይማኖቶች ራሳቸው ስሜታቸው እና ፍላጎታቸው በምሥራቅ እና በምዕራብ ስልጣኔ መሃል የተለጠጠ በመሆኑ የሕዝቡም ባህል እና ማንነትም እንዲሁ በምዕራባዊነት እና በምሥራቃዊነት ፍልስፍና እና ተመስጥኦ መሃል እየተምታታ ይገኛል። በዓለም ላይ እየዞርን ሕግጋትን እንደ ቡፌ ከማንሳት የራሳችንን ሕግጋት ማምረት መቻል ይኖርብናል። ይህ የሚሆነው ደግሞ ሃገሪቷ የራሷ የሕግ ፍልስፍና ሲኖራት አልያም ተፎካካሪ የሆነ የሥነ-ሕግ ቤተ-አስተምህሮችን ለይታ በማወቅ እነዚህ ቤተ-አስተምህሮዎች በትብብር እንዲሰሩ ማድረግ ይኖርባታል። እንዲህ ስንል ባህላዊ እና ልማዳዊ የሕግ ፍልስፍናዎችን የማንነታችን እውነተኛ መገለጫዎች እንደመሆናቸው እነዚህን ሕግጋት በቴክኖሎጂ እና ሳይንስ የቀደሙን ሀገራት ከሚያወጣቸው አስፈላጊ እና አስገዳጅ ሕግጋት ጋር ማዋሃድ ያስፈልጋል። ያልተዋሃዱ እና ያልተጣጣሙ ሕግጋት ሲያጋጥሙን ለራሳችን ባህላዊ እና ልማዳዊ ሕግጋት ቅድሚያ መስጠት ይኖርብናል።

ምዕራፍ ስምንት

ሕግ፣ ፍትሕ እና የፖለቲካ ርዕዮት ዓለም

የፖለቲካ ርዕዮት ዓለም ከሕግ ፍልስፍና ጋር ያለው ቁርኝት እጅጉን የጠበቀ ነው። የሕግ ፍልስፍና (Jurisprudence) ዘመናዊ የሕግ ስርዓት መዘርጋት ከተጀመረ በኋላ በሕግ አውጪው እና በሕግ ተርጓሚው፤ በማኅበረሰባዊ የሞራል አስተምህሮና በሰው ሠራሽ ሕጎች መሀከል ያለውን ግንኙነት በአንክሮት የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ ሊሆን ችሏል። የፖለቲካ ፍልስፍና ግን ከሕግ ፍልስፍና ቀዳሚ እና ሰፋ ባለ መልኩ የመንግስት ስርዓት እና የፖለቲካዊ አመራር ከልዩ ልዩ አመለካከቶች አንፃር ምን እንደሚመስል የሚዳስስ ነው።

በእነዚህ ንዑስ ርዕሶች ስር የምናነሳቸው የፖለቲካ ፍልስፍናዎች እና ፈላስፋዎች ከሕግ አወጣጥ እና ከፍርድ ቤቶች አሠራር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖራቸውም ሕግ ሊወጣ የሚችልበትን አስተሳሰብ የሚቃኙ ናቸው። በመሠረቱ ቀደምት ጠሊቅ አሳብያን ስለ ስርዓተ-መንግስት ሲፅፉ እና ሲመራመሩ የመንግስትነት ፅንሰ-ሐሳብን አጠቃላይነት ባለው መልኩ የሚመለከቱት በመሆኑ ስለ ሕግ እና ባህሪያቱ እግረ መንገዳቸውን ጠቅሰው ያልፋሉ እንጂ ሕግን ለብቻው ነጥለው በመውሰድ አያጠኑትም። ለምሳሌ ታላቁን ፈላስፋ አሪስቶትልን ብንወስድ ስለ ግብረገብነት እንደፃፈ ሁሉ ስለ ፊዚክስ ፅፏል። ይህ የሚያሳየን እውቀት አብዛኞቹ ቀደምት አሳቢያን የተጠቀለለ እና ወጥ እንደሆነ አድርገው ያስቡ እንደነበር ነው። ቅዱስ አኩይናስ የሥነ-መለኮት ምሁር ቢሆንም ስለ ሕገ-ሰብዕ እና ሞራል ፍልስፍናዎችም በጥቅሉ ፅፏል። በዘመናዊ የሕግ ፍልስፍና ደንብ ሕግ ራሱን

የቻለ ስርዓት ሲሆን ከሌሎች የትምህርት ዘርፎች ጋር ያለው ቁርኝትም ቢሆን እንዲሁ በልዩነት የሚጠና ነው። በዘመናዊው ዓለም የፖለቲካ ርዕዮት ዓለም መንግስት ለሚያወጣቸው ፖሊሲዎች መሠረት ሲሆን ሕግ ደግሞ እነዚህ ፖሊሲዎችን የሚያስፈፅም መሣሪያ ነው። በመሆኑም ከዚህ ምዕራፍ በፊት የተወያየንባቸው ቀደምት የግሪክ ፈላስፋዎችም ሆነ የመሀከለኛው ዘመን ፈላስፋዎች ስለ ሕግም ሆነ ስለ ፖለቲካ የጻፉት አያሌ ጉዳይ ቢኖርም ታዋቂ የሚባሉት የፖለቲካ ፈላስፎች ስለ ሕግ እና ስለ ሀገረ መንግስት ያወሱትን ለማሳየት ጥረት ተደርጓል። እነዚህ የፖለቲካ ርዕዮት ዓለም አቀንቃኞች አብዛኛውን ግዜ በተማረው የማኅበረሰብ ክፍል በስፋት የሚታወቁና አስተሳሰባቸው አከራካሪና ለዘመናዊው የፖለቲካ ዓለም ፋና ወጊ እና መሠረት ጣይ በመሆናቸው ሃሳባቸውን በጥቂቱ ለመዳሰስ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

ኒኮሎ ማኪያቬሊ- የልዑል መካሪ

"ሕግ እና ሰይፍ"

ኒኮሎ ማኪያቬሊ (1469-1527) በጣሊያኒቷ ፍሎረንስ ከተማ የሕግ ባለሙያ ከነበረው አባቱ ተወልዶ እርሱም ራሱ የተለያዩ የመንግስት ኃላፊነቶችን ሲወጣ ኖሯል። ኒኮሎ ማኪያቬሊ በስፋት የሚታወቀው በጻፋቸው ሁለት ድርሳናት ሲሆን እነዚህም "The prince/ልዑሉ" እና "Discourse/ሐተታዎች" በመባል ይታወቃሉ። ልዑሉ የተሰኘው ድርሳን በወቅቱ ከተማዋን ለሚያስተዳድረው ገዢ ማኪያቬሊ በእስር ላይ ሆኖ የጻፈው ምክር ነው። ምክሩ ግን ሰናይ ምግባር እና መልካምነትን የሚሰብክ ሳይሆን አንድ ገዢ በስልጣን ላይ ለመቆየት ማድረግ ያለበት እኩይ እና ሰናይ ተግባራትን በተለዋዋጭነት በመጠቀም መሆኑን የሚያስረዳ ነው። በመሠረቱ አንድ ልዑል በስልጣን ላይ ለመቆየት መከተል ያለበት የሞራል እሳቤ እና እሴት "Virtu" እንደሆነ ይገልፃል። ይህ እሳቤ በቀዳሚው ምዕራፍ ካየነው "Virtue ethics" እጅጉን ይለያል።

እንደ ማኪያቬሊ ሐሳብ “virtu”/ቨርቲዩ ከ “virtue”/ቨርቹ በይዘት እና ቅርፅ የሚለይ ሐሳብ ነው። ይህ የማኪያቬሊ እሳቤ ከምግባራዊነት እና ቀደምት የግሪክ ፈላስፎች ካስረዱት እና በወቅቱ ከተንሰራፋው ክርስቲያናዊ ሞራል የሚፃረር ነው። አንድ ሃገረ-ገዢ በሚያስተዳድረው ከተማ ውስጥ ሰላም እና የተረጋጋ መንግስት እንዲመሠረት ከፈለገ ከተለመደው ክርስቲያናዊ ምግባር ባፈነገጠ መልኩ አንዳንድ እኩይነት እና ጭካኔ የተሞላባቸው እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል። ምክንያቱም ሀገር ለመምራት ምግባረ ሰናይ ከመሆን ይልቅ የማይወደዱ እና የማይፈለጉ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው።

> As all those have shown who have discussed civil institutions, and as every history is full of examples, it is necessary to whoever arranges to found a Republic and establish laws in it, to presuppose that all men are bad and that they will use their malignity of mind every time they have the opportunity; and if such malignity is hidden for a time, it proceeds from the unknown reason that would not be known because the experience of the contrary had not been seen, but time, which is said to be the father of every truth, will cause it to be discovered[76].

በሀገረ መንግስት ምስረታ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች በሙሉ ማወቅ ያለባቸው አንድ መሠረታዊ ጉዳይ ቢኖር ሰዎች ሁሉ ክፉ እና መሰሪ እንደሆኑ ነው። ይህ መሰረታዊ ባህሪ ለጊዜው ተደብቆ የቆየ ቢመስልም እንኳን በጊዜ ሂደት ራሱን መግለጹ አይቀርም። በመሆኑም ልዑሉ ሁለት መልክ ሊኖረው ይገባል ፤ የጭካኔ እና የርህራሄ። ሁለቱንም እንደየአስፈላጊነቱ ሊጠቀምባቸው ይገባል። ሕዝቡ ገዢውን ሊወደውም ሊፈራውም ይገባል ፤ የማይወደው ከሆነ

76 Niccolo Machiavelli ,Discourses on Livy , 1517, BooK one, Ch 3, (as translated by LJ Walker and B Crick)

ግን ቢፈራው የተሻለ ነው። ምክንያቱም “በሆነው” እና “ሊሆን በሚገባው”/ “Is/Ought” መሀከል ሰፊ የሆነ ልዩነት መኖሩን መረዳት ይኖርብናል። በመሆኑም አንዳንዴ “ልዑሉ” የተሻለ ጥቅም ለማግኘት ሲል አነስተኛ ዋጋ የሚያስከፍል ጭካኔ እና እኩይነት ቢያሳይ ችግር አይኖረውም።

ዋናው ቁምነገሩ “ልዑሉ” መልካም ባህሪ ያለው መሆኑ ሳይሆን መልካም ባህሪ ያለው መስሎ መታየቱ ነው፤ምክንያቱም ሰፊው ማኅበረሰብ ልዩነቱን አይረዳም። ለዚህም ይረዳው ዘንድ ጭካኔን እና ጥላቻን የሚጠይቁ ሥራዎችን ለበታች ሹማምንት በመስጠት ተወዳጅነትን የሚያተርፉ ሥራዎችን ለራሱ ማስቀረት እና መጠቀም ይኖርበታል። በዚህም ምክንያት ሰዎች ለእኩይ ተግባራት የበታች ሹማምንቶችን ሲወቅሱ ለመልካም ሥራዎች ደግሞ ልዑሉን ያወድሳሉ። በመሆኑም ልዑሉ ሁልግዜም ቢሆን የሰፊውን ሕዝብ ድጋፍ ማግኘቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል። ከበታች ሹማምንቱ እና መሳፍንቱ የሚገኘው ታማኝነት ከሰፊው ሕዝብ እንደሚገኘው ድጋፍ እና ታማኝነት አይደለም። የበታች ሹማምንት ሕዝቡ ለልዑሉ ያለው ድጋፍ እየቀነሰ መሆኑን ከተረዱ በልዑሉ ላይ ያምፃሉ። ለአንድ ልዑል አስፈላጊ የሆነ ግብዓት ታማኝነት (Loyalty) በመሆኑ በጦር ሰራዊቱ ውስጥ እንኳን በተቻለ መጠን ቅጥረኞችን እና ባዕዳንን ከመቀላቀል መቆጠብ ይኖርበታል። ልዑሉ በተቻለ መጠን ከእርሱ የቀደሙ ሃያላን ገዢዎችን ሥራ እና ተግባር በመድገም ወይም የእነርሱን ንግግር እና ባህሪ ለማስመሰል መጣር እና እራሱን ማለማመድ ይኖርበታል።

በአጠቃላይ ልዑሉ በተከታዮቹ ልቦና ውስጥ በክብር እንዲቀመጥ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። ጭካኔን ቢጠቀምም ሊያስከብረው የሚችለውን ያህል እንጂ እንዲጠላ የሚያስደርገውን ያህል መሆን የለበትም። ልዑሉ የአንበሳንም የተኩላንም ባህሪ የተላበሰና እንደ ተኩላ የጠላቶቹን ሽር ቀድሞ የሚረዳ እና መሰሪ፤ እንደ አንበሳ ደግሞ በሕዝቡ የሚወደድ እና የሚከበር መሆን አለበት።

You must know, then, that there are two methods of fighting, the one by law, the other by force: the first method is that of men, the second of beasts; but as the first method is often insufficient, one must have recourse to the second. It is therefore necessary to know well how to use both the beast and the man. This was covertly taught to princes by ancient writers, who relate how Achilles and many others of those princes were given to Chiron the centaur to be brought up, who kept them under his discipline; this system of having for teacher one who was half beast and half man is meant to indicate that a prince must know how to use both natures, and that the one without the other is not durable. A prince being thus obliged to know well how to act as a beast must imitate the fox and the lion, for the lion cannot protect himself from snares, and the fox cannot defend himself from wolves. One must therefore be a fox to recognise snares, and a lion to frighten wolves. Those that wish to be only lions do not understand this[77].

ሕግን በተመለከተ ማኪያቬሊ ሲያስረዳ ጥሩ ሕግጋት ለስርዓተ-መንግስት አስፈላጊ ቢሆኑም መንግስት የሚፀናው ግን በሕግ እና በሰይፍ መሆኑን ይገልፃል። ልዑሉ ጥሩ ሕግጋት እንዲፀድቁ እና እንዲተገበሩ ጥረት ቢያደርግም ሰይፉን ግን መቼም መጣል የለበትም። ምክንያቱም ጥሩ ሕግጋት ያለ ሰይፍ ዋጋ የላቸውም።

77 Niccolo Machiavelli, The Prince,1513, Ch 18, Translated by Marriot(1908)

አንድ መሪ የቀበሮ እና የአንበሳ ባህሪን መላበስ ይኖርበታል ፤ ምክንያቱም ቀበሮ ሁልጊዜ በተኩላዎች ሲጠቃ አንበሳ ደግሞ የአዳኞችን ወጥመድ ማነፍነፍ አይችልም። አንበሳም ቀበሮም የሆነ ፍጡር ግን እንደ ቀበሮ ወጥመዶችን አነፍንፎ ሲደርስበት እንደ አንበሳ ደግሞ ተኩላዎችን ያባርራል። ልዑሉ አዲስ ግዛት በሚቆጣጠርበት ወቅት በዚያ ያሉ ቀደምት ሕዝቦች የራሳቸውን ሕግጋት እና ልማድ እንዲከተሉ ሊተዋቸው ይገባል ይላል። ይሁን እንጂ ሕግጋቱ በራሳቸው የሚተገበሩ እና የሚፀኑ ሳይሆኑ በልዑሉ የስልጣን ጥንካሬ ላይ የሚደገፉ ናቸው። ማኪያቬሊ ሕጋዊነት፣ ቅቡልነት፣ ሕገ-መንግስታዊነት የሚሉ ጉዳዮች አያስጨንቁትም። ሕግን የሚመለከተው አንድን ግብ የሚያሳካ መሣሪያ እንደሆነ አድርጎ በመሆኑ የሞራል ፍልስፍናው ከጠቀሜታውያን የሞራል ፍልስፍና ጋር የሚጣጣም ነው።

ፍሬድሪክ ሄግል - የታሪክ ተማሪ

"የታሪክ ምክንያታዊ እድገት"

የፍሬድሪክ ሄግል (1770-1831) የምሁርነት ግዝፈት እጅግ ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ ለእነ ካርል ማርክስ የመንፈስ አባት መሆኑን ያስተውሏል። የበርሊን ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት እስከ መሆን የደረሰው ሄግል በወቅቱ አውሮፓ ውስጥ የተከበሩ ምሁራን ከሚባሉት የሚመደብ ነበር። ፅሁፎቹ ከባድ እና ውስብስብ በመሆናቸው ጥቂት ሰዎች ብቻ እስከዛሬ ሊረዱት ችለዋል። ለሄግል ግለሰቦች እና ፍልስፍና የሚኖሩበት ዘመን እና ታሪክ ነፀብራቅ ናቸው። የማኅበረሰቦች ሕይወት፤የመንግስታት አወቃቀር፣ የሕግጋት ረቂቅ ፤ የሳይንስ እና የምርምር ውጤቶች ያሉበት ሁኔታ ታሪክ ብዙ ደረጃዎችን ተጉዞ የደረሰበትን አሻራ የሚሳይ ነው።

በመሠረቱ ታሪክ በዘፈቀደ የሚከናወን ሳይሆን የራሱ አላማ ያለው በመሆኑ አንድ ግለሰብም ሆነ ሀገር የራሱን የሕይወት አላማ እንዲረዳ

ከእርሱ በፊት የነበረው ታሪክ እንዴት ይከወን እንደነበር እና አላማው ምን እንደነበር መመርመር ይኖርበታል። ይህ በተለምዶ የታሪክ ፍልስፍና(Philosophy of history) በመባል የሚታወቅ ነው።

History, is a conscious, self-meditating process —

Spirit emptied out into Time[78]

የዓለም ታሪክ አላማ ፍጹም የሆነውን መንፈስ እና ሐሳብ (The Absolute Spirit and Idea) መግለጥ ነው። በታሪክ ውስጥ እያንዳንዱ ደረጃ አዲስ እና ልዩ በመሆኑ ሰዎች ዘመኑ ከሚጠይቀው አስተሳሰብ እና ሁኔታ ማምለጥ አይቻላቸውም። ይሁን እንጂ ታሪክ ሁልጊዜም ቢሆን በምክንያታዊ እድገት ውስጥ ይገኛል። ይህ ምክንያታዊ እድገት የሚገኘው ደግሞ በታሪክ ውስጥ በሚፈጠሩ ተቃርኖዎች ነው። እያንዳንዱ የታሪክ ደረጃ እና የጊዜ ሂደት የሚቃረነው ሌላ ታሪክ፤ ሐሳብ እና ደረጃ ይጋፈጣል። እነዚህ ሁለት የተፋጠጡ ተቃርኖዎች በአንብሮ ሌላ አዲስ የታሪክ ደረጃ እና መረዳት ይፈጥራሉ። ይህ የታሪክ እድገት ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ሲሻገር የሚፈጥረው ማኅበረሰብ የተሻለ ምክንያታዊ እና ፍትሐዊ እንደሚሆን ይታመናል። ሄግል የጀርመን ሐሳባዊነት(German Idealism) አቀንቃኝ ከነበሩት ፈላስፎች ቀንደኛው እንደመሆኑ Rationalism እና Empiricism ለማስታረቅ ጥረት አድርጓል።

ለሄግል ታሪክ ከምሥራቁ የዓለም ክፍል ወደ ምዕራቡ የዓለም ክፍል እያደገ የሚሄድ ፅንሰ ሐሳብ ነው፤ ሄግል በታሪክ እድገት ውስጥ አፍሪካን ፍጹም ያላካተተ በመሆኑ ብዙ ሰዎች ከፍተኛ ትችት ያቀርቡበታል። ሄግል በዚህ የታሪክ እድገት ውስጥ ሰዎች ያላቸውን ሚና በመገምገም በሦስት ይመድባቸዋል። የመጀመሪያዎቹ የታሪክ ሰለባዎች ሲሆኑ የሚኖሩበትን

78 Freidrich Hegel, The Phenomenology of spirit,1807, J B Baillie translation, P.575

የታሪክ እድገት ደረጃ የማይረዱ በመሆኑ ተደፍጥጠው የሚቀሩ ናቸው። ሁለተኞቹ ደግሞ ታሪካዊ ግለሰቦች የሚባሉ ሲሆን ያሉበትን የታሪክ እድገት ደረጃ የተረዱ ብቻ ሳይሆኑ ታሪክን ወደ ሌላ ደረጃ እንዲሸጋገር የራሳቸውን አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ናቸው። ሶስተኞቹ የታሪክ እድገትን ሞራላዊነት ወይም መሆን የሚገባውን የሚተቹ እና ብዙም ጠቃሚ ያልሆኑ እንደሆኑ ሄግል ይጠቅሳል። በመሆኑም ሀገረ-መንግስት(State) የእያንዳንዱ ግለሰብ መልካም ፍቃድ በድምር የሚገለጥበት በመሆኑ ከፍተኛ እና ሉዓላዊ የሆነ ታሪክ አካል ነው።

ግለሰቦችም የዚህ ፍፁማዊ የሆነ ሀገረ-መንግስት አባል በመሆናቸው ከፍተኛ ኩራት ሊሰማቸው እንደሚገባ እና ግዴታቸውንም ለሀገረ-መንግስቱ መወጣት ይኖርባቸዋል። ይህ ፍፁማዊ ሃገረ መንግስት እንዲመሠረት በአንደኝነት የሕግ የበላይነት የሚያስፈልግ በመሆኑ ሕግጋት የዜጎችን መብት የማይጨፈልቁ እና ሁሉን ዓቀፍ መሆን አለባቸው። እነዚህን ሕግጋት ለማስፈፀም እንዲቻል የሕግ እና የመንግስት አገልጋይ የሆኑ ሰዎች መደብ ሊፈጠር ይገባል፤እነዚህም ሰዎች በብቃታቸው ብቻ ሊመረጡ ይገባል። ሄግል የመንግስት አካላት ተከፋፍለው የሚፎካከሩ ሳይሆን በትብብር ሊሠሩ የሚገባ መሆኑን አፀንኦት ሰጥቷል። ለሄግል ሀገረ-መንግስት የዜጎች ነፃነት ነፀብራቅ በመሆኑ በተፈጥሮው የዜጎችን ነፃነት እና ምክንያታዊ አስተሳሰብ ሊጋፋ የማይችል በመሆኑ ዜጎች ሁሉ ፍጹም በሆነ መንገድ ሊታዘዙለት ይገባል።

አሌክስ ደ ቶክቪል- አሳሽ ፈላስፋ

"ግለሰባዊነት እና ዴሞክራሲ"

አሌክስ ደ ቶክቪል (1805-1859) በፈረንሳይ ሀገር ከከበርቴ ቤተሰብ ተወልዶ የፈረንሳይ መንግስትን በተለያዩ የሹመት ቦታዎች ተመድቦ አገልግሏል። ቶክቪል በስፋት የሚታወቀው "Democracy in America"/"ዴሞክራሲ በአሜሪካ" በሚባለው ድርሳኑ ነው። ይህንን መጽሐፉን ለማዘጋጀት ሲል ከፈረንሳይ ወደ ሀገረ አሜሪካ ተጉዞ ለረዥም ወራት በተለያዩ ግዛቶች ተዘዋውሮ የአሜሪካን ሕዝብና የአስተዳደር ባህል መርምሮ ያሰናዳው ነው። ዴሞክራሲ ፍቅረ-ንዋይ እና ቁስ አምላኪነት ይፈጥራል ብሎ በዚሁ ድርሳን አብራርቷል። በመሳፍንት እና ነገስታት የምትመራው ፈረንሳይ መሳፍንቱ የመሬት ከበርቴዎች የተቀረው ሕዝብ ደግሞ ነጋዴ እና ባለ እጅ እንደመሆኑ ሀብት ለማካበት የሚደረግ ትግል እና ፉክክር የለም። በአሜሪካ ግን ሰው ሁሉ እኩል በመሆኑ ሀብት ለማካበት የሚደረግ ከፍተኛ ቁስ አምላኪነት አለ።

በመሆኑም ዴሞክራሲ ሰውን ሁሉ እኩል በማድረጉ ሁሉም ሰው ታላቅነትን ይመኛል፤በውልደት የሚገኝ መሬት እና ስም ባለመኖሩ በሰዎች መካከል የሚፈጠር አነስተኛ የሀብት ልዩነት ቅናት እና ተስፋ መቁረጥን ይፈጥራል። በንጉሳዊ አስተዳደር ዜጎች በመወለድ የሚያገኙት ቦታ ስላለ በሀገሪቱ ውስጥ የታወቀ የኑሮ ተዋረድ አለ። ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ሙሉ ቢሰሩ የላይኛው የማኅበረሰቡ ጠገግ ላይ እንደማይደርሱ ስለሚያውቁ ባላቸው የኑሮ ደረጃ ተደስተው ይኖራሉ፤እነዚህ ሰዎች ብዙ በመሆናቸው የማኅበረሰብ ሕይወት የተረጋጋ ይሆናል።

በተጨማሪም በሀገረ ፈረንሳይ ንጉሳዊ አገዛዙ ጨቋኝ ይምሰል እንጂ በአሜሪካው ዴሞክራሲ በማኅበረሰቡ ውስጥ ገዢ የሆነውን ሐሳብ

የሚያራምደው የማኅበረሰብ ክፍል ከንጉሳዊ አገዛዝ በሚበልጥ ጨቋኝ ነው። ይህ የብዙኃኑ አምባገነንነት በማንኛውም መልኩ የተሻሉ እና ሊደመጡ የሚገባቸው ሰዎችን ተሰሚነት የሚነፍግ በመሆኑ መሃይምነት እና ንቅዘት የተጠናወተው ነው። ይህንንም የሚያደርገው የብዙኃኑ አስተሳሰብ በጋዜጣ እና መገናኛ ብዙኃን የሚሰራጭ በመሆኑ ግለሰቦች ጠያቂ እና ተመራማሪ እንዳይሆኑ በማሰናከል ነው።

> When an opinion has taken root in a democracy and established itself in the minds of the majority, it afterward persists by itself, needing no effort to maintain it since no one attacks it. Those who at first rejected it as false come in the end to adopt it as accepted, and even those who still at the bottom of their hearts oppose it keep their views to themselves, taking great care to avoid a dangerous and futile contest[79].

አንድ ሐሳብ በስርዓተ-ዴሞክራሲ ውስጥ ስር ሲሰድ እና በብዙኃኑ አእምሮ ውስጥ ሲደላደል በማንም ጥቃት ስለማይደርስበት ያለ ማንም ጥበቃ በራሱ ይቀጥላል። በመጀመሪያ ውሸት ነው ብለው የተቃወሙትም ይቀበሉታል። አሁንም ድረስ በልባቸው የሚቃወሙትም በታላቅ ጥንቃቄ ሃሳባቸውን ለራሳቸው በማድረግ ከአደገኛ እና ከጉንጭ አልፋ ክርክር ራሳቸውን ይጠብቃሉ። ዴሞክራሲ እና ካፒታሊዝም እጅ እና ጓንት ሆነው የሚሰሩ እንደመሆናቸው ሸቀጥ እና አገልግሎትን ለማስተዋወቅ ሲባል የማሻሻጥ ባህል እና ማስታወቂያ የግለሰቡን አእምሮ ጨምድዶ ይይዘዋል። በመሆኑም ሕይወት በዴሞክራሲያዊ አውሮፓ ሀገራት እንደሚወራው ብዙም የተንደላቀቀ እና ተምኔታዊ እንዳልሆነ ለማስረዳት ሞክሯል።

79 Alexis De Tocqueville, Democracy in America, Volume II, 1840, Book Three, Chapter XXI

ቶክቪል በመሠረቱ ወደ አሜሪካ ጉስታቭ ከሚባል ወዳጁ ጋራ ያቀናው የአሜሪካን የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ለማጥናት ቢሆንም ከዚያ ሰፋ እና ጠለቅ ያለ ምርምር አድርጓል፤እርሱ ራሱም ቢሆን ሕግ ያጠና ሲሆን ለተወሰነ ግዜ በሀገረ ፈረንሳይ በዳኝነት ሰርቷል። ወደ ፈረንሳይ ያደረገውን የጥናት ጉዞ በገንዘብ የደገፈው የፈረንሳይ መንግስት ነበር። በፈረንሳይ አብዮት ውስጥ ጉልህ ሚና እንደነበረው ሰው ከአብዮቱ ማለፍ በኋላ አብዮቱን እና ያመጣውን ጣጣ በመመርመር እና በመተቸት የራሱን አመለካከት በተለያዩ ጽሑፎች አብራርቷል።

ለቶክቪል የዴሞክራሲ ዋነኛ ባህሪ በተለይም በአሜሪካ እኩልነት “Equality of Conditions” እንደሆነ ያስረዳል። መሳፍንታዊ እና ባላባታዊ የስልጣን ተዋረድ ሙሉ በሙሉ በመፍረሱ ከፍተኛ የሆነ ”ግለሰባዊነት” እየተንሰራፋ መሄዱን ተችቷል። ዴሞክራሲ ግለሰባዊነትን የሚፈጥር እና የሚያበረታታ ቢመስልም በተግባር እና በሂደት ግን የብዙኃኑን አምባገነንነት የሚፈጥር በመሆኑ ግለሰቡ በብዙኃን አስተሳሰብ የሚጨቆን፤ ግለሰባዊነትም እየተዋጠ እና እየጠፋ “Conformity of Opinion” እየገነነ እንደሚሄድ ይጠቅሳል።

ግለሰቡ የሚሳተፍበት ማኅበረሰባዊ ተቋም ንጉሳዊ አስተዳደር በመፍረሱ ምክንያት ስለቀረ ግለሰቦች በካፒታሊዝም ስርዓት ተነጥለው እንዲመቱ ያደርጋቸዋል። ይህንን የካፒታሊዝምን ነጥሎ የመምታት ስርዓት ለማስቀረት ዜጎች የሲቪክ ማህበራትን በማቋቋም ሰናይ ተግባራትን በመፈፀም የግለሰባዊነትን ጫና መቋቋም እንደሚገባ አስረድቷል። ግለሰቡ በሲቪክ ማህበራት በንቃት የማይሳተፍ ከሆነ ካፒታሊስቱ እና መንግስት “Soft Despotism” በመፍጠር ግለሰቡ ዘገምተኛ እና እንደ መንጋ የሚመራ ሊያደርጉት እንደሚችሉ አስጠንቅቋል።

ኤድመንድ በርክ - ፀረ አብዮተኛ

"ዘመናዊ ወግ አጥባቂነት"

ኤድመንድ በርክ (1729-1797) ከሕግ ባለሙያ አባቱ በእንግሊዝ ሀገር ሲወለድ ቤተሰቡ የሕግ ሙያን ይቀላቀላል ብለው ገምተው ነበር። ይሁንና ወደ ፖለቲካው ዓለም ተቀላቅሎ የዊግ ፓርቲ አባል በመሆን የራሱን መንገድ መርጧል። ኤድመንድ በርክ በተለምዶ ወግ አጥባቂ ከሚባለው የፖለቲካ ዘርፍ የሚመደብ ሲሆን ሃይማኖት በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆን እንዳለበት ፅፏል። ከሁሉም በላይ የፊረንሳይ አብዮት ማኅበረሰባዊ ተቋማትን በሙሉ ማፍረሱን እና በተለይም ለሃይማኖታዊ እሳቤ ያሳየውን ንቀት እና አፍራሽ ሚና ክፉኛ ተችቷል። በርክ የአብርሆት ዘመን ውጤት የሆነው የማኅበረሰባዊ ውል (Social Contract) ፍልስፍናም ቢሆን ብዙም እንደማይወጥለት ከመግለፅ አልቦዘነም።

> Society is indeed a contract. Subordinate contracts for objects of mere occasional interest may be dissolved at pleasure — but the state ought not to be considered as nothing better than a partnership agreement in a trade of pepper and coffee, calico or tobacco, or some other such low concern, to be taken up for a little temporary interest, and to be dissolved by the fancy of the parties. It is to be looked on with other reverence; because **it is not a partnership in things subservient only to the gross animal existence of a temporary and perishable nature. It is a partnership in all science; a partnership in all art; a partnership in every virtue, and in all perfection. As the ends of such a partnership cannot be obtained in many generations, it**

becomes a partnership not only between those who are living, but between those who are to be born[80].

ማኅበረሰብ በርግጥም ውል ነው። ለጥቃቅን ጥቅሞች የሚደረጉ አነስተኛ ውሎች በዘፈቀደ ሊሰረዙ ይችላሉ ነገር ግን መንግስት እንደ በርበሬ እና ቡና፣ እንደ ጨርቃጨርቅ እና ትምባሆ እና ሌሎች አነስተኛ ግብይቶች በሁለቱ አካላት ፍላጎት እንደሚፈርስ የንግድ ሽርክና ስምምነት ሊታይ አይገባውም። ይልቅስ በአክብሮት ሊታይ ይገባዋል ምክንያቱም ስምምነቱ ለጊዜያዊው እና ለጠፊው ተፈጥሮ እና ፍጥረት ብቻ ተገዢ ስላለሆነ ነው። ሽርክናው በሁሉም ሳይንስ፣ በሁሉም ሥነ-ጥበብ፣ በሁሉም ሥነ-ምግባር እንዲሁም በሁሉም ፍፅምና ያለ ነው። የእንዲህ ዓይነቱ ስምምነት መጨረሻ በብዙ ትውልዶች የማይታይ ስለሆነ ሽርክናው አሁን ባሉት ትውልዶች መሃል ብቻ ሳይሆን ገና በሚመጡት/ በሚወለዱት መካከል ይሆናል።

ማኅበረሰባዊ ውል የሚባል እና ከሕገ-አራዊት የመነጨ ምናባዊ ውል እንደሌለ እና ቢኖርም እንኳን ማኅበረሰባዊ ውል ሊኖር የሚችለው ባለፈው ትውልድ፣ አሁን ባለው እና በሚመጣው መሀከል እንደሆነ እና ካለፈው ትውልድ ጠቃሚ እሴቶችን ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የሚደረግ መሆኑን አመላክቷል። ጠንካራ እና ጠቃሚ መንግስታዊ እና ማኅበረሰባዊ ተቋማትን ቅቡልነት የምናውቀው በማኅበረሰቡ ውስጥ ምን ያህል ቆይተዋል? ለምን ያህል ግዜስ አገልግለዋል?የሚለውን ባህል እና ልማድ በመገምገም እንደሆነ እና የግለሰቦች ሰብዓዊ መብትም የሚመነጨው ከአንድ ሀገር ውስጥ ከሚገኝ የስርዓተ-መንግስት ባህል እና ልምድ እንጂ ዓለም ዓቀፍ የግለሰብ መብት ከሚባል ነገር አይደለም።

በርክ ወግ አጥባቂ በመሆኑ አብዮትን ቢቃወምም ዝግመታዊ የሆነ ለውጥን ይቀበላል። የፈረንሳይ አብዮት ለፈረንሳይ ሕዝብ ባዕድ የሆነ

80 Edmund Burke, Reflections on the Revolution in France (1790), Vol III ,P 365

ልምምድን ያመጣ በመሆኑ የሚቃወመው ቢሆንም የአሜሪካን አብዮት እና የነፃነት ትግል በፅኑ ይደግፍ ነበር። የፈረንሳይ አብዮተኞች አብዮቱን በመላው አውሮፓ የማስፋፋት አላማ የነበራቸው በመሆኑ በሀገረ እንግሊዝም ያሉ ፈላስፎችም አብዮቱን እየደገፉ ይጽፉ ነበር፤ ከኤድመንድ በርክ በስተቀር። ከፈረንሳይ አመፀኛ እና ስር ነቀል አብዮት ይልቅ በእንግሊዝ ሀገር የተካሄደው "Glorious Revolution" የተሻለ እንደሆነ ያምን ነበር።

ለበርክ ሕግጋት በልማድ በትውልድ ውስጥ በቀስታ ያድጋሉ እንጂ ደም በሚያፋስስ አብዮት ውስጥ በድንገት አይወለዱም። የፈረንሳይ አብዮት አዋጅ "Rights of Men" በሚል የፈጠራቸው መብቶች ለበርክ መሠረት የሌላቸው ነበሩ። በመሆኑም የፈረንሳይ አብዮት የተፈጥሮ ሕግጋት እና ዓለም አቀፋዊ በሚል የፈጠራቸው ሕግጋት በረጅም ዘመን የዳበረውን የሕግ እና ፖለቲካ ልማድ የሚጥሱ ናቸው። በመሠረቱ የሰው ልጆች ሕጋዊ መብት የሚፈጠረው ታሪካዊ እና ማኅበረሰባዊ በሆነ ዓውድ (context) ውስጥ እንጂ ከመሬት ተነስቶ በሚፈጠር ደም አፋሳሽ አብዮት አይደለም።

ለበርክ አብዮት በነፃነት (Liberty) እና ልማድ (Tradition) መሀከል ያለውን ስምምነት እና ተወራራሽነት የሚያፈርስ ነው። በርክ ጥብቅ ሃይማኖተኛ እንደመሆኑ የፈረንሳይ አብዮት በግዜው ያራምድ የነበረውን ፀረ-ሃይማኖት እንቅስቃሴ እጅግ ይቃወም ነበር። ሃይማኖት እና ዘውዳዊ ሕገ-መንግስታዊነት (Constitutional Monarchy) ማኅበረሰብ እንዳይፈርስ ወግ፣ ታሪክ እና ባህሉን የሚጠብቁ ተቋማት እንደመሆናቸው ሙሉ ለሙሉ መፍረስ የለባቸውም ሲል ተከራክሯል። የፈረንሳይ አብዮተኞች የፈረንሳይ ካቶሊክ ቤተ-ክርስትያንን ማፍረስ የሚፈልጉት በአብዮት ስም የቤተ-ክርስቲያኒቷን ሰፋፊ መሬቶች ለመንጠቅ እንጂ ለማኅበረሰቡ ከማሰብ አይደለም። አንድ ማኅበረሰብ ከቀደመ ማኅበረሰብ ጥበብ እውቀት የሚያገኝ በመሆኑ ለለውጥ እና መሻሻል ሲነሳ ከቀደመው ታሪክ የሚያስፈልገውን ማቆየት እንዳለበት በመከራከሩ ብዙዎች የመጀመሪያው "Modern Conservative" በማለት ይጠሩታል።

አሌክሳንደር ሃሚልተን- ፌዴራሊስቱ

"ሕገ-መንግስት ለሀገር ግንባታ"

ሃሚልተን (1757-1804) የሀገረ-አሜሪካ መሥራች አባቶች ከሚባሉት መሀከል ነው። በመንግስት አስተዳደር ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ከመያዝ ባሻገር የአሜሪካ ሕገ-መንግስት በሚረቀቅበት ወቅት ሕዝቡን በማንቃት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። በኒው ዮርክ ከተማ በሚታተም ጋዜጣ በብዕር ስም ከሁለት ባልንጀሮቹ ጋር በመሆን ብዙ ጦማሮችን አሳትሟል። እነዚህ ጦማሮች "Federalist Papers" በመባል የሚታወቁ ናቸው። ጦማሮቹ ተሰባስበው የታተሙ ሲሆን፤ አብዛኛውን ጦማሮች የጻፈው ሃሚልተን ስለመሆኑ ከዓመታት በኋላ ሊታወቅ ችሏል። እነዚህ ጦማሮች ሕገ-መንግስቱ እየተዋወቀ ባለበት ወቅት ሰፊው ሕዝብ ስለ ሕገ-መንግስቱ አስፈላጊነት እንዲገነዘብ በሚል ቀለል ባለ ቋንቋ ስለ ዴሞክራሲ እና የመንግስት አስተዳደር የተቀመሩ አስተማሪ ጽሑፎች ናቸው።

> No Legislative act, therefore, contrary to the Constitution, can be valid. To deny this, would be to affirm, that the deputy is greater than his principal; that the servant is above his master; that the Representatives of the People are superior to the People themselves; that men acting by virtue of powers, may do not only what their powers do not authorize, but what they forbid. If it be said that the Legislative body are themselves the constitutional judges of their own powers, and that the construction they put upon them is conclusive upon the other departments, it may be answered, that this cannot be the natural presumption, where it is not to be collected from any particular provisions in the Constitution[81].

81 Alexander Hamilton, "Publius",The Federalist Paper 78 , New York Post, 1788

ሃሚልተን የሕግ ባለሙያ፤ወታደር እና የማዕከላዊ ባንክ ገንቢ ነበር። ሃሚልተን በተለምዶ “Federalist” ከሚባሉ ወገኖች የሚመደብ ሲሆን ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስትን ይደግፍ ነበር። በኒው ዮርክ ግዛት በሕግ ባለሙያነት እየሰራ ሳለ ግዛቱን ወክሎ የሕገ-መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ውስጥ ሊቀላቀል ችሏል። በሕገ-መንግስት ጉባኤ ውስጥ ኮንፌደራሊስቶችን በመቃወም ጠንካራ ፌደራል መንግስት እንዲቋቋም አድርጓል። የፌደራሊስት ጦማሮች በሃሚልተን፣ በጀምስ ማዲሰን እና ጆን ጄይ የተፃፉ ቢሆንም፤ከ85 ጦማሮች ሃሚልተን 51 ፣ ማዲሰን 29፣ ጆን ጄይ ደግሞ 5 ጦማሮችን ፅፈዋል። በወቅቱ ለመርቀቅ ተዘጋጅቶ የነበረውን ሕገ-መንግስት የሚቃወሙ “Anti-Federalist” የሚባሉ ጦማሮች የሚታተሙ በመሆኑ እነዚህን ለመመከት ሃሚልተን ታጥቆ በመነሳቱ እነዚህን ጦማሮች ልናገኝ ችለናል።

> Courts were designed to be an intermediate body between the People and the Legislature, in order, among other things, to keep the latter within the limits assigned to their authority. The interpretation of the laws is the proper and peculiar province of the Courts. A Constitution is, in fact, and must be regarded by the Judges, as a fundamental law. It therefore belongs to them to ascertain its meaning, as well as the meaning of any particular Act proceeding from the Legislative body. If there should happen to be an irreconcilable variance between the two, that which has the superior obligation and validity ought, of course, to be preferred; or in other words, the Constitution ought to be preferred to the statute, the intention of the People to the intention of their agents[82]

82 Ibid

ለሃሚልተን ፍርድ ቤቶች የተሰሩት በሕዝቡ እና በሕግ አውጪው መካከል ድልድይ እንዲሆኑ እና ሕግ አውጪውን በተበጀለት የስልጣን ገደብ ውስጥ እንዲሠራ ለማድረግ ነው። የሕግ ትርጓሜ ለፍርድ ቤቶች ልዩ እና ልክ የሆነ ክልል ነው። ሕገ-መንግስቱ በዳኞች ዘንድ እንደ መሠረታዊ ሕግ መታየት ይገባዋል ስለዚህም ሕገ-መንግስቱን እንዲሁም ከሕግ አውጪው የሚመጡ አዋጆችን ትርጉም ይሰጣሉ። በሁለቱ መካከል የማይታረቅ ልዩነት ቢኖር የበላይ ወይም ሕጋዊ የሆነው ሊመረጥ ይገባል፤ ይኸውም ሕገ-መንግስቱ ከአዋጆቹ በላይ፣ የሕዝቡ ፍቃድ ከ ወኪሎቻቸው በላይ ቀዳሚነት ሊሰጠው ይገባል። ከሕገ-መንግስቱ በተቃርኖ የቆመ ማንኛውም ሕግ የማርቀቅ ሂደት ተቀባይነት አይኖረውም። ይህንን መካድ ማለት ምክትሉ ከአለቃው፣ ባሪያው ከጌታው፣ የሕዝብ ተወካይም ከሰፊው ሕዝብ ይበልጣል እንደማለት ነው። ስልጣኑ ስላላቸው ብቻ የሚሰሩ ሰዎች ስልጣናቸው ከፈቀደው ገደብ ውጪ ብቻ ሳይሆን ስልጣናቸው የሚከለክለውን ጭምር ያደርጋሉ። የሕግ አውጪው አካላት የራሳቸው ስልጣን ሕገ-መንግስታዊ ዳኞች ናቸው ካልን፤ራሳቸው ላይ የሚያስቀምጡት ገደብ ሌሎቹንም አካላት የሚያጠቃልል ነው።

የሃሚልተን ዘመን ሃገረ አሜሪካ የተቋቋመችበት ዘመን ነበር። የመጀመሪያው ፕሬዝደንት ጆርጅ ዋሽንግተን የራሱን ካቢኔት መስርቶ ደፋ ቀና እያለ የነበረ ቢሆንም በካቢኔው ውስጥ ግን አደገኛ ክፍፍል እየተጠነሰሰ ነበር። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እና የጦር ሚኒስትር የሆኑት አሌክሳንደር ሃሚልተን እና ቶማስ ጀፈርሰን በመሃከላቸው እያገነገነ ያለው የሐሳብ ልዩነት ተፋፍሞ ሁለት ጎራዎች ተመሰረቱ። ይህንን ልዩነቶች ለማስታረቅ ዋሽንግተን ቢመክር ቢዘክር ሊሳካ አልቻለም። በሃሚልተን የሚመራው ጎራ ፌዴራሊስት ተብለው የሚጠሩ ሲሆን ጠንካራ ማዕከላዊ ባንክ እንዲኖር፤ ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ፤ የውጭ ንግድ እንዲያድግ፤ በአውሮፓ ደግሞ የእንግሊዝ አጋር እንዲሆኑ ጥረት ይደረግ ሲል በጀፈርሰን የሚመራው የሪፐብሊካን ቡድን በበኩሉ ጠንካራ ክልሎች እንጂ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት አያስፈልግም፤ ከኢንዱስትሪ ይልቅ ለግብርና ትኩረት ይሰጥ፤ በአውሮፓም አጋራችን እንግሊዝ ሳትሆን ፈረንሳይ መሆን አለባት ብሎ ይከራከር ነበር። የፌዴራሊስት ቡድን ውስጥ እነ ሃሚልተን እና ጆን

አዳምስ ሲገኙ በሪፐብሊካኑ ቡድን ውስጥ ደግሞ እነጄፈርስን እና ማዲሰን ይገኛሉ ፤ ሁሉም ከባድ ሚዛን ስለሆኑ ተፋጠዋል።

እንግዲህ የ1800 ዓ.ም ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ የመጣው በዚህ ውጥረት ውስጥ ነው። በድሮው አሜሪካ ፕሬዝዳንት እንዲህ እንደ አሁኑ በትግል እና ሕዝብ በማማለል ሳይሆን A man is not elected for presidency but stands for presidency ዓይነት አሠራር ነበራቸው የተማሩ እና የተከበሩ የሕዝብ እንደራሴዎች ከመሃከላቸው የተሻለውን ይመርጣሉ። በወቅቱ ለፉክክር የቀረቡት በስልጣን ላይ የነበረው ጆን አዳምስ እና ቶማስ ጄፍርሰን ሲሆኑ፤ ጄፈርሰን ምርጫውን እንደሚያሸንፍ አንዳች ጥርጣሬ አልገባበትም። ፌዴራሊስቶቹ በውስጣቸው በተለይ በሃሚልተን እና በጆን አዳምስ መሀከል በነበረው ሹክቻ ድምፃቸው ተከፋፈሎ ስለነበር የእነ ጄፈርሰን ቡድን በቀላሉ ነበር ያሸነፋቸው። ይሁንና አዳምስ ስልጣን ከመልቀቁ በፊት የቡዱኑን ዘላቂ ጥቅም ለማስጠበቅ ሲል የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ለማስረግ ባለቀ ሰዓት የእርሱን ወገን ፌዴራሊስት ዳኞች ሾሟል፤ እስከዛሬም የሚድ ናይት ዳኞች ይባላሉ-። ይሁን እንጂ ዳኞቹ ቢሾሙም “ኮሚሽን” የሚባል የሹመት ደብዳቤ አልደረሳቸውም፤ በተለምዶ ይህን ወረቀት የሚያደርሰው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሲሆን የአዳምስ ሴክሬተሪ ኦፍ ስቴት ጆን ማርሻል ምን ልቡን እንደሰረቀው አይታወቅም ወረቀቱን ሳያደርስ ይቀራል።

ጄፈርሰን አሸንፎ ከራሱ ሴክሬተሪ ኦፍ ስቴት ማዲሰን ጋር ሥራ ይጀምራሉ፤ ይሁን እንጂ የማዲሰን ቢሮ ጠረጴዛ ላይ ማርሻል ያላደረሳቸው የሹመት ደብዳቤዎች ወይም ኮሚሽኖች ቁጭ ብለው ያገኛል፤ ማዲሰን በሁኔታው ግር ተሰኝቶ ለአለቃው ፕሬዝዳንት ጄፈርሰን ወስዶ ያሳያዋል። የቀድሞ ሴክሬተሪ ኦፍ ስቴት የነበረው ማርሻል በመጨረሻ ሰዓት የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ ዳኛ ተደርጎ በጆን አዳምስ ተሹሟል፤ ጄፈርሰን የሹመት ደብዳቤዎቹን አይቶ ሸር መሆኑ ገብቶታል፤ የማንም የፊዴራሊስት አንጃ አቀንቃኝ ዳኛ በእኔ ዘመን ፍርድ ቤቱን አይሞላም ብሎ ደብዳቤዎቹን ያስቀራቸዋል። ዳኞቹ ቢጠብቁ የሹመት ደብዳቤው አይመጣም፤ ጎመን በጤና ብለው ብዙዎቹ ቢያልፉትም አንደኛው ማርበሪ የተባለ ዳኛ ነገሩ

አልዋጥለት ይለውና የሹመት ደብዳቤውን በሕግ እንዲያደርስ የሚገደደውን ሴክሬተሪ ማዲሰንን ፍርድ ቤት ይከሰዋል። ጉዳዩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይደርሳል ፤ የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰብሳቢ የሆነው ማርሻል በቀድሞ ስርዓት ደብዳቤዎቹን ማድረስ የነበረበት ግለሰብ እንደነበር አይዘነጋም።

የተከበሩ ዳኛ ጆን ማርሻል አጣብቂኝ ውስጥ ይወድቃሉ። ለማርበሪ ቢወስን ቀድሞም የፌዴራሊስቶች ወገን ስለነበር አደላ ሊባል ነው ፤ ለማዲሰን ቢወስን ራሱ ማድረስ የሚገባውን ደብዳቤ ባለማደረሱ የደረሰውን በደል ማባባስ ነው። ማርሻል ዳኞቹን አስተባብሮ ከጥቂት ዓመታት በፊት ኮንግረስ ያወጣው እና ፍርድ ቤቱ ሴክሬተሪ ኦፍ ስቴቱ ኮሚሽኖቹን እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል በሚል የወጣው የ writ of mandamus ሕግ ኢሕገ-መንግስታዊ በመሆኑ ሕጉ ራሱ ሊሰረዝ ይገባል የሚል ውሳኔ ፍርድ ቤቱ እንዲሰጥ ያስደርጋል።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይህ ሕግጋትን ኢ ሕገ-መንግስታዊ ናቸው እያሉ በፍርድ ቤት ውድቅ ማድረግ Judicial Review - ፍርድ ምርመራ የሚባል ስም ተሰጥቶት እስካሁን እየተሰራበት ይገኛል። አንዳንዶች ሲከራከሩ ግን "Judicial Review ታሪኩ ሲጠና ቶማስ ጀፈርሰን እና ጆን አዳምስ የፌዴራሊስት እና የሪፐብሊካን ቡድኖችን ደግፈው ያደረጉት የ ፖለቲካዊ ሽፍጥ ትግል ውጤት (Madison Vs Marbury[83]) እንጂ በሕገመንግስቱ የተቀመጠ አሠራርም አይደለም። ይሁን ቢባል እንኳ ፍርድ ቤቱ በታሪካዊ አጋጣሚ ያገኘውን ኢ ሕገ-መንግስታዊ ስልጣን ሰው ይታዘበኛል ሳይል በዘፈቀደ ሊጠቀምበት አይገባም። በመሠረቱ Judicial Review ማለት ፍርድቤቱ የኮንግረስ ሕግጋት እና የአስፈፃሚው ተግባራት ሕገመንግስቱን ሲቃረኑ እነዚህን ውድቅ የሚያደርግበት አሠራር እንጂ የሕገመንግስቱን አርቃቂዎች መንፈስ አወቃለሁ በሚል ሰበብ የፓርላማ ሕግጋትን እንደፈለገ የሚጨፈልቅበት አሠራር አይደለም" ይላሉ።

ታሪክ በእንዲህ ዓይነት እጥፋቶች የተሞላ ነው። ሀገርን የሚፈጥሩት

83 Marbury v. Madison, U.S. Supreme court 137 (1803)

ያልታሰቡ እና ድንገቴ ጉዳዮች እንደ ቅርስ መታሰቢያ ሆነው ሊቀሩ ይችላሉ። ያልተገመቱ መሪዎች እና ያልተጠበቁ ጦርነቶች ስንቱን አንስተዋል፤ ስንቱን ጥለዋል። እኛም በእንዲህ ዓይነቱ የታሪክ እጥፋት ላይ እንገኛለን። ይህ የፊደራሽን ምክር ቤት በኮሮና ነክ ሕገ-መንግስታዊ ቀውስ Corostitutional crisis ላይ የሚሰጠው አብስትራክት ትርጉም ወደድንም ጠላንም እንደ አሜሪካኖቹ የፍርድ ምርመራ ስርዓት በአጋጣሚ የተፈጠረ ግን ለሀገሪቱ አዲስ ምዕራፍ የሚከፍት እንደመሆኑ በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባል።

ማርክሲስት የሕግ ፍልስፍና

"ሕግ የጭቆና መሣሪያ ነው"

ማርክሲስም በመባል የሚታወቀው የኅበረተሰባዊነት የኢኮኖሚና የፖለቲካ ፍልስፍና በጀርመናዊው ፈላስፋ ካርል ማርክስ (1818-1883) የተፈጠረ አስተሳሰብ ሲሆን ዓለምን ከስር መሠረቱ የነቀነቀ ሐሳብ ነው። ካርል ማርክስ ጀርመን ውስጥ ሃይማኖተኛ ከሆነ ቤተሰብ የተወለደ ሲሆን ከልብ ወዳጁ ፍሬድሪክ ኤንግልስ (1820-1895) ጋር በመሆን አዲስ ፍልስፍና መሥርተዋል። ለካርል ማርክስ የሰው ልጆች ታሪክ የመደብ ትግል ታሪክ ነው። በመሆኑም በሰው ልጆች መሀከል እውነተኛ ፍትሕ ለማምጣት መደብ አልባ ማኅበረሰብ መፍጠርን እንደ ግብ አይተን ጭቁን የኅበረተሰብ አካላትን ማንቃት እንደሚገባ ያስባል። የሰው ልጅ በዝግመተ ለውጥ ከቅድመ ሰው ዝርያነት ተላቅቆ ጋርዮሻዊ ማኅበረሰብን ከፈጠረበት ጊዜ አንስቶ ፊውዳላዊ እና ካፒታሊስታዊ ማኅበረሰቦች እስከ ተፈጠሩበት ዘመን ድረስ አንዱ ስርዓተ ማኅበረሰብ በራሱ ጉያ ውስጥ የራሱን ተቃርኗዊ ስርዓት አቅፎ ካሳደገ በኋላ በዚያው ባሳደገው ፍልስፍናዊ ስርዓት ተደፍጥጦ እና ተውጦ ያልፋል። ይህ የዲያሌክቲክስ ፍልስፍና ሲባል የሰው ልጆችን ታሪክ እና አጠቃላይ ቁስአካላዊነት የምንረዳበት መንገድ ነው።

በዚህ ሂደት አማካይነት የሰው ልጆች የደረሱበት የመጨረሻው ስርዓተ ማኅበር ኢምፔሪያሊስታዊ ሲሆን ይህ ስርዓት የሰው ልጆችን

በተለይም የሠራተኛውን መደብ እጅግ የሚጨቁን እና የሚበዘብዝ ስርዓት በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ ሊፈርስ እና የማምረቻ መሣሪያዎች እና የምርት ፈጠራ ሂደቶች በሙሉ በማኅበረሰቡ አባላት እኩል ሊከፋፈል ይገባዋል። ምክንያቱም በዚህ ማኅበረሰብ የካፒታሊስት ስርዓቱ እጅግ ከመግነኑ የተነሳ ኢምፔሪያሊስት የሆነ የጨቋኝ መደብ ይፈጥራል። እነዚህ ጥቂት ካፒታሊስት ኤምፔያሪያሊስቶች የሰው ልጆችን ሀብት እና ገንዘብ በመሉ ለራሳቸው ተቆጣጥረው ሲያበቁ በየፋብሪካው ዕለት ተዕለት ሕይወቱን ለማሸነፍ ለሚሠራው የሠራተኛ መደብ አነስተኛ ክፍያ እና ትከሻ ሰባሪ ሥራ እየሠጡ ይበዘብዙታል። በመሆኑም የሠራተኛው መደብ በቁጥር ብዙ እና እጅግ የበረታ ኃይል ያለው እንደመሆኑ በቁጥር ትንሽ የሆኑትን እና ትንሽ ኃይል ያላቸውን ካፒታሊስቶች ፈንቅሎ በመጣል የምርት ሂደቱን እና አንጡራ ሃብቱን ሊቆጣጠር ይገባል። በዚያን ጊዜ እውነተኛ ኅበረተሰባዊነት የሚፈጠር ሲሆን ሰዎች የሚበዘበዙበትን ሥራ ሳይሆን ትርጉም እና እርካታ የሚያገኙበትን ሥራ ይሠራሉ፤ ያኔ ከሁሉም እንደየአቅሙ ለሁሉም እንደየፍላጎቱ ስለሚደርስ የሀብት ክፍፍልን አስመልክቶ የሚነሳ ፀብ አይኖርም። አጠቃላይ የማርክሲስም ፍልስፍና ሐሳብ እጅግ ባጠረ መልኩ ሲቀርብ ከላይ የተዘረዘረውን ይመስላል።

> When Marx says that, "The ideas of the ruling class are in every epoch the ruling ideas" (*The German Ideology*) and that, "Law, morality, religion are to [the proletariat] so many bourgeois prejudices, behind which lurk in ambush just as many bourgeois interests" (*The Communist Manifesto*), he is simply translating in to Marxian terms the Sophistic view "that the more powerful will always take advantage of the weaker, and will give the name of law and justice to whatever they lay down in their own interests." (W.K.C. Guthrie, *The Sophists* (1971), p. 60)[84]

84 Brian Leiter, Hermeneutics of Suspicion: Recovering Marx, Nietzsche, and Freud" ed. Leiter (Oxford: Clarendon Press, 2004), pp. 74-105

በመጨረሻም እውነተኛ ኮሚዮኒስታዊ ስርዓት ሲገነባ ሕግ ወይም መንግስት የሚባል ነገር አያስፈልግም። በካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ ያለ የሕግ ስርዓት በሙሉ የባለሃብቱን መብት እና ጥቅም የሚያስጠብቅ በመሆኑ ሕግ ራሱ የመበዝበዣ መሣሪያ ነው። በኮሚዩኒስታዊ ስርዓት ግን ሕብረተሰቡ በራሱ የምርት ሂደቱን እና ሃብቱን ተቆጣጥሮ ፍትሐዊ ክፍፍል ስለሚያሰፍን በሕግ መገዛት አይኖርበትም። በመሆኑም በማርክሲት ስርዓት ሕግ የራሱን መቃብር እንደሚቆፍር ባለፍርድ ከአገልግሎት ውጪ እስከሚሆን ድረስ ራሱን የጭቆና መሣሪያ ከመሆን እየቆጠበ እስከሚጠፋበት ጊዜ ድረስ መጠበቅ ይኖርበታል።

በየትኛውም ዘመን ገዢ የሆነው ሐሳብ ገዢ ከሆነው መደብ የሚመነጭ ነው። በመሆኑም ለካርል ማርክስ ሕግ የምንለውን ጉዳይ ከፖለቲካዊ ርዕዮት ለይቶ ማየት የማይቻል ነገር ነው። በካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ ሕግ የፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለሙ ነጸብራቅ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የገዢው እና ጨቋኙ ቡርዣዋ እና ካፒታሊስት መደብ መገልገያ መሣሪያ ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ሕግ በመደቦች መሀከል ያለውን ኢ-ፍትሐዊ የምርት ግንኙነት እና የሀብት ክፍፍል ለማፅናት የሚያገለግል ነው። በመሆኑም ሕግ ይህንን ሚናውን በመቀየር የካፒታሊስት ስርዓቱን ከማገልገል ተላቅቆ የሠራተኛ መደብ አምባገነንነት እንዲመጣ ጉልህ የሆነ ሚና መጫወት ይኖርበታል።

ምዕራፍ ዘጠኝ

ሕግ፤ ሳይንስና ቴክኖሎጂ

“ሕግ እና ቴክኖሎጂ የመጨረሻው መጀመሪያ”

በማደግ ላይ ባሉ ሃገራት እና ባደጉት ሃገራትም ጭምር የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ እድገት ፍጥነት ብዙ ማኅበረሰባዊ አወቃቀሮችን እየቀየረ እና አዳዲስ ተግዳሮቶችን እና መልካም አጋጣሚዎችን እየፈጠረ ይገኛል። በዓለማችን ላይ በፍጥነት እያደጉ ያሉት እንደ Artificial Intelligence፤ Cryptocurrencey፤ Social media እና የመሳሰሉት የቴክኖሎጂ ዕድገቶች የሠው ልጆች ሕይወትና የመንግስት አወቃቀር በእውኑ ዓለም ብቻ ሳይሆን በ Virtual world ውስጥም እየጠለቀ መሄዱንና ለወደፊቱም ይኸው የሚቀጥል መሆኑን የሚያሳይ ነው። በአሁን ወቅት አብዛኛው የሠው ልጆች የግል፤ የተቋም፤ የንግድ፤ የመንግሥት እና መሰል ግንኙነቶች እና ውሎች (transaction) የሚካሄዱት በኢንተርኔት አማካኝነት በተዘረጋው የግንኙነት መስመር ነው።

ቴክኖ-ሰዋዊነት እኛ እንደምንረዳው ሁሉ ሆሞ ሳፒያንስ ታሪካዊ ሩጫውን እንደጨረሰና በመጪው ዘመን የሚኖረው አስፈላጊነትም እንደሚያከትም ያምናል። ስለዚህ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ከሰው ልጅ እጅግ የላቀ ንድፍን ወይም ሆሞዲየስን መፍጠር አለብን የሚል ድምዳሜ አለው። ሆሞዲየስ የተወሰኑ መሠረታዊየሚባሉ

የሰው ልጅ ባህሪያትን ይዞ ቢቀጥልም እጅግ ከተወሳሰቡ ኢ-ነቃኤ-ልቦናዊ ስልተ ቀመሮች ሳይቀር ራሱን የሚከላከልበት የተሻሻለ አካላዊና አእምሯዊ ዐቅም ይኖረዋል። እውቀት ከነቃኤ ልቦና ጋር ፍቺ እየፈጸመ ስለሚገኝ እንዲሁም ኢ-ነቃኤ-ልቦናዊ እውቀት በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ስለሚገኝ ሰዎች ከጫወታው ውጪ ላለመሆን አእምሯቸውን ሊያሻሽሉ ግድ ይላቸዋል[85]።

ሃራሪ እንደሚነግረን የሰው ልጅ ሕይወት ብቻ ሳይሆን መሠረታዊ ውቅር እና ማንነት ራሱ በቴክኖሎጂ እድገት ሳቢያ የሚቀየር ከመሆኑ የተነሳ ከአንድ ዝርያ ወደ ሌላ ዝርያ መቀየሩ አይቀሬ ነው። ሕግ ደግሞ ከአፈጣጠሩም ቢሆን የሰዎችን ውል እና ግንኙነት ለመቆጣጠር፤ ለመምራት እና ለመገደብ የተፈጠረ ሰው ሠራሽ ግኝት ነው። በመሆኑም የሰው ልጆች ግንኙነት ከገሃዱ ዓለም ይልቅ ወደ ቨርቹአል ዓለም የጠለቀ እና ያጋደለ ከሆነ የሕግ አላማና ትኩረትም ወደዚሁ ዓለም ያነጣጠረ መሆን ይኖርበታል። ይሁን እንጂ እያደጉ ባሉ ዓለማት የቴክኖሎጂ መስፋፋት እጅግ አነስተኛ ከመሆኑም ባሻገር ይኸው የቴክኖሎጂ መስፋፋት በጣም ኃላቀር በሆኑ የመንግሥት እና የዲሞክራሲ ተቋማት፤ ደካማ ኢኮኖሚ፤ ብዙ ያልተማረ የሠው ኃይል እና ከፍተኛ ሥራ አጥነት በተንሠራፋበት ሁኔታ ላይ መደረቡ አስጊ ነው።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የቴክኖሎጂ እድገት ተግዳሮቶች ለአፍሪካ ሀገራት የማይረዱትን ጥያቄ የመመለስን ያህል የተወሳሰበ ነው። በመሆኑም ሕግጋቱ ይህንን የእድገት መንቀራፈፍ ከግምት በማስገባት ገንቢ እና ጠቃሚ አሰራሮችን መቀየስ ይኖርባቸዋል፤ ጠቃሚ ስንል ሕግ የሀገሪቱን ልማት መደገፍ አለበት እያልን ነው።

85 ኖህ ሀራሪ፤ ሆሞዴየስ-የመጪው ዘመን አጭር ታሪክ፤ ተርጓሚ ዳግም ጥላሁን፤ ሐምሌ 2012፤ ገጽ 332

ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሕግ እና ልማት መሀከል ያለውን ግንኙነት የሚያጠና ቤተ-አስተምህሮ እ.ኤ.አ በ1960 በሀገረ አሜሪካ ተመሥርቶ የነበረ ሲሆን ይህ አስተምህሮ በፎርድ ፋውንዴሽን እየተደገፈ ሕግ እያደጉ ባሉ ሃገራት ውስጥ ኢኮኖሚያዊ እድገትን በሚያመጣ መልኩ መቀረፅ እንዳለበት ያስተምር የነበረ ቢሆንም ብዙም ድጋፍ ሳያገኝ ሊቀዛቀዝ ችሏል። ከዚያ በመቀጠል ለሁለተኛ ጊዜ በ1980ቹ የኒዩ ሊብራል አስተሳሰብ ወደ አፍሪካ ሃገራት በሚሠረፅበት ወቅት በድጋሚ ይህ አስተምህሮ ተነሳስቶ በአደጉ ሃገራት መቀጣጠል ጀምሯል።

የሕግና ልማት ፅንሰ ሐሳብ በጥቅሉ ሕግጋት በአንድ ሀገር የሚመጣውን ኢኮኖሚያዊ እድገት ሊያደናቅፉ አይገባም የሚል ነው፤ የአፍሪካ ሃገራት ካሉበት የድህነት አረንቋ ለማውጣት ሰፊ እና ትላልቅ የልማት እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ይኖርባቸዋል። እነዚህ እንቅስቃሴዎች በሕግ እና ሕግ-ነክ የቢሮክራሲ ማነቆዎች መደናቀፍ የለባቸውም ይልና እንዲያውም ሕግ ይህንን የልማት ሂደት የሚያግዝ መሣሪያ መሆን እንዳለበት ያሳስባል። በአሁን ወቅት የሕግና ልማት ጥናቶች በአሜሪካና በአውሮፓ ባሉ ከፍተኛ ትምህርተ ተቋማት ውስጥ በሰፊው ይገኛሉ።

በቴክኖሎጂው እድገት ሳቢያ ባደጉት ሃገራት የወንጀል ሕግ አዲስ ዘርፎችን እያካተተ ይገኛል። እንደ Cyberbullying (የኢንተርኔት ማንጓጠጥ)፤ Hate speech (የጥላቻ ንግግር) ፤ Fake news (ሐሰተኛ ዜና) ፤ Hacking (የሚስጥር ቃል ሰበራ) የመሳሰሉት ጉዳቶች የአሜሪካ የፍትሕ ስርዓትን እየተፈታተኑ ይገኛሉ፤ ይሁንና በኢንተርኔት ላይ የሚደረግ የሕግ ቁጥጥር በገሃዱ ዓለም እንዳለው የሕግ ቁጥጥር ቀላል እና ምቹ ሊሆን አይቻልም።

ሰው ሰራሽ አስተውሎ (Artificial Intelligence)

ይህ ዘርፍ በተለምዶ የሮቦቲክስ ሳይንስ ከሚባለው በእጅጉ የተለየ እና የረቀቀ ነው። ማሺኖች እና ሮቦቶች የሰውን ልጅ ባህሪ እና ስሜት መረዳት የሚችሉ ፍጡሮች (Sentient beings) ሆነው እንዲፈጠሩ በሂደትም እውቀት እና ስሜትን እንደ ሰው እየተረዱ እንዲሄዱ መደረጉ አስፈላጊ እና አይቀሬ እየሆነ መጥቷል። በመሆኑም እነዚህ ፍጥረታት ወይም ማሺኖች ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ሰውኛነት እየቀረቡ እና እየመሰሉ መሄዳቸው እጅጉን አሳሳቢ እየሆነ ነው።

በመሆኑም ሰዎች በተለምዶ የሚሠሯቸውን ሥራዎች እየተኩ መሄዳቸው የማይቀር ነው። ይህ ደግሞ ሰዎች በገፍ ከሥራ ገበታቸው የሚያፈናቅል በመሆኑ እነዚህ ከሥራ የተፈናቀሉ ግለሰቦች ለወንጀል ፤ ለዕፅ እና ለተለያዩ ወንጀል ጠቀስ ሁነቶች መጋለጣቸው የማይቀር ነው። በመሆኑም እንዚህ ማሺኖች ራሳቸው የሚያስተምሩ አድርጎ መሥራት እና ማበልጸግ (Machine learning or deep learning) በረጅም ርቀት ከሰው ልጆች ጥቅም አንጻር የሚፈይደው ነገር ሊኖር መቻሉ ሊጠና እና ሊመረመር ይገባል።

በመጪው ዘመን ከዘመናዊው ዓለም ተነጥለን ለመኖር ካልወሰንን በቀር አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በከፍተኛ ሁኔታ ሕይወታችን ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀርም። አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የሰው ልጆችን ሕይወት የማቅለል ሰናይ ዓላማ አንግቦ ቢነሳም አንዳንድ የጎንዮሽ ጉዳቶች እና መላ ያላገኘንላቸው ሕጋዊ እና ሞራላዊ ጥያቄዎች ማስነሳቱ አልቀረም። የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ደጋፊዎች የሥራ ቦታን ቅልጥፍና በማሻሻል ሠራተኞችን ከአደገኛ እና ድግግሞሽ ከበዛው ሥራ በማትረፍ የሥራ እርካታን እንዲሁም ውስጣዊ ተስጥዖአቸውን አንዲሹ እድል ይከፍትላቸዋል በማለት ይከራከራሉ። ነገር ግን በቅርብ ጊዜያት በሰው ልጆች ብቻ ይከወናል ብለን የምናስበው የሥነ-ጥበብ ዘርፍ ውስጥ እራሱ በመግባት ይገኛል። ለምሳሌ

ሬምብራንት (Remberandt) የተባለውን የ17ኛው ክፍለ ዘመን እውቅ የደች ሰዓሊን 346ሥራዎች በመተንተን እና በመመርመር አንድ ሶፍትዌር “ቀጣዩ ሬምብረንት” የሚል ስዕል ከሰዓሊው ጎልፈት 351 ዓመታት በኋላ ይፋ ማድረግ ችሏል። ስዕሉ የሬምብራንትን የአሳሳል ዘይቤ እንዲመስል ተደርጓል፤በመቀጠልም በ3ደ ፕሪንተር በማተም የብሩሽ አጣጣሉን ጭምር መቅዳት ተችሏል። በተመሳሳይም ሁዋዊ (Huawei) የኦስትሪያዊው ሙዚቃ አቀናባሪ የፍራንዝ ሹቤርትን ሲምፎኒ ቁጥር 8 የተባለውን ያላለቀ ሥራ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንሱ ስሌት ሊያጠናቅቀው ችሏል።

አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠር ጥበብ እና ሥነ-ጥበብ ለማጎበረሰብ እድገት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው እሙን ነው። እነዚህ ሙከራዎች የሚደነቁ ቢሆኑም በሰው ልጆች የመፍጠር አቅም ላይ ሊያሳድሩት የሚችሉት ተፅዕኖ በጥንቃቄ ሊታይ ይገባል። የእነዚህ ሥራዎች ባለቤት ሁዋዊ/ማይክሮሶፍት ናቸው ወይስ ኤይ ስሌት መሣሪያው ወይስ ሬምብረንት እና ሹበርት/ ስለ ቅጂ መብት ፣ ፈጠራ ባለቤትነት እና ስለ አእምሮ ውጤት ስርቆት ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም።

ራስ ነድ መኪኖች አካባቢያቸውን በመረዳት በትንሽ ወይም ያለ ምንም ሰው እርዳታ የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ይህም ቴክኖሎጂ የመኪና አደጋ በእጅጉ የሚቀንስ እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች እና በእድሜ ለገፉ ሰዎች መልካም አማራጭ እንደሚሆን ይገመታል። ነገር ግን የአሽከርካሪዎችን ሥራ ከመስረቅ እና የግል መረጃን አሳልፎ ከመስጠት ባለፈ አንዳንድ የሞራል ጥያቄዎች እየተነሱበት ይገኛል። ይህም ተሳፋሪ ወይም እግረኛ እና ሌሎች ተሽከርካሪዎችን አደጋ ውስጥ ሊከት የሚችል ሁኔታ ሲገጥም መኪናው ምን ዓይነት ውሳኔ ማሳለፍ እንዳለበት የሚጠይቅ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን “የፉርጎው አጣብቂኝ” ነው፤አንድ በከፍተኛ ፍጥነት የሚሄድ ብልሹ ባቡር ሹፌር በትክክለኛው ሃዲድ ላይ በመንዝ የአምስት ሰዎችን ህይወት ይቅጠፍ ወይስ ወደሌላ ሃዲድ በመታጠፍ የአንድ ሰው ሕይወት ያሳጣ/ ይህ እንግዲህ በጠቀሜታዊነት እና ግዴታዊነት መሀከል

ያለ አጣብቂኝ ነው። አንድ ራስ-ነድ መኪና አንድ እግረኛ መንገዱ ውስጥ ቢገባበት እግረኛውን ለማዳን ወደ ሌላ መንገድ በመታጠፍ የተሳፋሪዎቹን ደህንነት አደጋ ውስጥ መጣል አለበት? እንደዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች በብዛት የማያጋጥሙ እና ሐሳባዊ ቢመስሉም ሌሎች በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ምግባራዊ ውሳኔን የሚሹ ሁነቶች መግጠማቸው አይቀሬ ነው።

አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ በፍርድ ቤቶችም ቦታ እያገኘ ነው። ለሕግ ምርምር ሥራ፣ ውሳኔዎችን ለመተንበይ እንዲሁም የባለጉዳዮችን ማህደር ለማስተዳደር እና የፍርድ ቤቶችን አፈፃፀም ለመገምገም ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል። አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ የዳኞችን ግላዊ ስሜት እና ድካም የመሰሉ ውጫዊ ጫና እና አድሎዎችን በመቀነስ የፍርድ ስርዓቱን የበለጠ ፍትሐዊ ያደርገዋል። ነገር ግን በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የታገዘ ውሳኔ አሰጣጥ በራሱ ከአድሎ የፀዳ አይደለም። ምክንያቱም እነዚህ ማሽኖች የሚበለፅጉት ተቋማዊ አድሎ ሊኖርባቸው የሚችሉ ሕግጋትን እንደ መረጃ በመመገብ ነው። አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ አንድን ዳኛ ለመተካት ጊዜው ገና ነው። ሥራው የሚጠይቀው አእምሯዊ ብቃት ከፍተኛ ሆኖ ሳይሆን አንድ ጥሩ ዳኛ የምርምር፣ የቋንቋ፣ የአመክንዮ፣ የማኅበራዊ እና የችግር አፈታት ክህሎቶች በጥምረት ስለሚያስፈልጉት ነው። አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ግን እነዚህ ክህሎቶች በየግል እንጂ በማኅበር አላዳበረም [86]።

ሐሰተኛ ዜና እና የጥላቻ ንግግር

በተለመደው የወንጀል ሕግ ስድብ ፤ ዛቻ ፤ ማስፈራራት እና ስም ማጥፋት እንደ ወንጀል የሚያስጠይቁ ቢሆንም የኢንተርኔት መስፋፋትን ተከትሎ በማኅበራዊ ሚዲያዎች የብሔር ብሔረሰቦችን፣ የእምነት ተቋማትን እንዲሁም የግለሰቦችን ክብር የሚነኩ ፅሁፎች እና ንግግሮች

86 Robin Hanson, The Age of Em. Work, Love, and Life when Robots Rule the Earth ,Oxford University Press 2016, 271ff.

ተበራክተዋል። ለዚህም ምክንያት የሚሆኑት ሰዎች በማኅበራዊ ሚዲያ ገፆች ላይ ራሳቸውን በመደበቅ ወይም የውሸት ስያሜ በመጠቀም ከማሕበረሰቡ የሚደርስባቸውን ግሳፄ በመፍራት ፊት ለፊት የማይገልጸቸውን እኩይ እና ፀብ አጫሪ ሐሳቦች በማኅበራዊ ሚዲያዎች ያስተላልፋሉ ይህም በመሆኑ ከማኅበረሰብም ሆነ ከሕግ ተጠያቂነት የሚያመልጡበት ሁኔታ ተፈጥሯል። የጥላቻ ንግግር የዘረኝነት ተግባር ውስጥ ለመሳተፍ ሥነ-ልቦናን በማዘጋጀት ዘር እነ ሃይማኖትን መሠረት ላደረገ ጥቃት እና ጭፍጨፋ በር ይከፍታል። ቃላት እና ሰዋሰው የጋራ ጠላትን በመግለፅ ማኅበረሰብን ከዚህ አላስፈላጊ መዝገር የማፅዳት የጋራ ጥቅምን ለመመስረት ሊውል ይችላል። በሕዝቦች መሃል መቃቃርን ለማስቀረት እንዲሁም የግለሰቦችን ክብር ለማስጠበቅ የጥላቻ ንግግርን ይገታሉ ተብለው የታመነባቸው ሕግጋት በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ሀገራት ሥራ ላይ እየዋሉ ይገኛል።

አንድ ንግግር የጥላቻ ንግግር ለመባል ምን መስፈርቶችን ማሟላት ይገባዋል? ንግግሩ የተደረገበት ዓውድ እና ዓላማ ከግምት መግባት የለበትም ወይ? እንዲሁም ከቃላት ተለዋዋጭነት የተነሳ ዛሬ በስፋት የምንጠቀማቸው ቃላት ነገ የጥላቻ መግለጫ ሊሆኑ አይችሉም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ። ሌላው ደግሞ የጥላቻ ንግግርን ከመናገር መብት ወይም ጥላቻ ንግግርን ከፖለቲካዊ መግለጫ እንዴት እንለያለን የሚለው ነው። ጥላቻ ንግግርን ለመገደብ የወጡ ሕግጋት የመናገር መብትን ይገድባሉ የሚሉ ተቃውሞች ይነሳሉ። እያንዳንዱ ግለሰብ ዘረኛ እና ጽንፈኛ ቢሆን እንኳን ሐሳቡን የመግለፅ ተፈጥሯዊ መብት አለው። ይህንን መብቱን መገደብ ግለሰባዊ ነፃነቱን እንደ መግፈፍ ይቆጠራል በማለት ይከራከራሉ።

ሌሎች ተቃዋሚዎች ደግሞ የንግግር ነፃነት ለማኅበረሰብ የሚያስገኘውን ጥቅም በማንሳት ይከራከራሉ። ማንኛውም ንግግር ላይ የሚጣል ገደብ እውነትን ፍለጋን የሚወስን እና የሐሳብ ገበያን የሚያጠብ ነው ምክንያቱም እውነት የሚጠነክረው እና የሚጠራው ከስሁት ሐሳቦች ጋር በመጋጨት ነው። ሌላው ደግሞ ጽንፈኞች እና ዘረኞችን ጥላቻ እና

ቁጣቸውን በንግግር እንዲገልፁት በማድረግ ይህ ስሜታቸው ቢታመቅ እና ተደራጅተው ህቡዕ ቢገቡ ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት ማስቀረት ይቻላል የሚል ሐሳብ የሚሰነዝሩም አሉ። ጽንፈኝነት እና ዘረኝነትም ምን ያህል በማኅበረሰቡ ሥነ-ልቦና ውስጥ እንደተሰራፋ እንደ አመላካች ወይም መለኪያ ልንጠቀምበት እንችላለን የሚሉም አልጠፉም።

ከዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ጋር በጥቂቱም ቢሆን የሚገናኘው Cyberbullying (የኢንተርኔት ማንጓጠጥ) ሲሆን በተለይ በወጣት ተማሪዎች ዘንድ እንደ ዓለም ዓቀፍ ችግር እየታየ ይገኛል። በድሮ ዘመን በትምህርት ቤት ውስጥ ጉልበተኛ እና ታዋቂ የሆኑ ተማሪዎች በደካማ ተማሪዎች ላይ የሚሰነዝሩት ጥቃት በኢንተርኔቱ ዓለም ደግሞ በዚሁ መልክ እየተገለጠ ይገኛል። በዚህም አማካኝነት ብዙ ተማሪዎች ራሳቸውን ለማጥፋት በቅተዋል። ሰዎች በተለምዶ በአካል ከሚያደርጉት እና ከሚናገሩት ይልቅ በኢንተርኔት ላይ የሚናገሩት እና የሚያደርጉት ነገር እጅግ የተጋነነ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ የሰዎች እለት ተእለት ኑሮ ለማኅበራዊ ሚዲያ ተግባቦት የተጋለጠ እንደመሆኑ በማኅበራዊ ሚዲያ የሚደርስባቸው ጥቃት ምናልባትም በአካል ከሚደርስባቸው ዛቻ እና ስድብ ይልቅ የሚጎዳ ሊሆን ይችላል።

በአሜሪካው የ2016 ምርጫ ለዶናልድ ትራምፕ መመረጥ በተገዳዳሪዎቹ ላይ የተሰራጨው ሃሰተኛ ዜና ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተ የማይካድ ሃቅ ነው። ለእዚህ ዜና መሰራጨት ዓይነተኛ ሚና የተጫወቱ የውጪ ኃይላት እንዳሉ ቢታወቅም እነዚህን ዜናዎች በተቀናጀ አልጎሪትም ለሚመለከታቸው መራጮች በመላክ ውጤቱ እንዲቀየር ለማድረግ መቻሉ ብቻ ለሃሰተኛ ዜናዎች ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጣቸው አድርጓል። እንደ አፍሪካ ሀገራት ያልፀኑ የዲሞክራሲ ተቋማት ሲኖሩ ደግሞ ጉዳዩ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደማለት ነው። በአፍሪካ ውስጥ ለተካሄዱ የድህረ ምርጫ ብጥብጦች እና መፈንቅለ መንግስቶች ዋነኛ ምክንያቱ የሐሰተኛ ዜናዎች መሰራጨት መሆኑ የማያከራክር ነው። ሐሰተኛ ዜና ከጥላቻ

ንግግሮች በዓይነቱ የሚለይ ሲሆን ምንም ዓይነት የጥላቻ ንግግር ያልያዙ እንዲያውም ወደ እውነተኛ ዜናነት የሚጠጉ ሆኖም አሳሳች እና ተቃራኒ ማስረጃዎችን የታጨቀባቸው ዜናዎችን ሆነ ብሎ መበተን የሚያስከትለው ውጤት ነው።

Cybercrime (የኢንተርኔት ወንጀሎች)

በአሁን ወቅት ያደገው ዓለም የኢንተርኔት ወንጀሎች ብሎ የፈረጃቸው ጉዳዮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፉ እና እየተወሳሰቡ ሄደዋል። ለምሳሌ የሚስጥር ቃላትን እና ቁጥሮችን በመስበር የተለያዩ ተቋማትን ሚስጥር አደባባይ ማውጣት እና አንደ ማስፍራሪያ በመጠቀም ገንዘብ እና ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት መሞከር ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ይገኛል። በዚህ ወንጀል ከግለሰብ እስከ ተቋም ድረስ ብዙ ጉዳት ተፈጽሟል። የሚስጥር ቃል ሰበራ በሀገር ኢኮኖሚ እና ደህንነት ላይ የሚጥለው ችግር ከፍተኛ መሆኑን የምንረዳው በአሁን ሰዓት ከትንሽ ቢሮ እስከ ኒውክለር ማበልጸጊያ፤ የውሃ እና መብራት አሰራሮች በሙሉ በኢንተርኔት የሚታዘዙ በመሆኑ ነው።

በግለሰብ ደረጃ አውርደን ብናየው እንኳ አንድ ግለሰብ የማኅበራዊ ደህንነት ቁጥሩ ፤ የባንክ አካውንቱ ፤ መታወቂያው ፤ የኤቲኤም ካርዱ፤ የመስሪያ ቤቱ ማህደር፤ የትምህርት ማስረጃው፤ ማኅበራዊ ድህረ ገጹ እና መሰል የማንነት ዘንጎቹ በሙሉ የሚገኙት በኢንተርኔት ላይ በመሆኑ እነዚህን በተቀናጀ መልኩ ከአንድ ግለሰብ ወደ ሌላ ግለሰብ ማዛወር መቻል ግለሰቡን ማንነት አልባ ሊያደርገው ይችላል። ይህ ባደጉት ሃገራት የማንነት ስርቆት Identity theft የሚባል ሲሆን ወደፊት አስጊ ከሚባሉ የኢንተርኔት ወንጀሎች መሀከል አንዱ ነው።

የዘረ መል ምህንድስና (Genetic Engineering)

የዘረ መል ምህንድስና (Genetic engineering) ከፍተኛ የህግ እና የሞራል ጥያቄዎች የሚያስነሳ ጉዳይ ነው። ብዙ ሰዎች ፈጣሪ ሰዎችን እና ዓለምን ረቂቅ በሆነ ንድፍ አዋቅሯል ብለው ያምናሉ፣ በዚህ ምክንያት ሰዎች በዚህ ረቂቅ ንድፍ ውስጥ ጣልቃ ገብተው ሊቀይሩት ወይም ሊያሻሽሉት እንደማይገባቸው ያምናሉ። የማይናቅ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በበኩላቸው ግዑዙም ሆነ ህያው የሆነው የተፈጥሮ ዓለም በዝግመታዊ ለውጥ የመጣ እንጂ ረቂቅ እና መለኮታዊ በሆነ ንድፍ የተዋቀረ መሆኑን አይቀበሉም። በመሆኑም ሳይንቲስቶች የሰውን፣ የእንስሳትን፣ የአዕዕዋትን የዘረ መል ውቅር ማሻሻል ወይም መቀየር ተገቢ እና ሞራላዊ መሆኑን ያምናሉ። በዚህ ምክንያት Genetically modified organisms - GMO ወይም ልውጥ ህያዋን የተለያዩ የምግብ አዕዝርትን ዘረ መል በማሻሻል የምግብ ዋስትናን እያረጋገጡ ቢገኙም በተጓዳኝነት ብዙ ክርክር እያስነሱ ይገኛል።

አንዳንዶች እንደሚከራከሩት ይህ አሳሄድ ተፈጥሩአዊ የምግብ ዘሮችን በማጥፋት ድብልቅ ዘሮችን በምርምር ማእከል ውስጥ በማምረት ለገበሬው ዘርን ከካምፓኒዎቹ ብቻ ገዝቶ ለተጠቃሚ እንዲያቀርብ የሚያስገድድ ነው። የኬሚካል ውህዶቹና ንጥረ ነገሮች በጤና ላይ ካንሰርን የመሰለ በሽታ እንደሚያመጣና ሰውነትን የሚመርዙ ውህዶች ያሉበት ነው: ገበሬው ዋናውን ዘር ካጣ በሁዋላ በገዛ መሬቱ በእዳና ብድር የሚያገኘውን አዲስ (GMO)ዘር መክፈል ስለማይችል በእዳና ተጽእኖ ስለሚዘፈቅና ለማህበራዊና ስነ ልቦናዎ ቀውስ ይዳረጋል፤ 100 ያህል ህንዶች ራሳቸውን በዚህ ምክንያት አጥፍተዋል፤ ከሁሉም በላይ ገበሬውና ህዝቡ በፈጣሪው ላይ ያለውን ጽኑ እምነት በሳይንስ አማካኝነት በመሸርሸር አምላኩን ሳይሆን ምርምር ማእከላት ላይ ተስፋና እምነቱን እንዲጥል ማድረግ ነው።

ይህ የዘረ መል ድቅል የምርት መብዛትን ቢያሳይም ተፈጥሯዊ ንጥረ ነገሮችን ስለሚያጠፋ ከተፈጥሮ ምግቦች የምናገኛቸውን በሽታን የመከላከል

አይነት ጥቅሞች ሊሰጠን አይችልም:: እንግዲህ በምግብ ራስን መቻል እና ሃገራዊ ሉዓላዊነትን ማስጠበቅ እያንዳንዱ ታዳጊ ሃገር የሚወስነው የህግ እና የሞራል ጥያቄ ነው። የሰው ልጅን ዘረ መል በማዳቀል ወይል በማጎልበት ካንሰርን የሚቋቋም ጠንካራ የሰውነት አቅም መገንባት እንዴት ይቻላል ለሚለው ጥያቄ ብዙ ሳይንቲስቶች እየተመራመሩበት የሚገኝ ቢሆንም ካንሰርን ከመዋጋት ባሻገር የሰው ልጅን ልዩ የሆነ ብቃት እና ሃይል ያለው ፍጡር አድርጎ መስራት ህጋዊ እና ሞራላዊ ጥያቄዎችን በማስነሳት እስካሁን መፍትኄ ሳይገኝለት ኖሯል።

ክሪፕቶከረንሲ(Cryptocurrency)

ገበያ ከተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ መገበያየት ግዴታ እየሆነ ሄዷል። በዚህም ምክንያት የመገበያያ መንገዱ በታሪክ ውስጥ የተለያየ ቅርፅ እየያዘ እዚህ ደርሰናል። በመሠረቱ ገንዘብ የዋጋ ወኪል ነው (Money is value) በመሆኑም ገንዘብ ከመፈጠሩ በፊት ዋጋ በተለያየ መንገድ ሲመዘን ኖሯል። ከተለያዩ የመገበያያ ስርዓቶች መሃል በዓይነት የሚደረግ ልውውጥ (Bartering) ታሪካዊ እና ጥንታዊው ነው። ይህም ማለት አንድ ጆንያ ጤፍ በአስር ጥይት፣ አስር ጥማድ በሬ በሁለት ወቄት ወርቅ ሊቀየር ይችላል። ይህ የግብይት ስርዓት ግን አድካሚ ፣ አዘጋጃሚ እና ወጥነት የሌለው በመሆኑ ሰዎች አዲስ የመገበያያ ስርዓት ለማበጀት ጥረት ማድረግ ጀመሩ።

በዚህም ምክንያት ወርቅ፣ ብር እና ነሃስ የመገበያያ መንገዶች ስለሆኑ ሰዎች የሸቀጥ እና አገልግሎት ዋጋን በእነዚህ የከበሩ ማዕድናት ዋጋ ትይዩ ማነፃፀር ጀመሩ። በእኛ ሀገር አሞሌ ጨው በዚሁ መንገድ አገልግሏል፣ በኋላ ይህም ቢሆን አድካሚ በመሆኑ ሳንቲሞች እና የብር ኖቶች የወርቅ ዋጋን ወክለው ተፈጠሩ። ይህም ማለት መንግስት ለእያንዳንዱ ሳንቲም እና ብር የተወሰነ የወርቅ ክምችት ለማቅረብ ቃል ኪዳን ገባ። ይህም ማለት ሰዎች ዕቃን ከማመን ይልቅ መንግስትን ማመን ጀመሩ። ይሁን እንጂ ይህም ቀልጣፋ ባለመሆኑ መንግስት legal tender ወይም Fiat

money ማተም ጀመረ። ይህም ማለት ከገንዘብ ጀርባ ያለው መተማመኛ የመንግስት ቃል ብቻ ሆነ ማለት ነው።

በመሆኑም የገንዘብ ኖት ማዕከላዊ በሆነ መንገድ በመንግስት ቁጥጥር ስር የሚተዳደር የመገበያያ መሣሪያ መሆኑ አስገዳጅ እየሆነ ሄደ። አሁን ባለንበት ዘመን ደግሞ የብር ኖት መያዝም እየቀረ በክሬዲት ካርድ እና በዲጂታል ትራንሰፈር መገበያየት ተግባራዊ በመሆኑ የብርኖት እና ሳንቲም መያዝ የኃላቀርነት ምልክት ሆኗል። በዚህ ዘመን ገንዘብ በባንኮች ሱፐር ኮምፒዩተር ውስጥ ያለ የሒሳብ ቀመር በመሆኑ አንዳንዶች Money is a digital of 1 & 0 በማለት ይገልፁታል።

እንግዲህ ክሪፕቶከረንሲ የሚመጣው እዚህ ጋር ነው፣ ገንዘብ በባንኮች ቁጥጥር ውስጥ ያለ ቁጥር ከሆነ ባንኮች የሚቆጣጠሩትን ሌጀር ለሕዝብ ሁሉ የሚታይ እና ሁሉም ሰው የሚቆጣጠረው ሌጀር (Digital ledger) በመፍጠር ለምን ባንኮችን ከጫወታው ውጪ አናደርጋቸውም የሚል አስተሳሰብ ክሪፕቶከረንሲ የሚል ስያሜ ይዞ እየመጣ ነው። የዚህ አስተሳሰብ አመንጪ ማንነቱን Satoshi Nakamoto በሚል ስያሜ ደብቆ ይህንን አሠራር ለሕዝቡ ያቀረበ ሲሆን አዲሱ የDigital currency ስያሜ ደግሞ Bitcoin ይባላል። ይህ አሠራር ብሔራዊ ባንክ የማይቆጣጠረው የመገበያያ መንገድ መፍጠር ነው። ይህ የአቻ ለአቻ መረብ peer to peer network እያንዳንዱ የቢት ኮይን ባለቤት የሚያወጣውን፣ የሚያስገባውን እና የሚያስተላለፈው የገንዘብ መጠን በዚያ ስርዓት Block chain ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ ያየዋል፣ ይቆጣጠረዋል። በመሆኑም የባንክ ስርዓት እና የመገበያያ መንገድ እንዲህ እየረቀቀ የሚሄድ ከሆነ ይህንን ግብይት የሞቆጣጠር ህግ ምን ያህል መርቀቅ እንደሚኖርበት መገመት አያዳግትም።

ሰው እና ዕጣ ፈንታው

የሰው ልጆች ታሪክ ማለት የሕግ እና ሞራል እድገታቸው ታሪክ ማለት ነው። የሰው ልጆች ሞራል እንዴት እያደገ እንደመጣ በጥቂቱም ቢሆን ተመልክተናል በመሆኑም የሰው ልጆች ታሪክ በኢንተርኔት እና ቴክኖሎጂ እድገት እና ይህን ተከትሎ በሚመጡ ችግሮች እና ጠንቆች እንደሚደመደም በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

የምንኖርበት ዘመን በእጅጉ ከተጫነው ድህረ ዘመናዊነት እና አንጻራዊነት ባሻገር አሁን ደግሞ በቴክኖሎጂ እና በማኅበራዊ ሞራል ዝቅጠት አንጻር ውዝግብ ውስጥ እየተንደረደረ ይገኛል። ይህ የድህረ እውነት ዓለም ከላይ ከተጠቀሱት አስተሳሰቦች ጋር ተደምሮ ግለሰባዊና ማኅበረሰባዊ ግብረገብነት እና ሥነምግባርን ከዚህ ቀደም ታይቶ ወደማይታወቅ ግዛት እና የሐሳብ አድማስ እየጎተታቸው ነው።

በግለሰባዊ ሞራል እና በማኅበረሰባዊ ሞራል መሀከል ያው ገመድ ዕለት ዕለት እየቀጠነ እና እየተወጠረ ይገኛል። ዓለማት በቴክኖሎጂና በካፒታሊዝም እድገት እየታገዘች የሰው ልጅን ከማኅበረሰቡ የተነጠለ ብቸኛ ፍጥረት እንዲሆን አስገድዳዋለች። ሁሉም ግለሰብ የራሱን የሞራል መስፈርት እና መለኪያ የሚያዘጋጅ ከሆነ የማኅበረሰባዊ ሞራል ዕጣ ፈንታ ምን ይሆናል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ አለብን።

ፍትሕን ዘመን ተሻጋሪ በሆነ መንገድ ለመረዳት ልንተረጉመው የሚገባው ከሕግጋት ጋር በማያያዝ ሳይሆን ከእውነት ጋር በጥልቀት በማገናዘብ ነው፤ ምክንያቱም እውነት የሆነው ነገር ምን ጊዜም ፍትሐዊ ነው። እውነት ደግሞ ዲበአካላዊ የሆነ ይዘት እና ትርጉም አለው። እውነት ስለዲበአካላዊነት ካለን አመለካከት ይመነጫል። ሰውን መግደል የተሳሳተ እና እውነት አልባ ተግባር የሚሆነው ከዚሁም ጋር ተያይዞ ኢ-ፍትሐዊ እንደሆነ በማሰብ የምንከራከረው “ግድያ” የተሳሳተ ተግባር መሆኑን የምንከተለው ዲበአካላዊ ፍልስፍና የሚያመላክተን ከሆነ ብቻ

ነው። አንዳንዶች እውነት የማይለውጥ እና የማያረጅ እንደሆነ ሲያስረዱ አንዳንዶች ደግሞ እውነት በጊዜ እና በዘመን የሚቀያየር እንደሆነ በማመን ይከራከራሉ፡ እውነት የሆነውን ነገር የምናውቅበት ፍልስፍና ደግሞ የእውቀት ፍልስፍና ይባላል።

በመሆኑም ፍትሕ በዓለምዓቀፍ የሕግ ስርዓት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ይገለጻል። እነዚህም የሀብት ክፍፍል ፍትሕ ፤ሥነ-ስርዓታዊ ፍትሕ; የእርምት ፍትሕ ፤ የተሃድሶ ፍትሕ; የተፈጥሮ ሀብትና ጥበቃ ፍትሕ እና የመሳሰሉት ናቸው። ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ለአያሌ የፖለቲካ አብዮቶች ምክንያት የሆነ ነው። ጥቂቶች በብዙኃኑ ሀብት እና ጉልበት ተጠቅመው እየተንደላቀቁ ሲኖሩ ሰፊው ሕዝብ ደግሞ በድህነት አረንቋ ውስጥ ሊዘፈቅ ስለማይገባው መንግስት በሀብት ክፍ ካሉት በግብር፤ መዋጮ እና ቅጣት ሀብት እየሰሰበሰበ ለብዙኃኑ ሊያከፋፍል ይገባዋል በማለት ያስተምራል። ሥነ-ስርዓታዊ ፍትሕ በአብዛኛው የሚገለጸው በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ቢሆንም ለፍትሐብሔር ጉዳዮችም ጠቃሚ ነው።

በመሰረታዊነት ሕግ ከግቡና ውጤቱ ይልቅ ሂደቱ ፍትሐዊ ሊሆን እደሚገባና በሀገርኛ አባባል "የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው" የሆነ አሠራር ኢፍትሐዊ መሆኑን ያስረዳል። በመሆኑም በወንጀል ሂደቱ አንድ ተጠርጣሪን በመደብደብ እና በመግረፍ የሚገኝ የእምነት ቃል በፍትሐዊ ሂደት ያልተገኘ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል። ፈረንጆቹ ይህንኑ ሐሳብ Due process of Law በማለት ይገልጹታል፤የፍትሕ ስርዓት ተገቢውን ሂደት ማለፍ ስለሚገባው በዚሁ መልክ የተገኙ ማስረጃዎችና ፍርዶች ብቻ ፍትሐዊ ናቸው ብለን ማመን አለብን። የእርምት ፍትሕ ከጉዳት እና ካሳ ጋር እንዲሁም ከወንጀል እና ቅጣት ጋር የሚገናኝ ነው። አንድ ሰው በእውቀትም ሆነ በቸልተኝነት በአንድ ሰው ላይ የወንጀል ድርጊት ከፈጸመ ተገቢ እና ተመጣጣኝ የእርምት እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል። ይህ እርምት የእርምት አላማ ማስተማርና ማረም፤ መቀጣጫነት፤ በቀል ወይም ማቀብ ሊሆን ይችላል።

ሌላው በቸልተኝነት የተፈጸመ ጉዳት ቢሆንም እንኳ፣ በአንድ ግለሰብ ላይ የአካል ጉዳት ያደረሰ ሰው ለዚሁ ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ለተጎጂው ወይም ለቤተሰቡ መክፈል ይኖርበታል። በመሆኑም የእርምት ፍትሕ በወንጀል ወይም በጉዳት አማካኝነት የተዛባውን ማበረሰባዊ ሚዛን መልሶ ማቀናት ነው። የተሃድሶ ፍትሕ ግን ሰዎች ባደረሱት ጉዳት ልክ ቅጣት ሊደርስባቸው አይገባም ምክንያቱም ይህ የፍርድ ሂደት የአሸናፊ እና ተሸናፊ ስነ-ልቦና የሚፈጥር በመሆኑ ዘላቂ የሆነ ሰላም እና ፍትሕ ለማጎበረሰቡም ሆነ ለባለ ጉዳዮች አያመጣም። በመሆኑም በእርቅ እና ድርድር ባለጉዳዮቹን በተቻለ መጠን ወደነበሩበት እ�ኳር ልንመልሳቸው ይገባል ሲል ይከራከራል። የተፈጥሮ ሀብትና ጥበቃ ፍትሕ በበኩሉ ፍትሕ ለሰዎች ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮ ለሚገኙ እንስሶች ፣ እጽዋት እና ግዑዛን ሁሉ ሊሠጥ እንደሚገባው ያስተምራል። በመሆኑም ሰዎች የአካባቢያቸው አስተዳዳሪ እንጂ ገዢዎች እና ባለመብቶች አይደሉም፤ ምክንያቱም ሰዎች ራሳቸው የተፈጥሮ አካል በመሆናቸው ተፈጥሮን የመበዝበዝ የተሻለ መብት የላቸውም። ይህ አይነቱ የገንዘነት እና የበዝባዥነት አስተሳሰብ ሰው የዓለም ማዕከላዊ እንደሆነ አደርጎ ከሚያስብ አስተምህሮ የመነጨ በመሆኑ አሁን የምናየው አካባቢያዊ ብክለት ሊያስከትል ችሏል። ይሁን እንጂ ሰዎች የተፈጥሮ አካል እንደመሆናቸው ለተፈጥሮ ሕግጋት መገዛት አለባቸው። ምክንያቱም በአካባቢያቸው ያለውን የተፈጥሮ ሀብት በባለ አደራነት መጠበቅ ይገባቸዋል፣ የመንግስት ሕግጋትም ይህንኑ ሊያጸኑ አንደሚገባ አስተምህሮው ያረጋግጣል። በዚህ ሰው እና ዕጣ ፈንታው በሚል ንዑስ ርዕስ ስር የሰፈረው ጽሁፍ ቀደም ሲል በመግቢያችን ፍትሕ እና ሕግ በሚል ንኡስ ርዕስ ስር ያሰፈርነው ነው፤ ለዚህ ምክንያቱ መጀመሪያችን እና መጨረሻችን ይህ እንዲሆን ስለተፈለገ ነው።

ታዋቂው እንግሊዛዊ ፈላስፋ " Power corrupts but absolute power corrupts absolutely " " ስልጣን ያነቅዛል ፍጹም ስልጣን ግን ፍጹም ያነቅዛል " ሲል አስጠንቅቋል። ስልጣን ፍጹም እንዳይሆን የሚከላከለው የሕግ የበላይነት ከሆነ ጠንካራ የሕግ የበላይነት እንዲኖር ጥሩ ሕግጋት

ያስፈልጋሉ። በዘመናዊው ዓለም ሉዓላዊ ስልጣን የሚያርፈው በሕዝብ ትከሻ ላይ በመሆኑ ፍጹም ስልጣን የተጎናፀፈ ሉዓላዊ አካል ሊኖር አይገባም። አበው "ሰማይ አይታረስ ንጉስ አይከሰስ " የሚሉት ዓይነት አገዛዝ ከዓለማችን የሕግ እና የፖለቲካ መዝገበ ቃላት ላይ ከተፋቀ ቆይቷል። ስልጣን ዉሃ ላይ እንደተቀመጠ ብረት ነው። ውሃ ላይ የተቀመጠ ብረት መዛጉ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በቀር የሚቀር አይደለም፣ ተፈጥሯዊ ነው።

በመሆኑም ብረቶች እንዳይዝጉ በየጊዜው እርጥበታማ ከሆኑ ቦታዎች አየተነሱ በዘይት መወልወል እና መድረቅ አለባቸው። የምናፍቀው በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃ እና ፍትሐዊ ምርጫ ተደርጎ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትክክለኛ የሀገሪቷ ፖለቲካዊ ምህዳር ነፀብራቅ ሲሆን ማየት ነው። ሰዎች በብቃታቸው እንጂ በብሔር ውክልናቸው ስልጣን የማይዙበት፣ በተናገሩት ነገር የማያሸማቀቁበት፣ ስልጣን ሕዝብን የማገልገያ መሰሪያ እንጂ ርስት እና መጠቃቀሚያ የማይሆንበት የመንግስት አስተዳደር እንዲመሠረት ነው። አዎ፣ የምናፍቀው ማንነታችንን በብሔር እና ዘውግ መተርጎም የማንፈልግ ሰዎች በገዛ ሀገራችን እንደ ባይተዋር የማንታይበት ቀን እንዲመጣ ነው።

ብረቶች ሊዝጉ አይችሉም ብሎ ውሃ ላይ ዘፍዝፎ ማስቀረት አንድ የብረትን ባህሪ አለማወቅ ወይም የውሃን አቅም ያለመገንዘብ ነው። "ከሰው ስህተት ከብረት ዝገት" የተባለው ያለ ምክንያት አይደለም። ልክ እንዲሁ ስልጣን ዝገትን፣ መበስበስን እና መንቀዝን ያስከትላል። በዚህ ምክንያት የሰዎች ስልጣን እንዳይዝግ ፣ እንዳይበሰብስ ሰዎቹንም አብሮ እንዳያነቅዝ እና እንዳያበሰብስ ፖለቲካዊ ስልጣን በየጊዜ መፈተሽ እና መፅዳት አለበት። ስልጣን የሚፈተሸው እና የሚፀዳው በሕግ ተጠያቂነት ከሆነ መፈተሻ እና ማፅጃ መሣሪያዎቻችን የሆኑት መሣሪያዎቻችን በትክክል የሚሰሩ መሆኑን በየጊዜ ማረጋገጥ አለብን። በዘመናዊው ዓለም የሕግ አላማ ሉዓላዊ እና ፍፁማዊ ተቋም እና ግለሰብ መፍጠር ወይም መለኮታዊ ሕግጋትን በምድር ላይ መትከል አይደለም። የሕግ ዓለማ ሕዝብን ማገልገል

በመሆኑ ከአገልግሎቶቹ ውስጥ አንደኛው እና ዋነኛው ስልጣንን በአግባቡ መገደብ እና ተጠያቂ ማድረጉ ነው። ሕግ የሰዎች የስልጣኔ ልህቀት ማሳያ በመሆኑ የሰለጠኑ ህዝቦች የሰለጠነ ሕግ ይኖራቸዋል። ህዝቦች በኢኮኖሚ ፣ በቴክኖሎጂ እና ሲያድጉ እና ሲራቀቁ ሕግጋቶቻቸውም እንዲሁ እያደጉ እና እ የረቀቁ ይሄዳሉ ይህ ማለት ሕግጋቱ ይበዛሉ ማለት ላይሆን ይችላል እንዲያውም ሲሴሮ እንደሚል “The numerous the laws the corrupt the state “ - “ ሕግጋቱ በበዙ ቁጥር የመንግስት ንቅዘት ይጨምራል “ ሕግጋት ይራቀቃሉ ማለት ይበዛሉ ማለት ሳይሆን የሚወጡት ሕግጋት ያለፉትን እና ወደፊት የሚመጡትን ትውልዶች ታሳቢ የሚያደርግ ግልፅ ግን ረቂቅ መሆን አለበት ማለት ነው።

ዋቢ መፃሕፍት እና ጦማሮች

- George white Paton A Text Book of Jurisprudence, ed. David Perhans, Oxford press, 1964
- Gerald H. Hughes, Aristotle on Ethics, Rutledge Philosophy Guide books, 2001
- Hans Kelsen, The pure theory of Law, University of California press, 1967
- Henry sidwigk, Outshines of the History of Ethics, Theory press, 1993
- Hugo Grotiuss, On the Law of War and Peace, 1625
- HLA Hart, The concept of Law, Oxford University press 1961
- Immanuel Kant, groundwork of the metaphysics of moral 1785
- Jeremy Bentham, Introduction to principles of morals & Legislation, 1789
- John Stuart Mill, UTILITARIANISM, 1863
- John Austin, Lectures on Jurisprudence, University of London 1885.
- Oliver Wendell Holmes, The path of the Law, Harrard Law review, 1897
- Oliver Wendell Holmes Jr, The Common Law. I. Boston: Little, Brown and Company, 1881
- St Thomas Aquinas, Summa Theologica, English Dominican province, 1947.
- John Rawls, collected papres, Harvard Press, 1997
- Ronald Dworkin, Taking rights seriously, Harvard press, 1977
- John M. Cooper, Plato's Complete Works (Hackett, 1997)
- Bertrand Russell, A History of Western Philosophy (1945)

- The Collected Works of Jeremy Bentham: Deontology, Amnon Goldworth(ed), (1983)
- G. K. Chesterton, The Spectator (27 February 1932)
- John Finnis, Natural Law and Natural Rights, Oxford: Clarendon Press
- David Hume, An Enquiry Concerning Human Understanding (1748)
- Raymond Wacks, Understanding Jurisprudence; An Introduction to legal theory,Oxford Universty Press,4th ed,2015
- Raymond Wacks, Understanding Jurisprudence; An Introduction to legal theory,Oxford Universty Press,4th ed,2015
- Jonah Goldberg (2007). Liberal Fascism: The Secret History of the American Left from Mussolini to the Politics of Meaning. NY: Doubleday
- Elise Nalbandian, Socioliogical Jurisprudence;Roscoe Pounds Discussions on legal interests and Jural Postulates, Mizan Law Review,Vol 5,No.1,2011
- Duncan Kennedy and Karl E. Klare, “A Bibliography of Critical Legal Studies,” Yale Law Journal, Vol. 94 (1984)
- Roberto Mangabeira Unger , The Critical Legal Studies Movement Another Time, A Greater Task (2015), Harvard Press, P.15
- Niccolo Machiavelli ,Discourses on Livy , 1517, BooK one, Ch 3, (as translated by LJ Walker and B Crick)
- Niccolo Machiavelli, The Prince,1513, Ch 18, Translated by Marriot(1908)

- Freidrich Hegel, The Phenomenology of spirit,1807, J B Baillie translation
- Alexis De Tocqueville, Democracy in America, Volume II, 1840,Book Three, Chapter XXI
- Edmund Burke, Reflections on the Revolution in France (1790), Vol III
- Alexander Hamilton, “Publius”,The Federalist Paper 78, New York Post,1788
- Bahru Zewdie, Poineers of change in Ethiopia, The Reformist Intellectuals of the Early 20th century,Ohio University Press,2002, p. 5
- Hugo Grotius, The Law of War and Peace, trans. Francis Kelsey (Carnegie edition, 1925), Prol. sect. 28.
- በአማን ነጸረ፤ ጽንዐ ተዋህዶ፤ ብራና መጻህፍት፤ 2012
- ብሩህ ዓለምነህ፤ የኢትዮጲያ ፍልስፍና ዘርዓያቆብና ወልደ ሕይወት ሐተታዎች ትንታኔ፤2011፤
- ዘርዓያቆብ / ወርቁ፤ ሐተታ ዘርዓያቆብ፤ 1640፤ በዳንኤል ወርቁ የተሰናዳ ድርሳን፤
- አበራ ጀምበሬ፤ የኢትዮጲያ ሕግና የፍትሕ አፈጻጸም ታሪክ ከ1426 እስከ 1966፤ ሻማ ቡክስ፤ 2006
- እንለ ገብረ ዮሐንስ፤ የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤1956
- ዶ/ር ጠና ደዎ ፤ ሰው ግብረገብና ሥነምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች፤ አአዩ ፕሬስ፤2008
- ዶ/ር ተስፋዬ ሮበሌ፤ ሥነ አመክንዮ የሙግት አደረጃጀት፤ አገማገምና አሰናዘር፤ተስፋ ዓቃብያነ ክርስትና ማኅበር፤ 2020

- ረ/ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ፤ የውል ሕግ መሠረት ሐሳቦች፤ አለዩ መጻህፍት ማዕከል ፤ ሦስተኛ ዕትም፤ 1999
- ልዑል ራስ ካሳ ሃይሉ፤ ፍኖተ አእምሮ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ 1953
- አዲስ አሰፋ፤ ክርስትና ለጠያቂ አእምሮ፤ ሮሆቦት አታሚዎች፤ 2006
- ዘውዴ ረታ፤ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ መንግስት ከ1923-1948፤ ሻማ ቡክስ፤ 2005
- ተስፋዬ ንዋይ፤ ሕግ እና አተረጓጎሙ፤ 2012
- እሸቱ ድባቡ፤ ተባእታይ አገዛዝ በኢትዮጲያ- ችግሩና የመፍትሄው መንገድ፤ አዲስ ጥራት ማተሚያ፤ ሰኔ 1997
- ፊታውራሪ ተክለሓዋሪያት ተክለማሪያም፤ የህይወቴ ታሪክ፤አለዩ ፕሬስ፤ 1998
- ልዑል ራስ እምሩ ሃይለስላሴ፤ ካየሁት ከማሰታውሰው፤ አለዩ ፕሬስ፤፤ 2002
- ኖህ ሀራሪ፤ ሆሞዩየስ-የመጪው ዘመን አጭር ታሪክ፤ ተርጓሚ ዳግም ጥላሁን፤ ሐምሌ 2012
- ኤፍሬም ስዩም፤ተዋነይ ብሉይ የግዕዝ ቅኔያት ፍልስፍና፤ ውርስ ትርጉም፤ 2006
- ብርሃኑ ድንቄ፤ አልቦ ዘመድ -ታሪካዊ ፈጠራ ፤ የህትመት ዓመት አልተጠቀሰም

US Supreme Court Cases

- Roe v. Wade, 410 U.S Supreme court (1973)
- Marbury v. Madison, U.S. Supreme court 137, (1803)
- Dred Scott v. Sandford, U.S. Supreme Court, 393 (1857)
- Loving Vs Virginia, 388 US Supreme Court 388 (1967)